በዚሁ ጊዜ ፒያኖ «እኛ የመጣነው ለሰርጎት ቢሆን ኖሮ ባዶ እጃችንን እንዴት በእርስዎ እጅ እንገባለን» ብሎ ንግግር ሲጀምር ራስ አሉላ በቁጣ ኮራዶውን በእጃ እየያዙ «ጦር ካላለክ ትገደላለህ» አለው። ሚሊያየቢ ቅር እያለው አንደገና ሌላ ደብዳቤ ገፈ «መታደርቼ ከተባሉት ቦታዎች ካልተመለሱ ጥንቅቃትችን ተቀርጦ ነው የሚላካቹሁ» ብሎ ጻፈ! ከሳሱቱ ሹሞች አንዱ መጣ ለሚሊፈለን ራስ አሉላ ከመታደርቼ አንዱ አጫ የተባለ ወደ ምጽዋ ሄዶ በሁለት ቀን ውስጥ መልስ ይዞ እንዲመጣ ታዘዘ። ለመጀመሪያው ደብዳቤ መልስ መጫ ሚሊያየቢ ጥንቀት ስላደረብት የራስ አሉላ ወገድም ከንቲባ ከፋ «የሀበተኛ መልቶች ወሬ እየሰማ ነው እንጂ ኢጣሊያ በምፅዋ ሰርጎት አትፈልግም ብለህ ለራስ አሉላ ንገርልን» አለው። ራስ አሉላም «አንተ ወሸታም ነህ የሰሐቲ መድፎች ካልተነሱ ከመታደርቼ ጋር ከምንኩሉና ከሰሐቲ መሐል ባለው መንገድ እንደምደርስ አላይሃለሁ» አለው።[1] ከምንኩሉና ከሰሐቲ መሐከል ያለውም ቦታ ዶጋሊ ነው። ተሰፋይ በተባለው የአክሱም ተወላጅ ሰው ሌላ ደብዳቤ ተገፈ። ጀንዋሪ 20/1887 ዓ.ም አጫ የተባለው የኢጣሊያ መዳር ይዞት ለሄደው ደብዳቤ መልስ ደረሰ። ነገር ግን ጀነራል ጀኔ ካለፈው ጊዜ ሐሳቡን ስለለወጠ ራስ አሉላ ተናደዱ። ለምርኮኞቹ ለያቸቸውና ለያንገላቷቸው ጠባቂ አደረጉባቸው። ጫማ ቸውን ካስሊም እንዲያወልቁ አደረጓቸው። ራስ አሉላ ጣሊያኖች እየተሰደቡ በሜዳው እንዲጓጉተቱና ምግባም እንዲደበደቡ አዘዙ። በዚሁ ጊዜ ከየአቅጣጫው ብዙ ጦር ወደ ጊንዳዕ መሰብሰብ ጀመረ። ከምጽዋም በቅርብ ጊዜ ውስጥ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መሀል ግጭት እንደሚኖር የሚሉ ዜናዎች ተሰራጩ። በተሰፋይ ለተላከው ደብዳቤም ጀነራሉ ሀሳቡን ግደለውም ወና። ጀንዋሪ 20/1887 ዓ.ም የኢጣሊያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለጦሩ ዋና አዛዥ ራስ አሉላ በእስረኞቹ ላይ አንድ ጉዳት ቢያደርሱባቸው የሚከተለው እርምጃ ከባድ እንደሚሆን ለራስ አሉላ እንዲነገረው! ተጨማሪ ኃይልም የሚላክለት መሆኑን ማረጋገጫ ለጀነራል ጀኔ ደደርሰታል። ጀንዋሪ 22/1887 ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲጽፍ ከራስ አሉላ ጋር ውጊያ እንደቀጠለ ነው። ከራስ አሉላ በጣም ኃይለኛ ደብዳቤ ደርሶኛል። የማስፈራሪያ ቃል ግን የለውም።

ራስ አሉላና ወታደሮቹ ሊያጠቁን እየመጡ ናቸው! ምክንያቱም ገና ከእኛ ጋር መቀራረብ አይፈልጉም። እስረኞቹ በሕይወት እንደታሰሩ ናቸው። ራስ አሉላ ግን እንደቀድሞው የሚፈጽምባቸው አይመስልም። እስረኞችን ለማስለቀቅ ራስ አሉላ ፈቃደኛ ካልሆን በጦር ኃይል ማስለቀቅ እንደምችል ወታደርና መሣሪያ ተጨማሪ እንዲላክ ያስፈልጋል። በወቅቱ ከምጽዋ ብዙ ቴሌግራሞች አደጋ መቃረቡን የሚገልፁ ወደ ሮማ ደረሰው። ስለዚህ ጀንዋሪ 24/1887 ዓ.ም የኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኢጣሊያ ፓርላማ ተገኝቶ ስለሁኔታው እንዲያብራራ ጥያቄ ቀርቦለት ሚኒስትሩ የጉዳዩን የንቀት ቃል «በኢትዮጵያ የምንረግማቸው አራት ዘራፊዎች (ሽፍቶች የሚባሉ) ናቸው» ብሎ መልስ በመስጠት ሲጠየቁ የሚኖሩ ቃላቶች ሆነው በታሪክ ተመዝግቧል።[2]

1. Carlo Zaghi:Ibd p.25

2. Carlo Zaghi: Ibd p. 126



ለምዕራባዊቷ ዓለማ ለምዕራባዊቷ ርዳታ አይመጥኑትም ነበር። የጎረቤ በረሀ አካርማ ዘላ ወደ ቀይ ባሕር አካባቢ ደርሳ ርዳታ ላይ ዓለማ ላይ የምትቀመጥ ዝናብን ተከትሎ ከደጋው ክፍል ሀገር እየወረደ የሚያርሰው ገበሬ ለብዙ ዘመናት ለእርሻነን ቀርቦና ለጥበብ! ከኢጣሊያ የበለጠ ኃያላን የሆኑ የምጽዋ ገዢዎች ግድቦቻቸር! የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ነፃነቷ በመሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ምልክት ሆኖ የኖረው! የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች እንዴት ሊደፍሩት በቀ ለሚለው ጥያቄ መልሱ እኛ ራሳችን መርተን ለስልጣናቸው ነው! የሚገርመው ግን እውነም ከወትታችን ባለመገራችን ነው። በኢጣሊያ የእርስ በርስ ጦርነት እንጂ ብዙዎቹን ጣሊያኖች ጦርነት ንጉሠው ያስነሱበት ወቅት አልነበረም። ይኸም የሚያሳፍረንና የሚያሳዝን መሆን ይገባናል። ከሀገራችን አልፈን ወደ ሶማሌና ወደ ሊቢያ ጂደን ለጣሊያኖች ዝናና ክብር ደግፈንን አፍሰናል።

በተለይ የኤርትራና የሶማሊያ ተወላጆች በ1928 ዓ.ም (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) የኢጣሊያ ወረራ በሰሜንና ደቡብ ጦር ግንባር ከጣሊያኖች ጉን በግንባር ቀደም ከመሰለፍ አልፎ በደቡብ ጦር ግንባርም ኤርትራውያን ተሰልፈው ተዋግተዋል! ሶማሌዎች ግን ከደቡብ ጦር ግንባር በቀር በሰሜን ጦር ግንባር አልተሰለፉም። ወደ ሊቢያም አልተላኩም። በዚህ ብቻ አላበቃም ከዛሬት በኋላ በኤርትራ ለሠላሳ (30) ዓመታት የተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት በተዘዋዋሪ መንገድ ጣሊያኖች ያስጨረሱትን ጦርነት ነው ለማለት ይቻላል። ጣሊያኖች ናቸው ኤርትራውያን ኢትዮጵያን እንዲጠሉዋት እንዲጠሉት መርዝ የሆነ ከደማቸው የሚደለቅ ትምህርትና ሥልጠና ነው የሰጧቸው። ኢጣሊያ ኤርትራ የምትባል ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ቅኝ ግዛት ይህ ሁሉ በመገደላቸው ላይ ጥላቻና ደም መፋሰስ ሊደርስ አይችልም ነበር። የኤርትራ ችግርና የኤርትራ ጥያቄ የሚለውም ባልተፈጠረ ነበር። የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች እየተባለን ለሁለት አንከፈልም ነበር። ኢትዮጵያን የወረረች ኢጣሊያ ብቻ አልነበረችም። በወቅቱ ከነሱም ኃያላን መንግሥታት አንዱ የነበረው ግብፅ የአፍሪካን ቀንድ መንግሥት እንዲሁ የኢትዮጵያን የባሕር ወደቦች በቁጥጥሩ አድርጎ በበረ ጊዜ ወደ መሀል ደጋይቱ ሀገራችን ለመግባት ተደጋጋሚ ያደረገው ሙከራ ሁሉ እርስ በርሳችን ለማጋጋት ስላልቻለ አሉት መቶ ዓመት በወረራቸንን ቢቀይም ዓላማው አልተሳካላትም። ግብፅም በተለይ ባለፈው ምእተ ዘመን በኤርትራ፣ በሱዳን፣ በሶማሊያ፣ በአውሳ መሀል ኢትዮጵያ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ሀገራችንን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የአባይና የባሕር ጫና ባለቤት ለመሆን የነበራት ምኞት በተመሳሳይ ሁኔታ አልተሳካላትም።

ኢጣሊያ ምጽዋን ወረራ በምትይዝበት ጊዜ ምን ነበር ዓላማዋ ለሚለው ጥያቄ ኢትዮጵያን ለመያዝ ማረማመጃ ለታደርጋት የቀርቦና የሩቅ ዓላማ ነበራት? ወይንም የእንግሊዝ መንግሥት ኢጣሊያን ገፋፍቶ ምጽዋንና የቀይ ባሕር ወደቦችን ከግብፅ አስለቅቃ ወረራ እንድትይዝ ሊያደርግ ኢትዮጵያ እንድትይዝ የመገፋፋት ዓላማ ነበራት ወይ የሚለው ጥያቄ መልሱ ሁለቱ መንግሥታት እንደዚሁ ያለ ዓላማ እንዳላነበራቸው እነሬዳሉን። በእንግሊዝ መንግሥትና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል የተገፈ ውል ዓይነቶች ከምጽዋ መያዝ በኋላ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሲደረጉ በነበሩ መደበኛ የዲፕሎማቲክ ደብዳቤ ልውውጦች

ከጦርነቱ በኋላ ተጠይቆ ሲመልስም «ከጥቂት ቀን በፊት የተናገርኳቸው ታላቆች ትክክል አልሆኑም። ስለዚህ አሁን ስህተት ተናገርኩ ብዬ ግመን ችግር የለብኝም» ብሏል። ጀንዋሪ 26/1887 ዓ.ም የዶጋሊ ጦርነት ተደረገ። በኢትዮጵያ በኩል ስንት ወታደር እንደ ተካፈለ አይታወቅም። በኢጣሊያ በኩል ግን 540 (አምስት መቶ አርባ ወታደሮችና) ሃምሣ ባሺ ብዙክ ባጠቃላይ 590 በጦርነቱ ተካፋይ ሆነው ነበር[1]። «ባሺቡዙክ» ማለት ከሀገሩ ሕዝብ በጉብዞች ተመልምለው የነበሩ ወታደሮች ወደ ጣሊያኖች የተላለፉ ናቸው። ከአምሥት መቶ ውስጥ አራት መቶ አሥራ ሶስት በግዳው ሲሞቱ የቀሩት በሙሉ ቆስለው የሞቱ መስኳቸው ኢትዮጵያውያን የተዋቸው ነበሩ። ከእነሱም ውስጥ በደረሰባቸው ከባድ ቁስል ጦር ሰፈራቸው ሲደርሱ የሞቱ ነበሩ። ከባሺቡዙክ ግን ማንም ሰው አልቆሰለም፤ አልሞተም፤ አለተዋጉም ማለት ነው። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ጀንዋሪ 25/1887 ዓ.ም በራስ አሉላ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦርና በሻለቃ ቦሬቲ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር መካከል የሰሐቲ ጦርነት ተካሄዷል። በሰሐቲ የተዋጋው የኢጣሊያ ጦር ዶጋሊ ከተዋጋው በሰው ኃይል አነስተኛ ነበረ። ነገር ግን በሶስት መቶ ባሺቡዙክ የተጠናከረ ነበር። በኢጣሊያ የደረሰ ጉዳት ቀላል ነበር።

አንድ መቶ አለቃ በደረሰበት የመቁሰል አደጋ ሞተ። ሁለት የኢጣሊያን ወታደሮች ቆሰሉ። እንደዚሁም ሶስት ባሺቡዙክ ሞቱ። አንድ ቆስሏል። በሰሐቲ ኢጣሊያኖች እንዴት የዶጋሊ ዕድል አላጋጠማቸውም ለሚለው ጥያቄ የኢትዮጵያ ጦር ጠንካራ ተቃውሞ ለመጀመሪያ ስላጋጠመው በሙሉ ኃይል ሳያጠቃ ወደ ኋላ አፈገፍጐ ወደ ዶጋሊ አምርቶ በሙሉ ኃይሉ አጥቅቶ የነበረውን የኢጣሊያ ጦር በሙሉ ሊደመስስ ችሏል። የዶጋሊ ጦርነት የምናስታውሰው በጥቂት ሰዓቶች ብዙ የኢጣሊያ ወታደሮች የተገደሉበት የራስ አሉላና የኢትዮጵያውያን ጀግንነት በታሪክ የተመዘገበበት በመሆኑ ብቻ አይደለም። የሰሐቲና የዶጋሊ ጦርነቶች በዓይነ ሕሊናችን በጥልቀት ሊያሳስቡን የሚገባን ትምህርት ሊሰጡን የሚችሉ ሁኔታዎች ገና በእነዚህ ሁለት የመጀመሪያዎቹ ጦርነቶች ተከስቷል። የዶጋሊ ጦርነት ለዘለዓለም ሲያኮራን የሚኖር የሚገባ በኢትዮጵያውያንና በኢጣሊያኖች መካከል ብቻ የተካሄደ ጦርነት ሲሆን የሰሐቲ ጦርነትና ሌሎችም ከሱ በኋላ እስከ 1933 ዓ.ም (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) ከኢጣሊያኖች ጋር ያካሄድናቸው ጦርነቶች ሁሉ ግን ጣሊያኖች ብቻቸው የገጠሙን ጊዜ የለም። ግማ ሾቻችንን እየመለመሉ በገንዘብ እያታለሉ በወንድሞቻችን ላይ ዘምተን ሀገራችንን ወግተን ደማችንን አፍስሰን ወገናችንን ገድለን የሀገራችንን መሬትና ሕዝቦቿን በጣሊያኖች በባርነት እንዲገዙ እናስረክብ ነበር። በመሀል ሀገር እንዲሁም በጠረፍ የእኛ ትብብር ባያገኝ ኖሮ ጣሊያን በምጽዋ ገብቶ በጦርነት ለመግጠም ባልደፈረን ነበር፤ የአርበርቡዕ ገደላ ገደሎችና የዓሊ ጌደ፤ የሰያሕ ገደ፤ የሐዳስ ሸለቆዎች ዘልቀው ለመግባት ባልቻሉ ነበር። የጎርሰይ፤ የመተተን፤ የአባ ሐኒ ተራራዎች በምንም ታአምር ለመውጣት ባልቻሉ ነበር።

1. Carlo Zaghi: ibd p. 128



እንደምንረዳው ኢጣሊያ ግብጽ ከነበራት ይዞታዎች ብቻ እንድትወሰን የሚያስገነዝቡ ነበሩ። የእንግሊዝ መንግሥት የተነሳበት ዓላማ ግቡን ከመታለት በኋላ ወዲያውኑ ራሱን ለማገለል መርጧል። የኢጣሊያ መንግሥት በእንግሊዝ መንግሥት ግፊት በመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የቅኝ ገዢነት ለመያዝ ከታላላቆቹ መንግሥታት ቁጥር በመግባቱ ተደስቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀስ በቀስ በተጠናከረ መልክ ወረራውን ቀጥሎ ፍልሚያው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል ብቻ ተወስኖ በ1928 ዓ.ም መላውን ኢትዮጵያ በመያዝ መደምደሚያ መስሏት ነበር። ይህ የተባለው ፍልሚያ በጦር ሜዳ ብቻ ሣይሆን በዲፕሎማሲም ጭምር ስለሆነ ሁኔታውን ለማብራራት አንዳንድ የታሪክ መዝገቦች ማገላበጥ ያስፈልጋል። ምጽዋ በወረራ እንደተያዘች ከአንድ ወር ተኩል በኋላ የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ ምጽዋ ዘምቶ በነበረው ጦር ማይሣ ለተባለው በምጽዋ የኢጣሊያ መንግሥት ተጠሪ የኢትዮጵያና የግብጽ ወሰኖች በዝርዝር እንዲያስረዳው በጠየቀው መሠረት ሲኞር ማይሣ ማርች 19/1885 ዓ.ም በፃፈው ማብራሪያ ደብዳቤ እንደሚያስረዳው በምጽዋ አውራጃና በኢትዮጵያ ያለው ወሰን በአጭሩ በሚከተለው አኳኋን ገልጾታል።[1] «ስለ ወሰን ጉዳይ ግብጾችና ኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት አመለካከት የላቸውም። ኢትዮጵያውያን ወሰናቸው እስከ ባሀር መሆኑን ራሷ ምጽዋም ወደ ባቸው መሆንዋን ሲያምኑ ግብጾችም ወሰናቸው እስከ ደጋ ሀገር ስር ይደርሳል ብለው ያምናሉ።

በተጨባጭ ግን ባለው ሁኔታ የጆንስቶን ካርታ በመመርኮዝ ሰሐቲ የግብጽ መንደር ለትሆን ዓይለት ግን የኢትዮጵያ መንደር ናት፤ ስለዚህ ወሰኑ መሆን ያለበት በሁለቱ መንደሮች መሀል ነው። ከምጽዋ እስከ ሰሐቲ የአራት ሰዓት የእግር መንገድ ነው። ከሰሐቲ እስከ ዓይለት ደግሞ የሌላ አራት ሰዓት የእግር መንገድ ነው። ስለዚህ ወሰኑ የሚገኘው ከምጽዋ የስድስት ሰዓት መንገድ ላይ ነው። ሞንኩሉ ከምጽዋ የአንድ ሰዓት መንገድ ነው። ሲኞር ኑካርዲ በምጽዋ ነዋሪ የኢጣሊያ ዜጋም ይህንኑ ሀቅ ነው ያረጋገጠልኝ። ማርኩጕሉ በይ የግብጽ ዜጋ የጉምሩክ ሠራተኛም እንግሊዛዊ አድሚራል ሒወት በኢትዮጵያ በእንግሊዝና በግብጽ መሐከል ለምምነት ቡተፈራረሙበት ጊዜ የዓይለት ጉዳይ በቃል ተነጋግረንበት የኢትዮጵያ ግዛት መሆንዋን በቃል የተስማማንበት ጉዳይ ነበር ብሎ አስረድቶኛል። አድሚራል ሒወት ዓድዋ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ስላደረገው ውይይት Blua Book Abysainia 1884 page 3 በፃፈው መጽሀፍ እንደገለፀው ንጉሡ (አጼ ዮሐንስ) የግብጽ ወታደሮች የሞንኩሉ ለቀው በሙሉ ወጥተው እንደሆን ብለው ቢጠይቁኝ እነሱተኛ ቁጥር ብቻ አሉ ብዬ መለስኩላቸቸው፤ ብሎ መግለፁ ይህ ቦታ አግብጾች የተፈቀደላቸው የመጨረሻ የወሰን ክልል መሆኑን ያስረዳል። ስለሆነም በአሁኑ ሁኔታ ዛሬ ዓይለት የኢትዮጵያ ስለሆነች ከንጉሡ ጋር መቆራረጥ ካልተፈለገ ዓይለት ልንይዛት አንችልም። ከምጽዋ በስተደቡብ ከባህር እስከ ተራራዎች ያሉት የሻሆ ጐሣዎች ግብጽ በስም የእኔ ግዛት ናቸው ስትላቸው በተግባር ለኢትዮጵያ ግብር ስለሚከፍሉ የኢትዮጵያ ግዛት ናቸው።

1 Vico Mantagazza: Da Masawa a Saati p. XI

ሌላ ከኢጣሊያ መንግሥት ተልኮ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ለመነጋገር ፈልጎ አሥመራ ደርሶ ወደ አድዋ ጉዞውን ለመቀጠል ከራስ አሉላ ፈቃድ ይጠብቅ የነበረ ፌራሪ የተባለው መልእክተኛ አሥመራ እንደደረሰ ከአሥመራ (ትግሬ)[1] ብሎ ማርች 23/1888 ዓ.ም ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጻፈው ደብዳቤ ኢጣሊያ ምኞቷን መፈጸም በመቃወም አጼ ዮሐንስ ግደለው? እንደሆነ ሊሆን እንደቻለ ብሎ ጥያቄዎች ራስ አሉላ አትርዉሳት? በሱዳን በኩል የግብጽ እስረኞች ለመክሰስ? መሆኑን ስለገለፁላቸው ቅሬታው ሊበርድ ችሏል። ከዚህ በኋላ ስለተጠቀሰው ሊቸር ፈራሪ አጼ ዮሐንስ ዘንድ በኢጣሊያ መንግሥት ስም ስለደረገው ተልእኮ የኢትዮጵያ ወዳጅ የነበ ረችው ሩሲያ በሴንት ፒተርስበርግ ይወጣ የነበረው ጋዜጣ[2] ጁን 25/1885 ከአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የዜና ወኪል እንዳስታወቀው ያወጣው አትመ? አጼ ዮሐንስ ለፈራሪ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በወዳጅነት እንዲኖሩ ከተፈለገ፤ 1ኛ. ከምጽዋ በስተቀር ማንኛውም የተያዘ ሀገር ወደበኋ? እንዲለቁ 2ኛ. የኢጣሊያ ወታደሮች የኢትዮጵያ መሬቶች ከሆኑ ከአርቄቆ፤ ሞንኩሉና አራፋሊ እንዲለቁ 3ኛ. ኢጣሊያ ከሸዋ ንጉሥ ጋር ያላት ግንኙነት አቋርጣ ሚሲዮናውያን እንዳትልክለት 4ኛ. ኢጣሊያ የንግድ ውል ከኢትዮጵያ ጋር እንድታደርግ በአንፃሩም ንጉሡ ምፅዋ የኢጣሊያ ይዞታ መሆኑን ያውቁላታል የሚል ነበር።

ስለ ሰሐቲ ጉዳይ በኢጣሊያ ወታደሮች መያዝ በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ከራስ አሉላም ሆነ ከኢጣሊያ ባለሥልጣኖች ደብዳቤ ተለዋውጠውበት ስለነበረ የኢጣሊያ የጦር ሚኒስትር ሪቴ? ኖቬምበር[3] 12/1886 ዓ.ም ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጻፈው ደብዳቤ እንደ ሚከተለው ያብራራል። «በወታደራዊ ትችም? ስንመለከተው ሰሐቲን ይዞን መቆየት የሚደገፍ አይመስለኝም። ምክንያቱም ራቅ ያለ ስለሆነ ለእኛ ድክመት ሊያመጣብን ይችላል። በሚሸኩትክ? ይዞን መቆየት ግን እደግፋለሁ። ጠላት አደጋ ለመጣል ቢሞክር ልንመልሰው፤ ልንማርከው፤ ወይንም ልንደመስሰው እንችላለን። ይህ ከተከሰተ ደግሞ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን በአስቸኳይ መንቀሳቀስ እንችላለን። ነገር ግን ሰሐቲ በኢጣሊያ ወታደሮች ልንይዛትም እንችላለን። ይህ ከሆነ ግን ምሽግና የወታደር ሰፈር መሥራት ያስፈልገናል። ምክንያቱም ድንገት ጠላት አደጋ ቢጥልብን ዘምንኩሉ ወይንም ከምፅዋ እርዳታ እስከሚመጣላቸው መከላከል እንዲችሉ ማለት ነው። ነገር ግን የሁለተኛው የሰሐቲ መያዝ እግራውቅ? ከራስ አሉላ ጋር የሚያቀያይመን ስለሆነ ብናስወግድ ይመረጣል። ስለዚህ የመጀመሪያ ዘዴ ብንጠቀም የተሻለ ይመስለኛል» ብሎ ሃሳብ አቅርቦ ነበር። በሁኔታው ሁለቱ ሚኒስትሮች ስለተስማሙበት ለጦር አዛዥ በተግባር እንዲያውሉት ትእዛዝ ይተላለፍለታል። በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጻፈው ደብዳቤ የሮማና ሰሐቲ በወታደርና በመድፍ ያጠነከርን ስለሆነ ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ያረጋግጣል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. XVII

2 . Vico Mantegazza: Ibd p. XXIII

3. Vico Mantegazza; Ibd p. XXI



ጀንዋሪ 18/1887 እንደገና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጻፈው ደብዳቤ የወታደሮችን በሮማና በሰሐቲ መስመር ራስ አሉላ የደነገጠ መሆኑን ገልጾ ከራስ አሉላ ጋር ይገኝ የነበረው ማሊምቢኒ ከፒያኖና ግቨዋሩ? የተባሉ ጣሊያኖች ራስ አሉላ እንዳሰራቸውና ጣሊያኖች ከተባሉ ቦታዎች ካልወጡም እንደሚገድላቸው የዛተ መሆኑን ገልጾ፤ ነገር ግን ሊያስፈራ ሩን ለመፈለግ ብቻ እንደሆነ እክሉ አስታውቋል።[1]

ጀንዋሪ 25 የሰሐቲ ጦርነት ተካሄደ። ራስ አሉላ ጣሊያኖች ሰላየሉበት ወደኋላ አፈገፈገ። ወደ ድንኳኑ ተመልሶ እስረኞች በሙሉ አንገታቸውን እንዲቆረጡ አስቦ ነበር። ነገር ግን ፈረንሣዊው ቄስ አባ ኩልቦ[2] ፍቃት ሊሰጣቸው ከሰፈሩ ከአኩሩር መጥቶ ስለነበረ ራስ አሉላን ለምኖ አስጣላቸው። ቄሱ አባ ኩልቦ ቄስ ብቻ አልነበረም ምሁርም ነበረ። የኢትዮጵያ ሐቀኛ ወዳጅ ነበረ። ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ጠውልቃዊ መጽሀፍ ፅፏል። ጣሊያን ሀገራችን ስትገባ የማይፈለጉ ተብለው ከሀገር ሲባረሩ በምትካቸው የመጡ የኢጣሊያ ዜጎች ሚሲዮናውያን ግን ከመንግሥታቸው ጋራ ከማደር በቀር በትምህርት ያልበሰሉ ነበሩ። ምሁራን ኢትዮጵያውያን ቄሶች ለማፍራት ፍላጎትም ችሎታም ያልነበራቸው ነበሩ። ፈርዲናንዶ ማርቲኒ በ1891[3] በደረሰው መጽሀፍ በኤርትራ ስለነበሩ ሶስት ፈረንሣዊያን ሚሲዮናውያን ላዛሪስት አስተያየት ሰጥቷል። 1ኛ. አቡነ ክሩዜ የመሰው ኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ጳጳስ ሥጋ ሥርዓት የተሞላበት አነጋገር አላቸው ብለው አወድሷቸዋል። 2ኛ. አባ ኩልቦ በመጀመሪያ ጊዜ ጣሊያንን ይቃወም ስለነበረ ከኢጣሊያ ባለሥልጣኖች እገዳ ደርሶበት ነበር፤ አሁን ግለሰቡ አክሩር ነው የሚኖረው፤ እኛው ሐጂ አላገኘሁትም፤ አላየሁትም፤ ስለሱ ምንም አላውቅም መናገርም አልችልም ብሎ ነበር። 3ኛ. አባ ፒካር የያ እምሥት ዓመት በከረን ዘኖራል። ከሱ ጋር ረጅም ውይይት አድርጌያለሁ። ለማተርብለት ክርክር ሁሉ በመጀመሪያ ጊዜ ቄስ በመሆን መልስ ሰጠኝ። በኋላ ግን የፖለቲካ ሰው በመሆን የሃይማኖት ሰብ የምታወም መሆኑን ስለገለፀኩለት ለአንድ ኢጣሊያዊ ዜጋ የፓርላማ አባል ስለሕሊና ነፃነትና ስለ ሃይማኖት ነፃነት ማስተማሩ የገረመው መሆኑን ገለፀልኝ፤ እኔም እንዲ ሳመኝ አልክድም፤ ስለዚህ ይህ ሰው ካወቁቸው ሁሉ ከፍተኛ ብቃት ያለው ተናጋሪ ጥልቅና ትክቢታዊ ሙልሶች የሚሰጥ ሰው ሆኖ አገኘሁት ብሎ አስተያየቱን ሰጥቷል። የሁለቱ ሰዎች ማርቲኒና ፒካር አለመግባባት ሲገመገም እውነትም የሚገርም ነው። የያ እምሥት ዓመት በአፍሪቃ የኖረ አንድ ተራ ቄስ ለአንድ የፓርላማ አባል ስለነፃነት ማስተማር ሲችል ሁለቱ የካቶሊክ የሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ላቲናውያን የሚባሉ ናቸው። እንደደንቡ ከሆነ ኢጣሊያም እንደ ፈረንሣይ በፓርላማና በዲሞክራሲ የምትመራ ሀገር ነበረች። ነገር ግን የፈረንሣይ ዲሞክራሲ ከሀገሩ ሕዝብ የተዋሃደ ስር የሰደደ ስለሆነ ለአንድ ኢጣሊያዊ የፓርላማ አባል ለአንድ የኢጣሊያ ሚኒስትርም ስለ ዲሞክራሲና ነፃነት አንድ ፈረንሣዊ ተራ ሰው ለማስተማር ይችላል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. XLI

2 Carlo Zaghi Ibd p. 127

3 F: Martini: Nell' Africa Italiana p.236

የማርቲኒ ፍላጐት ፈረንሣውያን ሚሲዮናውያን ከኤርትራ እንዲባረሩ ከፒካር ፍንጭ ለማግኘት ነበረ። ለምሳሌ እንግሊዝ ይሄቺው ከነበሩ ቅኝ ግዛቶች ዜጐቻቸው ያልሆኑ ሚሲዮናውያን የሚያባርር ቢሆኑ ኖሮ እንዲሁም ፈረንሣዮች ዜጐቻቸው ያልሆነ እሚያባርሩ ቢሆኑ ኖሮ ዛሬ የሚታየው የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ከሞላ ጐደል በእኩል ደረጃ መስፋፋት አይታይም ነበር። እነዚህ ሁለት በዲሞክራሲ የሚያምኑ ሀገሮች ግን እንዲህ ያለ እርምጃ አልወሰዱም፤ ኢጣሊያ ብቻ ናት እንዲህ ያለ ግፍ ለመፈፀም የምትችለው። ጉዳዩ የሶስት ፈረንሣውያን ሚሲዮናውያን ጉዳይ አይደለም። ጉዳዩ ዘረኝነት ነው። የዲሞክራሲና ፀረ ዲሞክራሲ ትራኔ ነው። ዛሬም ቢሆን ጣሊያኖች ዲሞክራሲ የተቀበሉት ስለተሸነፉ ሣይወዱ በግድ ነው። ሁለቱ አገሮች ስለነፃነትና ዲሞክራሲ ያላቸው ርእዮተ ዓለም ዲያሜትሪካል ተቃራኒ የሆነ አስተሳሰብ ነው። ሁለት የተለያዩ ሕዝቦች መሆናቸውን ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ፈርዲናንዶ ማርቲኒ አክራሪ ዘረኛ ነኝ ባይ ነበረ፤ የነጭ ዘር ነኝ ብሎ መቶ ጊዜ ቢያወራ አሪያን ዘር እንዳልሆነ የታወቀ ነው። እንዲሁም ሃምሣ ከመቶ የሚያህሉ ጣሊያኖች ነጭ ዘር አርያን አይደሉም። አባ ፒካር ግን እማርቼ ዘሩን ባላውቅም ንፁህ ነጭ ዘር አርያን ሣይሆን እንደማይቀር ይታመናል። ነገር ግን እንደ ሀገሩ ሕዝብና መንግሥት በዘረኝነት ስለማያምን ለአንድ ኢጣሊያዊ የፓርላማ አባል ስለ ዲሞክራሲ ትምህርት ሊሰጥ ችሏል። ጀንዋሪ 26/1887ዓ.ም. የዶጋሊ ጦርነት የተካሄደበት ዕለት ነበር። ከጦርነቱ በፊት የተፈፀሙ ሁኔታዎች ላይ እንደገለፅኩ ሆኖ ራስ አሉላ ሣሊምቢኒ እጁን ታስሮ በዓይነ ቁራኛ እየተጠበቀ በአንድ ተራራ ሆኖ የጦርነቱ ተመልካች እንዲሆን አድርገውት ነበር።[1] ራስ አሉላ ስለ ጦርነቱ ውጤት ለአፄ ዮሐንስ ሲጽፍ አምስት ሺህ የኢ ጣሊያ ወታደሮች እና[2] ስድስት ጀነራሎች ተገድለዋል ብሎ ነበር የነገረው። ከአፄ ዮሐንስ በፊት ግን የኢትዮጵያ ድል ዜና የሰማ ንጉሥ ምኒሊክ ነበረ። ለሱ ግን (1500) አንድ ሺህ አምሥት መቶ[3] ጣሊያኖች ተገድለዋል ብሎ ነበረ ያበሰረው። ከራሱ ወገን ግን (200) ሁለት መቶ ብቻ እንደሞቱበት የተጋነነ የሣሊምቢኒ ግምት ግን 2000 ኢትዮጵያዊያን በዶጋሊና ሰሐቲ ጦር ነቶች እንደሞቱና እንደቆሰሉ ብሎ ነበረ። ቆይቶ ግን ከአፄ ዮሐንስ ለምኒልክ የተጻፈ ትክክለኛው ለማወቅ ተችሏል።[4] አዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ ጣሊያኖች ወደ ሀገራቸው ሪፖርት ሲያስተላልፉ በዶጋሊ ጦርነት የተገኘው ድል ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሸዋ ሰዎችም ጭምር ከልክ በላይ ደስታቸውን እየገለፁ ናቸው ብለዋል።

በእንጦጦ ይገኝ የነበረ ትራቬርሲ[5] የዶጋሊ ድል በእንጦጦ ሲሰማ የነበረው ሁኔታ ለአንድ ጓደኛው በፃፈው ደብዳቤ በሚከተለው ዓይነት ያብራራዋል።

---

1. Carlo Zaghi: ibd p.129
2. Vico Mantegazza: ibd p.74
3. Carlo Zaghi: ibd p.145
4. Carlo Zaghi: ibd p.144
5. Carlo Zaghi: ibd p.145



እንደ አንድ መብረቅ ነው ጭንቅላቴ መሀል የመታው፤ ብዙ ድካሞችና ገንዘቦች የፈሰሰባቸው ብዙ አትዶች መክሸፋቸው ብቻ ሣይሆን ሀገሬ በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ገንዘብና ብዙ የሰው ሕይወት ሊጠፋበት የሚችል የጦርነት አዘቅት እንደወደቀች ይታየኛል። አቢሲኒያን 20–30 ሺህ ወታደር አስልፎ ማሸነፍ አይቻልም። ንጉሠ ነገሥቱ (300,000) ሶስት መቶ ሺህ ገደማ ወታደሮች ማሰለፍ የሚችሉ መሆናቸውን ስናስብ የኢጣሊያ ሠራዊት ከተለው ቁጥር (20,000) ሃያ ሺህ እጥፍ ማሰለፍ ይኖርብናል (40–60 ሺህ ወታደር)። የራስ አሉላ ዜና በደረሰበት ዕለት የሐበሾች ደስታ ሽቀዎቼም ጭምር እስከ ማበድ ደርሶ ነበር። ንጉሡ ብቻ (ንጉሥ ምኒልክ) ይመስለኛል አዝነው ነበር። ምክንያቱም በጣም ከፍት የሆነ እንጎል ያላቸው ሰው ስለሆኑ እሳቸው ብቻ ናቸው የሁኔታው ከባድነት ሊገምቱ የሚችሉ። እርስዎም ሊገባዎት እንደሚችል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተገኘው ድል ከሀረር ጋራ በማያያዝ አሁንም በዶጋሊ በተገኘው የራስ አሉላ ድል በእነዚህ «ኔግሮች» ጭንቅላት የማይሸነፉ መሆናቸውን የሚል እምነት ሊያድርባቸው ችሏል።

እኛ እርምጃ በምንወስድበት ጊዜ ግን ይህ ሁሉ ደስታቸው ወዴት እንደሚገፋፋቸው አላውቅም። እዚህ እኛ ሁላችን ደህና ነን። እኔ እንደሚመስለኝ የሚያሰጋን አደጋም የለም፤ ነገር ግን ከዛሬ ነገ ከሀገር እንድንወጣ ከንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ይመጣል ብዬ እየጠበቅሁ ነው በማለት ጽፈዋል። እዚህ ላይ ስለ ዶጋሊ ጦርነት ሲነሳ ማስታወስ የሚገባን አንድ ነገር አለ። የጠቡና የጦርነቱ መነሻ ጣሊያኖች በሰሀቲ ጦር ሰፈር ሠርተው ራስ አሉላ ለቀው እንዲሄዱ ደጋግመው ቢለምኗቸው እንለቅም በማለታቸው ነው። ጣሊያኖች በዶጋሊ ጦር ሰፈር አልነበራቸውም፤ ራስ አሉላ ግን ከጊንዳዕ ከመነሳቱ በፊት ለጣሊያኖች እስረኞች ከሰሀቲ እና ሞንኩሉ መሀል ሄጄ እዋጋለሁ ብሞትም ግድ የለኝም ብሎ ሲነግራቸው እንደ ትንቢት ነበር የተናገራቸው። ጦርነቱ እንዲካሄድ በሁሉ ሰው ሲጠበቅ የነበረው በሰሀቲ ነው። እንደታሰበም ጀንዋሪ 25/1887 ዓ.ም. በሰሀቲ ጦርነት ተከፈተ። የራስ አሉላ ጦር ግን መጠነኛ ተቃውሞ ስለአጋጠመው አፈገፈገ።

በዚህ ጊዜ ጣሊያኖች አሸነፍን ብለው ተደሰቱ። የራስ አሉላ ጦር ግን ጦርነት ፈርቶ አልነበረም የሸሸው። የአንድ ትልቅ ጀነራል የጦርነት ስልት ነበር ያካሄደው። ጣሊያኖች ራሳቸው የዚሁ ዓይነት ስልት አድናቆታቸውን ገልፀዋል። የራስ አሉላ ጦር ወደኋላ አይደለም ያፈገፈገ ወደ ፊት ወደ ሞንኩሉ ነበር የገሰገሰው። ወደ ሞንኩሉ በሚገሰግስበት ጊዜም ሰሀቲ የነበረው የኢጣሊያ ጦርም እንዳይንቀሳቀስ መንገድ ዘጋበት። ይህ በዚህ እንዳለ ባልታሰበ ሁኔታ ከሞንኩሉ ለእርዳታ ወደ ሰሀቲ ይጓዝ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ጀንዋሪ 26/1887 ዓ.ም. ከጧቱ በ2:00 ሰዓት በዶጋሊ ተገናኙ። የራስ አሉላ ጦር በረቀቀ የጦር ስልቱ በመጠቀም ወዲያውኑ ተኩስ አልከፈተም። ወደ ሰሀቲ የሚወስደው መንገድ አስቀድሞ ተዘግቶ ነበር፤ አሁን በጐን ግራና ቀኝና ከሞንኩሉ የሚያገናኘው መንገድ ከበባና መዝጋት ተያያዘው።

የራስ አሉላ ጦር ከበባ በሚያደርግበት ጊዜ ገገር ተራራዎችን በቁጥጥሩ እ ውሉ ነበረ። የኢጣሊያ ጦር ሁኔታውን ከተረዳ በኋላ ወደ አንድ ኮረብታ ተሰበሰበ። የተኩስ ልውውጥ

እየቀጠለ ነበር፡ ዋናው ጦርነት የተካሄደው ግን ከበባው ካለቀ በኋላ ነው። የቆየው ለጥቂት ደቂቃ ብቻ ነበር። ከቀኑ 6:00 ሰዓት ጦርነቱ አብቅቶ ነበር። ጣሊያኖች ከሞንኩሉ ለእርዳታ ለሄደው ጦር (ማለት በዶጋሊ ያለቀው) ሌላ ጦር ለእርዳታ ልከው ነበር።

የራስ አሉላ ጦርም ድል አደረኩ ብሎ አልተቀመጠም። ምናልባት በሞንኩሉ ላይም አደጋ ለመጣል ወይም ለስለላ ብቻ ፈጣን ፈረሰኞች ወደ ሞንኩሉ ሲያመሩ ለእርዳታ ከሚመጣው የኢጣሊያ ጦር ተገናኙ። ጣሊያኖች ጦርነት ለመግጠም የመጡባቸው መስኳቸው ቦታ ቦታቸውን ያዙ። የኢትዮጵያ ፈረሰኞች ግን በመጡበት አኳኋን ተመለሱ።



Ras Alula.



Tommaso De-Cristoforis.

1. ራስ አሉላ በዶጋሊ ጦርነት የኢትዮጵያ አሸናፊ ጦር መሪ 2. ኮሎኔል ዴ ክሪስቶፎሪስ በዶጋሊ ጦር ሜዳ የተገደለ 3. ጀነራል ጂኔ የምፃዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በዶጋሊ ሽንፈት ምክንያት ስራውን እንዲለቅ የተደረገ።



ጀነራል ጂኔ በምፅዋና አካባቢው ሰፍሮ የነበረ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በዶጋሊ ጦርነት ጣሊያኖች ከደረሰባቸው ሽንፈት በኋላ ከስልጣኑ ወርዶ ተወቅሶ ወደ ሀገሩ የተመለሰ በምትኩ የተሾመ ጀነራል ሳሌታ በምፅዋ የመጀመሪያ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በቅድሚያ ያከናወነው ሥራ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በጦርነት ፍልሚያ የሚገኙ ሀገሮች መሆናቸውን አጥኖ በማውጣት ነው፡፡

Generale Genè



## 2. ስለ ዶጋሊ ጦርነት የሻምበል ታንቱሪ ሪፖርት

የውጊያዊ እርዳታ የተሰጠው የኢጣሊያ ጦር ይመራ በነበረው ሻምበል ታንቱሪ የተላከው ነበር። እሱም ሀሳቦች የሌሉ መሆናቸውንና መንገድ ክፍት መሆኑን ከአረጋገጠ በኋላ ትዕዛዙን ቀጠለ። ከአፈፀመው ተልእኮ ራሱ የፃፈው ሪፖርት በሚከተለው አኳኋን [illegible]። «ጥቂት[1] ጊዜ በኋላ አንድ ባዶ ግምባ ጥይት የነበረበት አየሁ፤ ፍተሻ ያረገ [illegible] የሞላት ወታደር አዩ። አስተርጓሚው ሁለት የአካባቢ ሰዎችን ወደፊት [illegible] ጦር በሙሉ እንዳለቀና አውነም ኢትዮጵያውያን ብዙ እንደሆኑ በታቸውን እንደያዙ መሆናቸውን ነገሩኝ። እኔ ግን የማጋገነ ሙሰለኝ፤ ጉዞውን ቀጠልኩ፤ አስተርጓሚው በፍርሀት ተውጦ ወተሰኘ። ትንሽ እንደሄድን ፊት እየሄዱ የሚፈትሹ የነበሩ ወታደሮች የሀበሻ ፈረሰኞች እየገ ብለው ነገሩኝ። ቦታ ቦታችንን ያዝን። ሶስት ወታደሮች የኢትዮጵያ ፈረሰኞች ወደ ሄዱበት እንዲከታተሏቸው ላክሁ። በዚሁ ጊዜ አስተርጓሚውና ባሺቡዙኮች ጠፉ። የላኳቸው ሶስት ወታደሮች ወደ ሰሁቲ በፍጥነት የሚጓዙ ሶስት አራት የሀበሻ ፈረሰኞች ብቻ አየን ብለው ተመልሰው ነገሩኝ። እርግጠኛ ለመሆን የመቶ አለቃ ማንቶሪ ከጥቂት ወታደሮች ጋር መንገዱን እንዲፈትሽ ላክሁት። እሱም ተመልሶ ጠላት እንደሌለ፡ የሞቱ ግመልና የግመል መጫኛ፤ የጥይት ባዶ ግጥኖች፤ የሥጋ ቁርቁሮች አየሁ ብሎ ተመልሶ ነገረኝ። በቦታው ደገኙ የነበሩ ሁለት የማጋሚያ እረኞችን ይዞ አስርኳቸው። እነሱም ሀበሾች የእኛን ወታደሮች ያጠቁበትን ቦታ አሳዩኝ። በቦታው ስንደርስ በቅርብ ጊዜ ከተቀበሩ ጥቂት የሀበሻ ሬሳ በስተቀር ሌላ ምንም ምልክት አልነበረም። እለፍ ብለን በአንድ ትንሽ ኮረብታ አንድ የቆሰለ የኢጣሊያ ወታደር አገኘሁኝ። እሱም የእኛ ወታደሮች በሙሉ እንደሞቱ ነገረኝ፡ ትንሽ እለፍ ብሎም ሬሳቸው እንደሚገኝ ነገረኝ። የዚሁ አማኝ ዜናም አላመንኩም። ወደ ነገረኝ ቦታ አመራሁ። በትንሿ ኮረብታ ስር ትልቁን አደጋ ተመለከትኩ። ሁሉም በመስመር ተጋድመው ነበር፤ አንደ አንድ ሰልፍ። የሪፖርቱ የመጨረሻ ቃላቶች አከራካሪ ሆነው በታሪክ ተመዝግቧል። በመጨረሻ የኢጣሊያ ወታደሮች ጥይት ስላለቀባቸው በሳንጃ ጨበጣ ውጊያ ነበረ የተዋጉት። በሳንጃ የተዋጉ ወታደሮች በመስመር ሆነው ተጋድመው ሞተው ሊገኙ አይችሉም። በተጨማሪ የዶጋሊ ጦርነት በሚከበርበት ጊዜ እነዚህ ቃላቶች እንዳይደጋገሙ ትዕዛዝ ተላልፎ ነበር።

## 3. ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ጀነራል ጂኔ ያወጣው ፕሮግራም

ጃንዋሪ 29/1887 ዓ.ም. በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጂኔ ሁለት ሪፖርቶች ለሙሉ ጉዳይ ሚኒስትር ጽፏል። በጽሁፉም የሰነዘረው ሀሳብ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው።

1 F.I.C.I Vol. I p.[illegible]

ስለ ሰሀቲና ዶጋሊ ጦርነቶች ከገለፀ በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት መቋረጡ ገልጦ ከ8–10 ሺህ ወታደሮች የጦር መርከቦችና ሌሎችም እንዲላኩለት ጠይቆ በጃንዋሪ 25 እና 26 በተደረጉ ጦርነቶች በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ፍልሚያ እንገኛለን በማለት ገልጦ አሁን ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው ብሏል። አፋጣኝ እርምጃ ወስደን በጦር ሜዳ ሽንፈታችንን መበቀል ነው። ወታደራዊ ንቅናቄዎች በምናደርግበት ጊዜ በሚከተሉት ሁኔታዎች መታገዝ አለበት። 1ኛ) ሐባብ፣ ቤኒዐምር የመሳሰሉት ወዘተ...ከእኛ ጋር የሚስማሙ ጎሣዎች በእኛ እርዳታና መሪነት በሰሜን በኩል ወደ ኢትዮጵያ መገፋፋት፣ 2ኛ) የሱዳን ደርቡሾች በመረብ በኩል ወደ ዓድዋ በአዝማን ዱግማ አሥራ ሁለት ሺህ ተዋጊዎችም አሉ ስለሚባል ወደ ጎንደር መተማ እንዲያመሩ ማድረግ፣ 3ኛ) በራሱ በሐማሴንም በራስ አሉላ አገዛዝ ያልተደሰቱ ሰላሉ በግልፅ የማይታይ ግን ኃይል ያለው የእስላሞች ወገንም ከሀበሻ ጭቆና ለመላቀቅ ስለሚፈልግ ማደፋፈር። በዚሁ ሁኔታ በጉስና አሥመራን መያዝ እንችላለን። ወደ ከሰላና ካርቱምም የሚወስደው መንገድ አቋርጠን ኢትዮጵያን በእኛ ላይ አቅመ ቢስ ልናደርጋት እንችላለን። ምክንያቱም በሁሉም መንገድ እንዳየነው ከኢትዮጵያ ጋር በሠላም ለመኖር ወይንም ውሎች ማድረግ ጨርሶ የማይቻል ነው። በደጋ ኢትዮጵያ ይዞታችን ማረጋገጥ ከቻልን ተጽእኖ አለው። ጄኔራሉ ሌላ ደብዳቤም ጽፎ ነበር። ሚኒስትሩ ግን ሀሳቡን ውድቅ አድርገውበታል። አሥመራ ውስጥ ሰላዮች ናችሁ ተብለው አራት ጣሊያኖች ታስረው ይገኙ ነበር። ራስ አሉላ እነዚህ ጣሊያኖች እንዲለቀቁ አንዳንድ ከጣሊያኖች ጋር የሚተባበሩ ሰዎችን አሳልፈው እንዲሰጡት፣ አንድ ሺህ ጠመንጃዎች ወደ ራስ አሉላ እንዳይገቡ በጣሊያኖች ትእዛዝ የታገዱበት እንዲላኩለት ጠይቆ ነበር። በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጄኔራል ጄኔ ለራስ አሉላ ጥያቄ አሟልቶ አንድ ሺህ ጠብመንጃዎችን መላኩ በሰማ ጊዜ ከኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሮቢላንት ማርች 18 ቀን 1887 ለጄኔራል ጄኔ ደብዳቤ ጽፎ አድራጎቱን ተቃውሞ ጄኔራል ጄኔ ከቦታው ተነስቶ በምትኩ የመጀመሪያ ጊዜ ኢጣሊያ ምፅዋን በወረረች ጊዜ የጦር አዛዥ የነበረው ጄኔራል ሣሌታ የተሾመ መሆኑን ይገልፁለታል።[1] የጠብመንጃዎች የሽፋን ምክንያት ሆነ እንጂ ለጄኔራሉ የስልጣን መውረድ ዋና ምክንያት ግን በዶጋሊ ጦርነት መሸነፍ ነው።

ይህም በዶጋሊ ጦርነት ምክንያት በኢጣሊያ መንግሥት ምን ያህል ውዝግብ ተፈጥሮ እንደነበረ ያስረዳል። የደብዳቤው ይዘት በአጭሩ እንደሚከተለው ነው። «የጦር መሣሪያዎች ለራስ አሉላ መስጠትዎን ስሰማ በጣም ነው የደነገጥኩ። በተለይም ስለዚህ ጉዳይ ጥብቅ መመሪያ ተሰጥቶ ስለነበረ ነው። ሁኔታውን ለምኒስትሮች ም/ቤት መቅረብ ስለነበረበት መስሉም ስለታየኝ አቅርቤው የክቡርነትዎ አድራጎት በሙሉ ድምፅ የማይደገፍ መሆኑን አምኖበት ይኸውም ለእርስዎ እንዲነገርዎት ስለታዘዘ ይኸም በሚሆንበት ጊዜ እርስዎ አሁን ባሉበት ስልጣን ለመቆየት የሚታረን በመሆኑ ያስከተለው ውጤትም እርስዎ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረው እንዲሰሩ ስለተወሰነ በጦር ሚኒስትሩ አቅራቢነት ጄኔራል ሣሌታ በቦታዎ ተተክቶ እንዲሰራ ተወስኗል።»

1. Vico Mantegazza,ibd, p.49-50



# 4. ፈረንሣይ፣ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ

የሀገራችን የባህር ወደቦች በቅኝ ግዛት መያዝ ይፈልጉ ከነበሩ ሀገሮች አንዷ ፈረንሣይ ናት። ስለዚህ ጉዳይ በፈረንሣይ የኢጣሊያ አምባሳደር ማርች 24/1887 ዓ.ም. ለሀገሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የፃፈው ደብዳቤ በአጭሩ መጥቀስ ጠቃሚ ይመስላል።[1] በአንድ ግብዣ ላይ አምባሳደሩ የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አነጋገር ስለምፅዋ ወረራ የሰሀቲ የዶጋሊ ጦርነቶች ወዘተ... አንስተው ሲነጋገሩ ፈረንሣይና ኢትዮጵያ የወዳጅነት ውል ለማድረግ እቅድ እንደነበረ አምባሳደሩ ለሚኒስትሩ አስታውሰው ከውሉ ዋና ዋና ነጥቦች፣ 1ኛ) በሁላና አካባቢዋ የፈረንሣይና የኢትዮጵያ ጥምር አስተዳደር እንዲመሰረት፣ 2ኛ) ከኢትዮጵያ ወይንም ወደ ኢትዮጵያ የንግድ እንቅስቃሴ ከጉመሩክ ነፃ እንዲሆን፣ 3ኛ) ፈረንሣይ ለኢትዮጵያ ከማንኛውም ሌላ ሀገር ወረራ ዋስትና እንድትሆናት የሚሉ ይገኙባቸው እንደነበረ ሲገልፁላቸው ሚኒስትሩም እቅዱ የቆየና በምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል የቀረበ መሆኑን ገልፀው፣ ነገር ግን የፈረንሣይ መንግሥት ዓላማ ስላልሆነ ቆንስሉ ከእንዲህ ያለ አድራጎት እንዲቆጠብ መመሪያ የተሰጠው መሆኑን ነገረኝ፣ እኔም በበኩሌ ቆንስሉ ከፈረንሣይ ሚሲዮናውያን ተገፋፍቶ ሊሆን እንደሚችል ከገለጽኩላቸው በኋላ እሳቸውም የፈረንሣይ መንግሥት ለጊዜው ኢጣሊያ በምፅዋ መግባት አምና ተቀብሉታል፣ ምፅዋ በእንግሊዝ እጅ ከምትሆን በኢጣሊያ ቁጥጥር ብትሆን የፈረንሣይ መንግሥት ምርጫ መሆኑን አረጋግጠውልኛል ብሏል።

ብዙ ጊዜ እንደሚነገረው ኢጣሊያኖችን ገፋፍቶ ወደ ሀገራችን ያመጣቸው የእንግሊዝ መንግሥት መሆኑን ነው። ከዚህ በላይ በጠቀስኩት ጽሁፍ ደግሞ የፈረንሣይ መንግሥት ሥጋትም እንግሊዝ ምፅዋን እንዳትቆጣጠር መጣር ብቻ የተወሰነ ስለሆነ ኢጣሊያ ምፅዋን ብትቆጣጠር የፈረንሣይ መንግሥት የማይቃወም መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

በምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል ጽ/ቤት ጉዳዩ በቀላሉ የተፈታ አልነበረም። ለብዙ ጊዜ በሁለቱ ሀገሮች ውዝግብ ሲፈጥር ቆይቷል። ለምሳሌ ከላይ ከተጠቀሰው የሐሳብ ልውውጥ አንድ ዓመት በኋላ አፕሪል 1888 ዓ.ም. ማንቴጋትሣ የተባለው በምፅዋ የCorriere della sera. Illustrazione Italiana መጽሔቶች የዜና ወኪል የነበረው ስለ ፈረንሣይ ቆንስላ የሰጠው አስተያየት እንደሚከተለው ነበር።[1]

«ፈረንሣይ በምፅዋ የቆንስላ ጽ/ቤት ያላት ብቸኛ ሀገር ናት። የምታቀርበው ሰበብም የግሪክ ዜጎች መብት ለመጠበቅ ነው የሚል ነው፣ ምክንያቱም የራሷ ዜጋ በምፅዋ አንድ ሰው እንኳ የላትም።

1 Vico Mantegazza,ibd, p.49-50

ሁሉም እንደሚያውቀው በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል መልዕክትን ሁኖ አይደለም የሚተመጠው። በዶጋሊ የደረሰው ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት በምፅዋ በቁም መቶ የሚቆጠሩ ሐበሾች በመሃም ይኖሩ ነበር። ከዶጋሊ ጦር ኮት ማግስት ግን ሁሉም ተባረሩ። ይኸውም ማንም ሊገርመው አይችልም። እሩት የታወቁ ሐበሾች ግን ለክ እንደ ሌሎች መባረር ሊገባቸው ያልቻለት ተሰመሩ። ተፈላጊው ግን በፈረንሳይ ምክትል ቆንስል መኖሪያ ቤት ተገኙ። ምንም እንኳን ቆንስሉ መዝ ሉሚኝ ያለታረመ አብራተኛ ወዳይ የሰረው ቢሆንም የእኛ ጦር አዛዦች እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥበው ነበር። ሁሉም ያውቃል ምንም እንኳን ሐበሾች ፈረንሳይ የምትወዳቸው ዜጎች ባይሆኑም በፈረንሳይ ቆንስል ጽ/ቤት ከፍ ያለ የመጠጊያነት አተማመል ያገኙ እንደ ነበር የታወቀ ነው። ለሌ ቆንስል መርሰፕ ተቀደር ቢመጣም ሁኔታዎች እለ ተቀየሩም። ገልቶች ጉዳር እንዳይከናወኑ ብለ ፈረንሳይ የፈጠረችው ክርክር ብሎ ውዝግብ ፈጥሯል። ከእዚ በኋላ የተጠናከረው ኢጣልያና[1] ፈረንሳይ አምስት ጦር ተደምሮ ሊሆን ሚያዝያ 22/1887 ዓ.ም የሚከተለውን ዜና አሰራጭቶ ነበር። «ዛሬ ጠዋት ከዚህ በፊት በፈረንሳይ ቆንስል ጽ/ቤት እና በሐበሾች መካከል እንደኖ አውንም ቢሆን ይህ የጠየ ሥራ ለመተጠል የማይመለ ሁኔታ ክ/ማርያም የተባለው ቄስ እዚህ ምፅዋ ገብቷል። እሱ ደብዳቤዎችን ለመውሰድ በየወሩ ከከረን ምፅዋ ይመጣል። ደብዳቤዎችን እሱ ከመረከቡ በፊት የኢጣልያ ጦር ዕዝ ከፍቶ ያነባቸዋል። ምናልባት መንግሥታችን በጦርነቱ ምክንያት ወሰኑ ዝግ ነው ብሎ በእወጀበት ጊዜ እስረፈኝ ቀሬጥንት አሳለፈም። የሆይማኖት ሚሲዮና ውያን ቢሆኑም ለአገሬ ተገር መሆን ነበረባቸው። ለእሆንም ሉቁ እስተያየት ማድረግ ባለተገባ ነበረ። ምክንያቱም እንደሚታወቀው ይህ የይማኖታዊ ሚሲዮን ከሃይማኖት ጋራ ምንም ግንኙነት የሌለው ተግባር ሲያከናውን ነው የሚታየው። ነገር ግን የፈረንሳይ ሪፑብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ መንግሥታችን ባደረገው ተደጋጋሚ ጥያቄ መሠረት ደብዳቤዎችን ለመቀበል በየወሩ አንድ ቄስ ከከረን ወደ ምፅዋ እንዲመጣ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ተደርጓል። «ቄሱ ሐጉስ እዚህ በሚመጣበት ጊዜ እስከሚሄድ ድረስ በወታደር ዕዝ ታስር ይቆያል።

እሱም ሆነ አብረው የሚመጡ ሰዎች ከማንም እንዳይገናኙ ተደርጐ በልዩ ወደ መጠብት ይመለሳሉ። ነገር ግን ባለፈው ጊዜ አንድ ጠባቂ ኢጣልያዊ መኮንን ክልክል መሆኑን እያወቀ አንድ የፈረንሳይ ቆንስል አሽከር ከቄሱ ጋር ተገናኝቶ ለማነጋገር ደጋግሞ ሁለት ሶስት ጊዜ በመሞከሩ በኃይልም በመጠቀም ለመከላከል ተገዶ ነበር።»

በሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት ማለት በፈረንሳይና በእንግሊዝ የነበረው ተፎካካሪ ምክንያት የተጉዳን እኛ ነን። ኢጣልያ እንኳንስ ከዛሬ ወዲያ ቀኝ ግዛቷ ሊያስተዳድር የራሷን ሀገርም ለማስተዳደር የበቃችው ገቢት ዓመታት ወደ ሀገሬችን ከመምጣቷ በፊት ስለሆነ ሌሎች ሕዝቦች ለማስተዳደር ልማድና ችሎታ ያልነበራት የእንግሊዝ መንግሥት ለኢጣልያ እባልፎ መስጠት እኛን መጉዳቱ መገንዘብ ይኖርብታል።

1. Vico Mantegazza: Ibd p. 56



ኢጣልያ ነጻነቷን እንድታጣ ያገኘችው በናፖሊዮን 3ኛ የፈረንሳዮች ንጉሠ ነገሥት 140,000 /መቶ አርባ ሺህ/ ጦር በማገዙት፣ እንዲሁም በእንግሊዝ መንግሥት የዲፕሎማሲ ድጋፍ ነበረ። ኢጣልያ ግን ውለታዋን ረስታ እነዚህን ሁለት ሀገሮችን በመቃወንት መገፈስ ታያቸዋለች።

## 5. በኢትዮጵያ ላይ የጀነራል ባለታ የጦርት ዓዋጅ

የዶጋሊ ጦርነት ያስከተለው መዘዝ ቀላል አልሆነም። ጣሊያኖች የሽንፈታቸው መበቀል በሌለው ተያያዙት። የመጀመሪያ ሥር ፋሽሚያ በጎደጥ በደረሰባቸው ሌላ ሁለተኛ ክፉር ሽንፈት ድረስ አላደረሰም። ጣሊያኖች በአብሬት ተነሳስተው ከአጼ የሐንስ ምት በኋላ ትግራይን በሙሉ ይዘው አምባላጂ ደርሰው ወደ መሀል ሀገር በገሰገሱበት ጊዜ አጼ ምኒልክን አስቆጥቶ የአድዋ ጦርነት እንዲያስከትል ሁሉ፤ ኢጣልያ ከምፅዋ አልፋ ወደ ደጋው የኢትዮጵያ መሬት ማስፋፋት ተገፋ የዶጋሊ ጦርነት ካስከተለ በኋላ በኢትዮጵያ ላይ አወያየይ ጦርነት በእኛም ዓዋጀ እንደ ሚታወቀው አጼ የሐንስና መላውን ኢትዮጵያን አስነቀኗ‍ውና ስላሳው አጼ የሐንስ ጣሊያኖችን ከሀገሬችን ጠራርጎ ለማስወጣት ከተት መሪዊት ብሎ ዘምቶ እንዳለበው ግዳቀሰት በመትረፉ ጣሊያኖች እንዚእብሔርን ማመስገን ሊገባቸው በተቀጠት ግምት የዶጋሊ ሽንፈታቸውን በጦር ሚዳ ለማተበቀሉ ለበለጠ እብሪት ተነሳስተው ወረራቸውን ቀጥለው አምባላጂ ደርሰው ጎደጥ ላይ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተደረገው የጦር ሜዳ ፋሽሚያ በኢጣልያ ተሸናፊነት የመጀመሪያ ሥር መደምደሚያ ሆነ። በዶጋሊ ጊዜም የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሊቸር ሮቢላንት የኢትዮጵያ ጦር አራት ዘራፊዎች ናቸው ብሎ በመናገር የተሳለቀ ግምት እንደሰጠ ሁሉ በ1891 ዓ.ም ፈርዲናንዶ ማርቲኒ ስለ ኢትዮጵያ የጦርነት ብቃት ሊገልፅ «አቢሲኒያ በእውነት ጊዜ በምንም ደካማ ሀገር ስለሆነች ከንጉሥ እስከ ወይንም ንጉሦ ሁሉ አንድ ላይ በመሆን በኢጣልያ ጦርነት አውጀው ሊያሸንፉ የሚችሉ አይደሉም» ብሎ ነበር። ይህ የተሳለቀ አመለካከታቸው ወደ ጎደጥ ጦርነት ሽንፈት ዳረጋቸው።

አዲሱ በምፅዋ የኢጣልያ ጦር ዋና አዛዥ ጀነራል ባለታ ኢጣልያና ኢትዮጵያ በጦርነት ፍልሚያ የሚገኙ መሆናቸውን አውጆ ለአካባቢ ይህንን አዋጅ በኢጣልያ መንግሥት በሐምሌ 4/1887 ዓ.ም በሊቦሊስ አርማታ መንግሥታት የተላለፉ ደብዳቤዎች፤

1ኛ. በምፅዋ አካባቢ የሚገኙት የቀይ ባሕር ወደቦች የተዘጉ መሆናቸውን

2ኛ. በእነዚህ ወደቦች ከሌሎቹ ሀገር ወይንም ከሌሎቹ ሕዝብ ጋራ ንግድ ማካሄድ መከልከሉን

3ኛ. ማንኛውም መርከብ ይህንን አዋጅ ጥሶ ቢገኝ በሌሩ መንጃል ተዘግ ፍርድ ቤት ቀርቦ ትቀጣለች ብሎ ሊያስታውቅ፤ በዚሁ ለማንም ለለ ደብዳቤ በፈረንሳይ የኢጣልያ

አምባሳደር የተገደለው ጀኔራል ባለታ ከምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል በኩል በሚከተሉት ነጥቦች የተሰጠው መሆናቸውን ይገልፃል።

1ኛ. የፈረንሣይ ሚስዮኖች እቡን ከሌሎቹ ትርጉሜና ሚስዮናች በቀጥታ መገናኘ የሚችለው በሞት ምክንያት ሚሲዮናዊ ክቦታ በሚለቅበት ጊዜ ሚስዮኑ ሲዘረፍ ብቻ ነው።

2ኛ. አቡኑ ከሌሎቹ ትርጉሜፎች ሊገናኙ የሚችሉ በየሁለት ወር ወይንም በአሥመራ በኩል ከእኛ ኃላፊነት ቁጥጥር ውጭ ሆኖ ነው።

3ኛ. ይህን ስምምነት አቡኑ ወእክሩር ትንሜና በኩል ለሌሎቹ ትርጉሜፎች ያስተላልፋል። ሚያዝያ 14/1887 ዓ.ም የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለኢጣሊያ በፈረንሣይ ሀገር አምባሳደር በፃፈው ደብዳቤ ጀኔራል ባሌታ በጦር እየጃ ምክንያት መገናኘ ጨርሶ የተከለከለ ቢሆንም ለፈረንሣይ ሚሲዮናውያን ልዩ አስተያየት የተደረገ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ቆንስሉ ግን ከቦታው እንዲነሳ ጥረት የተደረገ መሆኑን አስረድቷል። በርግ የፈረንሣይ አምባሳደር ሚያዝያ 7/1887 ዓ.ም[1] ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ደብዳቤ በኢጣሊያ መንግሥት አድራጎት ተቃውሞ አሰምቷል።

በምፅዋ እና አካባቢዋ በቀይ ባህር ወደቦች የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀኔራል ባለታ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ኢጣሊያ ሙሉ ጦርነት ያወጀች መሆንዋን ከሚገልፁት ሰባት አንቀፆች አንደኛውና ዋነኛው ከዋና ጉዳይ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው።[2]

1. ከኢትዮጵያ ጋር ማንኛውም ግንኙነት ተቋርጧል። ስለዚህ በጦርነት ፍልሚያ የሚገኙ ሁለቱ አገሮች ማንኛውም ዓይነት ንግድ የተከለከለ ነው። ስለዚህ ማንኛውም የንግድ እቃዎች ውርስ ይሆናሉ።

2. ከኢትዮጵያ ጋር ወይንም ከጉንዋ የቆሙ ጉሣዎች ሁሉ ማንኛውም ዓይነት መገናኘ ወይንም መስማማት ለመንግሥት ፀጥታ አስጊ በመሆኑ ከህደት ነው። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሁሉ በሞት ወይንም እድሜ ልክ፣ በግዳጅ ሥራ ይቀጣል።

ስለዚህም ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ፣ ሀ/ ስጠላት መጠለያ የሰጠ ወይንም ያሰጠ ለ/ ለድብቅ በምፅዋ አካባቢ ጦር ሠፈሮች ማስረጃ ሲፈልግ ወይም ሲሰጥ የተገኘ ሐ/ በማድረግም ሆነ ማድረግ የሚገባው በመቀጠብ የኢጣሊያ ጦር አደጋ የጣለ ወይንም በአንድ ጦርነት ጥፋ ውጤት እንዲደርስ ያደረገ።

መ/ በሰው ኃይል፣ በገንዘብ፣ በቀለብ፣ በጦር መሣሪያ በጦር ትጥቅ ለጠላት የረዳ በዚሁ ተራ ቁጥር መሠረት ይቀጣል።

3. የውጭ ሀገር ዜጎች በቂ መተዳደሪያ የሌላቸው መሆናቸው የተጠረጠሩ ሰዎች ከሀገር ሊባረሩ ይችላሉ።

1. Vico Mantegazza: Ibd. p. LIV

2. Vico Mantegazza: Ibd. p. LXIII



4. ማንኛውም ሰው በጦርነት የሚገኙ በሁለቱ ሀገሮች መኖሪያ ሊመርጥ አይችልም። ስለዚህ በስምንት ቀን ውስጥ አንድ የመኖሪያ አድራሻ መርጦ ማስታወቅ ይኖርበታል።

5. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይንም ማንኛውም ከኢትዮጵያ ተባባሪ የሚባሉ ጉሣዎች ያልሆነ የኢጣሊያ ጦር ከያዛቸው መሬቶች ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ነዋሪ ቢሆንም ወይንም በማንኛውም ዓይነት በኢጣሊያ ጦር ሠራዊት የገቡ የተለያየ ፈቃድ ካልተሰጣቸው የኢጣሊያ ጦር ምርኮኛ ይሆናሉ።

6. የኢጣሊያ ጦር የበላይ ዕዝ ተባባሪ ጉሣዎች ብሎ የሚጠራቸው ሁሉ በኢጣሊያ በተያዘው መሬት መኖርና መዘዋወር ይችላሉ። ነገር ግን ከታወቀ የጉሣቸው መሪዎች የተሰጣቸው ፈቃድ መያዝ ይኖርባቸዋል።

7. የውጭ ሀገር ሰዎች /የገለልተኛ ዜግነት ያላቸው/ በተያዘው መሬት መኖር ከፈለጉ በስምንት ቀን ውስጥ መደበኛ የመኖሪያ ፈቃድ ከጠቅላይ ጦር ዕዝ ካላገኙ ከሀገር ይባረራሉ።

## 6. ስለ ራስ አሉላ የተሰጠው አስተያየት

የዶጋሊ ድል የተገኘው በራስ አሉላ የጦር ታክቲክ ልዩ ችሎታ መሆኑን አያጠራጥርም። ምንም እንኳን ራስ አሉላ ተገቢ ክብርና ቦታ ከሀገሩ ባያገኝ ለምሣሌ በሀገር እቀፍ፣ ጉበና በሸዋ፣ አሉላ በትግሬ ተብሰው የተገጠሙና የመሣሰሉት በይበልጥ ቢዳብር የሀገራችን ታሪክ እንደዳበረ ይቆጠራል። በፀረ ኢትዮጵያ የታወቀው የኤርትራ ታላቁ ሀገረ ገዢ የነበረው ማርቲኒ[1] በ1891 ዓ.ም ስለ ራስ አሉላ የሰጠው አስተያየት ከዚህ በታች መጥቀሱ ይጠቅማል። "ይህ ራስ አሉላ የተባለው ቀድሞ የኩበት እበት ሰብሳቢ የነበረው ዛሬ ራስና ቁርክ ፓሻ በሀገሩ ታሪክ ምናልባት አንድም ምልክት ለማስተላለፍ ያልተጨነቀ በኢጣሊያ ታሪክ ግን አንድ ታሪክ ሠርቷል።

ምስጢራዊ ፍጥረት ነው። ብዙ ሰዎች እናውቀዋለን ይላሉ። ምናልባት ግን ማንም አያውቀውም። ከሚወዳቸው ጋር ቸር ሩህሩህ ነው ተብሎ ይነገርለታል። ጠላቶቹ ግን አንድ ቀን እንኳ የጠላቸው ያሰማጸረጥ የሚያላድድ፣ ምህረት የለሽ ነው የሚሉ በእኛ ግዛት ዛሬ የሚገኙ ድር የሚያውቁት ሰዎች የሚሰነዝሩዋቸው አስተያየቶች ናቸው። የተቃዋሚዎች ኃይለኛ ጥላቻ ከመሆኑ የተነሣ ምንም የሰብአዊነት ባህርይ እንደሌለው ይናገራሉ። በወታደራዊ ችሎታም ምንም እንደሌለው ይናገራሉ። 1ኛ. ከዶጋሊ ሌላ በጦር ሜዳ አሸንፎ አያውቅም፣ ይኸውም በጣሊያኖች ስህተት እንጂ በራስ አሉላ ችሎታ እንዳልሆነ ያምናሉ። 2ኛ. በአራማት ዐጋሜ በሥቁምና ስብሐት ተሸንፏል። 3ኛ. ከግብጾች ጋር በአሳቂረ ሁኔታ ሸሽቷል። 4. በጉራዕ የተገኘው ድል በአጼ ዮሐንስ ብርታት ብቻ ነው፣ ራስ አሉላ ምንም አልተካፈለም። 5ኛ. በኩፊት ሠራዊቱ ካሰጨረሰ በኋላ የአስማን ዲግማ ደርቡሾች ብላታ ጉበሩ ራሱን መስዋእት በማድረግ ባያድኑት ኖሮ እሱንም ይገድሉት ነበር። 6ኛ. በመተማ ነገሩ ተስፋ እንደሌለው አይቶ ፊቱን ወደ ኋላ አዙሮ ነው የተመለሰው።

1. F: Martini: Ibd p. 147

7ኛ. ጥሩ ክርስቲያንም አይደለም፤ መስቀል በጠብመንጃው ሲያላትም ከእስላሞች ጋር በሚሆንበት ጊዜ ግን እስላሞች ሲሰግዱ እሱም አብሮ ይሰግዳል።»

በሌላ በኩል ግን ስለ ራስ አሉላ ወታደራዊ ችሎታ በአንድ ኮረብታ ሆኖ የዶጋአሊ ጦርነት ይመለከት የነበረው ሻለቃ ፒያኖ አንድ ኤውሮፓዊ የጦር ጀነራል ራስ አሉላ ለወታደሮቹ ከሰጣቸው ትእዛዝ የተለየ አይሰጥም ነበር፤ በማለት የባለሙያ በከፍተኛ አድናቆት ቃሉን ሰጥቷል። ማርቲኒ ራስ አሉላ ኢትዮጵያ በእሱ የምትመሰል፤ እሱ ብቻ የኢትዮጵያ ተወሬ ወኪል መሆኑን ያምናል። የአጼ ዮሐንስ ልጅ ራስ መንገሻ የንጉሠ ነገሥት ዙፋን ካላስጧኑ የሀሊና ዕረፍት አያገኙም ብሏል።

# 7. የዶጋዓሊ ጦርነት በጣልያኖች ላይ ያስከተለው ድንጋጤ

ከሰሐቲና ዶጋሊ ጦርነት ማግሥት ጀንዋሪ 27 ጣሊያኖች ከሰሐቲና ከሞንኩሎ ከሌሎችም ይዞታቸው ከነበሩ ቦታዎች ለቀው ወጥተው በምፅዋ ብቻ ለመቀመጥ ተወስነው ተቀመጡ። ጣሊያኖች ቢያሸንፉም ቢሸነፉም ሁል ጊዜ ስለ ጀግንነታቸው ብቻ ነው የሚያወሩት። ካርሎ ዋጊ በሁለቱ ጦር ሜዳዎች የሁለቱ ሀገሮች ስላሳዩት ጀግንነት ሲፅፍ «በእርግጥ በሁለቱ ጦር ነቶች ለኢጣሊያ ጦር ትልቅ ክብር ተመዝግቧል። ሆኖም ሐበሾችም እንዲኮሩባቸውና አብሪት እንዲያደርባቸው አስችሏቸዋል። ራሱ ከሰሐቲና ከሞን ማፈግፈግ እነሱ በሰጡት ማስጠንቀቂያ ፈርተን ሳይሆን አነስተኛ ቁጥር የነበረው ጦራችን በማሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን ስለአመንበት የተወሰደው እርምጃ ከእኛ ጠላቶች ለእነሱ በሚጠቅም ለእኛ ክብር ግን በኃይል የሚጎዳ አመለካከት ተርጉመውታል» ብሏል።

ጣሊያኖች በምፅዋ ተወስነው ሊቀመጡ ለምግባቸው ከባሕር ማዶ ካልሆነ ከኢትዮጵያ ማግኘት ስላልቻሉ ጀነራል ጄኔ የነበረው አማራጭ አዲስ ተጨማሪ ጦር በመጠየቅ ሽንፈታቸውን መበቀል ያስብ ነበረ። ራስ አሉላ በበኩሉ ጣሊያኖች በማፈግፈጋቸው ተደስቶ ወዲያ የነበሩ የኢጣሊያ እስረኞች አያያዝ ማላላት ጀመረ። በምፅዋ ከኢጣሊያ እስረኞም መፃፍ ተደርጎ በጣሊያኖች በጉምሩክ ተወስደውበት የነበሩት አንድ ሺህ ጠብመንጃዎች ስለተመለሱለት ላሹዋሩ በቀር ሌሎች እስረኞች ተለቀው ምፅዋ ገቡ። ላሹዋሩ 15,000 ማሪያ ተሬዛ ብር ከፈሉ በኋላ ከእስር ተለቀቀ። የዶጋሊ ጦርነት በኢጣሊያ ሀገር ከባድ ውጥረት ፈጥሯል ብሔራዊ ሐዘን እንዲባልም ታስቧል።

1. አንዳንድ የፓርላማ አባላት ኢጣሊያ ከአፍሪካ ለቃ እንድትወጣ ሐሳብ ሲያቀርቡ፣

2. ሌሎች ደግሞ በመደበኛ ብቻ ተወስነ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እንዲመሠረት ጠይቀዋል።

3. አብዛኛው የፓርላማ አባላት ግን ኢጣሊያ በዶጋሊ የወደቁ የኢጣሊያ ወታደሮች እንድትበቀል ጠይቀዋል።



ለሁሉም ግን ስለ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ያስጨበጠ ነበር። ኢት ዮጵያ ጣሊያኖች ይገምቷት እንደነበረች አውነተኛ ማንነቷ ለማወቅ ያስቻለው ጦርነት ነበረ። ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የውጭ ጉዳይና የጦር ሚኒስትሮች ከሥልጣናቸው እንዲለቁ ሲገደዱና አዲስ ጠቅላይ ምኒስትር ሆኖ የተመረጠውም ጦርነት የናፈቀው የቅኝ ግዛት የማስፋፋት ደጋፊ የነበረው ክሪ ስፒ ነበር።

# 8. ስለ ሰሐቲና ዶጋዓሊ ጦርነቶች ከኢጣሊያ መንግሥት የተሰጠ ይፋዊ መግለጫ

ስለ ሰሐቲና ዶጋሊ ጦርነት በወቅቱ በኢጣሊያ መንግሥት የተሰጠው ይፋዊ መግለጫ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነበር።

ጀንዋሪ 22 ስለ ራስ አሉላ ዓላማዎች የሚያስጉ ዜናዎች ይደርሱ ነበር። ራስ አሉላ ብዛት ያላቸው ወታደሮችን አስከትሎ ከጊንዳ ወደ ሰሀቲ ወርዶ እንደነበርና 5 ኪሎ ሜትር ከዚህ ቦታ ርቆ ሰፍሮ እንደነበረ ታውቆ ነበረ።

ሻለቃ ቦሬቴ ይህን ሁኔታ እንደሰማ በ25 ፍተሻ አድርጎ ነበረ። ነገር ግን ወታደሮቹ ከአንድ ኪሎ ሜትር ትንሽ የሚበልጥ እንደተጓዙ የጠብመንጃ ተኩስ ስላጋጠማቸው ወደ ኋላ ተመለሱ። ሆኖም ወደ ደሰት /Desset/ ሸለቆዎችና ወደ ሌሎች አነስተኛ ሸለቆዎች የሚያምሩ የሰሐቲ ይዞታ የሚከቡ በርካታ ወታደሮች መኖራቸውን ማሥረጃ ለመሥጠት ችሏል። ወታደሮቹ ወደ ጦር ሰፈራቸው እንደተመለሱ ኮረብታዎች በኢትዮጵያ ወታደሮች የተሞሉ ነበሩ። ቦሬቲ አደገኛ ከበባ ለማስወገድና ጠላትን ወደ መድፎች ተኩስ ዓላማ ለመሳብ የመቶ አለቃ ኩሞዋ ግማሽ የኢጣሊያ መቶ አለቃ ጦርና ሁለት የመቶ አለቃ ይዞ እንዲወጣ አዘዘው የመቶ አለቃ ፈዶሪኮ ኩሞዋ ወደ ፊት በሚራመድበት ጊዜ የሸለቆው ዝቅተኛ ቦታቸውን እንደያዙ አንድ መቶ የሚያህሉ ሐበሾች በድንገት ደረሰባቸው፤ ተኩስም ከፈተባቸው፤ ይህ የማጥቃት ምልክት ነበር።

ጠላት ወዲያውኑ ሁሉን ኮረብታዎችን ያዘ፤ የእኛ ሰዎችም በተላከላቸው ሌላ ግማሽ የመቶ አለቃ ጦር እየተረዱ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ምሽ ወደሆነ ቦታ አፈገፈጉ። በዚሁ የመጀመሪያ ግጭት የመቶ አለቃ ኩሞዋ /Cuomo/ ከባድ የመቁሰል አደጋ ደረሰበት። ብዛት ያላቸው ሐበሾች እንደ አውሬ እየጮሁ ወደ ማጥቃት ተንቃነቁ፤ አንዳንዶቹ ከምሽጉ 300 ሜትር ርቀት ደርሰው ነበር። ሆኖም ከእኛዎቹ ወታደሮች ለሁለት ሰዓት የቆየ የጠላ ት ኃይለኛ ተኩሥ በመቋቋም ጠላት ማጥቃቱን እንዲያቆም አስገድደውታል፤ ወደ ኋላ በመመለሥ በመጀመሪያ በሥነ ሥርዓት ሆኖ፤ ቀጥሎ ግን ወደ ሽሽት ተለወጠ በዚሁ ቀን ጠላት የደረሰበት ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ በመውሰዱ ለማወቅ አልተቻለም፤ ከእኛ ወገን ግን የመቶ አለቃ ኩሞዋ /Cuomo/ ጭምር የሞቱ 5 የቆሰሉ 3 ነበሩ።

ማታውን ሁሉም ኮረብታዎች ተለቀው ነበር። ምግብ ትጥቅ እና ተጨማሪ የሰው ኃይል በመጠየቅ ቦሬቲ በላከው ቴሌግራም የውጊያው ዜና የተሰ ማው በምፅዋ ከቀኑ 11 ሰዓት ነበረ። ጀነራል ጄኔም ሌሊቱ ሥንቅ አጅቦ ወደ ሰሐቲ የጦር ሰፈር እንዲሄድ ለቴና

ኮሎኔል ደ ክሪስቶፎሪስን /De Cristoforis/ አዘዘው። የእርዳታ ቡድን ጃንዋሪ 26 ከጠዋቱ 11 ሰዓት ከ20 ከመንኩሉ ተነሳ። በመቶ አለቃ ኮሚ የ37ኛው እግረኛ የሚመራ መደበኛ ያልሆኑ ወታደሮችና መደበኛ የሆኑ አንድ መቶ አለቃ ጦር ከ15ኛ ሻለቃ ጦር ፊት አጥቂ ጦር በመመደብ ነበር። ከቅርብ እርቀት ሁለት መድፎች በበቅሎዎች እየተጎተቱ 20ኛና 41ኛ ሬጂመንት፣ እንዲሁም 6ኛ እና 7ኛ ጦር በ24 በዚሁ ወር ከጣሊያን የመጡ እግረኛ የመቶ አለቃ ጦር ይከተሉ ነበር። እንዲሁም ትጥቅና ስንቅ በበቅሎዎችና በግመሎች የተጫኑ ነበሩ። የደጀን ጦር ግን ግማሽ የመቶ አለቃ የ48ኛው እግረኛ ጦር ነበረ።

ከጠዋቱ 2:30 ሰርጋታብ /Sergatab/ ትንሽ ወንዝ ጦሩ እንደተሻገረ በቅድሚያ የሚገኘው ጦር ሰሐቲ ለመድረስ አንድ ሰዓት የእግር ጉዞ ሲቀረው ባሺቡዙኮች በፊት አጥቂ ጦር ጠላት እንዳለ ተመለከቱ። ጉዞውን አቋርጦ ሌቴናኮሌኔሉ ከሻምበል ሚኬሊኒ ጋራ ሆነው የ17ኛ መድፈኛ በፍጥነት ወደፊት አመሩ። ሚኬሊኒ /Micheiini/ ወደ ሰሐቲ የሚሄደው የሻለቃ ቦሬቲ ጦር ለማጠናከር ከመቶ አለቃ ቲሮኒ /Tironi/ እሱም የ17ኛ መድፈኛ ጋራ ሆኖ የመድፈኛ አዝ በሰሐቲ ለመረከብ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት መድፎችን በመያዝ ነበረ።

ሐበሾች በዚሁ ጊዜ በ800 እና 1000 ሜትር ርቀት በቡድን ተከፍለው መሥመር ይዘው ነበረ። የፊት አጥቂ ጦር መድፎችን በመያዝ አፈታቸው ቦታውን ያዙ፣ ቀሪውን ጦር ፊትለፊት በሚገኘው ኮረብታ ቦታውን ያዙ። ተኩሱ ከጠላት ተጀምሮ ብቅ እያሉ እያቋረጡ የሚጠፉ ሰዎች ነበሩ። አጠፋውን የተኩሥ ምላሽ ከመድፎች ይደርስባቸው ነበር። ነገር ግን ሰትንሽ ጊዜ ነበረ፣ ምክንያቱም ከመድፎቹ አንዱ ወዲያውኑ ተበላሸ። ሁለተኛውም ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሥራውን አቋረጠ፣ ሁለቱም ተወረወሩ። የጠላት ጥቃት ዓላማ ጥበብ የተሞላበት ለመከበብ ስለነበረ ዋናው የእግረኛ ጦር ወታደሮች በጠላት እንዳይያዝ በሥተኋላ ከነበረ ኮረብታ በመመለስ ቦታውን እንዲይዙ ትዕዛዝ ተሰጣቸው። ይህ እንቅስቃሴ የተካሄደው በቡድን ሲሆን ኃይለኛ ተኩሥና ጩኸት ከሐበሾች እየተከሄደበት ነበር ወደ የተመደበላቸው ቦታ የደረሱ።

የእኛ ወታደሮች በእውነተኛ ጀግንነት አቋም ተኩሥ እየከፈቱ «ቪቫ ሊታሊያ» (Viva L'italia) እያሉ ነበረ በበኩላቸው ይጮሁ የነበረው። ነገር ግን በደረሰባቸው ጉዳት የሰውና የመሣሪያ እጥረት እየተከሰተ ቢመጣም ለቀሩት ጥቂት ወታደሮች በትጥቅ ከፍል የነበሩ ጥይቶች ታደሉ። አዲስ የጠላት ኃይለኛ ጦር ሲመጣ ግን በእጅ መሣሪያ፣ በጩበጣና በጎራዴ፣ የሰው በሰው ትግል ተበፋ የሌለው ትግል ለማድረግ ተገደዱ።

በእኩለ ቀን ገደማ (ከቀኑ 6 ሰዓት) የእኛ ጦር ሙሉ በሙሉ ተደምስሶ ነበር። ከዚህ በኋላ አሰቃቂ የልብስ ማስወለቅ፣ የወደቁትን ማቁሰል፣ ከሞት የተረፉት ቁስለኞች በመውደቃቸው የሞቱት ስለመሰላቸው ዘርፈው ራቁታቸው እየወጡ ሳይወጉዋቸው በመቅረታቸው ነው። በጦርነቱ መጨረሻ በጣለው ኃይለኛ ዝናብ በጭቃ ላይ ተጥለው እየደሙ መንቀሳቀስ ሳይችሉ መቀመጣቸው ስታያቸው ምን ያህል እንደነበረ ለመገመት አያዳግትም። አንዳንዶቹ



በብዙ ችግር መንኩሉ ደረሱ። የቀሩት በሻንበል ታንቱሪ (Tanturi )፣ የሚመራ ዱቺ (Duci)፣ ፖርታና (Porta )፣ ሳንቶር ( Santoro)፣ ያሉበት የ54ኛው የመቶ አለቃ ጦር ከብዙ ሰዓት በኋላ ለእርዳታ መጥተው ለቅሞ እስከ ሚወስዳቸው ድረስ በመሬት ላይ ተጥለው ነበር የቀሩት።

ይህ ሻንበል በ5 ሰዓት በእርሳስ የተፃፈ ወደ ዶጋሊ እርዳታ የሚጠይቅ ከኮሎኔል ደ ክርስቶፎሪስ እንደደረሰው ወታደሮቹን ሰብስቦ ወዲያውኑ ተነሳ። እግረ መንገዳቸው ሲጓዙ ባሺቡዙኮች የሐበሻ ሬሣዎች ተመለከቱ። በዚሁ ጊዜ በተጠንቀቅ በመሆን ይዟቸው መጥተው በነበሩ መድፎች ተኩሥ ከፈቱ። ይህ ተኩሥ የጠላት ድምፅ እንዲጠፋ እንዲሸሽ አደረገው። በመቶ አለቃ ታንቱሪ (Tanturi ) ወደ ፊት ያሉ ቦታዎች ፍተሻ ሲደረግ መንገዱ ነፃ ሆኖ ተገኘ።

ኩባንያው ወደ ጦር ሜዳ ሲደርስ የእልቂቱ እውነተኛ ገፅታ ሊገነዘብ ችሏል። ከታንቱሪ በ27 ለጀነራል ጄኔ የተፃፈው ሪፖርት የሚከተለው ቃል ተገልጾ ነበረ «ሁሉም ሬሳቸውን ሆኗል፣ በጀርባቸው ተኝተዋል፣ ከባድ ቁስሎች ነበሯቸው፣ በተራ በመሥመር እንደተቀመጡ ተጋገድመው ነበር፣ ምንም ጠብመንጃ፣ ልብስ፣ ባዶ ኮዳም አልነበሩ ቸውም፣ ሁሉም ተወስዶባቸዋል። ሻንበሉ በሌላ ሪፖርቱ ይህ ጀግንነት የተሞላበት የሰው እልቂት በማየት ኩባንያውን ሰብስቦ ለወደቁት ወታደሮች የብረት ሰላምታ አድርጎላቸዋል።

ከ500 በደ ክርስቶፎሪስ ይመሩ የነበሩ ወታደሮች ውስጥ 413 ሞተዋል፣ 86 በከባድና በቀላል ቆስለዋል፣ አንዳንዶቹም በደረሰባቸው ጉዳት ቆይተው የሞቱ ነበሩ ከመኮንኖች ውስጥ 22 ሞተዋል፣ ቆስሉ ሻምበል ሚከሊኒ (Michelini ) ብቻ ተረፈ። የመቶ አለቃ ኮሚ ቆስሎ የ37ኛው እግረኛ ጦር በብዙ ችግር ሞንኩሉ ለመድረስ ችሎ ነበር፣ ከዚያም ወደ ምፅዋ ተወሰደ፣ ሆስፒታል መርከብ «ጋሪባልዲ» ተኝቶ ፌብሯሪ 3 ዐረፈ። የሞቱት በስፍራው ተቀበሩ። የኮሎኔል ደ ክርስቶፎሪስ አስከሬን ግን ወደ ምፅዋ ተወስዶ ከመቶ አለቃ ኮሚ አስከሬን ጎን ተቀብሯል።

# ምዕራፍ 8

# በአጼ ዮሐንስ የመትመራው ኢትዮጵያ ላይ በጣሊያኖች የተፈጸመባት የማዳከም ስውር ደባ

## የሰር ፓርታል ተልእኮ

### 1. ዝግጅትና ጉዞ

ጁን 30/1887 ዓ.ም በእንግሊዝ ሀገር የኢጣሊያ አምባሳደር[1] ለሀገሩ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲፅፍ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ሣሊስበሪ ተገናኝቶ ተነጋግር እንደነበርና ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም ለመኖር የምትፈልግ ከሆነ የእንግሊዝ መንግሥት የሽምጋይነት ሚና ለመጫወት ፍላጉቱ መሆኑን ገልፀውልኛል ይላል። አምባሳደሩ እንደገና ጁላይ[2] 16/1887 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ ከሎርድ ሣሊስበሪ ጋራ በድጋሚ ተገ ናኝቶ የተነጋገረበት መሆኑን ይገልፃል። በዚሁ ዕለትም በሌላ የፃፈው ደብዳቤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለንግሥት ቪክቶሪያ አንድ ደብዳቤ መፃፉን ገልጾ አንዳንድ ነገርም በመግለፅ ንጉሠ ነገሥቱ በኢጣሊያ መንግሥት አቋም ሰሞታ አመልክቶ ከአድሚራል ሒወት የተደረገ ውልም የተጣሰ መሆኑን ገልፀዋል። አምባሳደሩ በሌላ ደብዳቤ ጁላይ[3] 21/1887 ዓ.ም. ከሎርድ ሣሊስበሪ ካደረገው አዲስ ውይይት የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ለአጼ ዮሐንስ ወደ ምፅዋ ባለሥልጣን ልካ ሰላም ብትለምንና ጣሊያን የምትሰጣቸው ትድመ ሁኔታዎችን ጠይታ ቢቀበል ብሪታንያ ልታደርገው የምትች ሰው ብቸኛ የሽምጋይነት ተግ ባር ነው። ሣሊስበሪም በበኩሉ የኢጣሊያ መንግሥት ፈታድ ከሆነ ብሪታንያ የሽምጋይነት ተግባር ማድረግ ዝግጁ መሆንዋን በግለት ገልጿል። የኢጣሊያ አምባሳደር በለንደን ጁላይ[4] 21 ፡ 28 እና 30 አራት ደብዳ ቤዎች በመጀመሪያ የአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ በኢጣሊያንኛ ተተርጉሞ ልኪያለሁ ይላል። ቀጥሎም አጼ ዮሐንስ ንግሥት ቪክቶሪያ በሽምጋይነት በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል እንድትገባ መጠየቋን የሚል ዜና ከአንድ የዜና ምንጭ ተነገሯል።

ከዚህ ቀጥሎም የመቅደላው ጀግና ሎርድ ናፒየር በእንግሊዝ ፓርላማ ለሎርድ ሣሊስበሪ መንግሥታቸው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ያለው ጠብ በሽምጋይነት ገብቶ ደም መፋሰስ እንዳይከሄድ የአድሚራል ሒወት ውል መጀመሪያ እንቀጽ በተግባር እንዲውል አርምጃ እንዲወሰድ ጥያቄ እንዳ ቀረበና ጥያቄም ከቀረበ በኋላ ሎርድ ሣሊስበሪ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለእንግሊዝውያን ወዳጅ ነበረ።

1 Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXIII

2 Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXIV

3 Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXV

4. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVI-VII



በሌላ በኩል ደግሞ የኢጣሊያና የእንግሊዝ ወዳጅነት ረጅም ዘመን ያለው ነው። ሆኖም ሽምግልና ለማድረግ ከግሰብ በፊት ተቀባይነት እንዲለው ማይረጋገጥ የሽምግልና ሀሳብ ማቅረብ ጠቃሚነት የለ ውም ብሏል። ሎርድ ሣሊስበሪ ኢጣሊያና ኢትዮጵያን ለማስማማት ባሰው ጽኑ ፍላጉት ሰር ፓርታል ወደ አጼ ዮሐንስ ለመላክ መወሰኑን ገልጿል። እሱ እስከሚመለስ ግን ጦርነቱ እንዳይጀመር ተማጽኖ በተጨማሪ ለሚከተሉት ሶስት[1] ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት የኢጣሊያ መንግሥት መልስ እንዲሰጠው ጠይቀዋል። 1ኛ. ኢጣሊያ ያላት የመጨረሻ የመሬት ጥያቄ 2ኛ. ሰሐቲን ለኢጣሊያ ለመልቀቅ ኢትዮጵያ ከተስማማች በሰውጡ ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ስምምነት ውል ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነች 3ኛ. የኢጣሊያ መንግሥት ተጨማሪ ሌላ የመሬት ማስፋፋት የማያደርግ መሆኑን ቃል ይገባ እንደሆነ፤፤የኢጣሊያ መንግሥት ግን ለሶስቱ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ሳይሰጥ ቀርቷል። የእንግሊዝ መንግሥት በራሱ እነሳሽነት ሽምጋይ ለመሆን ባቀረበው ሀሳብ መሠረት ወደ ኋላ ሣይል በዕቅዱ ሎርድ ፓርታል[2] የንግሥት ቪክቶሪያ ልዩ መልእክተኛ በመሆን ለአጼ ዮሐንስ የተላኩ ብዙ ስጦታዎች ይዞ የመንገድ ርቀት ወይንም ሌላ ማንኛውም ችግር ሳያግደው ጉዞውን ጀመረ።

የተነሣበትን ዓላማ ግቡን ሣያደርስ ታሪካዊ ተግባሩን አከናወነ። እንደ ሎርድ ሣሊስበሪ እና እንደ ጀግናው[3] ናፒየር ድጋፍ ያለው ይህ የሎርድ ፓርታል ተልእኮ ለእንግሊዝ ኃላፊነትን ለመወጣት የታላቅነት ምልክት ነበር። ስለዚህ ቀድሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ስጦታዎች ወደ አጼ ዮሐንስ ይዞ በመሄድ ስለ ሁለቱ ሀገሮች ወዳጅነት ለመነጋገር ኢጣሊያዊ ጀነራል ፓትሶሊ የተባለው የኢጣሊያ የንጉሥ ኡምቤርቶ መልእክተኛ በመሆን ወደ ኢትዮጵያ አምርቶ ምጽዋ ደርሶ ነበር። ነገር ግን አጼ ዮሐንስ ይገኝ የነበረ በወሎ ከምጽዋ በጣም ሩቅ ቦታ ነው በማለት ጉዞውን አቋርጦ ወደ ሀገሩ ተመልሷል። የተሰጠውም ምክንያት ጀነራሉ በሀገሩ ብዙ ሥራ ስላለው ነው ተብሏል። የእንግሊዝ መልእክተኞች አድሚራል ሒወትና ሎርድ ፓርታል በሀገራቸው ሥራፈቶች መሆናቸው ነውን? በመልእክቱ ንግሥት ቪክቶሪያ ሎርድ ፓርታልን ወደ አጼ ዮሐንስ የላከችበትን ዓላማ ስታብራራ በጥብቅ ይዞታ ስለነበሩ መሬቶችና በኢትዮጵያ መሬት ወሰን ጉዳይ ኢትዮጲያና ኢጣሊያ ለማስማማት መሆኑን ገልፃለች።

በሌላ በኩል ደግሞ ሎርድ ሣሊስበሪ ለኢጣሊያ መንግሥት ሎርድ ፓርታል ከኢትዮጵያ ከመመለሱ በፊት ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ደጋግሞ አደ ራ ብሎ ሎርድ ፓርታል አክቶበር 14/1887 ዓ.ም.[4] ከለንደን ጉዞውን ጀምሮ በ20 እለክንድርያ ግብፅ እንደሚገባ ይጠበቅ ነበር።

1. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVI

2 . Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVII

3. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVIII

4. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVIII

ስለ ሎርድ ፖርታል ተልእኮ ጉልቶ የሚታየው የእንግሊዝ መንግሥት በጉ እመለካከትና በጉ ተግባር ነው። እንግሊዝ ሀገር ሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች የምታፈልቅ ሀገር ናት። የመቅደላው ጀግና ሎርድ ናፒየር ኢትዮጵያንና አጼ ዮሐንስን በሚገባ የሚያውቅ በመሆኑ ብቻ ሣይሆን ምናልባትም በሰብዓዊነት ተነሳስቶ ይሆናል በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀከል ሰላም እንዲሰፍን እንዲጥር ሎርድ ሣሊስበሪን የጻፉላቸው። በወቅቱ ሌሎችም ከሎርድ ናፒየር ጐን የቆሙ እንግሊዛውያን ሊኖሩ ይችላሉ። የእንግሊዝ መንግሥት ሰር ፖርታልን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ የወሰነው በኢትዮጵያና በኢጣሊያ ያለው ውጥረት እልባት ለማግኘት በማሰብ ነበር። ከባድ ችግሮች አፈታችን ተደቅነዋል፣ ጥረታችን ይሣካል ወይም አይሣካም ብሎ መተንበይ አስቸጋሪ ነው። ካልተሣካልን ግን የኢጣሊያ መንግሥት በእኛ ጉድለት እንዳልሆነ እንዲረዳልን ተስፋ አለኝ በማለት ነበር የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጥረቱን የጀመረ። ጣሊያኖችም በበኩላቸው በሀበሾች በኩል ጥቃት ካልደረሰባቸው ተኩስ እንደማይከፍቱ ለሎርድ ሣሊስበሪ አረጋግጠውለታል። በእንግሊዝ[1] ወገን ሎርድ ፖርታል ምፅዋ እንደደረሰ ጀነራል ሣሌታ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ መምጣቱን ለራስ አሉላ እንዲነግርለት ተፈልጎ ነበር።[2] ጣሊያኖች ግን ይህን ለማድረግ አልተስማሙም። እንዲያውም በራስ አሉላ በኩል ችግር የሚፈጠርበት ስለሆነ ወደ አጼ ዮሐንስ ለመሄድ በራስ አሉላ በኩል ማለፍ አይገባውም። ቀጥተኛ የሆነ አጭር መንገድ ጀነራል ሣሌታ ሊጠቁም ይችላል ብሎ ሀሳብ አቅርቦ ነበር። ይህ የጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ተቃውሞ ምን ያህል ጥላቻ በራስ አሉላ ላይ እንደነበረ ያሣያል። ጣሊያኖች ከልባቸው የእንግሊዝ የሽምጋይነት ሚናም እንደማይፈልጉት ያሳያል። ዕቅዱም እንዳይሳካ ፍላጎታቸው መሆኑን ያሳያል። ሎርድ ሣሊሰቡሪ ግን መመሪያ እኔ ራሴ ለሎርድ ፖርታል እሰጠዋለሁ በማለት[3] በአጭሩ ዘጋው[4] ኦክቶበር 29/1887 ዓ.ም. ሰር ፖርታል ምፅዋ ደረሰ። በእንግሊዝ መንግሥት በኩል ማጣራት ከሚፈልጓቸው ነገሮች 1ኛ. ሰሐቲ እና ዊዓ ለጣሊያኖች፣ ጊንዳዕ የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ የዐይለት ሜዳ ገለልተኛ እንዲሆኑ አጼ ዮሐንስ እንዲስማሙ ለማድረግ ከተቻለ በጉስም የኢጣሊያ እንዲሆን አጼ ዮሐንስ ከተስማማ በኢጣሊያ በኩል ሌላ የኢትዮጵያ መሬት ለመያዝ እንዳትመኝ ቃል ትገቡ እንደሆን ተብሎ ቢጠየቁ ጣሊያኖች አጥጋቢ መልስ ሣይሰጡ ቀርተዋል። በመቀጠልም ሎርድ ሣሊስበሪ ራስ አሉላ በጣሊያኖች ላይ አልቴት በመፈፀሙ አጼ ዮሐንስ ለኢጣሊያ መንግሥት ግዙን እንዲገልፅ ማድረግም ይቻል ይሆናል። አጼ ዮሐንስ ከዚህ በላይ ከተጠየቀ ግን ጦርነት ይመርጥ ይሆናል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. XC

2 Vico Mantegazza: Ibd p.XC

3 Vico Mantegazza: Ibd p.XCI

4 Vico Mantegazza: Ibd p.XCIII-IV



እርግጥ ውጥረቱ በጦርነት ይፈታል ከተባለ ኢጣሊያ ያለ ጥርጥር ድል ትቀዳጃለች። ነገር ግን የምትከፍለው መስዋእትነት በጣም ከባድ ይሆናል። በዚህ ቀን ኦክቶበር 29/1887 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም ለመኖር በኢጣሊያ መንግሥት ቅድመ ሁኔታዎች ሆነው የቀረቡት፣ 1ኛ. ንጉሡ አጼ ዮሐንስ[1] ባለፈው ጊዜ በተደረገው ጥቃት ግዙን እንዲገልጽ 2ኛ. ዊዓ እና ሰሐቲ የኢጣሊያ እንዲሆኑ ጊንዳዕ የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ እንድትሆን ሀይለት ሜዳ የኢጣሊያ እንድትሆን ቢያንስ በኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት እንድትሆን ወሰኑ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋራ በመሆን እንዲወሰን። 3ኛ. ንጉሡ /አጼ ዮሐንስ/ ኢጣሊያ የሀባብና ዐሳውርታ ጎሣዎች የበላይ ጠባቂ መሆንዋን እንዲቀበል። 4ኛ. ኢጣሊያ ከብሪታንያ ጋራ ተስማምታ ሰንሀይት እንድትይዝ። 5ኛ. የወዳጅነትና የንግድ ውል በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል እንዲደረግ። ኖቬምበር 9/1887 ዓ.ም. ፖርታል አሥመራ ገብቶ ከራስ አሉላ ጋር ተገናኝተዋል፣ በጉዞ ተደስቷል፣ ራስ አሉላ ጥሩ አቀባበል አድርጎለታል፣ ነገር ግን ራስ አሉላ ሰር ፖርታል ጉዞውን እንዳይቀጥል ከልክሎታል፣ ፖርታልም ተቃውሞ አሰማ፣ ራስ አሉላ ግን አልተቀበለውም። ሆኖም ሶስት ፈጣን ፈረሰኞች ወደ ንጉሡ የሚገኙበት ቦታ ተልከው ትእዛዝ እንዲሰጠው ጠይቋል። በ15 ፖርታል አሥመራ ነበር፣ መታሰር ግን አልታሰረም።

ኖቬምበር 19/1887ዓ.ም ፖርታል በ50 የራስ አሉላ ወታደሮች ታጅቦ ወደ ዓድዋ አጼ ዮሐንስ ወደ አለበት አምርቷል። ፖርታል ከአሻንጌ ሐይቅ አጠገብ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ተገናኝቷል።[2] ለጣሊያኖች አሳልፎ መሬት ለመሥጠት ጉዳይ ግን አጼ ዮሐንስ በሙሉ ውድቅ ነው ያደረጉበት።

ትንሽ ተስፋ ጭላንጭል የተሰጠው በእስላሞች ደርቡሾች ላይ ከመዝመት ፈንታ ከክርስቲያኖች ጣሊያኖች መዋጋቱ የሚያሳዝነው መሆኑን ገልጸውለታል። ከአድሚራል ሒወት ያደረጉት ውል በጣሊያኖች ተጥሷል ብሏል። በወቅቱም የምፅዋ ወደብ የኢትዮጵያ እንደሆነች ድምፅ አሰምቶ ሰጊዜው ብቻ ነበር በግብፅ እጅ እንድትቆይ የተስማማ።

ስለሆነም አጼ ዮሐንስ አንድ ስንዝር መሬት ለጣሊያኖች ከሚሰጥና የሀገሩ ዳር ድንበር ሰድርድር ከሚያቀርብ ጦርነት የሚመርጥ መሆኑን በድል አድራጊነትም እንደሚወጣ እርግጠኛ መሆኑን ለሰር ፖርታል ገልፀውታል።[3] ዲሴምበር 26/1887 ዓ.ም ሰር ፖርታል የአጼ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ምጽዋ ተመለሰ። በፖርታል አስተያየት አጼ ዮሐንስ በጦርነት አቋም መያዙ ብዙ ምክንያቶች አሉ። 1ኛ. ራስ አሉላ የሰጠው የተሳሳቱ መረጃዎች 2ኛ. ብዙ ጦር ሰብስቦና ከሌሎች ሹማምንቶቹ ተመካክሮ ጦርነት ለማድረግ በመወሰኑ 3ኛ. ከዚህ በላይ ራስ አሉላ እንግሊዝና ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለመክፈት ቅንበር እንዳላቸው የሚል ወሬ አሰራጭቶ ስለነበረ።

1. Vico Mantegazza: Ibd p.XCIV-XCV

2. Vico Mantegazza: Ibd p.CVI-CVII

3. Vico Mantegazza: Ibd p.CVII

አጼ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፈው ደብዳቤ ጦርነት እንደማይፈልግ ነገር ግን ከምፅዋና ከምንክሉ በቀር ሌላ አንድ ክንድ የኢትዮጵያ መሬት ኢጣሊያ እልፋ እንድትቆጣጠር የማይፈቅድ መሆኑንና ጦርነት ቢነሳም እንግሊዝ ከኢጣሊያ ጐን እንደማትሰለፍ ያለውን ተስፋ ገልፀዋል። በሰር ፓርታል አስተያየት ይህ ሁሉ የአጼ ዮሐንስ እቅም በራስ አሉላ ወሬ በመመራቱ ነው። ራስ አሉላ በደምብ አልተቀበሉኝም፤ አሥመራ ላይ ለአምር ቀን እንደ እሥረኛ ያዙኝ፤ ንጉሡ አስቀድሞ ከራስ አሉላ የተላከ መልእክት ከእኔ ጋር ከመገናኙ አንድ ቀን በፊት ባይደርሰው ኖሮ ያቀረብኩለት እንዳንድ ትድመ ሁኔታዎችን ይቀበል ነበር። በዚሁ መልእክቱ ራስ አሉላ ኢጣሊያኖች ወደ ሰሐቲ እየመሩ መሆናቸውን ገልፀውለታል። ከዚህ በኋላ ነው ንጉሡ ስለ እኔ ተልእኮ ጥርጣሬ ያደረበት። ሆኖም እኔ የእንግሊዝ መዳጀኑትና ገለልተኝነት ለማስረዳት ችያለሁ። ከሁለት ወር በፊት ተልኬ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ሌላ ይሆን ነበር።

## 2. የፓርታል ወደ ምፅዋ መመለስ የአጼ ዮሐንስ እምቢዮች

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የአጼ ዮሐንስ እምቢታዎች ለሎርድ ፓርታል ያሰማው በአንድ ቦታ ተቀምጦ በማነጋገር ወይንም በጽሁፍ በአንዱ ደብዳቤ አይደለም። ሰር ፓርታል የሰማቸው ብዙ አስተያየቶች የራሱ ግምገማ ናቸው። አጼ ዮሐንስ እምቢ ለሀገሬ ሰንዝር መሬት አሳልፌ ለጣሊያኖች አልሰጥም ብሎ ሐሳቡን የገለፀው በለየ ልዩ መንገድ ነው።

ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ማንቴጋትዛ ዲሴምበር 30/1887 ዓ.ም ባወጣው እትም ከእንግሊዝ መልእክተኞች አካባቢ ያገኘሁት ነው ብሎ ያወጣው ዜና በሚከተለው ዓይነት ይገልፀዋል።[1] 1ኛ. በሎርድ ፓርታልና በቢቼስ የሚመራ የእንግሊዝ መልእክተኞች አጼ ዮሐንስ የተቀበሏቸው በቀዝቃዛ አቀባበል ነበር። ይኸውም አንደኛ እምቢ ሆነ። 2ኛ. አጼ ዮሐንስ መልእክተኞችን ተቀብሉ ሳያነጋግራቸው ሶስት ቀን ደጅ እንዲጠኑ አደረጋቸው። ይኸውም ሁለተኛ እምቢ ሆነ። 3ኛ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቀበሏቸው የንግስት ቪክቶሪያ ደብዳቤ የተቀበሉበት ቀን በጣም ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው ያነጋገራቸው። 4ኛ. ንጉሡ ምንም መልስ ሳይሰጥ አሰናበታቸው። 5ኛ. በማግስቱ ቢት አጼ ዮሐንስ ስለ እንግሊዞቹ ሳይጨነቅ ተነስቶ ጉዞውን ቀጠለ። እንግሊዞቹም ተከተሉት። 6ኛ. ለብዙ ቀናት በጉዞ አብረው ቢቆዩም ዲፕሎማቶቹም ወደ ምፅዋ ለመመለስ እንደሚፈልጉትና መልስ እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ንጉሡ መልስ ሳይሰጣቸው ዘጋቸው። በአሥራ ሁለተኛው ቀን ብቻ ለአጭር ጊዜ ተቀብሉ ካነጋገራቸው በኋላ አንድ ገን ደብዳቤ ለንግሥት ቪክቶሪያ የሚሰጥሰጣቸው እንዳይከፈት አስጠነቀቃቸው። 7ኛ. ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደላቸው።

1 Vico Mantegazza: ibd p.78



ነገር ግን በሌላ ጊዜ እንደሚደረገው እጅ መንሻ ማይሰጣቸው የሚያስፈልጋቸው በታምቻን በመመለስ አንድ የመንገድ መሪ ብቻ ሰጣቸው። 8ኛ. በመጀመሪያ ቀን ከንጉሡ የተመለሱ ጉዞ ሲያከናውኑ ሎርድ ፓርታል ቢሩፋት ማያደርግ ጉዞውን ለመቀጠል ፈለጉ ነበር፤

የአካባቢው ሀገረ ገዢ ግን ተቃውሞት፤ ፓርታል በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርብ ሀገረ ገዢው የወታደሮቹን ጠባቂዎች ወደ እንግሊዞች በመደብደብ በኃይል በመጠቀም ለማስፈራራት ገድ ሆኖበት ነበር። እንደገና ከንጉሡ ትእዛዝ ተቀብሎ ነው ጉዞአቸውን ሊቀጥሉ የቻሉ። 9ኛ. የአጼ ዮሐንስ እምቢ ማለቱ ምልክት የበረው ለእንግሊዝ መልእክተኞችም ሆነ ለንግሥት ቪክቶሪያ ስጦታ አለማበርከቱ ነበር።

አጼ ዮሐንስ የሀገሩን መሬት ቆርሶ ለጣሊያን ለመስጠት እምቢ ማለቱ በሌላ ወትትም ገለፀል። በኢጣሊያና በአጼ ዮሐንስ የተፈጠረው ውጥረት ለማርገብ በንጉሥ ምኒልክና ከታወቀው ቢረ ኢትዮጵያ ነበረት እጅግ የበረው አንቶኔሊ ምክር[1] ንጉሥ ምኒልክ በሸምጋይነት እንዲቀርብ ሁኔታ ቀርቦ ስለነበረ በኢጣሊያ በኩል እንግሊዝ በገሩ የተቋቋመበት ስለሆነ የሸዋ ንጉሥ ሽምጋይነት አስፈላጊ አይደለም የሚል አቋማቸው የበረው ቢሆን አንቶኔሊ ፌብሩዋሪ 20 1888 እንደጻፈው ምኒልክ በእንግሊዝ ሽምጋይነት ብቻ ዕርቅ እንዲሆን ስጋት ነበረው ምክንያቱም ከዕርቁ በኋላ አጼ ዮሐንስ[2] የሚሆምተው በምኒልክ ላይ ይሆናል ብሎ በመስጋት ነው። አጼ ዮሐንስም ለሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ኅዳር 12 ቀን 1880 ዓ.ም /ኖቬምበር 21/1887 ዓ.ም/ በጻፈው ደብዳቤ «የእንግሊዝ መንግሥት ሌኔ ማታ ስታውቅ ምፅዋን ለምን ለኢጣሊያ መንግሥት እንደሰጠ አይገባኝም። ከእንግሊዝና ከግብፅ ጋር ያደረግነውን ውል በማፍረስ ጣልያኖች ለእኔ ዜጎች ጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈል ጀመሩ፤ በዚህ ምክንያት ራስ አሉላ ከኢጣሊያኖች ጋር ሰላም እንዲፈርስ አደረገ፤ እኔ ግን ለራስ አሉላ የፈጸመውን ድር ጊት እንዲፈፅም ትእዛዝ አልሰጠሁትም። ዛሬ ሁለቱ የጦር መሪዎቹ ፊት ለፊት ቀጥ በሚገኙበት ጊዜ ሰላም ለማድረግ የሚቻል ከሆነ እኔ ወደ አንድ ሰላምነት ለመድረስ ዝግጁ ነኝ።» ብሎ ነበር።[3] ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፈው በሌላ ደብዳቤም ደግሞ እንዲህ በማለት ነበር የደመደመው።

«የግርማዊነትዎ ፍላጐት በእኛና በኢጣሊያኖች መሀል ሰላም ለመፍጠር ከሆነ ይህ ሊሆን የሚችለው እነሱ ሀገራቸው ላይ ሲሆኑ እኛም በሀገራችን ስንሆን ብቻ ነው፤ ነገር ግን ዛሬ በሁለቱ ወገኖች ፈረሶች የተጫኑ ስለሆነ ጉራዴዎችም የተመዘዙ በመሆናቸው የኔ ወታደሮች እንደ እሾህ ብዙ ናቸው፤ ጨዋዎቻቸውን ይዘው ለጦርነት ዝግጁ ናቸው። ኢጣሊያኖች ጦርነት ይፈልጋሉ። ነገር ግን ኃይል በእግዚአብሔር እጅ ብቻ ነው። የሚፈልጉትን ያድርጉ፤ እኔ በሕይወት እስካለሁ ድረስ እነሱን ፈርቼ በአንድ ጉድጓድ አልደበቅም።»

1 Vico Mantegazza: ibd p.CI

2 Vico Mantegazza: ibd p.CVIII

3 Vico Mantegazza: ibd p.CXII

# 3. አጼ ዮሐንስና ሠራዊቱ በዐይለት

አጼ ዮሐንስ ከነበረበት ከመሎ ተነስቶ ሠራዊቱን መርቶ ከምፅዋ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር የሚርቀው ዐይለት እንደደረሰ ከዚሁ መንደር አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ወደሚገኘው በሰሐቲ ሰፍር ለነበረው ለኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ሶስት ጊዜ ደብዳቤ ጽፏል።

በመጀመሪያ ደብዳቤው ከዐይለት ጦር ሠፈሩ ማርች 26/1888 ዓ.ም ለፋ ያለ ሊሆን ቀም ነገሩ[1] እኔና እናንተ ያልሰለጠኑ ሕዝቦችን አንድ ላይ ሆነን እንድንዋጋቸው ፍላጐቴ ነበር። አንድ አካል ሆነን ተዋግተን እናሸንፍ ነበር። እንግሊዞች ከግብጾች ጋር ያዋዋሉን ውል እናንተ አላከበራችሁም። በውሉ መሠረት ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ምፅዋ ላይ የጉምሩክ ቀረጥ መክፈል አይገባቸውም ነበር። በኢትዮጵያ ነገሥታት ሥር የነበሩ በኋላ ግን ግብጾች ይዟቸው የነበሩ መሬቶች በሙሉ ወደ እኔ እንዲመለሱ። ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ ሀገር ናት። ስለዚህ ሀገሬን ለቃችሁ ሂዱ፤ እናንተም በራሳችሁ ሀገር ሁኑ። እግዚአብሔር ኃይል ከሰጠኝ እናንተ በአንድ በኩል እኔም በሌላ በኩል በአንድ ላይ ሆነን ያልሰለጠኑትን ደርቡሾችን መዋጋት እንችላለን፤ ግዛታችንን በማስፋፋት እናወድማቸዋለን፤ ይህ የተሻለ ነበር፤ እኔ እንደ እናንተ ክርስቲያን ነኝ፤ ወንድማማች ነን፤ የእኛ ያለመግባባት ሌሎች እንዲስቁብን ብቻ ነው የሚጠቅመው። ራስ አሉላ ለእኔ ምንም ሳይፅፍ ያደረገውን አደረገ። እናንተም አልነገራችሁልኝም፤ የተፈፀመው የሴይጣን ሥራ ነው።

እናንተ ናችሁ ወደ እኔ ሀገር መጥታችሁ የምትወጉኝ፤ እኔ አይደለሁም ወደ እናንተ ሀገር የሄድኩኝ። እናንተን ለመዋጋት ወደ ሀገራችሁ አልመጣሁም፤ እኔ የመጣሁት ሀገርህ ተወሯል ስላሉኝ ወሰኖቼን ለመጠበቅ ነው። ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ። ሁላችን በየሀገራችን እንቀመጥ። ሁለተኛ ደብዳቤ የተፃፈው መልስ ለለዘገየበት ማርች 30/1888 ዓ.ም መጋቢት 22 ቀን 1880 ዓ.ም ነበር። በዚሁ ዕለት የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በሰሐቲ ጦር ሰፈሩ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ከምፅዋ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ከዐይለት የሚከተለው መልስ ለአጼ ዮሐንስ ተሰጠ። «ግርማዊነትዎ ሰላም እንደሚፈልጉና የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ገልፀውልኛል። የእኔ ንጉሥም የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ፍላጐቱ ነው። በሁለታችን ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ ግን የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። 1ኛ. ኢጣሊያ የዐሳውርታና የሀባብ ጐሣዎች የበላይ ጠባቂ መሆንዋን ኢትዮጵያ እንድትቀበል 2ኛ. ሰሐቲና ዊዓ እስከ ባህር ጠረፍ የኢጣሊያ መሬቶች መሆናቸውን ኢትዮጵያ እምና እንድትቀበል፤ 3ኛ. ከሰሐቲ ወደፊትም የአንድ ቀን የእግር መንገድ የኢጣሊያ መሬቶች እንዲሆኑ ኢትዮጵያ እንድትቀበል። 4ኛ. ጊንዳዕ የኢትዮጵያ ትሆናለች። ዐይለት ከነሸለቆዎቿ ለኢጣሊያ እንዲሆኑ፤ ወሰኑ በሁለቱ ሀገሮች ምልክት ይደረጋል። ግርማዊነትዎ በዚሁ የሚስማሙ ከሆነ ወደ ጦር ሠፈሬ ወደ ሰሐቲ የሚያምኑትን ሰው ይላኩልኝ የሚል ነበር።

1 Vioo Mantegazza: ibd p.CXVII



የአጼ ዮሐንስ ሶስተኛ ደብዳቤ አጠር ያለ ነው። «የእናንተ ሀገር ከባህር ሮማ ድረስ ነው። የእኔ ደግሞ ከባሕር ወዲህ እስከ እዚሁ ወደ ኢትዮጵያ በኩል ነው። እሚያጣላን ነገር የለም። አያቶቼ ነገሥታት ይገዙት የነበረ መሬት እንዴት አድርጌ ጽፌ ማህተም አድርጌ ለእናንተ እሰጣለሁ? ክርስቶስ ነው ለኔ የሰጠኝ። የክርስቲያን ደም የሚፈስበት ቦታ የት እንገናኛለን፤ እኔ የምገኘው አንድ ቦታ እናንተም የምትገኙ በሌላ ቦታ ነው። የሚያገናኘን ነገር የለም። ከእንግዲህ የእኔ መልእክተኛ ወደ እናንተ አይሄድም። የእናንተም ወደእኔ እንዳይመጣ» የተፃፈው መጋቢት 23/1880 ዓ.ም። የአጼ ዮሐንስ አቋም ግልፅ ነው፤ የሚያኮራን ነው፤ የሚደነቅ፤ በማያወላውል ሁኔታ በኢትዮጵያ መሬ ት ላይ ድርድር አላደርግም ብሏል፤ አንድ ክንድ መሬት አልሰጥም ማለቱ በታሪክ ለዘለዓለም ሊያስመሰግነው የሚኖር ነበር።

ጊዜው በኢትዮጵያ ታሪክ ወሳኝ ወቅት ነበር። የፓርታል ተልእኮ ለምን ከሸፈ ብለን በምናስብበት ጊዜ ብዙ አስተያየቶች ሊሰጡ ይችላሉ። ግብጾችና ቱርኮች ሸንፈት ሊደርስባቸው ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምረው ነው ምፅዋንና ቀይ ባህር ወደቦችን የያዙ። ነገር ግን ወደቦቹን ብቻ በመያዝ እስከ ተወሰኑ ድረስ ኢትዮጵያ ከወደቦች ለቀው እንዲወጡላት ለማድረግ በቂ ኃይል ስላልነበራት ልታባርራቸው አልቻለችም። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ በሰላም ይኖሩ ነበር። አልፎ አልፎም ወደ ደጋው ክፍል የኢትዮጵያ መሬትን ለመያዝ ዘልቀው ገብተው በተገኙ ጊዜ ሁሉ ሸንፈት ተከናንበው ነው ወደ ሰፈራቸው ይመለሱ የነበረ። ጣሊያኖች ግን አመጣጣቸው መላው ኢትዮጵ ያን ለመያዝ ስለነበረ እንደ ግብጾችና ቱርኮች መሆን አልፈለጉም። ይህ የጣሊያኖች የነበራቸው ጽኑ የመሬት መስፋፋት ዓላማ የፓርታል ተልእኮ ሊሳካ ያልቻለበት ዋና ምክንያት ነው። ጣልያኖች የእንግሊዝን ሽምጋ ይነት ይፈልጉ ይመስሉ የነበሩ ጊዜ ለመውሰድ ብቻ ነበረ ለማለት ይቻላል። በሁለተኛ ደረጃም ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ በይፋ ጦርነት በማወጃቸው ነው። ሰር ፓርታልም ጣሊያኖች ይህን አዋጅ እንዲሽሩ ለማድረግ አልሞከረም። በኢትዮጵያ በኩልስ ተልእኮው እንዳይሳካ ምን ጉድለት ተገኘ ለሚለው ጥያቄ ጥፋታቸው ሎርድ ፓታልን አስታራቂ ሳይሆን እንደ ጠላት ከኢጣሊያ ጐን የተሰለፈ አድርገው መገመታቸው ነው። የአሰብ ኢጣሊያዊ አስተዳዳሪ የነበረው ሊቸር ሊሞኒ ለኢጣሊያ የጦር ሚኒስትር[1] ጀነዋሪ 4/1888 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የአጼ ዮሐንስ ቃል ነው ብሎ ጠቅሶ ያስተላለፈው ፅሁፍ ማገበብ ይበቃል። አጼ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ሀሳባቸውን ገልጠዋል። «ለእኔ የመጡብኝ ችግሮች ሁሉ ከእንግ ሊዞች የመጡብኝ ናቸው። እነሱ ውል ለማድረግ ወደ ሀገሬ መጡ ነገር ግን እንደ አንድ ልጅ ነው የተጫወቱብኝ። ዛሬ ከነሱ ጋር ሰላም ነኝ። ነገር ግን በእነሱ እምነት የለኝም። ምን ዓይነት ሀሳብ ይዘው እንደሚቀርቡ ማየት እፈልጋለሁ። ሀሳባቸው ጥሩ ከሆነ እቀበለዋለሁ። ሆኖም ሌሎች አስታራቂዎች ቢሆኑ እመርጣለሁ። ዕቅዳቸው የሚጐዳኝ ከሆነ እታወጣለሁ። እንደ ሩሲያ ወይንም እንደ ፈረንሣይ ያሉ ሀገሮች ሽምጋዮች መጠቀም ይገባኝ ነ በር፤

1 Vioo Mantegazza: ibd p.CXI-III

ነገር ግን ከመጀመሪያዋ ሀገር ጋር የጠበቀ ወዳጅነት የለኝም። ቢሊርንግጌርም እምነት የለኝም። ምክንያቱም ንጉሥ የላትም። ምንሊክ ሸምጋይ ለመሆን ሁሉ ካለው በእንግሊዞች ሙሉ ለሙሉ ለአልተቻለ እሱ ይገፋፉት፤ ካልቻለ እውነት ጦርነት ማድረግ ያስፈልጋል። በጦርነትም ምንም ተቅም እንደማይደርኝ እጣምራ እውቃለው። የሚል ነበረ። ስለሁለቱ ሀገሮች የኃይል አሰላለፍ ሚዛን ሰር ፓርታል ከኢትዮጵያ ሲመለስ ያደረገው ሪፖርት መጥቀስ ይበቃል።[1] ሰር ፓርታል አጼ ዮሐንስን ያገኘው ወሎ አሽንጌ ሐይቅ በሆነም ዋና ከተማቸው ግን ጉንደር ደብረ ታቦር /ማምሬ/ ናት ብሏል። ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጣ ጦር ዝግጅቱን አጠናቅቆ ከኢጣሊያ ጋር ጦርነት ለመግጠም ወደ ምፅዋ በመጓዝ ተንቀሳቅሶ እንደነበረ አግኝቼዋለሁ ብሏል። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት የሰው ኃይል ብዛት ከፍ ያለ መሆኑን ገልጿል።

1. የራስ አሉላ ጦር 16,000 ወታደር
2. የራስ ሐጎስ ጦር 20,000 ወታደር
3. የንጉሥ ነገሥቱ ልዩ ዘብ 5,000 ወታደር
4. የራስ ሚካኤል የወሎ 25,000 ወታደር
5. ራስ ሀ/ማርያም የንጉሡ የመንደም ልጅ እኔ እሳቸውትም እንደ ሰማሁት ግን ከራስ አሉላ ጦር ይበልጣል
6. ደጃዝማች መሸሻ 5,000 ወታደር
7. ራስ አርዓያ ሥላሴ የንጉሡ ልጅ 40,000 ወታደር
8. ዋግሹም ጉበና የበጌምድር ገዢ
9. ዋግሹም ብሩ
10. ደጃዝማች ተሰማ
11. ንጉሥ ተ/ሃይማኖት
12. ንጉሥ ምንሊክ

ስለ ወታደሮችም ሲያሩ በደንብ የተያዙ ናቸው። የደጋው ተራራው ሀገር ተወላጆች ናቸው፤ በሚጊዜው የተከበሰ ልምድ ያደርጋሉ።

በተፈጥሮም የመዋጋት ችሎታ አላቸው፤ ብዙ ጊዜ ምግባቸውን የሚያገኙት ከሚያለፋባቸው ቦታዎች ነው። እንዳንዶቹ ግን የራሳቸው ለንቅ አላቸው። ጦሩ የሚዘም ትበት የአሥመራ አካባቢ በእርሻ ሀብታም ካለመሆኑም በላይ የራስ አሉላ ጦርና የራስ ሰብሀት ጦር በመቀለብ ላይ ስለሆነ ተጨማሪ ጦር አይችልም። ስለሆነ እንደተባለው በአሥመራ አካባቢ ጦሩ በሙሉ በሚሰበሰብበት ጊዜ ንጉሡ ሁለት አማራጮች አለው። 1ኛ. ወይንም ለጥቂት ጊዜ ውስጥ ጦሩ ወደ መሀል አገር መመለስ አለበት። 2ኛ. ወይንም ቶሎ ብሎ ወደ ኢጣሊያ ጦር በመጓዝ ፈጣንና ወሳኝ ጦርነት ማካሄድ ይኖርበታል።

1 Vico Mantegazza: ibd p. CXV



ንጉሡ ነገሥቱ የሁለተኛዋ ምርጫ አለቀድም የመረጠ መሆኑን ተገንዝቧል። ስለሆነ ለጣሊያኖች የሚከብዳቸው ተመጣጣኝ የሰው ኃይል ማሰለፍ ያለቻሉ እንደሆነ ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ጦር በሰው ኃይል ከ100,000 በላይ ነው። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት በጉራዕ በጉንደት፤ ከግብጾች ጋር እንዲሁም በቅርቡ በዶጋሊ ከኢጣሊያኖች ጋር ባደረጋቸው ጦርነቶች በችሎታው ስለሚኩራራ በልበ ሙሉነት እሸንፋለሁ ብሎ የሙሉ ሠራዊት ነው። በኢጣሊያ በኩል የኢጣሊያ ጦር በ20,000 ወታደሮች የተወሰነ ጦር ነበር። ከእነዚሁ ውስጥ 3,000 ባሺ-ቡዙክ ናቸው። በተጨማሪም 19,000 መደበኛ ያልሆኑ የደበበ ጦር ነበሩ። በሌላ በኩልም ጣሊያኖች ከንጉሥ ምንሊክ እርዳታ እንደሚያገኙ ተስፋ ነበራቸው። የእንግሊዝ መንግሥትም ጣሊያኖች በሁሉ ከእኛ ጋር ቆመል ብለው ያምኑ ነበር። ኢጣሊያ የጦር መሣሪያ የበላይነት ያላት ብትሆንም በወታደራዊ ብቃት በቂ የጀግንነት ታሪክ ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ጋር እንደማትወዳደር የታወቀ ነው።

ይህ ሰፊ ዝግጅት ቢተደረገበት የዓድዋ ጦርነትን ሊያስቀር ይችል የነበረ ጦርነት፤ ከዓድዋ ጦርነት የበለጠ ለኢትዮጵያ ዝና ሊያተርፍ ይችል የነበረ ለምን አልተካሄደም? ጦርነቱ ተካሄዶ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በአሸናፊነት ትወጣ እንደነበረ በኢጣሊያ ወታደሮች ሰፍና የነበረ የሞራል ውድቀትና ሽብር የሚጠቁም ነበረ። ኤርትራውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ተገንጥለው በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ቀንበር ወድቀው ኤርትራውያን የሚል ስም ተሰጥቷቸው ተረግጠው ሰብዓዊ መብታቸውን ተገፈው እድገ ዘም ነበር። ዛሬ እንደሚነገረው የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች እየተባሉ ሁለት ሀገሮች አይኖሩም ነበር። በአጼ ዮሐንስ ትመራ የነበረችው ኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀል የተካሄደው ትግል አጼ ዮሐንስ የክርስትና ሃይማኖት እምነት አክራሪ ተከታይ ሆኖ ግትር አቋም ይዞ በመጠሰት ሲቀርብ በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች በኩል ግን በረቀቀ ተንኮልና ደባ የተመረዘ አቋም ነበራቸው። በስነ ልቦና በኩል ፋሺስታዊ ተመጣጣኝ አልነበረም። ጣሊያና ች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቅኝ ግዛታቸውም ለማድረግ ያልሸረቡት ሴራ አልነበረም። ምንም የሴራ ቅራታ ማይሰማቸው 1ኛ. የሙስሊም ኢትዮጵያውያን እስላሞች 2ኛ. የወሎ ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን እስላሞች 3ኛ. ከክርስቲያኑ የሸዋ ንጉሥ ምንሊክ የጦር ወዳጅነት መስርተው ነበር። 4ኛ. ከእስላሞቹ የሱዳን መሃዲስቶችም የጦር ወዳጅነት እትድ አውጥተው ነበር። በሥራ ላይ ያልዋለ በት ምክንያት መርተው ወደ ሀገራቸን ካመጧቸው ከእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣናት እንዳይደገፉ በመፍራት ብቻ ነው። የእንግሊዝ መንግሥት ከሱዳን መሃዲስቶች የከረረ ጦርነት ማካሄዱ የሚታወስ ነው። 5ኛ. ጣሊያኖች ከክርስቲያኑ ንጉሥ ተ/ሃይማኖትም ወዳጅነት ፈጥረው ነበር። 6ኛ. ጣሊያኖች በትግሬይ፤ በኤርትራ፤ ሸዋ፤ ከፋ፤ ጅማና ወለጋ ከነበሩ የኢጣሊያ ሚሲዮኖቻቸው ቅርብ ግንኙነት ፈጥረው የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን መሣሪያ ያደርጓቸው ነበር። ካቶሊካውያን የነበሩ የፈረንሳይ ሚሲዮኖቻቸው ግን ዓላማቸውን ለማያራምዱ የአንድ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የአንድ ገዳም ማኅበር /ካፑቺን/ ከነበሩ የኢጣሊያ ዜጎች ለይተው እየተቀረጹ ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ አደረጓቸው። አጼ ዮሐንስ የጣሊያኖች እርመኔነት ተረድተው ቢሆን ኖሮ ግን ሱዳኖች እስላሞች ለሆኑ ቀንደኛ ጠላት፤ ጣሊያኖች

ክርስቲያኖች ስለሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ጠላቶቹ እያደርጋቸውም ነበር። ከሱዳኖች ጋር ተወያይቶ ይህ ከባህር ግዶ የመጣ የጋራ ጠላታችን አንድ ላይ ሆነን እናባርር ባለ ነበር። አጼ ዮሐንስ ከመላው ኢትዮጵያ ተወጣጥቶ ኢጣሊያኖችን ከምፅዋ ለማስወጣት ምፅዋ አካባቢ የሰፈረ በእሱ የሚመራ 120, 000 የሰው ብዛት እንዳለው ይገመት የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ጣሊያኖችን ከምፅዋ ለማስወጣት ብታት እያለው ደርቡሾችን ለመዋጋት ትድሚያ በመስጠት ወደ መተማ ፊቱን እንዲያዞር ማድረጉ እንቆቅልሽ ሆኗዋል። ጣልያኖች ይህን ማድረግ በመቻላቸው አጼ ዮሐንስን ያስፈሩ ስለመሰላቸው ከነበራቸው የሞራል ውድቀት ሊያንሰራሩ ችሏል። በጦርነት እንዳሸነፉ መስሎ ታይቷቸዋል። የአጼ ዮሐንስ የክርስትና እክራሪነት ውጤት ነው።

Il falso allarme al forte Margherita.

*Essendo stata segnalata la comparsa di una banda di abissini di pozzi di Tata, furono dal forte Margherita sparati alcuni colpi di cannone, che spassarono immediatamente la via.*





Re Giovanni

በኢጣሊያ ሰፈር ሽብር ሰፍኖ ነበር

አፄ ዮሐንስ

የአፄ ዮሐንስ ጦር ዓይለት ሲሰፍር በጣሊያኖች ላይ ሰፈኖ የነበረ ፍርሐት



# 4. በኢጣሊያ ሰፍሮ የነበረበው ፍርሐት

የመሸነፍ ጽዋ የማያውቅ በጀግናው አጼ ዮሐንስ የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት በትኩስ መንፈስና ኃይል ወደ ምፅዋ ዘምቶ ጣሊያኖችን ከምፅዋ ለማስወጣት በወኔ መጥቶ ነበረ። የኤውሮጳ ታላላቅ መንግሥታት ማይቀሩ ሥጋት ላይ ሊጥላቸው የነበረ ለአፍሪካውያን ፀረ ቅኝ አገዛዝ እን ቅስቃሴ እገዛና ማነቃቂያም ሊሆን ይችል የነበረ፡ በጀግንነት ብዙ እማይ መሰገነው በአጼ ምኒሊክ ይመራ የነበረው በዓድዋ ጦርነት ካላየው የጦር ጀብዱ የበለጠ ጣሊያኖችን ለማንበርከክ ዕድል የነበረው ዐይለት ደርሶ ፊቱን ወደ ኋላ ለምን እንዳዞረ ለእኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንድ አንቆቅልሽ ሆኖብናል። በእርግጥ የጠላት እጅ ያለበት ነው። 46 መድፎች እሰልፎ የነበረው የግብጽ ጦር በጉራዕ የደመሰሰ አጼ ዮሐንስ ጣሊያንም ከዚህ የበለጠ ኃይል እንደማይኖረው ስለሚገመት በአሸናፊነት የማይወጣበት ምክንያት አልነበረም። ከዘጠኝ ዓመት በኋላ እንኳን ጣሊያን በዐድዋ ጦርነት ያሰለፉቻቸው 56 መድፎች ብቻ ነበሩ። አጼ ዮሐንስ ለሽንፈት የተዳረገው በጦር ሜዳ ተሸንፎ አይደለም። የተሸነፈው በተደቀነበት ከአጼ ምንሊክና ከጣሊያኖች ጥምር የስለላ መረብ ነው።

አጼ ዮሐንስ በዐይለት የመጨረሻ ደብዳቤው ከእሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት በሰሐቲ የኢጣሊያ ጦር ሠፈር ይገኝ ለነበረው ለኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ዋና አዛዥ ከፃፈ በኋላ ጦሩን በሙሉ ወደ ኋላ እንዲመለስ አደረገ። ይህ ውሳኔ ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ እሳዛኝ መራራ ትክክለኛ ያልነበረ ውሣኔ መስሎ ነው የሚታየው። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ቀን በየዓመቱ የሀዘን ቀን ተብሎ ታስቦ መዋል ነበረበት። በተለይ የኤርትራ ተወላጆች የሆኑ ሁሉ ለጅ ቦች የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ሰጡን ብለው መውቀስ ይገባቸዋል። በጣሊያኖች ግምት አጼ ዮሐንስ ጦርነት መግጠም ያልፈለገበት ምክንያት፤ 1ኛ. አጼ ዮሐንስ ከጣሊያኖች የበለጠ ደርቡሾችን ስለሚጠላ 2ኛ. ጣሊያኖችን ለማሸነፍ እንደማይችል ስለተረዳ 3ኛ. የምግብ እጥረት ስላጋጠመው ነው በማለት በቴሌግራምም በደብዳቤም ደስታቸውን ወዲያውኑ ከምፅዋ ማስተጋባት ጀመሩ። ነገር ግን ስለ ስንቅ እጥረት አጼ ዮሐንስ አስቀድሞ ያሰበበት ስለሆነ ምክንያት ሊሆን አይችልም። ጣሊያኖችን መፍራትም የማይታሰብ ነው። ራስ አሉላ በዶጋሊ ያረዳቸው ጣሊያኖች አጼ ዮሐንስን ሊያስፈሩ አይችሉም። በኢትዮጵያ ወኩል በወቅቱ ለሠራዊቱ ወደ ኋላ ፊቱን ማዞር የተሰጠ ምክንያት የለም። በንጉሡ በሹማምንቱና በጦሩ መሀል የሀሳብ ልዩነት እንደነበረ የተገኘ ፍንጭ የለም። በሌላ ይኹ ያልሆኑ ታሪክ መጣጥበት ስናገ ላብጥ ግን እንዳንድ ፍንጮች ለማግኘት እንችላለን። ስለሆነም በረጋ መንፈስ ሲታይ አጼ ዮሐንስ ከዚህ ውሣኔ የደረሰው የደርቡሾችን አደገኛ ሁኔታ ስለተገነዘበ ሊሆን ይችላል። የጐንደር አቢያተ ክርስቲያናት ይታጠሉ ነበር፣ ክርስቲያኖች ይቃረሉ ነበር። የዚህ ሁሉ ሁኔታ የሕዝቡ ብሶት ከእልቂት እንዲያድናቸው በመማፀን ጥያቄ ከጐንደር ሕዝብ በየቀኑ ይደርሰው እንደነበረ የታወቀ ነው። ለዚህ ይሆናል አጼ ዮሐንስ ደርቡሾችን የመጀመሪያ ጠላቶቹ በማድረግ ወደ ኋላ ለመመለስ የወሰነው። ሠራዊቱ 700–800 ኪሎ ሜትር በእግር ተጉዞ መጥቶ ከምፅዋ 45 ኪሎ ሜትር ብቻ ርቀት

በዐይለት መኖር ኃይሉና ወኔው ሚያተነሳ ለመጣበት ዓላማ ማይለግሉ እንዲመለስ ማድረግ በሙራሮቱ የሞራል ውድቀት እንደሚያጋጥም አያጠራጥርም።

ስለሆነም አጼ ዮሐንስ ለዚሁ ድርጊቱ እኛ የዛሬ ትውልድ ለንወቅሰው አይገባም። እንዲያን በአጼ ዮሐንስ ጊዜ በእሱት በመኖችን በ21ኛው ክፍለ ምዕት ዘመን ዋዜማ በምድረ ሱዳን ክርስቲያኖና እስላም በሃይማኖት ምክንያት ሲፋጁ ይታያሉ። በሱዳን ብቻ አይደለም፤ ከፓኪስታን እስከ ሞሪታኒያ ያሉት ብዙ እስላም ሀገሮች እንደ ኢራን እስላማዊት ፋንዳሊዝ በኋላ ስም በሀገራቸው መንግሥት መመሥረት የሚመኙ ጥቂቶች አይደሉም። ክርስቲያናዊ ፋንዳሊዝ ብሎ በመሰየም መንግሥት ለማቋቋም የሚመኝ ክርስቲያን ሕዝብ ግን በመላው ዓለም የለም። በኢትዮጵያ ታሪክ ለአጼ ዮሐንስ ተደጋግሞ የሚወሳው የክርስትና ሃይማኖት ከልክ በላይ አክራሪ መሆን ነው። አጼ ዮሐንስ በትግሬና በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ላይ በፈፀሙው የማያወላውል ጀግንነት ተገቢ ውለታና ክብር አልተሰጠውም። ስለ ኤርትራ መሬ ጠር በምንጽፍበት ጊዜ አጼ ዮሐንስ በመተማ ባይሞት ኖር ኤርትራ የምትባል ሀገር አትፈጠርም ነበር። ወይንም ደግሞ በምትኩ አጼ ምንሊክ ሳይሆን ሌላ ንጉሥ ለምሳሌ አጼ ተ/ጊዮርጊስ ነግሶ ቢሆን ኖር ኤርትራ የምትባል የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አትፈጠርም ነበር።

በሀገራችን በምፅዋ አካባቢ ወረው በያዙት መሬት ሆነው ለመዋጋት ፍላጎት የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ጦርነት ለመግጠም ይጠባበቅ የነበሩ የኢጣሊያ ወታደሮች በዶጋሊ ከባድ ሽንፈት ደርሶባቸው ስለነበረ ከባድ የመንፈስ ጭንቀት እንደነበራቸው በዕቅት ራጣቸው ሚሲዮናች ሊጽፏቸው የነበሩ ጽሁፎች እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎች ሊቀርቡ ይችላሉ።[1] ይህ ሥዕል ቁ. 1 ፎቶ ኮፒ ኢትዮጵያውያን ሚይታዩቸው ኢትዮጵያውያን መጠጡን ብሎ አንድ የኢጣሊያ ወታደር ማስጠንቀቂያ በለጠፈት ጊዜ በአንድ ጦር ሠፈር ተጠምደው የነበሩ መድፎች በበዶ ተከማቸውን ሲያሳመ ያሣያል።[2] ማርች 29/1888 ዓ.ም ትልቁና ለተባለው ጋዜጣ በምፅዋ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ሆኖ የዜና ወኪል ጋዜጠኛ ያቀረበው ጽሁፍ የሶስት ቀኖች ሽብር በኋላ እርዕስት ማርች 26፣ 27፣ 28 ያሳውንና የሰማውን ሲገልፅ የኢጣሊያ ወታደሮች ምን ያህል የአንጎል ሽብር እንደነበረባቸው እንረዳለን። «በሰሐቲ (ጦር ግንባር) ወደ ምፅዋ ተመለሰኩ፤በሁለት ሰዓት ነበር፡አንድ መልእክተኛ እኔ ዘንድ መጣና ጌታዬ ቶሎ ብለው ወደ ሰሐቲ ይመለሱ። ዛሬ ማታ ወይንም ነገ ጧት ንጉሡ ይመጣሉ ብሎ ነገረኝ። እኔ ጦርነት እንደሚይከሬት ዓምንበትም በዐቢሮ ተሳፍሬ ወዲያውኑ እመራው። ሰሐቲ ለመድረስ ግማሽ መንገድ እንደደረስኩ ከሰሐቲ ጦር አዛዥ የማስጠንቀቂያ ደወል ተሰማ። በተጠንቀቅ ሁኑ ተባለን። እኔ በመሰከት ምንም ነገር አላየሁም። ወታደሩ ግን ድምፅ ለምቻለሁ እያለ ከመናገር አላቋረጠም። በየጦር ሠፈሩም ተኩስ ነበር። ዓይኑ ተኩሶ ተከፍቶቢታል በኋላ ፍራቻ ሁሉም ሰው መሣሪያ መያዝ ጀመረ።

1 G.Piccini: Guerra d;Africa Compapagna 1888 Parte IV p.225

2 G.Piccini: Guerra d;Africa Compapagna 1888 Parte IV p.258



ወደ ሰሐቲ ደርሰን በመጀመሪያ ያገኘሁትን ወታደር ጠየቁት፤ ጦርነቱ ሚይጀመር አይቀርም ከሰሐቲ ወጣ ብሎ ያለው የጦር መድረኛ ክፍል ዘንድ ፳፰ ቸምበሩን እኒያን ርኩት፡ እዛው እጀን ከጨበጠኝ በኋላ አመሰቅኖት ነበር ታዲያስ ቀኑ ደረሰ ወደ ብዬ ጠየኩት «ዛሬስ አያጠራጥርም ጦርነቱ መጀመሩ ነው አለኝ። ግን ማስጠንቀቂያ ደወል የሰማችሁ ለምንድነው ብዬ ጠየኩት። እደም የሚጨምቅ ኃይለ ከአበሾች ተኩስ ተከፍቶ ስለነበረ ነው አለኝ። መድፎቼን ተዘጋውረን አየን፤ የጠላት ወታደሮችን ለማጥቃት ምክርን እለመጥን የዛሮች የተፈጠር ድምጽ ካለሆነ ሌላ ድምጽ አልሰማንም። ሌሊት ደረሰ ሁላችንም በድንኳን ውስጥ ማደሪያን በመድፎች ስር ተኝተን አደርን ጧት እዛው ቀጠ ቀለኝ። ዙሪያው ሁሉ እንቅስቃሴ ነው። አኔም በቀኝ እጄ አርጓስ ይዣለሁ፤ በአገሬ ጠብመንጃ ተተምቄአለ፤ ሽጉጥ ታጥቄያለሁ፤ አንድ ፈረስ ታስሮ ተጭኖ ቆሟል፤ ለእምባሲያን ዜና ለማስተላለፍ ተዘጋጅቻለሁ። ፋት የሚያሳይ መነፅር አካባቢውን ሁሉ ብመለከት ምንም የለም። መረጃ የሚጠይቃቸው ሁሉ የተለያዩ ሀሳቦችን ይሰጡኛል። አብዛኛው ንጉሥ ነገሥቱ ዐይለት እንደደረሰ ይነግሩኛል፤ ከ100,000 ሺህ ወታደር ሌላ ሽምግሌዎች፣ ሴቶች ልጆችም አሉ ይላሉ። ይህ ሁሉ የት ነው። ሁለት ቀን በፊት ምፅዋ ግባው የምንኩሉ አርቂቁ አትምሉ፤ ሊምቢሬምጊ ነዋሪዎች ዐሙሉ ወደ ምፅዋ ሲገቡ አይቻለሁ። የበረሶች ጉዞ ነበር ያስገረመኝ፤ እግረኞች፣ በበቅሎ፣ በግመል ነበር የሚጓዙት፤ መተላለፊያ አልነበረም። በረሶች ከቢታቸው ለቀው መሄድ የማይወዱ ሲሸሹ ማየት አንድ አደጋ በእርግጥ እንዳለ ያስገነዝባል። አትምሉ የሚገኘው የስዊዲን ሚሲዮን እንኳን ማይ ቀር በዶጋሊ ጊዜ ያልተነቃነቀ ሊቀን ለቀው መጥቷል። ይህ ሁሉ፤ ሌላም የነበረ ትርምስም ሐበሾች አይመጡም ብዬ ያለደረኩት ውርርድ እስከ ራሰሁ ብዬ ጥርጣሬ እድርብኝ ነበር። ብሸር ግን ደስ ይለኛል። ማርች 27 የሌሊት ወይንም የሀሰት ማስጠንቀቂያ ሳይሰማ ቀላን፤ ማታ ለመተኛት ወደ ድንኳናችን ሄድን፤ እንቅልፉችን ረጅም አልሆነም፤ ሰዓት ሰገት ሲሆን ና እያሉ በአገሬ ጉተቱኝ፤ ማስጠንቀቂያ ተደውሏል፤ ወታደሮች በታ በታቸውን ይዘዋል አሉኝ። ዓይኔን እያሸሁ ለብሼን ማወላት ስለነበረ የተኛሁ መሳሁ። በእርግጥም ከ4–5 ኪሎ ሜትር ርቀት ተኩሶች ይሰሙ ነበር። ለግማሽ ሰዓት ቀጠሉና ቆሙ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ከአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ሌላ ተኩስ ተሰማ፤ ዋና ጦር ሠፈር የተቃጠለ መሰለኝ፤ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወታደሮች ወደ ሠፈራቸው እያፈገፈጉ ሲመለሱ አየን፤ በኋላም ተኩሱ በጠላት ወታደሮች እንደነበረ ተነገረን። ጥቂት ጊዜ በኋላ ፈረስ እየጋለበ ሁለት ሰዎች አንድ ኮሎኔልና አንድ መቶ አለቃ ወደ እኛ መጡ። ማን ነው ተኩስ የከፈተ ብለው ጠየቁ ኮሎኔሉ ከእኛ ዞሮ ጠየቂዎች ተብሎ መልስ ተሰጠው። እሱን ለምን በቦታቸው የሉም ብሎ ጠየቀ። ከጠላት ጋር ከተገናኙ በኋላ ወደ ኋላ አፈግፍገው ነው ብለው መልስ ሰጡት። «ቦታን ላይ ነበር የተቀየሩት» ብሎ ጠየቀ እንደገና፤ «ብልጭ ፈረሰኞች ላይ» የሚል መልስ ተሰጠው። እሱም «ብልጭ ፈረሰኞች የምትሏቸው እኔ ነበርኩ፤ ቢሆንም በታቸውን ለቀው የሸሹት በጣም በጥፋት ነው፤ እሱንም ወደ ክፍለ ጦር በታ ተመልሰው በታቸውን እንዲይዙ ብሎ ተናገረ ሰው ዋና እሉ ይህ ሁሉ እስከሚያልቅ

የሀሰት ማስጠንቀቂያ ለማስወገድ ማስጠንቀቂያዎች ለወደፊት ያለመኩንኖች ትእዛዝ እንዳያስጡ ብሉ ለሁሉም ትእዛዝ አስተላለፈ። ከአራት ቀን ወዲህ የምንሰማው ሐበሾች በሁሉ ቦታ እንዳሉ ነው፤ የተገኙበት ቦታ ግን የለም። የማራይታ ተራራ ከፍቅ የሚያማይ መነፅር የሐበሻ ጦር ይታያል አሉኝ። እኔም ማራይታ ተራራ ሄጄ አየሁ። እኔ ግን ያየኋቸው የኢጣሊያ ባሺቡዙክ ናቸው ጠብመንጃቸውን መሬት አስቀምጠው። አራት ኪሎ ሜትር ወደ ዐይለት የሚወስደው መንገድ ባሺቡዙክ ተዝናንተው የነበሩት የጠላት እንቅስቃሴ እንዳልነበረ ምልክት ነው። እኔ ጠቅላይ አዛዡ እንደሚለው ንጉሡ ዐይለት እንዳሉ አልክድም፤ ጦሩም ኃይለኛ መሆኑን አልክድም፡ እማይገባኝ ግን ይህ ሁሉ አጋነው ማውራት ነው። ሐበሾች ምናልባት ይመጡ ይሆናል ልናያቸው ይሆናል፡ ነገር ግን አሁን የሉም ማይኖሩ እንዴት አሉ ለማለት እንገደዳለን። አመመን ብለው ከቦታቸው እማይገኙ ወታደሮች እየጨመረ ነው። ለምሣሌ ከ240 ፈረሰኛ ወታደሮች አሁን እቦታቸው የሚገኙት 37 ብቻ ናቸው።

ማርች 8 የእጼ ዮሐንስ ጦር በጉራዕ ግብጾችን ያሸነፈበት ቀን ዋዜማ ነበር። ይህንን ያስታውሱ የነበሩ ጣሊያኖች ቀኑ እንደ ጥንቆላ የሚቀናን ቀን ነው ብለው ሐበሾች ጦርነት የሚከፍቱብን ቀን ሊሆን ይችላል ብለው ፈርተው ስለነበረ እንደ አጋጣሚ አነስተኛ ተኩስ ሲሰማ ሐበሾች ወረሩን ብለው ተሸብረው የዋሉ መሆኑን ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ማንቴጋትሣ በዚሁ ዕለት ባስተላለፈው ዜና ጣሊያኖች በሽብርና በፍርሃት እንደነበሩ ያስረዳል። የማስጠንቀቂያ ተኩስ ለመጀመር የተተኮሰው ከአንድ ኢጣሊያ ጦር ሰፈር ነበር። ሽብሩ ከሰሐቲ ጀምሮ እስከ ምዕዋ ተዛመተ። በሰሐቲ ወታደሮች ወደ ሰፈራቸው ገብተው ቦታቸውን ያዙ። በምጽዋ ቀኑ እሁድ ስለነበረ ሰዓቱም 12:00 ሰዓት የመዝናኛ ሰዓት ስለነበረ ወታደሮቹ ወደ ከተማ የሚወጡበት ሰዓት ነበር። ወታደሮቹም፡ ባህር ኃይሉቹም በከተማዋ ተበታትነው ነበር። በዚሁ ጊዜ የማስጠንቀቂያ ምልክት በተሰማ ጊዜ በየቦታው ወታደሮቹ ሲሮጡ ይታዩ ነበር። የታየው አንድ አስጨናቂ ትርኢት ነበር። ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ሁሉም ሂሣብ ሣይከፍሉ በለሄዱ ከስረዋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ጦር ሣይዋጋ ይመለሳል ተብሎ እይገመትም ነበር።

የባቡር ሀዲድ መንገድ ያፈራርሳሉ የሚል ስጋትም ነበረን፤ ነገር ግን ይህ የጥቂት ወንበዴዎች ሥራ እንጂ ብዛት ያለው ጦር ለዚህ ዓላማ እንደማይነሳ ተገነዘብን። ሰኞ ማታ ስንተኛ ማክሰኞ እንወረራለን የሚል እምነት ነበረን፤ በዚሁ እምነት ብዙዎቹ ሣይተኙ ነበር ያደሩ። የታይምስ ጋዜጣ የዜና ወኪልም ከእኛ ጋር ነበር፤ ከለሊቱ 6:00 ተኛን፤ ነገር ግን ወዲያውኑ ማስጠንቀቂያዎች ተሰተሉን። ማክሰኞ ብዙ አዲስ ነገር አልታየም። ምሣችንን መብላት ስንጀምር ግን አዲስ ማስጠንቀቂያዎች ተሰሙ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ ቀኖች አለፉ። አንድ ቀን ግን ሁለት ቡቲቲ ልብስ የለበሱ ሐበሾች ከንጉሡ ተልከናል ብለው ወደ እኛ መጡ። የመጡበትም ጉዳይ ንጉሡ ሰላም እንደሚፈልጉ ለኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ለመንገር ነበር። የጦሩ ዋና አዛዥ ጥያቄው በቃል ሊሆን አይችልም። ንጉሡ ስለ ሠላም መደራደር ከፈለገ ደብዳቤ መፃፍ እንዳለባት ተነገሯቸው ወደመጡበት ተመለሱ። በአሁኑ



ጊዜ ዋናው የንጉሡ ጦር በዐይለት ሜዳ እንደሰፈረ ታውቋል። ንጉሡ በሕይወቱ ከአሥመራ ገደላ ገደሎች አልፎ የማያውቅ ለሽርሽር እንዳልመጣ ስለሚገመት የእኛ ወታደሮች ቀንና ለሊት በተጠንቀቅ እንዲሆኑ ተደረገ። ለሶስት ለሊት በመደዳ አነስተኛ ተኩሶች ሁለቱ ወገኖች ይለዋወጡ ነበር። ደበበ አሁን ከንጉሡ ጋር ስለሆነ ጣሊያኖች ደካሞች ናቸው የወታደር ብዛት የላቸውም እያለ ያሳምናቸው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንድ ሹማምንቶች ጦርነቱ ቶሎ እንዲጀመር የትዕግስት ማጣት ሁኔታ ነበር። በተለይ ራስ አሉላ ሰላዮችም ወዶገቦችም በአንድ ቃል እንደተናገሩ በራሱ ሀሳብ ጥቃት ለመጀመር አሻፈረኝ ብሎ ነበር።[1] ንጉሡ ግን አልቸኮለም ነበር። በንጉሡ እና በራስ አሉላ ብዙ ስምምነት እንዳልነበረ የሚያስረዳው ከንጉሡ የተላኩ ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ መልእክተኞች ራስ አሉላ በሰበብ እንዳያስቀራቸው ንጉሡ የላካቸው ራስ አሉላ በሰፈረበት ቦታ ሣይሆን ሌላ ራስ በሰፈረበት ነበር። ረቡዕ አንድ ቄስ ወደ ኢጣሊያ ጦር ሰፈር ርቦኝ ነው የመጣሁ ብሎ ገባ። ሐሙስም እንደዚሁ ሌላ ቄስ መጣ። ሰላዮች እንዳይሆኑ ስለተጠረጠሩ እጃቸውን በብረት ታስረው ወደ ምፅዋ ተወሰዱ። ምግብ ተሰጧቸዋል። እንደረሀብተኞች ብዙ በሉ። ጥያቄ ተደረገላቸው፡ ከሁለቱ ቄሶች አንዱን አነጋግሬው ነበር።

ስለጣሊያኖች የባቡር ሀዲድ አደነቀ። ስለ ራስ አሉላ ሲጠየቅ ጣሊያኖችን እጠቃለሁ ብሎ መፈለጉ ዕብድ[2] ነው ብሏል። ስለ ደበብ[3] ተጠይቆ ከንጉሡ ጋር መሆኑ ገልጦ ነገር ግን ሹመት እንዳልተሰጠው ተናግሯል። ራስ አሉላ በደበብ እንደሚቀኑም ነግሮኛል። አሁን ሌሎች ሁለት የንጉሡ መልእክተኞች ደብዳቤ ይዘው መጥተዋል። በዚሁ ደብዳቤ ንጉሡ ሰላም እንደሚፈልግ ገልጸዋል፤ ሁለተኛም ደብ ዳቤም ጽፈዋል።

የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ከመንግሥቱ ከተመካከረ በኋላ ሰላም ለማድረግ ንጉሡ የማይቀበላቸው ቅድመ ሁኔታዎች በመጠየቅ ለንጉሡ ደብዳቤ ላከለት። ሰኞ ጠዋት ንጉሡ ለኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ እንደገና ደብዳቤ በመጻፍ በሁለቱ መልእክተኞቹ እማካኝነት ለጊዜው የሰላም ውይይት መቀጠል እንደማያስፈልግ ገልጾ ጻፈ፤ በማግስቱ ማክሰኞ ጦርነቱ ይጀመራል ተብሎ ተፈርቶ ነበር፤ ነገር ግን ጠዋት ሐበሾች ሰፈራቸውን ለቀው እንደሄዱ ታወቀ።

የኢጣሊያ ጦር የነበረው ሌላ ችግር የጦር አዛዦች መቀያየር ነው። ከመጀመሪያ የምጽዋ ወረራ ፌብሯሪ 1885 ዓ.ም. እስከ ማርች 30/ 1888ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ተፋጠው በነበሩበት ጊዜ አራት ጄኔራሎች የጦር አዛዦች ተቀያይረዋል። ይህም የአመራር ድክመት የሚያሳይ ነው።

---

1 Vico Mantegazza: ibd p.264

2 Vico Mantegazza: ibd p.266

3 Vico Mantegazza: ibd p.266

ጠቅላይ ሚ/ሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና የጦር ሚኒስትሩም በዶጋሊ ጦርነት ምክንያት ስራቸውን ለቀቁ።

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁኔታ በኢጣሊያ ጦር ሠራዊት በኩል የነበረውን የመረበሽ ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ሁኔታ ለመረዳት(Tribuna) በተሰኘው መጽሔት በወቅቱ ያወጣው አትመው አነስተኛ ምሣሌ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል። መደበኛ ያልሆኑ የኢጣሊያኖች ቅጥረኛ ወታደሮች ባሺ ብዙክ በኢትዮጵያ በኩል የነበረ በራስ መተማመን ስሜት ከፍተኛ እንደነበረ ለመረዳት አንድ አነስተኛ ምሣሌ የሚሆን አንድ ባሺ ብዙክ ቡድን ኀይለት ድረስ በድንገት ዘልቆ ሄዶ መንደሩን ተቆጣጥሮ አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ምርኮኛ አድርጎ ወደ ጣሊያኖች በቀረበበት ጊዜ በከፍተኛ ኩራት «የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ» ራስ አሉላ መጥቶ ይበቀለናል ብሎ እንደተናገረ ጽፏል።

የዚሁ ምዕራፍ ጭምሩ ሲገመገም የሰር ፓርል ተልኮ የተሳካ ነበረ ለማለት ይቻላል፣ የሁለቱ ወገኖች ሆማብ ዳሰሰ፤ ተገቢ ትብብር አላገኘም፣ የእንግሊዝ መልእክተኞች በጣሊያኖች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት አትርፈዋል። እንግሊዞች ገና ከካይሮ ሳይነሱ ጣሊያኖች ለራስ አሉላ የሚመጡ መሆናቸውን እንዲነግሩላቸው ቢጠይቋቸው ጣሊያኖች በኢትዮጵያ በኩል ፈርቶን ነው አግላጅ የላከብን እንዳይሉባቸው ፈርተው፣ ማይተባበሩዋቸው ቢቀሩም፣ እንግሊዞች ምጽዋ እንደደረሱ ራሳቸው ለራስ አሉላ መልእክተኛ ልከው በአጭር ጊዜ እስረቅደው ጉዞቸውን መጀመር ችለዋል። ይዘውት የመጡት አስተርጓሚያቸው በኃይለኛ ፀሐይ ቢሞትባቸውም ንብረታቸው ቢሰረቅባቸውም ጉዞአቸውን አቋርጠው ከመንገድ ተመልሰው እንደገና ጉዞቸውን ጀምረው አሥመራ ሊደርሱ ችለዋል። አሥመራ ከደረሱ በኋላ ወደ አጼ ዮሐንስ ያለበት ወዲያውኑ ለመንዝ ጠይቀው ራስ አሉላ ግን ንጉሠ ነገሥቱን ሳላስፈቅድ አትሄዱም፣ እውነት እንግሊዞች መሆናችሁን አለመሆናችሁን ብሎ ከለከላቸው። ያለ ውዴታቸው አሥመራ ለ15 ቀኖች ቢቀ መጡም እስረኛ ሆነናል ብለው ተቃውሟቸውን ከማሰማት በቀር ወደ ኋላ ለመመለስ ሳያስቡ የተላኩበት ገዳጅ በደህና ለማከናወን በቅቷል።

በኢትዮጵያ በኩል የአጼ ዮሐንስና የራስ አሉላ ጸረ ኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ወረራ በማያመላውል ሁኔታ አቋም በመውሰድ የተንጸባረቀበት ጊዜ ነበረ። (Crispi) ክሪስፒ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ሲመረጥ ኢትዮጵያንና ኢጣሊያን ለማሥታረቅ ብሪታኒያ ተማጸን የጀመረችበት ወቅት ነበረ። ከክሪስፒ በፊት የነበረው ጠቅላይ ምኒስትር ዴፕሬቲስ (Depr-etis) ጣሊያኖች በዓላማ የሚመሩ ባለመሆናቸው በኢትዮጵያ ላይ ምን እርምጃ እንደ ምንወስድ አናውቅም በማለት የእንግሊዝ መንግሥት ሽምጋይነት ለመቀበል ፍቃደኛነቱን ለመግለፅ ዝግጁ አልነበረም። ክሪስፒ ግን ለራሱ ዓላማ እንዲጠቀምበት የእንግሊዝ ሽምጋይነት በደስታ ነበረ የተቀበለው።



የእንግሊዝ ሽምጋይነት መነሻ የሆነው አጼ ዮሐንስ የሒወት ተብሎ የሚጠራ ውል አልተከበረም በማለት ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፈው ደብዳቤ መሠረት ነበር። ክሪስፒ ብዙ ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ ነበረ የእንግሊዝ ሽምጋይነት የተቀበለው።

(Carlo Zaghi) ካርሎ ዛጊ ዴፕሬቲስ ጥሩተኛ አድርጎ ክሪስፒ ትክክለኛ ነው ብሎታል። የእንግሊዝ መንግሥትም ሽምጋይነት መቅረቡ ከልብ የመነጨ ነው ብሎታል። ጠረኛ ከሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ኢጣሊያ እንዲትጋፈጥ በማሰብ ነው ኢትዮጵያውያንም በሱዳን እንግሊዝ ከደሩቡሾች የነበራት ውጥረት እገዛ እንዲያደርጉላት አስቦ ነው ብሎታል።

ጣሊያኖች ከእኛ ጋራ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደካሞች ናቸው። ከጥንት ጀምሮ አንድነታቸውን ሊመሰርቱ ለዚሁ ያበቋቸው ሀገሮች ባለውለታ መሆን አልቻሉም። ጣሊያኖች ከጥንት ጀምሮ ምንም የማይጠቅሟቸው ከጀርመኖች ጋራ መቀራረብ ነው የሚወዱ። አሁንም ጀርመኖችን ማድነቅ አላቋረጡም። የጀርመኖች ጭራ ተከትለው ከመሄድ የእንግሊዞች ጭራ ተከትለው መሄድ ይበጃቸው ነበረ። የሚወዱት ከሀገራቸው ተሰደው ወደ አዲስ ሀገሮች ለመስፈር ጥቅም ሊያገኙ ይችሉ ነበረ። እንደዚሁም የፈረንሳይ የእስፔን የትንሿ የፓርቱጋል ጭራ ተከትለው ቢጓዙ በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ ለመስፈር ጥቅም ያገኙ ይችሉ ነበር። የኢጣሊያዊው ክሪስፒ በአፍሪካ የቀኝ አገዛዝ ዓላማ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች እንዲሁም ፓርቱጋሎች ከሚያራምዱት ለየት ያለ ነው፤ የሚለይበትም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገሩን ሕዝብ ፈጅተው፤ ጨርሰው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጣሊዮኖችን ለማስፈር ነበር።

እንግሊዞች ጣሊያኖችን የቀይ ባሕር ጠረፎች እንዲቆጣጠሩት የሚገፋፏቸው ዓላማቸው ምን እንደሆነ ሳይገነዘቡ ጣሊያኖች በሱዳን ወታደራዊ እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ፈልገው ይሆናል ብለው ጥርጣሬ ነበራቸው። ይህ አባባል ግን እንግሊዞች አስተባብለውታል፤ ሊሆንም የማይችል ነው ምክንያቱም በጦርነቱ ቢካፈሉም ጥቅም መፈለጋቸው አይቀርም ነበር።

## 5. የሸዋ ፖለቲካና የትግራይ ፖለቲካ

እንደሚባለው ሁሉ ራሳቸው ጣሊያኖች ሸዋ የነበራቸውን ከምኒልክ የተሰጣቸው ትንሿ ልጥ ግረሬያ የምትባለው መሬት የመላው ኢትዮጵያ ገዢዎች ለመሆን የረዳቻቸው መሆኗን ከተለያዩ ደራሲያን የተጻፉ መጽሀፍቶች ያስረዳሉ። ፕሮፌሰር ላፔቶ ኢጣሊያ አሰብን እንዲገዛ በማድረጉ መላው ኢትዮጵያን ለመያዝ በቅተናል አላሉም፣ ወይንም ሌላ ምክንያት አላቀረቡም። የጠላት ወራሪዎች ኢትዮጵያ ላይ ይመጡ የነበሩ በሙሉ በቀይ ባህር ጠረፎች ነው ተብሎ በተደጋጋሚ የሚነገረው ስህተት መሆኑን እንረዳለን። ሸዋ በንጉሥ ምኒልክ ተባባሪነት ከፍተኛ የኢጣሊያ የስለላ ድርጅት ተቋቁሞበት ነበረ፤ ከመታደሉ ወረራ የስለጠ ተግባር አከናውነዋል። አሰብን በመግዛት ኤርትራን የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት እንድትሆን መሰረት



Re Giovanni!




በትግራይ ፖለቲካና በሸዋ ፖለቲካ ዋና ተዋንያን 1.አፄ ዮሐንስ 2. አፄ ምኒልክ 3. ኮንት አንቶኔሊ



የማስ ፕሮፌሰር ጁሰፔ ሳፔቶ አልነበረም ተቀማጭነቱ ሸዋ የነበረው ካርዲናል ማሳያ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እንድታስፋፋ ከሳፔቶ የበለጠ አስተዋጽኦ አድርጓል ቢባል ስህተት አይሆንም። ካርዲናል ማሳያ ከ1846 ዓ.ም. ጀምሮ 35 ዓመት በኢትዮጵያ ተቀምጧል። በአጼ ዮሐንስ ትዕዛዝ ከኢትዮጵያ ከመባረሩ በፊት እስከ 1880 ዓ.ም. የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ አማካሪና ወዳጅ በመምሰል የትግራይና የአጼ ዮሐንስ ቀንደኛ ጠላት የሸዋና የንጉሥ ምኒልክ እውነተኛ ወዳጅ በመሆን ግልጽ አቋም በመውሰድ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሱ እንዲታታሩ ደከመዋል። በንጉሥ ምኒልክ ዘንድ በነበረው ተደማጭነት እንደ አንቶኔሊ የመሳሰሉት ብዙ ጣሊያኖች በሸዋ ተቀምጠው ፀረ ኢትዮጵያ ነጻነትና ጸረ ኢትዮጵያ አንድነት ስራቸውን እንደልባቸው እንዲያካሂዱና እንዲያስፋፉ ከፍተኛ ድጋፍ ሰጥቷል። ሸዋ የተቀመጡበት የመጨረሻ ዓመታት ከንጉሥ ምኒልክ ጎን ተቀምጦ የፖለቲካ ስራ ከማከናወን በስተቀር የመንፈሳዊ ስራ ችላ ብለው እንደነበረ ራሱ በጻፈው መጽሐፍ ገልጧል። ካርዲናል ማሳያ ብዙ ጊዜ የሚመራው በሀይማኖት ነው፣ ምኒልክን ካቶሊክ ማድረግ የደብረ ሊባኖስ ገዳማትን ካቶሊክ ማድረግ ይመኝ ነበር። ነገር ግን በሀይማኖት ብቻ አልተወሰነም አጼ ዮሐንስና ንጉሡ ምኒልክ ጦርነት ቢገጥሙ ምኒልክ አሸናፊ እንደሚሆን እምነት ነበረው። በዚሁ የተነሣ ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ ላይ ጦርነት እንዲያስነሳ ከማነሳሳት አላረፈም ነበር። በአጼ ዮሐንስ ላይ በአጠቃላይ በትግሬዎች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ነበረው፣ ለምሳሌ አንድ ትግሬ የአንድ ልጅ ፍቅር ይዞት በካቶሊክ ሀይማኖት ጋብቻ ለመፈጸም ቢጠይቀው ትግሬዎች እንደ ሰይጣን ስለሚታያ ቸው ትግሬ ልብ አለው ወይ ፍቅር ያውቃል ወይ ብሎ ተችቷል። አጼ ዮሐንስ ከኢትዮጵያ ባያባርረው ኖሮ የውጫሌ ውል በኢጣሊያ መንግሥት ስም ከምኒልክ ጋራ ለመዋዋል ከኢጣሊያ መንግሥት የታጨ ካርዲናል ማሳያ ነበረ። ነገር ግን አይቀጨውም አጎቱን ማሣያ ተክቶ አንቶኔሊ ነው የተሾመው የአንቶኔሊ አጐት በዋናው የቫቲካን መንግሥት ካርዲናል ሆኖ ይሠራ የነበረ ነው ስለዚህ ካርዲናል ማሳያ ሲባረር የአንድ ካርዲናል የወንድም ልጅ ነው የተተካ።

ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ ሁለት ዓይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ነበራቸው የሸዋ ፖለቲካና የትግራይ ፖለቲካ። በኢትዮጵያ ግዛታቸውን በማስፋፋት ማለት ሸዋ ያለው ባለሥልጣንን መደገፍ ወይንም ትግራይ ያለው ባለሥልጣንን መደገፍ። ካርዲናል ማሳያ የሸዋ ፖለቲካ ደጋፊና መስራች ነበረ ለማለት ይችላል። ከርሱ ቀጥሎም እነ አንቶኔሊና አንቲኖሪ መዘት ነበሩ። በኢትዮጵያ ወገን የሸዋ ፖለቲካ ደጋፊ አጼ ሚኒልክ ብቻ ነበረ። የትግራይ ፖለቲካ ደጋፊዎች የኢጣሊያ የወታደር ክፍል ነበረ። ነገር ግን በመንግሥታቸው በኩል ተሰሚነት አልነበራቸውም። ምክንያቱም 1ኛ. እስከ መጨረሻ ጊዜ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት በሸዋ የፖለቲካ ሙሉ እምነት አሳድሮ ነበረ 2ኛ. ራሣቸውም ቢሆኑ ራስ አሉላና አፄ ዮሐንስን እያስታወሱ ጠንካራ አቋም አልነበራቸውም ትግራይን ብናጠቃር ከሸዋ የባሰ ጠላታችን ሊሆን ይችላል የሚል ፍራቻ ነበራቸው። ሸዋ ግን የበደለችን ነገር የለም። የሸዋና የትግሬ ፖለቲካ የተፈጠረውና የተጠናከረው ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ነው። አጼ ዮሐንስንና ራስ አሉላን ለማውደም የታቀደ ነው። ቂም በቀላ ቸውን ለመወጣት ነው። ሁለቱም እንደ

አንድ ሰይጣን ሆነው ይታዩዋቸው ነበረ።[1] ለምሳሌ በአንድ ወቅት አጼ ዮሐንስ የእርም ህዝብ ተበደለ ባሪያ ሆኖ እየተሸጠ ነው ብሎ ሀሳብ በሚያቀርብበት ጊዜ እሱ አንድ ሰይጣን ሆኖ ለእርም ህዝብ ርህሩህ እንዴት ሊሆን ይችላል እያሉ ያፌዙበት ነበረ።

አጼ ምኒልክ ለነበረው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለመጫን ዓላማ ለማስፈጸም ካርዲናል ማሳያ አባቴ ብሎ እየጠሩ በረቀቀ ዘዴና ብልሀት ከተጠቀሙበት በኋላ ለአጼ ዮሐንስ አስረክበው ወደ ሀገሩ እንዲሄድ አድርገታል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንቶኒሊን እያታለሉ ከተጠቀሙበት በኋላ በንዴት ከሀገር እንዲወጣ አደረገው።

ኤንሪኮ ቼሩቲ (Enrico Cerruti) የተባለው የጣልያን ዜጋ በ1869 በአዲሷ ጊኒ ሶስት ደሴቶች ነዋሪዎች የኢጣልያ የበላይ ጠባቂነት ሞግዚትነት መቀበላቸውን የሚያረጋግጥ ሶስት ኮንትራቶች ይዞ ወደ ሀገሩ መጥቶ የኢጣልያ መንግሥት ለመረከብ ስላታተው ሳይሳካ ቀርቷል። ጣልያኖች ኢትዮጵያ እንደ አዲሷ ጊኒ ያለምንም ደም መፋሰስ በመጀመሪያ ሸዋን አጼ ዮሐንስ ከሞተ በኋላ መላዋን ኢትዮጵያን ውል በመፈራረም ብቻ በቁጥጥራቸው ለማድረግ (ፕሮቴክቶሬት) ጉጉት ነበራቸው። በኢጣልያና በሸዋ መካከል በተደረገው የወዳጅነትና የንግድ ውል በአንኮበር ነበር፣ ቀኑም ግንቦት 14 ቀን 1875 ዓ.ም. (ሜይ 21/1883) ነበረ፣ ተዋዋዮቹም ንጉሥ ምኒልክና አንቶኒሊ ነበሩ። በሁለቱ መንግሥታት መካከል እንደ ተደረገ ውል ነበረ። ንጉሥ ምኒልክ ከትሮፒካል አፍሪካ ኢጣልያን ለማወቅ የሚፈልጉና ወዳጅነት የሚፈልግ አፍሪካዊ መሪ እየተባለ እየተወደሰ ስም አትርፎ ነበር። ንጉሥ ምኒልክ ከኢጣልያ መንግሥት ጋራ መገናኘት ሲጀምር የኢጣልያ ቪክቶሪዮ ኤማኑኤል ዳግማዊ ይባል የነበረው ንጉሥ ስለሞተ በምትኩ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ ሲነግሥ ምኒልክ በዚሁ አጋጣሚ ለአዲሱ ንጉሥ ደብዳቤ ሲጽፍ ሟቹ ንጉሥ የመንግሥቴ ጠባቂ ለእኔም እንደ አንድ አባት በማለት ገልጾ ነበር። በሌላ ደብዳቤው ደግሞ «በሟቹ ንጉሥ የነበረውን ወዳጅነት እርስዎ እንደሚቀጥሉ፣ እንደ አጋጣሚ ጠላት በእኛ ላይ አደጋ ለመጣል ቢሞክር እርዳታ እንደሚያደርጉልኝ ተስፋ አለኝ» ብሎ ጽፎ ነበር። በተጨማሪ «የሟቹ ንጉሥ እርስዎ ተከትለው የእኛ ጠባቂ እንደሚሆኑ እተማመናለሁ» ብሎ ነበር። እነዚህ ደብዳቤዎች አሥራ አንድ ዓመት ከውጫሌ ውል በፊት የተፃፉ ለውጫሌ ውል ቅድመ ሁኔታዎች ያዘጋጁ እንደነበሩ ያስረዳሉ። እነሱቸው ሸዋን ወይንም መላውን ኢትዮጵያ የኢጣልያ ፕሮቴክቶሬት ለማድረግ አስቀድመው እቅድ እንደነበራቸው የሚገልፁ ነበሩ። ጠላት ተብሎ የሚጠራው አጼ ዮሐንስ መሆኑን ግልፅ ነው። እነዚህ የኢጣልያ አማካሪዎች አስተሳሰብ እሚያንፀባርቁ መሆኑን አያጠራጥርም። ስምንት ወር ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ሁለት ዓመት ከውጫሌ አስቀድሞ ጥቅምት 10 ቀን 1880 ዓ.ም. (ኦክቶበር 20/1887 ዓ.ም.) የወዳጅነትና የኅደኝነት ውል የሚል ስያሜ ምኒልክና[2] አንቶኒሊ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈራርመዋል።

1.A. Gaibi Manuale die storia Politica delle Colonie Italiane p.09

2.1 Carlo Zaghi: Ibd p.140



በሁለት መንግሥታት የተደረገው ውል ነው የሚመስለው። ይህ ውል በኢጣልያና በአጼ ዮሐንስ ጦርነት ቢነሣ ምኒልክ ከኢጣልያ ጐን እንዲሰለፍ የሚያደርግ መሆኑን ታምኖበት ነበር። ቀደም ብሎም የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለፐቶምበር 11/1887 ዓ.ም. ለአንቶኒሊ በጻፈው ደብዳቤ የሚከተሉት ጉዳዮች ከንጉሥ ምኒልክ እንዲጣሩ ጠይቆ ነበር። 1ኛ/ ምኒልክ እኛ በአጼ ዮሐንስ ላይ በምናደርገው ጦርነት በተግባር ለመተባበር ፈቃደኛ እንደሆን 2ኛ/ የዚህ ትብብር ውጤት ምን ሊሆን እን ደሚችል። 3ኛ/ ትብብሩ ተግባራዊ ካልሆነ ከምኒልክ ጦር ጋግሽ የአጼ ዮሐንስ ጦር ወረራ በመጠበቅ በደቡብ እንዲቆሩ ለማስገደድ ወይንም ምኒልክ ፍፁም ገለልተኛ እንዲሆንልን ዋስትና ማግኘት እንችላለን ወይ የሚል ነበር።[1]

አንቶኒሊ ንጉሥ ምኒልክ የኢጣልያ መንግሥት ታማኝ መሆኑን ለማስረዳት ሲያቅተው በንጉሡ ሙሉ በሙሉ እተማመናለሁ ነገር ግን የንጉሡ ጀነራሎችና ሹማምንቶች ብዙዎቹ የሰሜን ተወላጆች ስለሆኑ ጦርነት ቢነሣ ለአጼ ዮሐንስ እንዳያደሉ ያሰጋል ብሎ ጽፎ ነበር። አንቶኒሊ ሰሜን ብሎ የሚጠራው ትግሬይ፣ ወሎ፣ ጎንደር፣ ወዘተ... የሚያጠቃልል ነበር።

በተለይ እቴጌ ጣይቱ እንደ ትግሬ ነበር የሚቆጥሩት፣ ከኢጣልያ መንግሥት ስለ ምኒልክ ታማኝነት ተጨባጭ ነገር አላሳየም ተብሎ በሚወቀስበት ጊዜ ያቀርበው የነበረው ምክንያት ንጉሡ ከኢጣልያ ጋር እንደሚሰለፍ አልጠራጠርም፣ ነገር ግን በትግሬዎችና የሰሜን ሰዎች ስለተከበበ እንደልቡ ለመሆን ነፃነት የለውም የሚል ነበር። ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው እንደ ትራቨርሲ እሱም ጦርነት ቢነሣ አጼ ዮሐንስ 200,000 ወታደር ማሰለፍ ስለሚችል ኢጣልያ ወደ 50,000 ወታደር ማሰለፍ ያስፈልጋታል ብሎ ያምን ነበር። 10–20,000 ሺህ ወታደር ማሰለፍ ውድቀት ያመጣብናል ብሎ ተንብየው ነበር። በአጼ ዮሐንስ ጦር ላይ እንዲገጥሙ ኢጣልያ ያሰለፈቻቸው ወታደሮች 19,182 ብቻ ነበሩ። የጦሩ ጥንካሬ የሚለካው ሊያሰለፍ በሚችለው የመድፎች ብዛት ሲሆን ኢጣልያ አጼ ዮሐንስን ለመግጠም ያሰለፈቻቸው 48 መድፎች ብቻ ነበሩዋት። አጼ ዮሐንስ ከጣልያኖች ብቻ የማረኳቸው 24 መድፎች ነበሩት። ከእንግሊዞችም የተረከባቸውም ነበሩት፣ ስለዚህ በጦር መሣሪያም ሁለቱ ወገኖች ኃይላቸው ተመጣጣኝ ነበር። አጼ ዮሐንስን አነጋግረው ወደ ምፅዋ የተመለሱ የሉርድ ፖርታል መልእክተኞች እነሱም ለኢጣልያ ወታደራዊ ባለሥልጣናት ኢትዮጵያን ለመቋቋም በቂ ኃይል እንዳላዘጋጁ ነገሯቸው ነበር። አንቶኒሊ ምኒልክን ከኢጣልያ ጐን ለማሰለፍ አጋጣሚኝ ብሎ የሚያቀርበው የነበረ ሌላ ችግር አጼ ዮሐንስ የቤተክህነት ሙሉ ድጋፍ አለው፣ ስለዚህ ነው ምኒልክ[2] ፍራቻ የሚያድርበት የሚል ነበር፣ ይኸውም ለምካል ምክንያት ነው። በተረፈ በምኒሊክ የነበረው ተሰሚነት የተነሣ አዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ ሌሎች ኤውሮጳውያን ምኒልክ አይደለም ንጉሥ አንቶኒሊ ነው ብለው ሲቀልዱበት፣ እሱ ግን ይኮራበት ነበር፣ በጣልያን ዜጎች ሳይቀር ተወቅሷል አዲስ አበባ

1 Carlo Rossetti: Ibd p.80

2. Carlo Rossetti storia diplomatica dell' Etiopia Durante Menelik II

ይኖሩ የነበሩ ፈረንጆች ነጋዴዎች ስለሆኑ አንድ ንጉሥ ነጋዴዎችን ማበሳጨር ስለማይገባው ምኒሊክ ከፈረንጆቹ ጋራ እንዳይገናኙ አድርጎት ነበር። በተለይ ገንዘብ ከልክ በላይ በመስጠት ከሁሉም ወገን ከራሱ ዜጎች ሚይቀር ተወቅሷል። እሱ ግን ኩራት ስለሚሰማው በአዲስ አበባ አነስተኛ ታዋቂነት ያለው ሰው ቢያገለ አሥር ብር ከእኔ ያላገኘ አይገኝም እያለ ይኩራበት ነበር። አንቶኔሊ ጁላይ 2/1888 ዓ.ም. ከምኒሊክ ጋር ተነጋግር ውርንት ቢኑ ከኢጣሊያ ጋር ተሰልፌ እዋጋለሁ ብሎ ነግሮኛል ብሎ ሪፖርት ለመንግሥቱ ይፅፋል። ምንሊክም[1] ጁላይ 6/1888 ዓ.ም. ለኢጣሊያ መንግሥት ሲፅፍ አጼ ዮሐንስ ሀገሬን ለመውረር እየተዘጋጀ ነው እኔ ግን ለመከላከል ዝግጁ ነኝ። አንቶኔሊ 5,000 ጠብመንጃዎች ፈሚንከቶን እንደሚላክልኝ ተስፋ ሰጥቶኝ ነበር። እኔ ሀገሬን በምከላከልበት ጊዜ በከንቱ የፈሰሰ የግር ማሮንትም ዜጎች ደም እበቀላለሁ። አሁን እኔ የምጠይቀው ጠብመንጃዎቹ ከ10,000 እንዳያንሱ ነው። በዚሁ ቀን ምኒሊክ ለጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ደብዳቤ ሲፅፍ «ለኢጣሊያ መንግሥት ኃያልነቱና ወዳጅነቱ የማሳይበት ጊዜ ደርሷል ብሎ ጽፎ ነበር። የኢጣሊያ መንግሥትም ኃያሉና ወዳጅነቱ ለእኔ የሚያሳይበት ጊዜ ደርሷል» ብሎ ጽፎ ነበር። ኦገስት[2] 11/88 ዓ.ም. አንቶኔሊ ረዘም ያለ ሪፖርት ለመንግሥቱ ልኮ ነበር። አንዳንድ ነጥቦችን ለመጥቀስ የሸዋ ተለፋና የሸዋ ዝንባሌ ወደ ኢጣሊያ መሆኑን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ። የአርአያ ሥላሴ ሞት በምኒሊክና በአጼ ዮሐንስ የነበረው የዝምድና ግንኙነት ተቋርጧል። በሁለቱም መካከል የነበረውም መሀላ ተቋርጧል። ምኒሊክ ለአጼ ዮሐንስ ወታደራዊ እርዳታ የመስጠት ግዴታ የለበትም። ይህ ከዛሬ 10 ዓመት በሁለቱ ወገኖች መሐል የተደረገው ስምምነት አልተጠቀሰም። ስለዚህ አጼ ዮሐንስ መጠየቅ የማይገባውን ነገር ነው የጠየቀ። በተጨማሪም አጼ ዮሐንስ በውለታም አያመስግ ንም። የወዳጅነት መንፈስም አያሳይም። ስለዚሁ ጉዳይ የገባበት መሀላ ቃል እላከበረም ምኒሊክም ከመሀላ ቃልነ ይሆናል። ምኒሊክ በመወራጨትና ባልተለመደ ሁኔታ ቁርጥ ያለ ውሣኔ በመያዙ አዲስ ሰው ሆኖ ነው ያገኘሁት የኢጣሊያ መንግሥት የማይከዳው መሆኑን እኔ ቃል እንድገባለት ጠይቆኛል። ለንጉሣችን የፃፈው ደብዳቤ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ያላቸው ያልተጣጣመ ሁኔታ በመግለፅ ነው። በተደጋጋሚ የጦር መሣሪያ ይጠይቃል። በዶጋሊ የሞ ቱ ወታደሮችን ሬሳ ለመበቀል ይፈልጋል። ምኒልክ እውነት አይናገርም ብዬ ጥርጣሬ የለ ኝም። በሚቀጥለው ጥቅምት ወይንም ኅዳር አጼ ዮሐንስ ሸዋን እንደሚወር እርግጠኛ ነኝ። በዚሁ ጊዜ ምኒሊክ ለሁለተኛ ጊዜ ለአጼ ዮሐንስ ሊንበረከክ አይችልም! ይዋጋል። ምኒልክ በቃሉ ይረጋል! በዚሁ አጋጣሚ እኛ ማንጠቀምበት ብንቀር ትልቅ ስህተት ይሆንብናል ብሏ ል። አንቶኔሊ ጣሊያን ሀገር ሄዶ 4,700 ጠብመንጃዎችና 220,000 ጥይቶች / [3] ጃንዋሪ 22/1889 ዓ.ም. አዲስ አበባ በገባበት ጊዜ ከፍተኛ አቀባበል ተደረገለት።

1 Carlo Rossett: ibd p.51

2 Carlo Rossett: ibd p.52

3. Carlo Rossett: ibd p.54



ለወደፊት የሚፈረመውን የውል ረቂቅ ይዞ ነበረ የመጣው። ፌብርዋሪ[1] 20/1889 ዓ.ም. አንቶኔሊ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ሪፖርት በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ እንደሚከተለው ያብራራል። የውሉ ረቂቅ በሚመለከት (በውጫሌ የሚፈረመው ውል ማለት ነው።) ችግር የሚያመጣ አይመስለኝም፤ ብቻ ንጉሡ መሬቱን በለመስጠቱ ጉዳይ የመሬቶቹ ባለቤት እሱ መሆኑን ሳይረጋገጥ ቃል መግባት እንቅፋት መስሎ ይታየኛል። የኢጣሊያ መንግሥት ንጉሠ ነገሥት ለመሆን ሲረዳው ጉዳዩ ወደ ፍፃሜ ሲደርስ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀል ሰላምና ወዳጅነት የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ እርግጠኛ ለመሆን እንደሚፈልግ አስረድቶኛል። ምንሊክ አብዛኛዎቹ የትግራ ይ መኳንንቶች በአጼ ዮሐንስ መጥፎ አስተዳደር የወደሙችና የደኸዩች ሀገራቸው ኢጣሊያ ብትገዛቸው በደስታ የሚቀበሉ መሆናቸውን አረጋግጠውልኛል።

እነዚህ አጋጣሚ ሁኔታዎች እንዲያመልጡን አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ትግራይ እንዳታንሰራራና እንዳትጠነክር ጊዜ በመስጠት ስህተት ከሠራን እንደገና ለአዲስና አስከፊ ጥቃቶች እንጋለጣለን።

በሸዋ በኩል አንድ ወዳጅ የሆነ ንጉሥ አለን፤ የእኛ እርዳታ ካልተጓደለው የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለማግኘት ጥሩ ዕድል አለው። እኛ አሁን ለምናደርግለት ውለታ በሰፊው ይከፍለናል። በዚሁ ደብዳቤ ላይ የሚታዩ ነገሮች ሀ/ ንጉሥ ምኒሊክ በጣሊያኖች እይዞህ ባይነት የትግራይ መኳንንቶች በንጉሠ ነገሥቱ በአጼ ዮሐንስ መንግሥት ላይ እንዲያምፁ ያነሣሣቸው እንደነበረ ግልጽ ማስረጃ ነው። ይህም በአጼ ዮሐንስ መንግሥት ላይ የተፈ ፀመው ሴራ የኢትዮጵያ ጦር ጣሊያኖችን ከምፅዋ ጠራርጎ እንዳያወጣ እንዲሁም በመተማ የኢትዮጵያ ጦር መሸነፍ ምክንያት ሆኗል። የትግራይ መኳንንቶች ግን አፄ ዮሐንስን እንዳልከዱት ከመተማ በኋላ በእስከሬኑ ዙሪያ ተሰብስበው የሞቱ ሰዎች በቂ ምስክር ነው። ለ/ አንቶኔሊ ምን ያህል ጥላቻ በትግራይ ላይ እንደነበረው ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ይህ ሁኔታ ደግሞ የአንድ ግለሰብ ስሜት ብቻ አልነበረም። የኢጣሊያኖች ሁሉ ጠቅላላ ስሜት እንደነበረ አያጠራጥርም። በአንድ ወቅት አንቶኔሊ ንጉሥ ምኒሊክ ጋር አነስተኛ አለመስማማት ተፈጥሮ በነበረ ጊዜ ምኒሊክ በትግራይ በኩል ወደ ሀገርህ ሂድ ብሎ በተናገረው ጊዜ አንቶኔሊ ይህ የምኒሊክ ሀሳብ የአጼ ዮሐ ንስ ትእዛዝ መሆኑን ስለሚያውቅ እምቢ የሚል መልስ ሲሰጥ እርስዎ የበቅሎዎች፣ ፈረሶች፣ ወርቅና ባሮች ግብር ለአጼ ዮሐንስ ከፍሏል። ነገር ግን የአንድ ነጭ የሆነ ሰው ግብር አይከፍሉትም እኔም በብረት ታስሬ ካልሆነ በትግራይ በኩል ወደ ሀገሬ አልመለስም ብሏል። ይህም አቋሙ በትግራይ ላይ የነበ ረውን ጥላቻ ሌላ ማስረጃ ነው። በአጼ ዮሐንስ አስተዳደርም ትግራ ይ ተብሎ ይጠራ የነበረው የአሁንዋ ትግራይ ብቻ አልነበረም፤ ኤርትራም ጭምር ነበረች። ጣልያኖች የሸዋ ፖለቲካ የሚሉት ይሄ ነው።

1. Carlo Rossett: ibd p.56

# 6. ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የፈጸሙት ተጨማሪ ስውር ደባ

በአዲስ አበባ ይፈፀም የነበረው ማእከላዊ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ወደ ምፅዋ ጓዶም ተንፀባርቋል። ማንቴጋትሣ የተባለው የኢጣሊያ ጋዜጠኛ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ዛሬ ነገ ይፈነዳል ተብሎ ተፈርቶ የነበረው ጦርነት እንዲከታተል ወደ ቦታው ተልኮ የነበረ ከምፅዋ ያስተላልፋቸው የነበሩ ጽሑፎች ብናነብ አጼ ዮሐንስ ከመኳንንቶቹ ጋር በተለይ ከራስ አሉላ ጋር ለማጣላት ይደረግ የነበረ እንቅስቃሴ ምን ያህል ስር ሰዶ እንደነበረ እንረዳለን። ነገሩ በከፍተኛ ምስጢር ይካሄድ የነበረ ስለሆነ ምንግዜም እውነቱን ማወቅ ስለማይቻል በተገኙ አንዳንድ ፍንጮች ብቻ መወሰን ግድ ይሆንብናል። የአጼ ዮሐንስ ጠላቶች በጦር ሜዳ ሊያሸንፉት እንደማይችሉ በሚገባ ስለተረዱ በእጅ አዙር በስነ ልቦና ጦርነት ተጠቅመው ሊጥሉት ችለዋል። ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ዲሰምበር[1] 8/1887 ዓ.ም. ባስተላለፈው ዜና «በኢትዮጵያና በኢጣሊያ የሰላም ድርድር እቅድ እንዳለ ስለ ሰላም ድርድሩ በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት አስተያየት ሲሰነዝር «ንጉሡ ነገሥቱ ለጣሊያን መሬት የመስጠት ጉዳይ በአንደኛ ደረጃ ሲሆን ይኸውም እቢሲንያ መስጠት የምትፈልገው የራሷ ያልሆነ መሬት ስለሆነ ከረን ቢሰጠን የተሻለ አማራጭ ነው፤ በዐይለት አካባቢ እሰጣለሁ ቢል የተቃጠለ መሬት ስለሆነ ምንም ጥቅም የሚሰጠን አይደለም። ስለ ጥራል ካሣም ይወራል ይኸውም ራስ አሉላ እንዲቀጣና ከሥልጣን እንዲወርድ የሚል ነው። በእኔ አስተያየት የሰላም ስምምነት ቢደረግ እንኳን፤ ራስ አሉላ ከሥልጣን ይወርዳል ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ንጉሡ በራስ አሉላ ላይ ሙሉ እምነትና ልባዊ ፍቅር ስላለው ነው።

ሆኖም ሁሉም ነገር ሊሆን የሚችል ነው፤ በሐበሻ ሀገር የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፤ ተወዳጅነት የነበረው አንድ ራስ በአንድ አፍታ ከሥልጣን ተባሮ፤ የባሰም ዓይኑ ታውሮ በአንድ አምባ እንዲቀመጥ የሚደረገው የሚያጋጥም ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ለራሱ አይደለም የሚሰጋው፤ ራስ አሉላ የሚታየው የልጁ ቀንደኛ ጠላት እንዳይሆነው በመፍራት ነው» ብሎ ጽፏል።[2] ዲሰምበር 22/1887 ዓ.ም. ጋዜጠኛው ባሰራጨው ሌላ ዜና ደግሞ ራስ አሉላ በራስ ሐጐስ ስር መሆኑን ወሬ መሰማቱ ከገለፀ በኋላ አስተያየቱን ሰፋ በማድረግ እንዲህ ይላል። ከሐበሻ ሹማምንቶች ራስ ሐጐስ በዕድሜ ከሁሉም የሚበልጥ ነው። በንጉሡ ላይ ሐሳቡ ተቀባይነት አለው፤ ንጉሡም ያዳምጧል፤ ምክሮቹም በሥራ ላይ ያውላል። ራስ ሐጐስ ረጋ ያለ ሰው ነው።

እዋቂ ነው፤ ለንጉሡም ታማኝ ነው፤ የሚነፍሰው ዜና እውነት ከሆነ ከራስ አሉላ የተሻለ ተብሎ መመረጡ ንጉሡ በራስ አሉላ ላይ እምነት እንደሌለውና የችኩላ እርምጃ እንዳይወስድ የሚፈራው መሆኑን ያሳያል።

1. Vico Mantegazza: Ibd p. 56

2. Vico Mantegazza: Ibd p. 58



ራስ ሐጐስን ከላይ በተጠቀሱ ፀባዮቹ ለዚሁ ደረጃ መመረጡ ያሳያል፤ ነጭ ጠሎ በአንድ ጥቁር ሰው ላይ ራስ ሐጐስ እንደ ኤውሮጳዊ ያስመስለዋል። በሌላ በኩልም ከሌሎች የእሱ ዘር የሆኑ ሰዎች ለየት በማለት በኤውሮጳውያን ላይ ጥላቻ አሳይቶ አያውቅም። ለሚቼ ቢያንኪ ወዳጅ ነበረ። ብዙ አገልግሎቶችም አበርክቶለታል፤ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሀገር ጉብኚዎች እንደ ብራንኪ እና ነራዚኒ ከእርሱ እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ትብብሩን በሚጠይቁበት ጊዜ አገልግሎቱን አበርክቷል። ዲሰምበር 28/1887 ዓ.ም. ነበር ሎርድ ፖርታል ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተነጋግሮ ምፅዋ የተመለሰ። ጋዜጠኛው ጠይቆ እንደተረዳው ሎርድ ፖርታል ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመቋቋም ቢያንስ አሁን ካሏት የጦር ኃይል እጥፍ ማስለፍ ይኖርባታል የሚል አስተያየት ሰጥቷል። 40,000 ወታደር ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ጀንዋሪ 30/1889 ዓ.ም. በአስተላለፈው ሌላ ዘገባ ስለ ራስ አሉላ ከሥልጣን መውረድ በሚከተለው መልክ ያብራራዋል።

«ራስ[1] አሉላ የበለጠ ሥልጣንና ክብር እንዳይኖረው ትዕግስት የማጣት ሁኔታውም እንዲቀዘቅዝ ለማድረግ ንጉሡ ራሱ አስደናቂ ነገር እያደረገ ይመስላል። ራስ አሉላን ደበብ መግሪያ በማድረግም ቢሆን እየነካካ ይመስላል፤ ስለዚህ ትዕግሥት ማጣት በጭንቅላቱ ስላለ ንጉሡን ያልገመተው አንድ አደጋ ሊጥለው ይችላል። በአሁኑ ሰዓት ንጉሡ ራስ አሉላን በደህና ዓይን እያየውም ይህ የልጁና የራሱ ስውር ጠላት፤ ሊያጠፋ እመቺ ሁኔታ እየጠበቀ ነው፤ ጦርነቱ ጥሩ ውጤት ካላመጣለት የቀረው እድሜው ዓይኑን አጥፍቶ በአንድ ተራራ እንዲኖር ያደርገው ይሆናል። ንጉሡ ጦሩን ራሱ መምራቱ ሹማምንቶች እርሱ ከሌለ እርስ በእርሳቸው እንዳይጣሉ በመፍራት ነው። የጣሊያኖች የስለላ መረብ በአጼ ዮሐንስ ሰፈር ላይ ምን ያህል ስር ሰዶ እንደነበር ስናይ አጼ ዮሐንስ በመተማ በሞተበት ጊዜ ጥይቱ ከማን እንደተተኮሰ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። ደበብ ስብዙ ጊዜ ሽፍታ ሆኖ ለጣሊያኖች አድሮ ከቆየ በኋላ አሁን ንጉሡ ያለበት ገብተዋል። እሱም ስለ ንጉሡ የሰጠው አስተያየት ጋዜጠኛው ያሰራጨው ዜና እንደሚከተለው ነበር። ንጉሡ እንደ ድሮ አይደለም አካባቢው ያሉት ሁሉ ይጠረጥራቸዋል ይፈራቸዋል። ለአንዱ ሹመት ይሰጣል ለሌላው ይነጥቃል ራሶችም እርስ በእርሳቸው ስምምነት የላቸውም፤ አንዳንዶቹ በትንሽ ገንዘብ ለእኛ እንዲያድሩ ሊገዙ ይችላሉ፤ በንጉሡ ላይ ሊያምጹ ይችላሉ፤ ንጉሡ ማንንም አያምንም። ይህ አስተያየት የተሰጠው ለወ/ር ናረቲ ነው። ኢጣሊያዊ ጋዜ ጠኛ ፌብርዋሪ 10/1889 ዓ.ም. ባሰራጨው ዜና[2] ደበብ በአሁኑ ጊዜ ጣሊያኖችን ከድቶ ከንጉሡ ጋር ታርቆ ተቀላቅሎ ይገኛል። ሀሳቡ እንዲለውጥ ያስደረገው ምን ምክንያት ይሆናል ብለው ጣሊያኖች በሚመረምሩበት ጊዜ ምናልባት ይሆናል ብለው ያመኑበት በራስ ሚካኤል ላይ ቅናት ስለነበረው ብለው ያምኑ ነበር። ጣሊያኖች የወሉው ራስ ሚካኤል ከአጼ ዮሐንስ ከድቶ ወደ ጣሊያኖች እንዲገባ ንግግር ጀምረው ነበረ፤ ውጤቱን ለማሳየት ተቃርቦ ነበር።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. 66

2 Vico Mantegazza: Ibd p. 72

ይህ ሁሉ ደግሞ ደበብ ያውቅ ነበር። በአቢሲኒያ ራስ ሚካኤል ከፍ ያለ ደረጃ ያለው ነው። እሱ ወደ ኢጣሊያ ከገባ ደበብ ተደማጭነት ያጣል። ንጉሥ ምኒልክ ፌብርዋሪ 20/1889 ዓ.ም.[1] ለኢጣሊያ ንጉሥ በፃፈው ደብዳቤ። «ግርማዊነትዎ ከምዕዋ በኩል ያለው ወሰን በሚያሰቡት ሁኔታ እኔም በሙሉ ተስማምቼበታለሁ። እግዚአብሔር አንድ ቀን እነዛ መሬቶች በእኔ ግዛት ውስጥ ካደረገልኝ የሁለታችን ሙሉ ስምምነትና የልብ ወዳጅነት ለማደፍረስ ምንም አይነት ችግር እንደማይገጥመን ግርማዊነትዎ እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ ብሏል። ንጉሥ ምኒልክ ይህ ሁሉ ውል ሲፈራረም ደብዳቤዎችም ሲጽፍ የሸዋን ህዝብ አስተያየት ጠይቆ ወይንም ተከትሎ አልነበረም። የሸዋ መኳንንት አንዳንድ ጊዜ ለዞብ ባለ አጽም እንዳንዴም ጠንካራ አቋም በመያዝ ሁሉም ግን ስለወሰኑ ጉዳይ መሬት ለጣሊያን እንዳይሰጥ ተቃሚዎች እንደነበሩ ጣሊያኖች መዝግበውታል።

ከነዚህ የአንቶኔሊና የምኒሊክ ሁለት ዳብዳቤዎች በኋላ ማለት ከፌብርዋሪ 20 /1889 ዓ.ም. 20 ቀን በኋላ አጼ ዮሐንስ ለሀገሩ፣ ለሀይማኖቱ እየተዋጋ የጀግና ሞት በመተማ ሞተ አንቶኔሊና የኢጣሊያን መንግሥት አቅዳቸው የተሳካላቸው መስኋቸው ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ ሊፈርምላ ቸው ተዘጋጅቶ የነበረ ውል ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ እንዲፈርም አረጉት።

# 7. የአጼ ዮሐንስ ታላቅነት

ጣሊያኖች ስለአጼ ምኒልክ አስተያየት ሊሰጡ ከመጀመሪያ ጀምረው እስከሞተ ድረስ የጣሊያን ወዳጅ ነበረ ይላሉ። ወደ ዓድዋ ጦርነት የገፋፋቸው ባለቤቱ እቴጌ ጣይቱ ናት ይላሉ። የ17ኛው የውጫሌ ውል አንቀጽም የአላላተው ግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚው ነው ይላሉ። ስለ አጼ ዮሐንስ ጣሊያኖች የሰጡት አስተያየት ስለ አጼ ምኒልክ ከሰጡት አስተያየት ተቃራኒ ነው። አጼ ዮሐንስ የጣሊያን ቀንደኛ ጠላት እንደነበረ ሲናገሩ፣ ኢትዮጵያውያን ነን፣ ኢትዮጵያ ሀገራችንን እንወዳለን የሚሉ እውነተኛ ኢትዮጲያውያን ካሉ አጼ ምኒልክን አይደለም መውደድ የሚገባቸው፣ ጀግና ሆኖ የኖረ በጀግንነት አንድ ጊዜ ታሉን ሳያጥፍ ለሀገሩ የተሰዋው አጼ ዮሐንስን ነው መውደድና ማክበር የሚገባቸው ብለው ጽፈዋል። ጣሊያኖች እንደዚህ ማለታቸው ብዙ ምክንያቶች ስላላቸው ነው። እኔ ግን እዚህ መጥ ቀስ የምፈልገው ሁለት ለአጼ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ የተጻፈ ደብዳቤዎች ናቸው የአጼ ዮሐንስ ታላቅነት እና የሀገር ወዳጅነት የሚያሳዩ ማስረጃዎች ናቸው። እነሱም 1ኛ. ከምጽዋ ወረራ አስር ወር በኋላ ኖቬምበር 26/1885 ዓ.ም.[2] የተጻፈ ሲሆን 2ኛ. ከዶጋሊ ጦርነት 10 ወር በኋላ ኖቬምበር 21/ 1887 ዓ.ም. የተጻፈ ነው።[3] በወርቅ ፊደላት ሊጻፉ የሚገባቸው ቃላቶች ናቸው።

---

1. Carlo Rossett: ibd p.57-58
2. Leopoldo Travarsi:Les Marefia p.306
3. Carlo Rossett; ibd p.47



1. የአንደኛው ደብዳቤ ሙሉ ቃል «የኢጣሊያኖች ጉዳይ በሚመለከት የነርሱ ማጭበርበርና ተንኮል ምንጊዜም አያቋርጥም፣ በመጀመሪያ በሰላም መንገድ እኔጋ መጡ፣ ለንግድ የሚጠቅም መንገድ እንሰራለን በሚል ሰበብም አውሳን ለመያዝ ፍላጎት ነበራቸው፣ እኔ ግን ለዚህም ለሌሎችም ያቀረቧቸውን ሀሣቦች ሁሉ አልተቀበልኳቸውም፣ ወሬያቸውን ሳላዳምጥ ሸኘኋቸው፣ ባደረኩላቸው አሸኛኘት ተበሳጭተው ምጽዋና በግብጾች እጅ የነበሩ አካባቢዎችን ያዙ፣ በምጽዋ ለምሽግ ትላልቅ ጉድጓዶችን ሰሩ። ወደ ሀገራችን አቅጣጫም አንድ ቤት ለበሽተኞች ብለው ሰሩ። የታመሙትን ወደ ሀገራቸው ይልኳቸዋል። ደህና የሆኑ ያስመጣሉ አንዳንድ ሀገር ጉብኚዎች ሀገሬን ለማጥናትና ወሰናቿን ለማወቅ ቆደም ብለው መጥተው ነበር። እኔ ግን ወደ ኋላ መለስኳቸው ላያቸውም ወሬያቸውም ለመስማት አልፈለኩም፣ ቁም ነገር ያላቸው ሰዎች አይደሉም አታላዮዎች ናቸው፣ ነገር ግን እንግሊዞች የሚሰሩብኝ ሥራ መሆን አሰበት ጣሊያኖች እዚህ የመጡ። በሀገራቸው የገጠሸ መሬት እና ሳር ስለሌለ አይደለም እዚህ የመጡት። በእብሪተኝነት ትልቅ ለመሆን ነው፣ ምክንያቱም ብዙ ናቸው። ሀብታሞችም አይደሉም። ነገር ግን በእግዚአብሔር እርዳታ ተዋርደው፣ አገሰው በዓለም ፊት ክብራቸው ዝቅ ብሎ ይመለሳሉ። እነዚህ ሰዎች ሊያስፈራሩን የሚችሉ ሰዎች አይደሉም፣ እኛ በአንድነት መቆም አለብን። አንተ ወደ እኔ መምጣት አትችልም ምክንያቱም ሀገሩ የገጠሸ መሬትና እህል የለውም። ስለዚህ ወደ ኦሮሞ አገር በኩሉ በኩል ሁሉም ነገር የሚገኝበት ስለሆነ አብረን ብንሄድ የተሻለ ነው። ለጊዜው አንተ የባህር መንገድ መዝጋት አለብህ። በአውሣ በኩልም ሆነ በጨርጨር ዘይላ በኩል ማንም ሰው ማሳለፍ የለብህም ባገርህ የሚገኙ ሁሉ እንዲሄዱ ታደርጋለህ። በዚሁ አይነት ሁሉም ይዋረዳሉ። እኛ ሁለታችን ሁልጊዜ አንድ ሆነን ከኖርን በእግዚአብሔር ብርታት እንኳንስ እነዚህ ደካማ ጣሊያኖች የሌላ ሀገር ኃይለኛ ዜጎችም እናሸንፋቸዋለን። አዳም በእብሪት ከእግዚአብሔር የበለጠ ትልቅ ለመሆን ፈልጎ የተከሰከሰ ፍሬ እንደቀመሰና ቅጣትና ውርደት እንደደረሰበት ጣሊያኖ ችም እንደዚሁ ያጋጥማቸዋል።»

በደብዳቤው አጼ ዮሐንስ እንደገለጠው ወደ ምዕራብ ሀገሮች ዘመቻ በማድረግ እንደቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት የኢትዮጵያ አንድነት ለማስ ከበር የቀድሞ ዳር ድንበሩዋን ለማስከበር እቅድ እንደነበረው ያሳያል። አጼ ዮሐንስ ራሱ ባይመቸውም የተባለው በህብረት የሚካሄድ ዘመቻ ተግባራዊ ለማድረግ ልጁ እርአያ ሥላሴን ወደ ሸዋ ልኮ ነበር። ነገር ግን በአጼ ምኒልክ ራስ ወዳጅነት ሀሳቡ ሳይሳካ ቀረ።[1]

2. የሁለተኛው ደብዳቤ ሙሉ ቃል። ከኢጣሊያ ንጉሥ ጋራ ወዳጅነታችን ከፍ ያለ መግባባት ነበረን እርሳቸው ስጦታዎችን ይልኩልን ነበረ እኔም ስጦታዎች እልክላቸው ነበር። ቆንስሉ ጆቫኒ ብራንኪ ወደ እኔ መጣ በታላቅ ክብር ተቀበልኩት፣ በመኖሪያ ቤቴ አሳረፍ ኩት፣ እርሱን ለማስደሰትና ለማክበር ሁሉም ነገር አደረግሁ፣ ደስ የማይል በርሱ ላይ የሰራ ሁት ሥራ ያለ አይመስለኝም።

---

1 C.Zaghi: Le Origini della Colonia Eritras p.65

ከዚያ በኋላም የእንግሊዝ መልእክተኞች መጡና እንዲህ አሉኝ «እኛ ከግብጾች ጋራ ሰላም እንድታደርጉ እንፈልጋለን፤ እነርሱ የያዙት መሬታችሁን ለቀው ይወጣሉ እናንተም በመሬት በራሳችሁ ሀገር ባለቤት ትሆናላችሁ፡፡ምጽዋ የእናንተ ትሆናለች እናንተም በመሬት የጉምሩክ ቀረጥ ታገኛላችሁ ወደቡን በምጽዋ ማስተማር ትችላላችሁ፡፡ በምትፈልጉት መጠን የጦር መሣሪያ ይተላለፍላችኋል፡፡ ብሉኝ ነበር፡፡ ይህ ለማድረግ የእርስዎ ፈቃድና ማንተም ካለበት የጦር መሣሪያ ንግድ ለእርስዎ ነፃ ይሆናል፡፡ለዚሁ ሁሉ ማካካሻ በግሌ ሰዎች ላይ በምናደርገው ጦርነት እርዳታ ታደርጉልናላችሁ፤ መተማና ከሚላ ያሉት የግብፅ ወታደሮች ለቀው እንዲወጡና እስላሞችን ለመዋጋት የእርስዎ ወታደሮች ከእኛ ወታደሮች ጋር ይስማማሉ፡፡ እኔ የእንግሊዝ መንግሥት ያቀረበልኝ ሀሳብ ተቀበልኩ፡፡ ሆኖም የእንግሊዝ ወታደሮች እርዳታ እያሰፈልገኝም እልኳቸው እኔ ብቻዬ በእኔ ወታደሮች ብቻ እስላሞችን ልወጋቸው እንደምችል ነገርኳቸው፡፡ ስለሆነም የፈለ ክሁትን አደረክሁ፡፡ ለእኔ ማያስታውቅ የእንግሊዝ መንግሥት ለጣሊያኖች ለምን ምፅዋ እንደሰጣቸው አውንም አልገባኝም፡፡ ጣሊያኖች በምፅዋ ሰፍረው መጠናከር ጀመሩ፤ ያለ እኔ ፈቃድ እኔ ልሰጠው ለማልፈል ገውም የጦር መሣሪያ ሰጡ፡፡ ለእኔ ዜጎች ከእንግሊዝ ጋር ባደረግነው ውል መሠረት መክፈል የማይገባቸውን ጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍሉ አደረጉ፡፡ በተጨማሪ ም ወታደራዊ ምሽጎችን በመሥራት ለእኔ ወደ ተመለሱልኝ መሬቶች እያ መሩ ናቸው፡፡ በዚሁ ምክንያት ራስ አሉላ ከጣሊያኖች ጋር ሰላም እንዲደፈርስ አደረገ፡፡ እኔ ግን ራስ አሉላ ያደረገው ነገርን እንዲያደርግ ትእዛዝ አልሰጠሁትም፡፡

ዛሬ ሁለቱ ሠራዊቶች ጦርነት ለመግጠም ፊት ለፊት በሚገኙበት ጊዜ ሰላም ማድረግ የሚቻል ከሆነ እኔ በበኩሌ ለስምምነት ዝግጁ ነኝ፡፡ የኢጣሊያ መንግሥት ለማንኛውም ስምምነት ተታራኒ መሆኑን ማስረጃ አለኝ፡፡ ለትዳሴ የሚያገለግል ኬላ (ወይን ጠጅ) እንኳን ማይቀር ከምፅዋ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳያልፍ አይፈቅድም፡፡ በበኩሌ የኢጣሊያ መንግሥት ሀገሬን በቁጥጥሩ ለማድረግ ካልመጣብኝ፤ ከምፅዋም ሽቀጣ ሽቀጦች እንዲተላለፉ ነፃ ካደረገ፤ ሰላም ለማድረግና ወደ አንድ ስምምነት ለመድረስ ዝግጁ ነኝ፡፡

# 8. አጼ ምኒልክ

አጼ ምኒልክ ለእነዚህ ደብዳቤዎች መልስ አልሰጡም፡፡ ጣሊያኖቹን እያታለለ ብዙ የጦር መሣሪያ እንደልቡ አግኝቷል፡፡ የት እንደዋሉ የማይጠየቅበት ብዙ ሚሊዮን ጥሬ ገንዘብ በልቷል፡፡ የተመኘው የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭና ለልጆቹ አውርሰዋል፡፡ በዚሁ ጎላም የተመኘውን ሁሉ ጊዜያዊ ክብርና ገንዘብ አግኝቷል፡፡ ዘላቂ ዘላለማዊ ክብርና ጥሩ ዝና ግን አላገኘም፡፡ ጊዜ የማይሽረው ዝና ለሀገሩ ያተረፈ አጼ ዮሐንስ ብቻ ነው፡፡ አጼ ምኒልክ ጣሊያኖችን ብቻ አይደለም ያታለለ፤ ከአጼ ቴዎድሮስም የአባትነት እንክብካቤ አግኝቷል፡፡ እንክብካቤ ካሳደገው በኋላ የራሱን ሴት ልጅ ለሚስትነት ድርታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አጼ ዮሐንስም ልፉ አክብሮት ሰጥቶታል፡፡ ልጅ አርአያ ሥላሴና የአጼ ምኒልክ ሴት ልጅ ዘውዲቱ እንዲጋቡ አድርገዋል፡፡ ሁለቱም ነገሥታት አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ አጼ ምኒልክ



ሥር ስለነበረ 3ኛ. ጎብጽና ቱርክም የቀይ ባሕር ወደቦች በሙሉ የእኛ ናቸው እያሉ የሚከራከሩ ስለነበረ ነው፡፡ ስለኤርትራ መፈጠር የተፈጸመው ሽያጭ ግን በግልከላዊ መንግሥት የተፈጸመ ስለሆነ ሕጋዊነቱ እያጠራጥርም፡፡ ሆኖም ይህ በሀገራችን ታሪክ የተከሰተው ታላቅ ክህደት ኤርትራን ለመገንጠል በቂ ምክንያት ለመሆን ከቶ ባልቻለ ነበረ፡፡ የአንድ ግለ ሰብ ክህደት ግለሰቡ ንጉሥም ቢሆን ሕጋዊነቱን የሚያስጠይቅ አልነበረም፡፡ የውጫሌ ውል ለኤርትራ መፈጠር መሠረት ድንጋይ የጣለ ስለሆነ ደረጃ በደረጃ ከዚህ በታች መዘርዘር አስ ፈላጊ ነው፡፡ ብፁእ ካርዲናል ማሣያስ በእርጥ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተብለው በርማ ጳጳስ የተሾሙት በ1846 ነበረ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለ35 ዓመታት በሀገራችን ተቀምጠዋል፡፡ በወለጋ፣ በጂማ፣ በሸዋ ሚስዮናችን መሥርቷል፡፡ በ1868 ወደ ሀገራቸው ሄደው ከከረሙ በኋላ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ወደ ኦርሞ ሀገር ለመሄድ በዐይላ በኩል ሸዋ እንደገቡ ንጉሥ ምኒልክ የፖለቲካ አማካሪው እንዲያደርጋቸው አስበው የሃይማኖት ሥራቸውም በሸዋ እንዲያከናውኑ ስለፈቀደላቸው እግቸውም ፈታደኛ ሆነው ስለተገኙ፤ በአጼ ዮሐንስ ትእዛዝ ከኢትዮጵያ እስከተባረሩበት ጊዜ ድረስ ለ11 ዓመታት በሸዋ ተቀምጠዋል፡፡

ብፁእ ካርዲናል ማሣያስ በሀገራችን ይካሄድ የነበረው እርስ በርስ የሥልጣን ሹኩቻ ስለ ኤርትራ መፈጠር ወሣኝ ሚና የተጫወቱ ሰው ናቸው፡፡ ንጉሥ ምኒልክ በካርዲናል ማሣያስ አማካኝነት ከኢጣሊያ መንግሥት ግንኙነት ለመፍጠር ፍላጉት ስለነበረው በ1872 አባ ሚካኤል የተባሉ መልዕክተኛ ከተላኩ በኋላ የመልዕክተኛውን ስም ማጥፋት ዘመቻ ስለተያያዙ ወደ ጣሊያን ሀገርም ደብዳቤ ጽፈው በደህና እንዳይቀበሉት ስላደረጉ የአባ ሚካኤል ተልእኮ ተሰናክሉ ሣይሣካ ቀረ፡፡ ነገር ግን የአባ ሚካኤል ወደ ኢጣሊያ ሀገር ጉዞ ጣሊያኖች ወደ ኢትዮጵያ ሸዋ እንዲያተኩሩ ገፋፋቸው፡፡ የሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ፈለግ በመከተል ከ1873 ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ ዓመታት ስብሰባ ካካሄዱ በኋላ በ1876 ዓ.ም. የኢጣሊያ የጂኦግራፊ ማህበር የሚል ማህበር መሠረቱ፡፡ ከዚህ እያይዘውም የጂኦግራፊ የሕክምና ጣቢያ በሸዋ ለመመሥረት ተሰማምተው ወዲያውኑ በአንቲናሪ የሚመራው የኢጣሊያ ቡድን ወደ ሸዋ የሚላኩ አባሎች ተመርጠው ማርች 8 ቀን 1876 ከኢጣሊያ ሀገር ተነስተው ሴፕቴምበር 18/76 ሸዋ ገቡ፡፡ ጃንዋሪ 18/77 ካርዲናል ማሣያ በመረጡላቸው «ልት ማረፊያ» የተባለው መሬት ለመኖሪያ፣ ለህክምና፣ ለዕረፍት፣ ለምርምር እንዲጠቀሙበት ከንጉሥ ምኒልክ ተሰጣቸው፡፡ ይህ ትንሹ መሬት ኢትዮጵያን ጠቅላላ ለመያዝ የረዳን፤ መሠረተ ድንጋይ የተጣለበት ቦታ ነው ብለው ጣሊያኖች ይኮሩበታል፡፡ እውነትም ይህ ቦታ ሲሰ ጣቸው በአርዕስቱ ለተጠቀሰው ዓላማ ሣይሆን ለኢጣሊያ መንግሥት ፀረ-ኢትዮጵያ ስለላ ማዕከል በመሆን አገልግሏል፡፡ ጣሊያኖች በመጀመሪያ ወደ ሸዋ በገቡበት ጊዜ ብዙ ስጦታ ዎች ለንጉሥ ምኒልክ ከመንግሥታቸው የተላከ ይዘው መጥተው ነበር፡፡ ንጉሥ ምኒልክ ግን በተለይ ያተኮረው ጣሊያኖች ለራሣቸው መከላከያ ብለው ይዘዋቸው የነበሩ 150 ጠብመንጃዎች ነበረ፡፡ ጣሊያኖች የተላኩበት ዓላማ ወደ መሐል አፍሪካ ኤክስፕሎሬሽን ሐይቆች ሄደው ለመስለልና ለማጥናት ነበረ፡፡ ነገር ግን ከትንሽ ጊዜ በኋላ የንጉሥ ምኒልክ ቁም እስረኞች፤ ከፈል እሥረኞች መሆናቸውን ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ የንጉሡ ዓላማ የንጉ

50,000 ወታደር ሞቷል። 20,000 ከግብፅ ወገን፤ 30,000 ከኢትዮጵያ ወገን። የዓድዋ ጦርነት ግን የሞቱት ወታደሮች 6,000 ከኢጣሊያ ወገን፤ 7,000 ከኢትዮጵያ ወገን ብቻ ነበሩ። የጉራዕ ጦር ነት ተገቢ ክብርና ትኩረት እንዳይሰጠው የተደረገው በቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት ምኒሊክና ኃይለ ሥላሴ ፍላጐት ስለነበረ ብቻ ነው። በደርግ ጊዜ ይህ ሁኔታ እንዴት አልተለወጠም? ግብጾች አፍሪካውያንና ዓረቦች ስለሆኑ ጣሊያኖች ኤውሮጳ ውያንና ነጮች ስለሆኑ ከፍ ዝቅ የሚያደርግ ልዩ መለኪያ ነጥብ ካልተሰጠ በቀር በሞቱ ሰው ቁጥር ሲታይ ግን ልዩነቱ የጎላ ነው። እንደዚህ በ1928 ዓ.ም. የጣሊያን የመጨረሻ ወረራ የተካሄዱ ጦርነቶችም አጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻ እንደተዋጋ ተደርጐ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለማይ ጨው ጦርነት ብቻ ነው እንዲያውቅ የተደረገ። በምጽዋ የሰፈሩ የኢጣሊያ ጦር መኮንኖችም የምኒልክ ደጋፊ ነበሩ። ጣሊያኖች የንጉሥ ምኒልክ ደጋፊዎች በ1898 (በኢትዮጵያ 1881 ዓ.ም) በምጽዋ አካባቢ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ጦርነት ለመግጠም ተቃርበው በነበሩ ጊዜ ምኒልክ ለሎሞናዊ ዘር የሆነ የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆን የሚገባው መሆኑን ለማስረዳት ይጥሩ ነበረ። በአንጻሩ አጼ ዮሐንስ በአመጽ ያለአግባብ በሥልጣን የወጣ እያሉ ቅስቀሣ ያካሂዱ ነበረ። የአጼ ምኒሊክ ዘር የሆኑ 30 ሰሎሞናዊ ነገሥታት 1270–1632 የነገሡ የስም ዝርዝር ካወጡ በኋላ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ የበለጠ ስራዊት እንዳለው ለማስረዳትም ይጽፉ ነበረ። ቀጥሎ ምኒልክ የመላው ኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው የኃይለ መለኮት ልጅ መሆኑን ገልጸው ኃይለ መለኮት በአጼ ቴዎድሮስ ተሸንፎ እስረኛ ሆኖ ተወስዶ ከእስር ለማምለጥ በመቻሉ ወደሸዋ ተመልሶ የሸዋ ንጉሥ ተባለ። በ1865 ሁሉም ግዛቶች ከአቢሲኒያ በስተቀር ለመቆጣጠር ችሎ ነበረ። መላውን ወሎ በጦርነት አሸንፈው ተቆጣጥሮ ወደ ጎንደር በመሄድ ንጉሠ ነገ ሥት ለመሆን ፈልጎ ነበረ። ነገር ግን በመቅደላ አጼ ቴዎድሮስ ሐበሾች በእንግሊዞች ተሸን ፈው ራሱን ስለገደለ እንግሊዞች አጼ ዮሐንስን ንጉሥ በማድረጋቸው ምኒልክ ጉጃምን ተቆጣጥሮ ወደ አቢሲኒያ በማምራት ንጉሥ ለመሆን ሲቃረብ አጼ ዮሐንስ በግብጾች ላይ ባደረገው ጦርነት ስለቆናው ምኒልክ እድሉ ለጊዜው አከተመ፤ ለዮሐንስ እጁን ሠጠ። ሆኖም ምኒልክ የሕዝቡና የጦሩ ታማኝነት አለው፤ የኢጣሊያም ወዳጅ ነው። አንድ ቀን ከጣልቃ ገቢው ከእረኛው ዮሐንስ በቅርብ ጊዜ ጦርነት ገጥሞ አሸንፎ የአባቶቹን ዙፋን እንደሚረከብ እያጠራጥርም ብሏል።

## 9. የውጫሌ ውል

በቀይ ባሕር በኩል የሀገራችን ለንዘር መሬት አንሰጥም ተብሎ ከፍተኛ ትግል በሚደረግበት ጊዜ በመሐል ሀገራችን ግን ያ የተከበረ መሬታችን፤ የታሪካችን አሻራ የሆነው የዐሚኗዊ የሀገራችን መሬት ለድርድር ቀርቦ ለኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች በገጸ በረከት ተሸጧል። አሰቡን ለኢጣሊያ የሸጡ ሱልጣኖች እንኳን ሕጋዊ አይደሉም፤ በኃላፊነት የሚጠየቁ አይ ደሉም ተብሏል፤ ምክንያቱም 1ኛ. አሰብ ራሱ በአውሣ ሡልጣን ሥር ስለሆነ 2ኛ. የመ ላው አፋሮች ሹም አንፋሪ የአውሣ ሡልጣንም በሙሉ በኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥት



ከሰለሞን ዘር ይወለዳል ብለው በግመን ከምኒልክ ጋራ በጋብቻ የመተሳሰር ፍላጎት ነበር የታየባቸው። አጼ ምኒሊክ በጣም ዕድለኛ ሊባል ይገባዋል። ይኸውም ዕድል በከፊል እያቶቹ ያቀፉለት ዕድል ነው ለማለት ይቻላል። የሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ግን የሰለሞን ዘር የለውም ማንነቱም የኦሮሞ ዝርያ ነው። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የሰለሞን ዘር አመጣጥ ዐይፉ የሚታ ወቀው በቀድሞ መሪዎች እንድናውቀው የተሰጠን ታሪክ መንዝ ላይ የቀረው ከአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ከአቤቶ ያዕቆብ የሚወለድ መሆኑን ይገልፁና አንድ ትውልድ ዘለው ከአቤቶ ያዕቆብ የልጅ ልጆች ከሆኑ አንዱ ከአቤቶ ነጋሲ ምስፍና ተጀመረ ይላሉ። ሌሎች ግን አን ደሚከተለው ያስቀምጡታል።[1] አጼ እያሱ ቀዳማዊ ሸዋን ለመጐብኘት በመጣ ጊዜ መርድ አዝማች ሹመት ሰጠው። አጼ ሱሲኒዮስ የካቶሊክ ሃይማኖት እምነት ተቀብሎ ነበር። አጼ ሱሲኒዮስ በቤተመንግሥቱ አንድ ፋሪስ የተባለው የኦሮሞ ዝርያ ሆኖ የየጁ ተወላጅ ነበር። እሱም እንደ ሱሲኒዮስ የካቶሊክ ሃይማኖት ተቀብሎ ነበር። አጼ ሱሲኒዮስና ፋሪስ በግድም ሆነ በውድም የካቶሊክ ሃይማኖት ለማስፋፋት ብርቱ ጥረት ቢያደርጉም በሕዝቡ ተቃውሞ አጼ ሱሲኒዮስ ከሥልጣን ሲወርድ ፋሪስም ራስ ሆኖ የወሎ ሀገረ ገዢ ሆኖ ተሹሞ ሄዶ ስለነበረ ራስ ፋሪስ በሞተ ጊዜ አንድ ሴት ልጅ ትቶ ነበር የሞተ። ለነበልት የምትባል ከአጼ ፋሲል ለመሸሽ ከወሎ ወደ መንዝና ግሽን መጥታ አንድ ሀብታም ሰው አግብታ ነጋሲ የተባለውን ልጅ ወለደች። ከነጋሲ ቀጥሎ ያለው ትውልድ ለውጥ የሌለው ቢሆንም መርዕድ አዝማች የተባለው ነጋሲ ማይሆን የሱ ልጅ አብዬ ነው። የትውልዱ ሀረግ 1ኛ. ነጋሲ 2ኛ.ሰባስቴ 3ኛ.አቢዬ /መርዕድ አዝማች/ 4ኛ. አምደእየሱስ 5ኛ. አስፋወሰን 6ኛ. ወሰንሰገድ 7ኛ. ሣህለ ሥላሴ (ንጉሥ) የነገሰበት ዘመን 1813 እያለ ይሄዳል። ነጋሲ ከአጼ ልብነ ድንግል እንደማይወለድ የሚያስረዳን አጼ እያሱ ቀዳማዊ የአጼ ልብነድንግል የልጅ ልጅ ሲሆን እንዴት ከጉንደር ለጉብኝት ወይንም ግብር ለማስከፈል ወደ ሸዋ ሲመጣ ብቻ ከነጋሲ ጋራ ተዋወቀ? ነጋሲ የንጉሥ ዘር ከሆነ እንዴት ሸዋ ተረስቶ ተቀመጠ? ለምን እንደሌሎቹ የመ ሣፍንት ዘሮች ወደ ወህኒ አምባ አልተወሰደም? የቅርብ ዘመድ ሆነው ተረስተው ሊቀመጡ አይ ችሉም። የምኒሊክና የኃይለ ሥላሴ የሰለሞን ዘር መሆናቸው መላው የኢ ትዮጵያ ሕዝብ አሜን ብሎ የተቀበለው ነው። የሌላ ነገሥታት ዝና እንዳይወራ በታሪክ እንዳይመዘገብ ከፍተኛ ጥረት ይደረግ ነበር።

የሀገራችን ታሪክ እንድናውቀው ይደረግ የነበረው ለቀድሞ ነገሥታት በሚያመች ሁኔታ ነበር። የታሪክ ፀሐፊዎችም ለነገሥታቱ ያደሩ ከነገሥታቱ ደመወዝ የሚከፈላቸው ነበሩ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገሩ ትክክለኛ ታሪክ ለማወቅ አልቻለም። በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ከፀረ ቅኝ ገዢዎችና ተስፋፊዎች በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል። ከተካሄዱት ጦርነቶች የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲያውቅ የተደረገው ስለዓድዋና ማይጨው ጦርነት ብቻ ነበር። በታሪካችን ውስጥ ከሁሉ ከባድ ጦርነት የተመዘገበው ግን በጉራዕ የተካሄደው በግብፅና በኢትዮጵያ መሀል የተካሄደው ጦርነት ነው።

1 Ceochi: Da Zeila alle fronitere di Caffa V I p 257-58

ው ንጉሥ ዘውድ ለመጫን ከአጼ ዮሐንስ ላይ በግመጽ ወደፊት በመግጠም የነበረው ሥውር ዓላማ የሚያገለግሉት ጣሊያኖች የጦር መሣሪያዎች እንዲያቀብሉት ነበረ።

ጣሊያኖችም የመጡበት ይፋዊ የሆነ ዓላማ ቢደናቀፍባቸውም ሥውር ዓላማቸው ግን ሀገራቸው ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ስለነበረ በከፊል እሥረኛ መሆን እምብዛም አልጠሉትም። ካርዲናል ማሣያ ራሣ ቸው በይፋ የተሰጣቸውን ሀገረ ስብከት የኦሮሞ ሀገር ቢሆንም በሸዋም ኦሮሞዎች ስላሉ በሸዋ መቀመጣቸው ለተሰጣቸው ተልዕኮ ተቃራኒ እንደማይሆን ይናገሩም ይጽፉም ነበረ። ሐቁ ግን ኦሮሞ ሀገር ለመሄድ ያልፈለጉት 1ኛ. ከኦሮሞ የመጡት ተባርረው ስለሆነ መመለስ ስለማይችሉ 2ኛ. ንጉሥ ምኒልክን ካቶሊክ ለማድረግ ተስፋ ስላደረባቸው 3ኛ. በኦሮሞ ሀገር በገንዘብ ዕዳ እንዳይያዙ ነበረ። ምኒልክ በእጁ ብዙ ማስፈራሪያዎች ይዟል። የጦር መሣሪያ እናቀብልም ካሉት በቃል የሰጡኣቸው መሬት በጽሁፍ አልሰጣችሁም፣ ወደ ጂማ ከፋ እንድትሄዱ አልፈቀድላችሁም፣ ከሀገር እባርራችኋለሁ ይላቸው ነበረ። ጣሊያኖች ሌላ ሥውር ዓላማ ስለነበራቸው ከምኒልክ ቃል መውጣት አልፈለጉም። በዚሁ መሠረት ከአባሎቹ አንዱ ሰባስቲያኖ ማርቲኒ የተባለው ዲሰምበር 5/1877 መሣሪያ ለማምጣት ወደ ኢጣሊያ ሀገር እንዲሄድ ተደረገ።


ከሁለት ዓመት በኋላ ኖቬምበር 1879 ስጦታዎችን፣ ኒሻኖችን፣ ደብዳቤም የወዳጅነት ውል ረቂቅና 210 ጠብመንጃዎችን ይዞ ሲመለስ አንቶኔሊ የተባለው የምኒልክ ወዳጅ ለመሆን የበቃና የውጫሌ ውል አቀነባባሪ የነበረው ለመጀመሪያ ጊዜ አብሮ ወደ ሸዋ መጣ። አንቶኔሊ የጦር መሣሪያ ለአፍሪካ እንዳይሸጥ የሚል ስምምነት በተለይ ብሪታኒያ በጥብቅ ትከታተለው የነበረው በመጣስ ማርቲኒ ወደ ሀገሩ ሲመለስ እሱን በመተካት ከምኒልክ ጋር የጦር መሣሪያ ንግድ ማድረግ ጀመረ። ሌሎች ሀገሮች በሚቆጣጠሩበት ወደብ መሣሪያ ለማስገባት ችግር ስለሚፈጥር በኢጣሊያ ቁጥጥር ስሆነው በአሰብ ወደብ መሣሪያዎቹ እንዲገቡ እቅድ አውጥቶ ተግባለት። በቫቲካን ካርዲናል የሆኑ አጐት ስለነበሩት፣ በዚሁ ዝምድና በመጠቀም የሮማ ጳጳስ ከመንፈሣዊ ሥልጣናቸው ሌላ የአንድ ሀገር መሪ ስለነበሩ፣ ከ1860 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ይህ ሥልጣናቸው ስላጡ በቫቲካን 2000 ሬሚንግተን ጠብመንጃዎች በሽያጭ ለምኒልክ ለማግኘት ለለተስማማ የኢጣሊያ መንግሥት በ1879 ካርዲናል ማሣያ ባለሙሉ ሥልጣን ኢጣሊያን ወክለው ከምኒልክ ጋራ እንዲዋዋሉ የተደረገው ስምምነት ካርዲናሉ ከሀገር በመባረራቸው አንቶኔሊ በቦታቸው እንዲተካ ተደርጐ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ተሾሞአል። ከምኒልክ ጋራም አንድ የወዳጅነትና የንግድ ውል ተፈራርመዋል። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ጣሊያኖች ምኒልክ መልእክተኛ ወደ ጣሊያን ሀገር እንዲልክ ይጐተጐቱት ነበር። ምኒልክ ደግሞ አጼ ዮሐንስን በመፍራት ይሆናል፤ ሁል ጊዜ እሺ እያሉ መልዕክተኛውን ከመላክ ተቆጥቦ ይኖር ነበረ። ጣሊያኖች ግን በጣም የተቸገሩበት ጉዳይ ነበረ፣ ምናልባትም የውጫሌ ውል ዓይነት ለሸዋ ብቻ ለማስፈረም አስበው ይሆናል። አሁንም ምኒልክ የመልክተኛው ወደ ጣሊያን ሀገር የመላክ ጉዳይ እያረሳሳ ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ በዶጋሊና በበይሉል የሞቱት ጣሊያኖች እኔ አበቀልላቸዋለሁ እያለ ጣሊያኖችን እያታለለ በምስጢር ከጣሊያን መንግሥት 5000 ሬሚንግተን ጠብመንጃዎች ለማግኘት ውል አደረገ።



ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ አንቶኔሊ ራሱ ተታሉ መንግሥቱን የሚያታልልበት የነበረ ዘዴ ንጉሥ ምኒልክ ገር ናቸው ጣሊያኖችን ይወዳሉ፣ ግዛታቸው ሸዋ በኢጣሊያ የበላይ አስተዳዳሪነት ሥር፣ (ፕሮቴክቶሬት) ለማድረግ ፍላጐት አላቸው (አካባቢያቸው ግን ብዙ ትግሬዎች አሉ) ከጦር አለቆችም ብዙ ትግሬዎች አሉ (ባለቤታቸውም ጣይቱ ትግሬ ናቸው) አብዛኛው የቤተ ክህነት መሪዎች የአጼ ዮሐንስ ደጋፊ ናቸው ወዘተ... በሚል እኑ ጋገር ነበረ ለኢጣሊያ መንግሥት ያስተላልፋቸው የነበረ ሪፖርቶች ዋና ፀረ–ትግራይ የሸዋ ወዳጅ የነበሩ ደግሞ ካርዲናል ማሣያ ነበሩ። አንቶኔሊም ከእሣቸው ተምሮ ፀረ– ትግራይ፣ ፀረ–ኢትዮጵያና የሸዋ ወዳጅ ፖሊሲ አካሄደዋል። ጣሊያኖች ቀንደኛ ጠላታችን ይሉት የነበረ አጼ ዮሐንስ በጀግንነት ለሀገሩና ለሃይማኖቱ እየተዋጋ በጦር ሜዳ መተማ ላይ መጋቢት 1ቀን 1881 ዓ.ም. (ማርች 10/1889) ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። አሁን ለጣሊያኖችና ለንጉሥ ምኒልክ መልእክተኛም ወደ ጣሊያን ሀገር ለመላክ ውልም ለመፈራረም መንገድ ክፍት ሆነላቸው። አንቶኔሊ ብዙ ጊዜ የተመኘው ክብር ያለምንም ውጣ ውረድ ራሱ ማግኘት ፈለገ። ድሮ ይመኘው የነበረ በሸዋ የጣሊያን የበላይነት አስተዳደር (ፕሮቴክቶሬት) ብቻ ነበረ። አሁን ግን ከተመኘው በላይ ማይታሰብ የመላው ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ሥር የበላይነት አስተዳደር አገኘሁ ብሎ ተደስቶ ውሉም የሚፈራረምበት አጼ ምኒልክ ወደ ጣሊያን ሀገር መልዕክተኞቹን ልኮ መሆኑ ቀርቶ አዲስ አበባ ላይም አልተደረገም ፤በወሎ በአንድ አነስተኛ መንደር ሚያ 2 ቀን 1889 በውጫሌ ውሉ[1] ተፈጸመ። ውሉ 20 አንቀጾች ያዘለ ነበረ። ኤርትራን በሚመለከት ግን ሶስተኛ አንቀጽ ብቻ ነበረ። እሱም በሁለቱ ወገኖች ያለመግባባት ለማስወገድ በወሰናቸው ልዩ ቋሚ ምልክት የሚያደርጉ ሁለት የኢጣሊያ፣ ሁለት የኢትዮጵያ መልእክተኞች በተውጣጡ ልዩ ኮሚሽን ይመሠረታል፣ የሚመራበትም በሚከተለው ይሆናል። ሀ/ የደጋ መስመር የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ወሰን ይሆናል ለ/ ካራፋሊ አካባቢ ተነስቶ ሐላይ ሰገነይቲና አሥመራ በኢጣሊያ ወሰን ውስጥ ይሆናሉ። ሐ/ አዲ ንፋስና አዲ ዮሐንስ በቦጐስ በኩል በኢጣሊያ ወሰን ውስጥ ይሆናሉ። መ/ ከአዲ ንፋስ ቀጥታ መሥመር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ የወሰን ምልክት ይሆናል የሚል ነበረ። በዚሁ ጊዜ አንቶኔሊ በደስታ ተውጦ ውሉን መፈረሙን ለሀገሩ መንግሥት ያበስራል፣ እክራካሪ ጉዳይ ሆና የቆየው የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ወደ ጣሊያን ሀገር መላክም እልባት ያገኛል። ከዚህ በፊት እንደተደረገው እንደ አባ ሚካኤል ማይሆን አጼ ምኒልክ የእኅት ልጅና ታማኝ ቀኝ እጁ የነበረው ራስ መኰንን መልዕክተኛ ባለሙሉ ሥልጣን አድርጎ ሾሞ ወደ ኢጣሊያ ይላካል። አንቶኔሊና ራስ መኰንን ኦገስት 21 ቀን 1889 ጣሊያን ሀገር ይደርሣሉ። ራስ መኰንን ኦክቶበር 1 ቀን 1889[2] ስለወሰኖች ማስተካከያ ከውጫሌ ተጨማሪ ውል ይፈራረማሉ።

1 Carlo Rossetti, Ibd p.41-45

2 Carlo Rossetti, Ibd p.41-45




የትግራይ ድንበር እስከ 1872 /1880



ይህ ውል በእኔ ምግብ የውጫሌ ውል አንቀጽ 16ን የሚቃረን ነው። ይህ ውልም 11 አንቀጾች ያዘለ ሲሆን ኤርትራን የሚመለከት ግን አንቀጽ 3 ብቻ ነው።

እሱም በአሁኑ ጊዜ በየይዞታቸው ባለው መሬት ወሰኑ እንዲከበር መሠረት በማድረግ የሆሉቱ ሀገሮች ወሰኖች ማስተካከያዎች ለመወሰን ሜይ 2 ቀን 1889 አንቀጽ 3 በተደረገው ውል መሠረት የኢጣሊያ ንጉሥና አጼ ምኒልክ መልእክተኞቻቸውን ይሾማሉ የሚል ነበረ።

የወደቁት የኢትዮጵያ መንግሥታት መሪዎች ገንጠዮችና ከሐዲዎች እየተባሉ ሲጠሯ ቸው እንደነበረ እናስታውሳለን፤ ነገር ግን ዋና ገንጣዮች ምኒልክና ጣሊያኖች ናቸው። የዛሬ ግን ገንጣዮች የቀኝ አገዛዝ የእጅ አዙር የቀኝ አገዛዝ ርእዮተ ዓለም ደጋፊዎች አፍሪካን ለመቀራመት የመጣው አቅድ በበርሊኑ ጉባዔ የተደነገጉ ውሣኔዎች በተግባር ደጋፊዎች፤ በጣሊያኖች ሰብከት ፀረ—ኢትዮጵያ አቋም ያደረባቸው ቢባሉ አይበዛባቸውም። ይህ ፀረ—ኢ ትዮጵያና ፀረ—አማርኛ ተናጋሪ ሕዝብ ጥላቻ በሚገት አብዛኛው በኤርትራ ነው ጉልቶ የሚታየው። በአንጻሩም ፀረ—ትግራይ ጥላቻ የሚሰማው በአዲስ አበባ ብቻ ነው፤ በሌሎች ክፍላተ ሀገራት አይሰማም ጣሊያን የረገጡበት ቦታ የሸዋ ፖለቲካ፤ የትግራይ ፖለቲካ እያሉ በሸዋ በስሜን ኢትዮጵያ ተቀምጠው እርስ በርሳችን ለማፋጀት የለኮሱብን እሳት ነው። ገንጣዮች ሌላ ተጨባጭ የሚያጣላን በቂ ምክንያት ሊያቀርቡ አይችሉም።

# ምዕራፍ 9

# ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገቻቸው ወረራዎችና ጦርነቶች

## ክፍል 2

## አከለጉዛይ የጦር አውድማ ሆናለች

### ሀ. ሰገነይቲ

ፊታውራሪ ደበበ የአጼ ዮሐንስ የወንድም ልጅ ነው። ከእዚሁ ተጣልቶ በረሐ ለበረሐ እየዞረ በውንብድና ሥራ የሚተዳደር ነበረ። ጣሊያኖች ይጠቅመናል ብለው በኢትዮጵያ ላይ ደፈጣ ውጊያ እንዲያደርግላቸው ከመለመሏቸው ብዙ ሰዎች አንዱ ነበረ። ከጣልያኖች በሚጣላበት ጊዜ ወይንም በጥርጣሬ በሚያዩበት ጊዜ የአማውርታ ጉማ ተያዥ ሆነው ያስታርቁት ነበረ። በዚሁ ምክንያት የእማውርታ ጉማዎች የደበበ ወዳጅ እያሉ ጣሊያኖች ይጠሩዋቸው ነበረ። በዓመት 5,000 ሊሬ ከጣሊያኖች ለደበበ ይከፈለው ነበረ። አገስት 1888 ግን ከጣሊያኖች ጋራ ተጣልቶ ሸፍቶ አስጨንቋቸው ነበረ። መደበኛ አድራሻውም ሰገነይቲ ነው ስለተባለ በወቅቱ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ የነበረ ጄኔራል ባልዲሴራ ከምፅዋ ወታደሮችን ልኮ በድንገት አደጋ ጥሎ ደበበን ለመግደል እቅድ አውጥቶ ይሄን እቅድ የሚፈጽምለት ሻንበል ኮርናኪያን (cornacchia) ይመርጣል። 400 ባሺብዙክ ይሰጠዋል። እንደዚሁም 4 የኢጣሊያ መቶ አለቆች አብረው ለዘመቻ እንዲሄዱ ይታዘዛሉ። የዘመቻው ውጤት ግን ከዶጋዓሊ በኋላ በጣሊያን ሕዝብ ላይ የደረሰ ከባድ ሽንፈት ነበረ። ጄኔራል ባልዲሴራ ለሻምበል ኮርናኪያ አገስት 1 ቀን 1886 ዓ.ም. በጻፈለት ደብዳቤ ደበበ በሚገኝበት በሰገነይቲ ድንገተኛ አደጋ በመጣል ደበበን እንዲይዙ ታዟል። በተቻለ ፍጥነት በሐዳስ ሸለቆ በኩል ወደ ሰገነይቲ ዘልቀው ሳይነጋ በለሊት እንዲደርሱ። ወደሰገነይቲ በሚጓዙበት ጊዜ ምንም ሰው ከእርስዎ በፊት እንዳያስቀድመ፤ በተለይ አክሩር እንደደረሱ ከአክሩር ወደ ሰገነይቲ ማንም ሰው እንዳይሄድ እንዲከለክሉ፤ ለላዮች ሊሆኑ ይችላሉ። ደበበን ወይም ተከታዮቹን ለመያዝ ወይንም ለመግደል ከቻሉ ተግባርን እንደፈጸሙ ምርኮኞቹን ይዘው በፍጥነት ይመለሳሉ። ደበበ በቦታው ካልተገኘ ከእሱ ቤቶች መግፊያዎችን ከተወሰዱ በኋላ አጠገቡ ላሉ ቤቶች አደጋ የማያመጣ ከሆነ ቤቶቹን እንዲቃጠሉ ያደርጋሉ። ይሄንን ትእዛዝ ተቀብሉ አገሰት 6 አክሩር አካባቢ ከቀኑ በ6 ሰዓት ደርሰው እስከሚቀጥለው ቀን ከቀኑ 9 ሰዓት ዕረፍት ያደርጋሉ። ጠዋት አገስት 8 ወደ ሰገነይቲ እምርተው ድንገተኛ ጥቃት ለመፈጸም በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ፤ ደበበ ከአገስት 6 ጀምሮ መምጣታቸውን ሰምቶ እንቅስቃሴያቸውን ይከታተል ስለነበረ፤ ሴት፤ ሽማግሌ፤ ልጅ ከመንደሩ አስወጥቶ ለውጊያው ተዘጋጅቶ ይጠባበቃቸው ስለነበረ ተኩስ ተከፍቶ ጦርነት ተካሄዶ በድምሩ 250 ባሺብዙክና አምስቱ የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች ሲገደሉ ሌሎቹ የቆሰሉ ወይንም ያልቆሰሉ ሸሽተው ምፅዋ ገቡ። ደበበ የሰው ኃይል 470 ጠበመንጃ የታጠቁ ተዋጊዎችና 400 ጎራዴና ሻንጃ የታጠቁ ተዋጊዎች ነበሩ። እዚህ ላይ ጣሊያኖች ሶስት ስህተቶች እንደፈጸሙ ይታያል። 1ኛ. ከምፅዋ ሰገነይቲ ለመድረስ አጭሩ መንገድ በሐዳስ ማይሆን በዓሊ ጊደ ነው። 2ኛ. አክሩር ላይ ከ24 ሰዓት በላይ መቆየታቸው ራሳቸውን በራሳቸው እንደተጋለጡ ይቆጠራል። 3ኛ. ጦርነት ማይገጥሙ መሸሻቸው። ጣሊያኖች ከዶጋዓሊ ቀጥሎ ከባድ ሽንፈት የደረሰባቸው በሰገነይቲ ጦርነት ነበረ። በሰው ኃይል ሁለቱ ወገኖች ተመጣጣኝ ነበሩ። የሞቱት ሁሉም ጣሊያናውያን ባይሆኑም በሞቱት የሰው ብዛት ሲታይ ግን ከዶጋዓሊ ጋራ የሚተራረብ ነበረ። በደበበ ጦር ላይ የደረሰው ጉዳት በጣም አነስተኛ ነበረ። ተኩስ እንደተከፈተ ጣሊያኖች መሸሽ ስለጀመሩ የተገደሉት አብዛኛው በመሸሸ እንዳሉ ለ5 ሰዓት እያሳደዱ የገደሉዋቸው ናቸው። ከብዙ ሰዓት ሽሽት በኋላ ከኢጣሊያ ጦር መኰንኖች አንዱ ወታደሮቹን አቁሞ ለመከላከል ሞክሮ ነበረ። ግን አልተሳካለትም፤ ራሱም ተገደለ። ስለዚህ ጦርነቱ በሰገነይቲ ሰም የሚጠራው የተጀመረበት ቦታ በመሆኑ ነው እንጂ ያበቃው የ5 ሰዓት ሩጫ ወደ ምፅዋ በሚወስደው መንገድ ነበረ። ሽንፈት ስለሆነ ከሰገነይቲ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች የሉም።




### ለ. ሐላይ

የአከለጉዛይ ሰገነይቲ ተወላጅ ደጃዝማች ባህታ ሐጎስ የሸፍቶች አለቃ በመሆን ከንራስ አሉላ እና ከጣሊያኖቹ ጋር እየተጣላና እየታረቀ በጉረቤቶቹ አማውርታ ጉማዎች ሆነር በረየዎች እንዲሁም ዘመዶቹ ባሉበት ሆነር በሐባብ ሳህል በረሃዎች ከኖረ በኋላ በመጨረሻ ለጣሊያኖች ያደረ መስሎ ከአንድ ኢጣሊያዊ መቶ አለቃ ስር በመሆን የአከለጉዛይ አውራጃ ገዢ ሆኖ በጣ ሊያኖች ተሹሞ ተቀማጭነቱ ሰገነይቲ ሆኖ በሚያስተዳድርበት ጊዜ የራሱ የሆነ ዓላማ ነበረው። ዓላማውም አመቺ ጊዜ ጠብቆ ጣሊያኖች በሀገሩ የዘረጉትን አዲስ ስርዓት ለማፈራረስ ነበር። በከሰላ ጦርነት ጊዜ የኢጣሊያ ጦር አለቆች ከጄኔራል ባራቲሪ

ጀምሮ ከትግራይ እደጋ ይደርስብን ይሆናል ብለው ስጋት ነበራቸው። ነገር ግን በኢጣሊያ ክሕደት የሚፈጽም ባህታ ሐጎስ ይሆናል ብሎ የገመተ ሰው ማንም አልነበረም። ከትግራይ መሪዎች ሁሉ እምነት ተጥሎበት የነበረ ከጣሊያኖች ታላቅ ክብር ያገኘ ነበረ። ለብዙ ዓመታት በበረሃ ከተንከራተተ በኋላ ከራስ መንገሻ በታች በመሆን ወደ ሀገሩ ገብቶ በሰላም ለመኖር እንደሚመርጥ የሁሉ ግምት ነበር። ጣሊያኖች ጀግና ብለው ይተማመኑበት ነበር። እንዲጠቀሙበትም ብዙ ሃሣብ ነበራቸው። ዲሰምበር 15 ባራቴሪ ከረን ሆኖ ስለክህደቱ ወሬ ሲሰማ ማመን አልቻለም ነበር። የከዳበት ምክንያት ጥርጣሬ ያደረባቸው ምክንያቱን በሚመረመሩበት ጊዜ ጣሊያኖች የፈረንሳይ ሳዛሪስት ቄሶች ይሆናሉ የሚል ነበር።

ፈርዲናንዶ ማርቲኒ በደረሰው መጽሐፍ የተጠቀሰው ፍራንኬቲ የተባለው ከአሰመራ በእንድ የኢጣሊያ ጋዜጣ ስለደጃዝማች ባህታ ሐጎስ ያወጣው ዘገባ ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

ስለእሱ ታማኝነት (ስለባህታ ሐጐስ) ጥርጣሬ ያለው ሰው ቢኖር እንኳሉ ትክክል አይደለም ይባል ነበር። ስለሆነም እሱ ዓመጽ እነሳ፣ ይኸውም የሆነበት በድንገተኛ ንዴት በደል ስለደረሰበት ለመበቀል አይደለም። በታላቅ ክብር ከበውት ሰገነይቲ በሚኖሩ ኑሮች ላይ ለረጅም ጊዜ ክህደትና ጥንቃቄ የተሞላበት ጨካኝ እልቂት ካዘጋጀ በኋላ ነው።

እሱ ከእኛ ከጣሊያኖች ደመወዝ ይቀበል ነበር፣ ውድ ስጦታዎች ከእኛ የተቀበለ በቅኝ ግዛት ለማንም ሐበሻ የማይሰጥ ሥልጣን ከእኛ አግኝቶ የነበረ ዲሰምበር 1894 ዓ.ም. ሐላይ ላይ በወታደር ምሽግ ላይ በሰጠነው መሣሪያ እኛን እየተዋጋ ሞቷል።

ከኤርትራ ስለተባረሩ ተናደው የፈረንሳይ ሳዛሪስት ሚሲዮናውያን ተገፋፍቶ ነው ተብሏል። ሊሆን የሚችል ነው። ባሕታ ሐጐስ ከላዛሪስቶች ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበረው። በአኩሩር ቤተክርስቲያን እንዲሰሩ እርዳታ አድርግውላቸው ነበር። በየጊዜው ይጠይቃቸው ነበር፤ ደብዳቤዎች ይጻጻፍ ነበር። ነገር ግን ለክሕደት የገፋፋው ይህ ብቻ ወይም ዋነኛ ምክንያት ሊሆን አይችልም። የተለመደው ዕስታዊ የግታ ውይይት ወደ ጐን ትቶ የመቶ አለቃ ሳንጉዊነቲ ካሰረ በኋላ ድል እንደሚቀዳጅ በእጭር ጊዜ እርግጠኛ በመሆን ወደ ሐላይ ባመራበት ጊዜ የሚከተለውን ለአከለጉዛይ ሕዝብ ጥሪ አስተላለፈ። ከነዚህ ከባህር ማዶ የመጡ ሰዎች ነጻ እወጣችሁአለሁ መሬታችሁን ወስደው ባዶ ሊያስቀሯችሁ ይፈልጋሉ። እኔ ከራስ መንገሻ ጋር ተስማምቻለሁ። ራስ መንገሻ ብዛት ያለው ጦር ይዞ ወደዚሁ እየገሰገሰ ነው። እስካሁን ያልተነሳሁ መልስ ከሩቅ ቦታ እጠብቅ ስለነበረ ነው። ጥሪውን ሕዝቡ የተቀበለው በጣም በከፍተኛ ስሜት ነው። ለጥሪው ምክንያት የሆነው ማንም ሰው ሊያስተባብለው የማይችለው ፍራንኬቲ ወደ ኤርትራ ያመጣቸው ኢጣሊያውያን ቤተሰቦች በሰራዬ ከጉዶ ፈላሲ እስከ ጉራዕ እንዲሁም ትንሹ መሬት ባህታ ሐጎስ ከሚያዝበት በአከለጉዛይ ውስጥ ጉራዕ አጠገብ የእርሻ መሬት ከ25 ሄክታር የማይበልጥ ተሰጥቷቸው ነበር። ይህ ጉዳይ ባህታ አስቆጥቶት ነበር። ሰንዐፌ በራስ መንገሻ ድንኳን የተገኙ ማስረጃዎች ውስጥም የደጃዝማች ቁጣ የሚገልጹ ነበሩ። ሶስት ጊዜ ለአጼ ምኒልክ ደብዳቤዎች ጽፎ ጣሊያኖችን ለማጥቃት እንደሚፈልግ ገልፀዋል፤ ይህ ካልተፈቀደለት ምኒልክ ጣሊያኖችን ሰፋሪዎች መሬት ማግኘት የሚችሉት ከሀገሩ ተወላጅ ሴቶች ሲጋቡ ብቻ እንደሆነ ብሎ ለኢጣሊያ



መንግሥት እንዲያሣልድለት ገልጾ ነበር። ሁለት ጊዜ እሱም ራሱ አጼ ምኒልክ መልስ እየጠበቀ ስለሆነ እንዲጠብቅ፤ መልሱ እንደመጣ ግን ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚነገረው መሆኑን ጽፎለት ነበር። ምኒልክ ይጠብቀው የነበረው መልስ የውጫሌ ውል ኮሚክ የሆነ የአንቀጹሊ አንቀጽ 17 እንዲሰረዝ ነበር። ባሕታ ሐጎስ የጠየቀው ፈቃድ ይሰጠው አይሰጠው አይታወቅም። ሆኖም የተፈተደ መሆኑን ምልክት የሚሆነው በኰዓቲት ጦርነት ጃንዋሪ 13 እና 14 /1895 ዓ.ም. በከፊል ወይም በሙሉ በሥራ ላይ የዋሉ አጼ ምኒልክ ለራስ መንገሻ 35,000 /ሰላሳ አምስት ሺህ/ ጥይቶች መላኩ ነው። ሰፈራን የሚቃወሙ ሰዎች ይኸውሳችሁ የእናንተ ሥራ ምናልባት ለሙከራ የተሰጡ መሬቶች ባይሰጡ ኖሮ ባህታ ሐጐስ አይሸፍትም ነበር፤ ለመንገሻ ዕርዳታ አይሰጥም ነበር። በሐላይና በኰዓቲት ድል ለማግኘት የከፈልናቸው በከንቱ የሰው መስዋዕትነትና ገንዘብ ይቀር ነበር ይላሉ በማለት ጽፈዋል።

ማርቲኒ በበኩሉ ለዚሁ ደብዳቤ መልስ ሲሰጥ ከሰላ ይዞ ማሕዲስችን እሸንፎ የተካ፣ ጋላባት፤ ገዳሪፍ የንግድ እንቅስቃሴ ወደ ምጽዋ እንዲመጣ እስተማማኝ ለማድረግ የማይፈለግ ከሆነ የኢጣሊያ እርሶ አደሮች በሀገራቸው በረሃብ የሚሞቱ በኤርትራ መሬት ተሰጥቷቸው ባለንብረቶች እንዲሆኑ ለማድረግ የማይቻል ከሆነ ይኸና የመሣሰሉት ለማድረግ የማይቻል ከሆነ እኛ ምን ልንሰራ ነው በአቢሲኒያ የተቀመጥነው? «እንዲጀኒ» ተወላጆቹ ከራሳቸው ዘር የሆኑ ዘራፊዎች እንድንከላከልላቸው ነውን? ወ.ዘ.ተ. ብሎ ነበር እስተያየቱን የደመደመው።

ከዚህም ሌላ ደጃዝማች ባህታ ሐጐስ ለክህደት ያነሳሳው በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፤ ምናልባት የፈረንሳይ ሳዛሪስቶችም ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህም በሰንዓፌ በራስ መንገሻ ድንኳን የተገኙ ወረቀቶች ፈረንሳይ በእኛ ላይ የምትፈጽመው መሰናክል ማዕከል እንደነበሩ አሳይቷል። በዚሁ ወቅት ከሚሲዮናውያኑም ሌላ እጅ እንደነበረ የኢጣሊያ ጦር ኃይል መጽሔት አትሞ እንዳወጣው ክሉሸት (Clochette) የተባለው ከፈረንሳይ መኰንኖች አንዱ ለባሕታ ሐጐስ መሸፈት እጅ እንዳለበት ከታመኑ የዜና ምንጮች የተገኘ ብሎ አውጥቶ ነበር።

ባሕታ ሐጐስ በቅርብ ጊዜ ነው ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት የቀየረ እንደ ባህታዊ ጸሎት ያዘ ነበር፤ ሰገነይቲ አጠገብ ከሚገኘው የላዛሪስት ቤተክርስቲያን ግንኙነት ነበረው። እንድ የሀገሩ ተወላጅ ኢንዲጀኖ ቄስ የነፍስ አባቱ የነበረው ላዛሪስት፣ ዓመጸኞች በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች ሁሉ ተካፋይ እንደነበረና ባህታ ሐጐስ ወደ ሐላይ በሔደበት ጊዜ አብሮ ይሔድ እንደነበረ ተረጋግጧል። ላዛሪስቶች በእኛ ላይ ይደረግ የነበረ ሴራ ያውቁ እንደነበረ ሌላ ማስረጃ የሚሆነው ሻለቃ ቶሰሊ በባህታ ሐጐስ እና በትግራይ ራሶች የተደረጉ ስምምነቶች በሙሉ ዝርዝር ከአንድ ኢንድጀኖ ላዛሪስት ያገኘው ነው። ይኸውም በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያረጋግጥ ነው።

ከሳንጉዊነቲ ጋር ፎርናሲዮና አርናልዶ የተባሉ ሁለት በሰገነይቲ የሚኖሩ የቴሌ እፕሬተሮች ታስረው ነበር። የእስተሳሰሩ ሁኔታ ሳንጉዊነቲ ራሱ ሲያወራ ማታ ዲሰምበር 14

መቶ አለቃው ቡና በሚጠጣበት ሰዓት እንደተለመደው ባህታ ሐጐስ ወንድሙ ሰንጋልና ሌላ ሹም ሆነው በየቀኑ ይጋብዛቸው የነበረ ቡና ይወዱት ስለነበረ ከቡናው የበለጠም ያጠግ ቸው የነበረ የአልኮል አረቄ ይወዱ ስለነበረ ወደ ቤቱ ገቡ። ቡናም እንዳለቀ ባህታ ሐጐስ ሰንጋል መቶ አለቃውን ዘለው በእጁ ያዙት። ሳንጉኒቲ (Sanguinetti) ለመከላከል ሞከረ። ነገር ግን ወደ መሬት እንዲዘረር አደረጉት፤ ባህታም አንድ ጉልበቱ ወደ ደረቱ አጥፎ እንዳይንቀሳቀስ አደረገው። መቶ አለቃው እግዚአብሔር ይቀጣሃል ኢጣሊያ ታላቅ ናት አለው። ባህታ ሐጐስም ኢትዮጵያ የበለጠ ታላቅ ናት አለው።

ዲሰምበር 16 በሻለቃ ቶሰሊ የሚመራ ጦር በጀኔራል ባራቴሪ ትእዛዝ የመቶ አለቃ ሳንጉኒቲ ለማስለቀቅ ሣዕረብ ደረሰ። የባህታ ሐጐስ በአከለጉዛይ ከብዙ ጊዜ በጣሊያኖች ላይ የታቀደ አመጽ ሊከሽፍ የቻለው ሣዕረብ ላይ ሻለቃ ቶሰሊ በሸረበው ተንኰል ነበረ። ሻለቃ ቶሰሊ ካቶሊክና የኦርቶዶክስ ቄሶች ሽምጋዮች ወደ ሰገነይቲ እየተመላለሱ የታሰሩ ሰዎች ለማስፈታት አዲስ ተጨማሪ ወታደሮች እስኪመጡለት ድረስ እውቀ እንዲዓተት አደረገው። ሐላይ የሚገኘው ከሻምበል ካስቴላትሲ ከሚመራው ጦርም በቴሌፎን ግንኙነት ፈጠረ። በአጠቃላይ 1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ወታደር ሊሰበሰብ ችሏል። በ18 ሰገነይቲን ለመውረር ተወሰነ። አመጸኞቹ ግን አልተገኙም፤ ለቀው ሒደው ነበር። በማግስቱ ባህታ ሐጐስ ከ1600 የሚበልጡ ተዋጊዎች ይዞ ወደ ሐላይ አምርቶ በድንገት ደርሶ ሐላይ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮችን ትጥቅ ለማስፈታት አስቦ ነበር። ባህታ ሐጐስ ሐላይ እንደደረ ሰ ወታደሮቹ መሣሪያዎቻቸውን እንዲያስረክቡና በሰላም ወደኋላ እንዲመለሱ እንደሚ ፈቀድላቸው ጠይቆ ነበር። እሁንም የጦሩ አዛዥ ካስቴላትሲ ጊዜ ለመውሰድ በቄሶች ሽም ጋይነት ንግግር ተጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ተኩል ተጓተተ። በ7 ሰዓት ተኩል ባህታ ሐጐስ ሁለት መቶ የምሳ /250/ የነበረው በኢጣሊያ ጦር ላይ ተኩስ ከፈተ። እስከ 10 ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ ቀጥሎ ኢጣሊያኖች ከሰገነይቲ ወታደሮች እርዳታ ስለደረሱላቸው በ12 ሰዓት ጦርነቱ አልቆ የደጃዝማች ባልቻ ተዋጊዎች ተበታተኑ። ከጣሊያኖች የሞተ የለም። የሞቱትና የቆሰሉ የቀለም ወታደሮች ኢንዲጆኒ አስከር ብቻ ነበሩ፤ 11 የሞቱ 122 የቆሰሉ የተሸለሙ ግን ጣሊያኖች ብቻ ነበሩ። ጣሊያኖች ስለደጃዝማች ባህታ አስከሬንና ከዓማጺያን ስንት እንደሞቱ ያሉት ነገር የለም። ማንቴጋሳ (Mantegazza) እንደዘገበው ጦርነቱ ሲያልቅ 12 ሰዓት ነበር፤ ቀኑ ብሉ ጨለም ነበር ኃይለኛ ጉም እንደነበረ ብቻ ጽ ፍዋል። በጥቂት ቀናት ውስጥ የኢጣሊያኖች ትእዛዝ አክብረው 1200 ታጣቂዎች ጠብመን ጃቸውን አስረክበዋል። ለ300 ታማኝ ተብለው የተገመቱ መሣሪያዎቻቸው እንዲይዙ ተፈቀደ ላቸው።

ደጃዝማች ሰንጋል የባህታ ወንድም፤ የኩዓቲቱ ተወላጅ ፊታውራሪ ተስፉ ከ500 ታጣቂዎች ጋር ወደ እንጥሙ ራስ መንገሻ ጋር ሸሽተው ገቡ። ልጅ ገብረመድህን የባህታ ልጅ ሃምሳ የሚገመቱ ሰው አስከትሎ ጣከ ጉበቶ በሽፍትነት ተሰማርቷል። ስለደጃዝማች ባህታ አስከሬን የት እንደተቀበረ ጣሊያኖች በጽሁፋቸው ባይናገሩም የቀበረው ታማኝ



ጭፍራው የድግማው ተወላጅ ሰጳር ባሕር መሆኑን ከጊዜ በኋላ ጣሊያኖች ጥቆማ ደርሷቸው ችላ ብለውት ነበር። ከነጻነት በኋላ በእንግሊዝ አስተዳደር ዘመን ሰጳር ባህር ሲሞት ለሌላ ሰው ቦታውን አሳይቶ ስለነበረ ከተቀበረበት ተቆፍሮ ወጥቶ በክብር በሰገነይቲ እንደገና ሥር ዓተ ቀብር ተፈጽሟል።

በሐላይ በደጃዝማች ባህታ ላይ የደረሰው ሽንፈት በኃላፊነት የሚጠይቀው ራሱ ደጃዝ ማች ባህታ ነው። ሁለት ቀን ሰገነይቲ ላይ አንድ ቀን ሐላይ ላይ ጣሊያኖች በጠመዱት ወጥ መድ ውስጥ በመግባት በሃለተኛ ቄሶች ሽምጋይ መልዕክተኞች በመታለሉ ምክንያት ነው። ባሕታ ሐጐስ የካቶሊክ ሃይማኖት የተቀበለው በቅርብ ጊዜ ስለነበረ ለአዲሱ ሃይማኖት የነበረው ፍቅር ለሽንፈቱ ተጽእኖ እንደሚያመጣ ተፈጥራዊ ሕግ ነው። «ነዮፊት» የሆነ ሰው ሁሉ በአዲሱ ሃይማኖት ምክንያት እምነቱ ከመጠን በላይ አክራሪ ስለሚሆን በቄሶችና በሃይማኖት ላይ ያልተቆጠበ እምነት ስለሚያድርበት ተንኰለኞች የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች ቄሶችን እንደመሣሪያ በመጠቀማቸው ደጃዝማች ባህታን ሊያታልሉ ችለዋል። ይህ ባይሆን ኖር በመሠረቱም የቄሶች ሽምግልና ተንኰል መሆኑን ተረድቶ መቀበል አይገባውም ነበር። ከሆነም ከፍጥነት የተለመደው በሕዝቡ እምነት የተጣለበትም ጀግንነቱ አጣሩ እርምጃ ወ ስዶ ማሳየት ይጠበቅበት ነበር። ወደመጨረሻ ሰዓት ጣሊያኖች ራሳቸው አደገኛ ከሆነ ጀምሮ የመጨረሻ ወሳኝ ጥቃት ለመሰንዘር ጥይታቸው እስኪያልቅባቸው ይጠብቅ እንደነበረ ጽፍ ዋል። ሕዝቡ ጥሪውን ተቀብሉ ከእሱ ጉን ተሰልፎ ነበር። ጣሊያኖች በመሣሪያ ቢበልጡትም ብቱ የሰው ኃይል ነበረው፤ 1600 ሰው ለ250። ቄሶች ጊዜውን ባይገድሉበት ድሉ የእሱ ነበር። ቄሶች ግን ነፍሱን አድነው ይሆናል፤ ሥጋው ግን በጣሊያኖች ዘረኞች እንድትገደል አድርገዋታል። ይህ በመሆኑ ጣሊያኖችን ለማጥቃት ሌላ (Dogali) የዶጋሊ ዓይነት ሽንፈት እንዲቀምሱ ለማድረግ በራስ መንገሻ እና በአጼ ምኒልክ ተቀነባብሮ የነበረ እቅድ ሊከሽፍ ችሏል።



ራስ መንገሻ ከጠላት ጣሊያኖች ሳይቀር በኩንቲት ዓየው የጦር ታክቲክ አድናቆት ያገኙ፡፡

IL GEN. ORESTE BARATIERI.

# ሐ. ኰዓቲትና ሰንዓፈ

ጣሊያኖች ደጃዝማች ባህታ ሐጐስን መደምሰስ በመቻላቸው ራስ መንገሻ የደስታ መግለጫ ልኮላቸው ነበር። ሰላም እንደሚፈልግም ለመነጋገር አንድ ቄስ.ወደ ጀኔራል ባራቴሪ ልኮ ነበር። ጀኔራሉ ግን ኃይሉን ለማሳየት የራስ መንገሻ ዋናው ከተማ ዓድዋን ተቃውሞ ሳይገጥመው ያዘ። ከዚህ በኋላ ራስ መንገሻ ብዛት ያለው ጦር 15 ሺህ የሚገመት በመምራት ወደ አክለጉዛይ ኰዓቲት እያመራ መሆኑን ስላወቀ አስቀድሞ ለመድረስ ዓድዋን ለቆ በመውጣት ከዓድዋና ከሠራዬ ተነስቶ ኰዓቲትን ይዞ ጠበቀው። ጀኔራሉ «ጥርጣሬ የሞኝነት ነው፤ መዘግየት አደገኛ ነው፤ ትዕግስት የደካማ ምልክት ነው። የሚል መፈክር በመያዝ በጦር ሜዳ ለመፋለም ይናፍቀው የነበረ ምቹ ቀን አገኘ። ራስ መንገሻም ጣሊያኖችን እስከ ቀይ ባህር ድረስ በማባረር በሚል ዓላማ ነበረ ወደ ኰዓቲት ለጦርነት የቀረበው። የኰዓቲት ጦርነት ቀላል አልነበረም። ራስ መንገሻ ቢሸነፍም ከጣሊያኖች ሳይቀር በጦር ስልቱ ችሎታ አድናቆት ያገኘበት ወቅት ነበር።

ከጥቂት ወራት በፊት ለአጼ ምኒልክ «ንጉሥ ተብዬ ለምን አልጠራም?» ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ ለዚሁ ጦርነት ሊገፋፋው የሚችለው እንዴት እድርጌ ንጉሥ ሳድርግህ ሰፊ ግዛት ከሌለህ? ትልቅ ለመሆን ሞክር። እኔም ፍላጎትህን እሟላልሃለሁ ብሎት እንደነበረ ይነገራል።[1] ለጊዜው የነበረ የኤርትራ ሀገረ ገዢ ጉዳዩን ሰምቶ ደርቡሾችን ለመዋጋት ራስ መንገሻ ከተባበረ በጋላባት መሬት እንደሚሰጠው ሃሣብ አቅርቦለት እንደነበረ ይባላል። ጀኔራል ባራቴሪ የፊት አጥቂ ጦር፤ የግራ፤ የቀኝ፤ የመሐል፤ ተጠባባቂ ጦር በማለት መድቦ 4,000 ወታደር አሰልፎ ዝግጅቱን አጠናቆ ነበር። በሐላይ፤ በኰዓቲትና በሰንዓፈ ወሳኝ ሚና የተጫወተው የመድፈኛ ክፍል ኃላፊ የነበረው በኋላም ለብዙ ዓመታት በአዲስ አበባ የኢጣሊያ አምባሳደር ሆኖ ያገለገለው ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶ ወይም ወዳጅ ይዞ ወንዶች ፊት ከነሶች እኩል በድፕሎማቲክ ግብዣዎች ሳይቀር እንድትገኝ በማድረጉ ወቀሳና ትችት ከፈርዲናንዶ ማርቲኒ የደረሰበት ቺኮዲኮላ ነበረ።

ጀንዋሪ 13 ጧት በ11 ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ የጣሊያን ጦር ጠላትን ለማጥቃት እንቅስቃሴ ጀመረ። 12 ሰዓት የቺኮዲኮላ ተኩስ በመከፈት ጀመሩ። ሐበሾች ምንም ሳያስቡበት በድንገት ተኩስ ብንከፍትባቸውም በፍጥነት እየተወረወሩ በቡድን እየሆኑ ቁጥራቸው እየጨመረ ገደላማ ቦታዎችን በአስደናቂ የመንቀሳቀስ ችሎታቸው እያቋረጡ በመሐድ ቁጥራቸውም እንዳይታወቅባው እየተደበቁ ገደላማ ቦታዎች እንደጋሻ እየተጠቀሙ ዒላማ እንዳ ይሆኑ እየነቁ በየጊዜው እንዳይታዩ እየጠፉ ወደ ጎድጓዳ ቦታዎች እየገቡ ወደፊት ሲገሰግሱ ይታዩ ነበር። ውጊያው በጨበጣ ሳይቀር እየተፋፋመ እያለ በሰፈው ከበባ እየተሞከረ መሆኑን ከባንዳዎች ተነገረን። ከ3ኛ ባታሊዮን ጦር ከበባውን እንዲያከሽፉላቸው፤ ምክንያቱም በሥፍራው የነበሩ ባንዳዎች እያፈገፈጉ ይገኙ ነበር።ሆኖም የተላከ የሻለቃ ጋሊያኖ ጦር ጉዳት ደረሰበት።

1 Vivo Mantegazza:Ibd p.290



ምክንያቱም የጠላት ጦር የወገን በመምሰል አታሏቸው ተኩስ ካቆሙ በኋላ ከበረኟቸው። ነገር ግን ሌላ ጦር ስለተላከ የደረሰብን ሽንፈት በአነስተኛ ጉዳት ለመወጣት ተችሏል። የጋሊያኖ ኩባንያዎች ጉዳት ስለደረሰባቸው ቦታቸው ባዶ ስለሆነ መሐል የነበረው የሂዳልጎ ጦር በቦታቸው ተተካ፤ በዚህን ጊዜ የመቶ አለቃ ስካልፋሮቶ (Scalfarrotto) ዓረፈ። የጠላት የመከበብ ሙከራ አልተቋረጠም ነበር። ከበባውም ይመጣ የነበረው ከምስራቅ በኩል ስለነበረ በምዕራብ የነበረው ጦር ወደ ምሥራቅ እንዲዛወር አደረከሁ፤ መድፎችም ወደ ምሥራቅ እንዲዛወሩ ተደረገ፤ እኔም ቦታዬን ወደ ምሥራቅ ቀየርኩ። በዚህ ዓይነት ግን የሶስት ዒላማ ሆን። ሆኖም የእኛ ወታደሮች ለመመለስ ችለዋል። በዚሁ ጊዜ የመቶ አለቃ ሳንጉዊኒቲ የመቶ አለቃ ካስቴላትሲ (Castellazzi) እና ወታደር ቤርቶያ (Bertola) ዓረፉ፤ ቦታውን እየለቀቅን እና እያስለቀቅን ከበባውን እያከሸፍን እን ደገናም እየተሞከረብን ብዙ ጉዳት ከጠላት ላይ እያደረስን እኛም ጉዳት እየደረሰብን የግልና የቡድን ጀግንነት የታየበት ነበር። በዚሁ ጊዜም ከኰዓቲት ሰሜን ከፍተኛ ቦታዎች የሰፈረ የጠላት ብዛት የነበረው ተኩስ ደረሰብን፤ ግን አደገኛ አልነበረም። ጀንዋሪ 13 እና 14 ያለው ሌሊት ጠላት ቀን ያልቀናው ሌሊት በጨለማ ጥቃት ይሞክር ይሆናል ብለን ስጋት ነበረን፤ ሌሊቱ ግን ተኩስ ሳይሰማ አደርን፤ ጧት 14 ጠላት በኃይለኛ ተኩስ ጀመረ፤ ግን ከባድ ጉዳት አላደረሱብንም፤ በምሥራቅም በምዕራብም አቅጣጫዎች ተኩስ ቀጥለው ነበር። ጀኔራል ባራቴሪ ጦርነቱ እንዲያልቅ አይቸኩልም ነበር፤ የሚጠብቃቸውን ስንቅና ትጥቅ ነበረው። ጠላት ግን ቀኑ በተራዘመ ቁጥር እንደሚከፋው ግምት ነበረው። ስለዚህ ለጀኔዋሪ 13 ጠቅላላ የማጥቃት እርምጃ እንደሚወስድ ዕቅድ አዘጋጅቶ ነበረ፤ በ14 ማታ አንድ የኢጣሊያ አስከር እስረኛ ሆኖ የነበረ ለማምለጥ ስለቻለ ጠላት ወደ ኋላ ማፈግፈጉን ገለጸልን። ባራቴሪ በ9 ሰዓት ተኩል ከሌሊቱ የጦር አዛዦች ስብሰባ ጠርቶ ጠላትን በሄደበት ለመከታተል ተወሰነ። ከትትሉ ቀጥሎ ከቀኑ 7 ሰዓት ተኩል ትኩንዳዕ አጭር ዕረፍት ሆነ፤ ጉዞውም ቀጥሎ ጠላት ወዳለበት ሰንዓፈ ማታው ሳይጨልም ገባን፤ ሰንዓፈም ብዙ ድንኳኖች ተተክለው አየን፤ ድንኳኖቹ በሩቅ በመድፍ ተደበደቡ። በዚህ ጊዜ ጠላት ተደናግጦ መሸሽ ጀመረ። ማታ በጨለማ ጣልያኖች ሰንዓፈ መግባት አልደፈሩም፤ ሲነጋ ሰንዓፈ ሲገቡ ጣል ያኖች ብዙ ዕቃዎች አገኙ። ጠቃሚ የነበሩ ግን ተረስተው ሳይወሰዱ የቀሩ ከላይ የተጠቀሱ የደጃዝማች ባሕታ ሐጐስ፤ ራስ መንገሻና አጼ ምኒልክ የተጻጻፉባቸው ደብዳቤዎች ብቻ ነበረ የተገኙ።

በደብዳቤዎቹ መሠረት ደጃዝማች ባሕታና ራስ መንገሻ አመጽ ማስነሳት ያሰቡትና ራስ መንገሻ ሊደርስ የሚችለው በዲሴምበር 20 ነበረ[1] በጦር ነቱ የተካፈሉ የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት 3934 ነበረ፤ የሞቱት 3 የኢጣሊያ መኰንኖች 2 ወታደሮች 90 ኢንዲጂኒ /ኤርትራውያን/ ፤የቆሰሉት ሁለት የኢጣሊያ መኰንኖች 227 ኢንዲጂኒ /ኤርትራውያን/ ነበሩ። ሽልማቶች ለጥቂቶቹ ልዩ ሽልማቶችና የወርቅ ኒሻን፤ አዛዦች የወርቅ ኒሻን ለ69 ልዩ ልዩ ማዕረግ ላላቸው ጣልያኖች እና ለ19 ኢንዲጂኒ የብር ኒሻን ለ29 ጣሊያኖችና ለ179 ኢንዲጂኒ የነሐስ ኒሻን ተሰጥቷቸዋል።

1 .Vico Mantegazza: Ibd p.324

# አቆርደት እና ከሰላ በጣሊያኖች ተያዙ

## መ. አቆርደት፤[1]

ጣሊያኖች በደጋዓሊ ሽንፈት ከገጠማቸው በኋላ ወደ አፍሪካ ከገቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ድል ዓገኙ አቆርደትን ለመያዝ ዲሴምበር 1893 ዓ.ም በደርቡሾች ላይ ባካሄዱት ጦርነት ጊዜ ነው።

ድሉን የተቀዳጁት ራሳቸው ተዋግተው አልነበረም። የቅጥር ተዋጊ የቀለም ወታደር ወይም «አንዳጀኒ» እያሉ የተሰየየ ስም የሚሰጧቸው ለኤርትራውያን ወታደሮች ተጠቅመው ነው። ከዚሁ ዘመን ጀምሮ ለወደፊት ሀገራችንን ለቀው እስከወጡበት ጊዜ ድረስ አንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1933 ዓ.ም /1941/ ድረስ ጣሊያኖች የሚጠቀሙት እርስ በእርሳችን ስማጨራረስ ነው። ብቻቸውን ሆነው ጦርነት ገጥመው ድል ያገኙበት ጊዜ የለም።

ጣሊያኖች አቆርደትን ስመያዝ በመጀመሪያ ጊዜ ከደርቡሾች ጋር ግጭት ያደረጉት 1890 ዓ.ም ነው። ስድስት ወር ኤርትራ የሚል ስም ከተሰጠ በኋላ ነው። የተካፈሉት በአንድ ሻምበል ፋራ (Captain Fara) የሚመሩ 250 የኤርትራ አስከሮች ነበሩ። አንድ አስከርና ሁለት ቤኒዓመር ሲቪል ነዋሪዎች ተገድለዋል። በዚሁ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች 1ኛ. ሻምበሉ የሳቮያ የወታደር ኒሻን 2ኛ. ሶስት መቶ ለለቶች የብር ኒሻን 3ኛ. አንድ መቶ አሰታ እና ሁለት አምሳ አለቆች የነሐስ መዳይ ኒሻን። በዚሁ መሠረት የባርካ አውራጃ ኤርትራ ስትመሠረት ያስነበረ ቆይቶ ከኤርትራ በኃይል የተቀላቀ አውራጃ ነው።

ጁን 1892 ዓ.ም ሳራ ቤት ላይ በሻምበል ሂዳልጎና የመቶ አለቃ ስፐሪያፊኮ(Cap. Hidalgo Tenent Spreafico) የሚመሩ ወታደሮች ጦርነት ገጥመው 40 ደርቡሾች ተገድለዋል። ሶስተኛውና ዋነኛው የአቆርደት ጦርነት ዲሴምበር 21 ቀን 1893 ዓ.ም ተካሂዷል። ተካፋይ የነበሩት 42 የኢጣሊያ መኰንኖች 33 ተራ ወታደሮች 2106 ኤርትራውያን ነበሩ። የሞቱት ሶስት የኢጣሊያ መኰንኖች አንድ የኢጣሊያ ወታደር 104 ኤርትራውያን ነበሩ የቆሰሉት አንድ የኢጣሊያ መኰንን እና አንድ ወታደር 121 ኤርትራውያን ነበሩ። በኢ ጣሊያኖች ግምት 1000 ማሕዲስቶች ተገድለዋል። በዚሁ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች፤

1ኛ. ኰሎኔል አሪሞንዲ ሚጀር ጀኔራል ተብሎ ተሾሟል። 2ኛ. ባራ ቴሪ ጀኔራል ባልተካፈለበት ትልቁ የኢጣሊያ ኒሻን ትዱስ ማውሪሲዮ ተሸልመዋል። 3ኛ. ሌተናል ኰሎኔል ኮርቴዜ ትልቁ የወታደራዊ ኒሻን ሳቮያ 4ኛ. ለሁለት ሻምበሎች ለአምስት የመቶ አለቆች የኢጣሊያ የዘውድ ኒሻን 5ኛ. ለአንድ ሻምበል የወርቅ ኒሻን 6ኛ. የብር ኒሻን ለአሥር ሻምበሎች ለ 6 መቶ አለቆች ለ10 ባለ ሌላ ማዕረጎች። 7ኛ. የነሐስ ኒሻን ለሁለት ሻምበሎች ለ22 የመቶ አለቆች ለአሥራ ሶስት ባለ ሌላ ማዕረጎች ለሰባት «አንዳጀኒ» የሀገር ተወላጆች።

1. V. Mantegazza: Ibd p.145



በኢጣሊያ ፓርላማ የደስታ ንግግሮች ተደርገዋል። የኢጣሊያ ንጉሥ የዘመቻው አዛዥ ለነበረው ለኰሎኔል አሪሞንዲ የደስታ ቴሌግራም ልኳል። የድሉ ባለቤት የሆነው የኤርትራ ተዋጊ ግን የሞተው እና የቆሰለው ጣሊያኖች እንዲሾሙና እንዲሸለሙ ብቻ ነበር። የነሐስ ኒሻን ያገኙት ሰባት አንዳጀኒ ብቻ ነበሩ።

## ሠ. ከሰላ[1]

ራስ አሉላ ኩፊት በዘመተ ጊዜ በከሰላ አካባቢ የሚኖሩ ሀለንጋ እና ሐደንደዋ የተባሉ ጎሣዎች ዘራቸው ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ጸረ ማሕዲስቶች ስለነበሩ ራስ አሉላን አንደ ነጻ አውጭ ነበር የተቀበሉት። ጣልያኖች ከሰላን በተቆጣጠሩ ጊዜ ከላይ የተቀጠሱት ጉሣዎች ሌሉችም ከሱዳን ጋር ከመኖር ይልቅ ከኤርትራ ጋር መተዳደር ይመርጡ እንደነበር የገልጹላቸው እንደነበረ ገልጸዋል። ማንቴጋትሣ የተባለው ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ በደረሰው መጽሐፍ እንደገለጸው ራስ አሉላ ወደ ኩፊት ሲዘምት 10.000 /አሥር ሺህ/ ወታደሮች ነበረው አስማን ዲግማ 8,000 /ስምንት ሺህ/ ወታደሮች አሰልፎ ነበር። አስማን ዲግማ በአባቱ ቱርክ ሲሆን በእናቱ ግን ከሐደንደዋ ስለነበረ በከፊል ኢትዮጵያዊ ነው። ጦርነቱ ከባድ ነበር፤ ሆኖም ድሉ የኢትዮጵያውያን ሆነ፤ 3,000 /ሶስት ሺህ/ ደርቡሾች ተገደሉ፤ በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው የሰው ጉዳት ባይገለጽም፤ ጉዳቱ መጠነኛ እንደነበረ የሚያስረዳ ከኩፊት መልስ ብዙ ጊዜ ሳይቆዩ ነው ዶጋዓሊ በጣሊያኖች ላይ ድል የተገኘው። በጉጀም በኩልም ንጉሥ ተከለሃይማኖት 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ የሚገመቱ ወታደሮች በመምራት ገላባትን ከደርቡሾች ለማስለቀቅ በተደረገው ጦርነት ታላቅ ድል ተቀዳጅቶ ነበር። ነገር ግን ደርቡሾች ተጠናክረው መጥተው እንደገና ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር ጦርነት ገጥመው ቤተ ክርስትያኖች እያቃጠሉ ብዙ ሰው ስለፈጁ ጣሊያኖች ስመዋጋት ወደ ምዕዋ ተጉዞ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት አቅጣጫውን ለውጦ ወደ መተማ ለመምራት ተገደደ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ አንግሊዞችና ግብጾች ከማሕዲስች ለተሰነዘረባቸው ብዙ ጥቃቶች ሽንፈት ስለገጠማቸው ማንኛውም ጦርነት አቁመው በመደራደር ብቻ ይገኙ ነበረ። በዚህ ወቅት ነበረ የሱዳን መሪ ማሕዲ በእንግሊዞች፤ በግብጾች፤ እንዲሁም በንጉሥ ተክለሃይማኖት ባገኘው ድል ተዝናንቶ ሱዳንና ኢትዮጵያ ፀረ ኤርጳውያን ግንባር እንዲፈጠር ፈልጎ የነበረ። ይህ ስማድረግ ግን አጼ ዮሐንስ የእስልምና ሃይማኖት እንዲ ቀበል ሃሣብ ለአጼ ዮሐንስ አቀረበለት። አጼ ዮሐንስ ግን በተለመደ እቢታው ሣይቀበለው ቀረ። ራስ አሉላ ወደ ከሰላ ዘምቶ የተዋጋ፤ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ወደ ገለባት ዘምቶ የተዋጋ አጼ ዮሐንስም ወደ መተማ ዘምቶ ሲዋጋ የሞተው የሀገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር እንጂ የሰው ሀገርን ወር ለ መያዝ አልነበረም። ሙንዚንገር የተባለው ዜግነቱ ሱዊስ ሆኖ የምሥራቅ ሱዳን የቦጐስ እና በምፅዋ በግብጽ መንግሥት ስም ያስተዳደር የነበረ ሰው ነው። ፀረ ኢትዮጵያ አቋም የነበረው ሰው ነበረ።

1 V. Mantegazza: Ibd p. 203-247

ሆኖም ምሁርና ተመራማሪ ነበረ። ግዛቱ ስለነበረው ከቀይ ባሕር እስከ ዓባይ ያሉ ሕዝቦች ታሪክ አንድ መጽሐፍ ደርሰዋል። ይህ መጽሐፍ ጠቃሚነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው። ከመጽሐፉ ጋራ ተያይዞ የነበረ ማፕ በጣም ጠቃሚነት ስለነበረው የእንግሊዝ መንግሥትና የኢጣሊያ መንግሥት ስለ ቀይ ባሕር አካባቢ በሚካለሉበት ጊዜ ይጠቀስ የነበረ ማፕ ነው። በአጭሩ መጽሐፉ የሚያስረዳው ከመጽዋ ወደ ምዕራብ እስከ አባይ ወደ ሰሜን እስከ ግብጽ ያሉት ሕዝቦች ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ነው።

ከዚህ በታች ደራሲው የጻፈው ከጀርመን ወደ ጣሊያንኛ ተተርጉሞ ስላገኘሁት እኔም የጣልያንኛ ፎቶ ኮፒና በአማርኛ ትርጉም ከዚህ በታች የማቀርበው ሰንጠረዥ በሚገባ ያስረዳል። ኢትዮጵያ የሰው መሬት አትፈልግም የራስዋን ደግሞ አሣልፋ አትሰጥም የሚል አነጋገር በዜና ማሰራጫዎች ተደጋግሞ ሲነገር እንሰማለን። ነገር ግን ከሱዳን የከሰላ ክ/ሐገር ወይንም የምሥራቅ ሱዳን ክ/ሐገር የሚገኘው 500 ሺህ እስኩየር ኪሎ ሜትር ሕዝቡንና መሬቱን አሣልፈን ለሰው ሰጥተን የምንገኘው እንጡራ ሐብታችን ነው። ይህ መሬት ለአራት ዓመት በኤርትራ ውስጥ ኤርትራ ተብሎ እየተጠራ በጣሊያን ቅኝ ገዢነት ቁጥጥር ገብቶ ነበረ። የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ግን ከእንግሊዝ ጋር ተደራድረውበት ሀገሩን ለቀው ስለወጡ አሁን መሬቱ የሱዳን መሬት ሆኗል። ሕዝቡም በመቶ ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያውነቱን ረስቶ ዛሬ ሱዳናዊ፡ ዐረባ ተብሎ ይጠራል። ሕዝቡ ኢትዮጵያዊነቱን እንዲያስታውስ የኢትዮጵያዊ ሁሉ ኃላፊነት ነው።

የከሰላ ጦርነት ጁላይ 17/1894 ተካሂዷል። 56 የኢጣሊያ መኮንኖች 41 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 2526 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስድስት/ ኤርትራውያን የጦርነቱ ተካፋይ ሆነው ውለዋል። በጦርነቱ አንድ የኢጣሊያ መኮንን ሲሞት 25 ኤርትራውያን ተገድለዋል። እንዲሁም 40 ኤርትራውያን ቆስለዋል። ከጦርነቱ በኋላ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ለኢጣሊያን ንጉሥ የደስታ ቴሌግራም ልከዋል። የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር የጦር ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለጦሩ አዛዥ ቴሌግራም ልከዋል። በከሰላ አዲስ የተሠራ ጦር ሠፈር በባራቴሪ ስም ተሰይሟል። በጦርነቱ ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች 1ኛ. ለጀኔራል ባራቴሪ አንድ ወታደራዊ ሣቮያ ኒሻን 2ኛ. እንዲሁም ለጀኔራል አሪሞንዲ 3ኛ. ለሻለቃ ሂዳልጐ 4ኛ. በሻምበል እስፐራያሬኮ 5ኛ. ለሻምበል ሣልሣ የሻለቃ ማዕረግ አግኝቷል። 6ኛ. ሻለቃ ቱሪቶ የቅዱስ ሞሪሲዮ ላዛር ኒሻን፤ 7ኛ. የመቶ አለቃ ፓቮኒ የዚሁ ዓይነት ኒሻን 8ኛ. የወርቅ ኒሻን የተቀበለ ካርዲዮ ማላቮልቲ /ሻምበል/ 9ኛ. የብር ኒሻን አምስት ሻንበሎች ሁለት መቶ አለቆች አንድ ባለሌላ ማዕረግ አራት የቀለም ወታደሮች፤ 10ኛ. የነሐስ ኒሻን ያገኙ አንድ ሻምበል 11 መቶ አለቆች 1 ምክትል መቶ አለቃ 10 ባለሌላ ማዕረጎች 11 አስከሮች ኢንዲጀኒ ፤ 11ኛ. የምሥጋና ወረቀት የተቀበሉ 8 ሻምበሎች 19 መቶ አለቆች 21 ባለሌላ ማዕረጎች። ከጦርነቱ በኋላ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ለጣሊያን ንጉሥ የደስታ ቴሌግራም ልከዋል። የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር የጦር ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚ/ሮች ለጦር አዛዡ ቴሌግራም ልከዋል። በከሰላ አዲስ የተሠራ ጦር ሠፈር በባራቴሪ ስም ተሰይሟል። ከሰላ ከኤርትራ ጋር እንድትቀላቀል ደማቸውን ያፈሰሱ ኤርትራውያን



ሲሆኑ፤ ጣሊያን ግን እርስ በርሣቸው ተሿሹመውበት በመጨረሻ ሀገሩን ለቀው ወጥተዋል። ይሄ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የፈሰሰበት ከሰላ ጣሊያኖች ለአራት ዓመት እስከ 1897 ይዘውት ከቆዩ በኋላ ያለአንድ በቂ ምክንያት ሜይ 1897 ለእንግሊዝ መንግሥት አስረከበው የአካባቢው ሕዝብ በተለይ ሐለንጋና ሐደንደዋ የተባሉ ጐሣዎች ከኤርትራ ጋር ለመቀላቀል እንደሚፈልጉ እየገለጹላቸው ከሰላን ለቀው ወጥተዋል።

ጣሊያኖች ከከሰላ የወጡበት ምክንያት በወቅቱ በከሰላ ከዋና ጦር ሰፈራቸው ከምፅዋ ሩቅ በመሆንዋ ነው ብለው ቢናገሩም ሐቁ ግን የወጡበት ምክንያት የደርቡሾች ፍራት ነው። በአፍሪካ በመጥፎ ስም በጣም ተዋቂ ሰው የነበረው ጣሊያኖች በሐሣባቸው ስለሚስማማ በጣም ይወዱትና ያከብሩት የነበረው ጀርመናዊው ሰቫይንፉርት (Schweinfurt) ስለ ከሰላ በጣሊያን ወታደሮች መያዝ ከኢጣሊያ ጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ ተደርጐለት በሰጠው አስተያየት፤ የከሰላ በጣሊያን እጅ መውደቅ አስደሣችም ነው በጣም አስጊም ሊሆን ይችላል ብሎ ነበረ። ጠቅሎልም ሐሣቡም በማብራራት ደርቡሾች ተስፋ በመቁረጥ የመጨረሻ ዕድላቸው ከመሞከር የማይመለሱ ናቸው ብሎ ነበረ። በከሰላ መያዝ ከፍተኛ ንዴት ሊያድርባቸው ይችላል። በአውሪነት ፀባያቸው እየተመሩ ወሣኝ ትግል ለማድረግ እን ደሚሞክሩ ይጠበቃል። ከሰላን ከኢጣሊያ ለማስለቀቅ 50 ሺህ እስከ መቶ ሺህ ሰው ሆነው ሊመጡ ይችላሉ። በዚሁ ጊዜ በኤርትራ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮች ለአንድ ቀን እንኳን ተዋግተው የመቋቋም ኃይል አይኖ ራቸውም። አብዛኛው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ማሠለፍ ያስፈልግ ይሆናል። ኤርትራ በሙሉ እንዳትጠፋ ያሰጋል ብሎ ከደመደመ በኋላ ጠያቂው በዚህ ጊዜ ጣሊያኖች አደጋ በሚደርስባቸው ጊዜ ብሪታኒያ እርዳታ አትሰጣቸውም ወይ ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ ሰቫይንፉርት (Schweinfu..rt) መልስ ሲሰጥ አይመስለኝም፡ ብሪታኒያ ቀጥተኛ የራ ስዋ ጥቅም ከሌላት እርዳታ አትሰጥም፤ ስለዚህ ጣሊያኖች ከብሪታኒያ እርዳታ እናገኛለን ብለው መጠበቅ የለባቸውም ብሎ ነበረ። ይኼ የስቫይንፉርት (Schwe-infu: rt) አስተያየት ነው ለጣሊያኖች ሽብር ፈጥሮባቸው ከከሰላ ሊወጡ የቻሉት። የስቫይ ንፉርት (Schwe-infu·irt)አክራሪ ዘረኛ ጠባብ አስተሣሰብ የነበረው ሰው ነው፤ ጣሊያኖ ችን ከፍ አድርጎ ማቅረብ ይወዳል። እናንተ ጣሊያኖች ታማኝ የሆኑ ባለቀለም ወታደሮች ለመፍጠር ችላችኋል! እንግሊዞች፤ ፈረንሣዮች እኛም ጀርመኖች እንደ እናንተ ማድረግ አንችልም ብሎ ሐሣብ ሲያቀርብ ጣሊያኖች ሣያመዛዝኑ ሐሣቡን በመቀበላቸው በብዙ ስህተት ሊወድቁ ችለዋል። ዘረኛው ጀርመናዊ ስቫይንትፉርት (Schweinfu ·rt) ወደ አፍሪካ ይሄደው ሀገሩ ጀርመን በአፍሪካ በሰፊው የቅኝ ግዛት ለማስፋፋት እንድትችል ነው።

ይህን ለማድረግ ግን ከሌሎች ሀገሮች ስለተቀደሙች እነሱን ማጥላላት ነበረባት። ጣሊያንም የጀርመን ፈለግ እንድትከተል ስቫይንፉርት ምኞቱ እንደነበረ ግልጽ ነው ስቫይንፉርት በአጭር አስተሳሰቡ የአፍሪካ ጎሣዎች አጥንቶ ይሆናል የወታደር ሙያ ግን ያለው ሰው አይደለም። ሌሎች ሰዎች በትምህርትና ሙያ አስትርሬቴጂ በመመርኩዝ ኤርትራን ከግሕዲሶች ወረ ራ ለመከላከል ከሰላን መልቀቅ ሳይሆን ከሰላን ይዞ ማጠናከር

ነው ብሏል። ከሰላን እስከ አትባራ ያለው መሬት መቆጣጠር ከተቻለ የግብጽ ሊቆች ወረራ እንዲያከትም ማድረግ ይቻል ነበር። ከዚህ ከተለቀቀቸው ግን ለወረራ መንገድ በመክፈት ምቹ እንዲሆንላቸው ብለው የሚፈልጉትን በመስጠት የሰሜይንተርት አስተያየት የተቃወሙ ነበሩ። ከሞንት ከእነ ዊርዊርላ የጀርመን ንጉሥ ነገሥት ጀምሮ ጀርመኖችና ጣሊያኖች መሬታቸር ነበራቸው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጀርመኖች የዘረኞች ቁንጮ ሳይሆኑ እንደ ሌሎች ባርባሪያን ሁሉ የስልጣኔ ሰው በነበራቸው ጊዜ ባርባሪያን ንጉሥ መሆን እንደማይችል የሚል እምነት ስለነበረቸው ጀርመናዊ መንግሥት ተብለው መጠራት ትተው ሮማዊ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ይጠሩ ነበር። የጀርመን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሆሊ ሮማን ኢንፓየር (Holy Roman Empire) እተባለ ይጠራ ነበር። ትልቁ የኢጣሊያ ቁንጽ አባት ዳንቴ አሊጌሪ ለእነ ባርባርላ ይገዙምላቸው ነበር። ጀርመኖችም በሮማውያን ላይ እንደ አምልኮት እምነት ነበራቸው ጣሊያኖችም በጀርመኖች ላይ እንደ አምልኮት እምነት ነበራቸው። በዚሁ መልኩ ነው ጣሊያኖች ለሻይንፉርት የተናገሩትን ሰምተው የሚያፋፍር ሽሽት ከከሰላ የወጡ። ስሻይንፉርት ስለ አንዳንድ የአፍሪካ ጎሣዎች ስም ዝርዝር ያውቅ ይሆናል እውቀቱ ግን የአንድ ጀርመናዊ ዘረኛ ሰው ከመሆን እያልፍም የወታደራዊ ሞያ ዕውቀት አልነበረውም።

ዛሬ ከአንድ መቶ አመት በላይ በኋላ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በአፍሪካ ከጣሊያኖች በጣም የተሻለ አመራር ይከተሉ እንደነበረ ለሻይንፉርት እና ለጣሊያኖች ማስረጃ ሊሆንዋቸው በተገባ ነበረ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ቢችሉ የቀድሞ ተግባራቸው ቢተገሉ ደስ ባላቸው ነበር። ዛሬ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በአፍሪካ በቀድሞው ቅኝ ግዛቶቻቸው ወዳጅ የሆነ ሕዝብና መንግሥታት አሏቸው እንጂ ታማኝ ሕዝቦች የላቸውም። ጣሊያኖችና ጀርመኖች ግን በዘረኝነታቸው ሆነ ታማኝ ሕዝብ ወይም ሀገር ሊያፈሩ አልቻሉም።

# ትግራይ ተወረረ

## ረ. የኢጣሊያ በራሪ ጦር፣ የደብረዓይላ ውጊያ[1]

የኩፃቲት ጦርነት ፍጻሜ ምክንያት በማድረግ የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ለባራቲሪ በላከው የደስታ ቴሌግራም ከእንግዲህ ትግራይ ለኢጣሊያ ክፍት ሆናለች፣ ካለያዝናት የኛ ስንፍና ይሆናል ብሎ ነበረ። ምናልባት በነዚህ ቃላቶች ተደፋፍሮው ጀኔራል ባራቲሪ ራስ መንገሻን ለመያዝ ያደረገው ድካም ከንቱ ስለሆነበት ትግራይን ለመውረር የተጀመረው፣ የጠብ አጫሪነት ነበር። ማርች 18/1895 ባራቲሪ ትጥቅህን ፍታ ብሎ ትእዛዝ ለራስ መንገሻ ይልክለታል «ኡልቲማቱም»። ነገር ግን ራስ መንገሻ በባስ ሁኔታ የጣሊያንን እንቅስቃሴ ያሰናከል ስለነበረ ጀኔራል ባራቲየሪ መንግሥትን አስፈቅዶ በኩፃቲት ባገኘው ድል የማይበገር መስሎት በእብሪት ተነሳስቶ ራስ መንገሻን ተከታትለው ለመያዝ ወሰኖ በይፋ ማርች 25 ወሰንን ጥሶ በመግባት ዓዲግራትን ያዘ።

1 V. Mantegazza:ibd p. 353



በራሪ ጦር ወይንም ተወርዋሪ ጦር የተባለው መንገድ ጠራጊ እስከ መቀሌ አስማራ። ጣሊያኖች ወደ አፍሪካ ሲገቡ ያገር ተወላጆች ወታደሮች በወገናቸው ላይ አይዋጉም ወይንም ደግሞ ፈሪዎች ናቸው በማለት ለውትድርና ብቁ አይደሉም የሚል እምነት ነበራቸው። በአቁርዳት፣ በከሰላ፣ በሐላይ፣ ከኩፃቲት ከተደረጉ ጦርነቶች ኋላ ግን በተቃራኒ ነጭ ሰው በአፍሪካ ለውትድርና ብቁ አይደለም የሚል እምነት ሊያድርባቸው ችሏል። ስለዚህ አብዛኛው ጦርነቶች የሚካሄዱት ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው በማጋጨት ብቻ ነበር። ጠላትም ከጀርባው እናጠቃዋለን ብለው ጣሊያኖች በሻለቃ ቶሰሊ የሚመራ ተወርዋሪ ጦር አራተኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ተብሉ የሚጠራው ወደፊት እየገሰገሰ ራስ መንገሻን በታውን እየለዋወጠ የሚሰፍርባቸው ቦታዎች ሊከታተል ከቆየ በኋላ በስተጀርባው የተባለው ቦታ የደረሰ መሆኑን ለጀኔራል ባራቲሪ አስታውቋል። ራስ መንገሻም ይገኝ የነበረው በደብረ ዓይላ ነበረ። ራስ መንገሻም የበታች ሹማምንቶቹ እንዲከላከሉ በመተው ወደ ያልታወቀ ቦታ ሸሽቶ ሄደ። ጣሊያኖች ደብረ ዓይላ ከነበረው የኢትዮጵያ ጦር ጦርነት ገጠሙ። በጦርነቱ ማብቂያ ጊዜ የኢጣልያ ወገን አስራ አንድ ኢንዲጂኒ ኤርትራውያን ሞቱ፣ 30 ቆሰሉ፣ ከጣሊያኖች የሞተ አልነበረም። ጣሊያኖች ራስ መንገሻ ወደ ሳምሬ ሄዷል ስለተባለ መከታተላቸውን አቁመው ወደ አምባላጌ አመሩ።

በደብረ ዓይላ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ሽልማቶች። አዛዥ ለነበረው ለሻለቃ ኤሚሊዮ የብር ኒሻን እንዲሁም ለሶስት ሻምበሎች ለሶስት መቶ አለቆች ለአንድ ተራ ወታደር ለሁለት ማዕረግ ያላቸው ኢንዲጀኖች የብር ኒሻል። የነሐስ ኒሻል የተሰጣቸው 13 መቶ አለቆች 6 ባለ ሌላ ማዕረግ ጣሊያኖች እንዲሁም 15 ማዕረግ ያላቸው ኢንዲጀኖች ነበሩ።

ከኩፃቲት ጦርነት በኋላ በቀለም ወታደሮች «በኢንዲጅኒ» ብቻ ተጠቅመው ጣሊያኖች ድል በመቀዳጀታቸው የኢጣሊያ መንግሥት በጣም ስላስደሰተውና ስለጣፈጠው የጦር ሚኒስትሩ ሞቼኒ (Mocceni) ለጀኔራል ባራቴሪ በላከው ቴሌግራም ቢያንስ እስከ 2000 /ሁለት ሺህ / «የኢንዲጀኒ» ወታደሮች እንዲመለመሉ ጀንዋሪ 17 ሐሣብ አቅርቦ ነበር።[1]

በደብረ ዓይላ የተዋጉ ኢትዮጵያውያን በበታች ሹሞች የሚመሩ ነበሩ። 1ኛ. የጎጋሜው ተሰፋይ ዕንግሉ 250 ጠብመንጃዎች 2ኛ. ሌሎች ሁለት ሹሞች 600 ጠብመንጃዎች 3ኛ. ቀኛዝማች ኃይለማርያም 400 ጠብመ ንጃዎች 4ኛ. አዝማች አብርሃ በጎንሰባ የመቶ አለቃ ቤቲኒ የገደለ 50 ጠብመንጃዎች 5ኛ. ደጃዝማች ዘገየ አባንብሩ የደበበ ወንድም ነበሩ። ቁስለኛ ሆነው ከታሰሩ ቀኛዝማች ኃይለማርያም እና የአክለጉዛይ ተወላጅ ሽፍታ ቀኛዝማች ስብሐት ይገኙባቸው ነበር።[2]

1 Vico Mantegazza:ibd p. 315

2 Vico Mantegazza:ibd p. 391

# ሰ/ የአምባአላጄ እልቂት

ጣሊያኖች በነበራቸው አስተሳሰብ ራስ መንገሻ በኲዓቲት በመሸነፉ ጦሩ ተበታትኖ ሥልጣን አልባ በመሆኑ እሱንም ተከታትሎ ለመያዝ የኢጣሊያ ጦር በራሪ ኃይል በመመደብ



ትምክህተኛው ሻለቃ ቶሰሊ ያለ አቅሙ በአምባ አለጄ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋራ ጦርነት ገጥሞ በከንቱ ሰው ያስጨረሰ፡፡

Ras Maconnen.

Maggiore Pietro Toselli.

የሚቋቋመው ኃይል ሊገኝ ባለመቻሉ፤ በራስ መንገሻ ሥር የነበሩ መሬቶች ሁሉ ከኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ከኤርትራ የተቀላቀሉ መሆናቸውን ወሰነዋል። የሸዋ ቤተ መንግሥትም በበኩሉ ራስ መንገሻ ያስተለት ሰው ስለሆነ፤ ሸዋ ለራስ መንገሻ ሲል ጦርነት እንደማያስነሳ ስለሚገመት፤ በሻምበል ፐርሲኮ የሚመራ አንድ በራሪ ጦር ከአምባአላጄ አልፎ እስከ በላኩ ደርሶ ነበር። ከዚህም ሌላ የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች በተሰጣቸው ኒሻኖች በእብሪት ተወጥረው ስለነበር በሌላ ርካሽ የሰው ነፍስ ትክሻ የበለጠ ክብርና ዝና ለማትረፍ ጉጉት ነበራቸው። አንድ ፈረንሳዊ ላዘሪስት ቄስ የኢጣሊያኖችን ሃሣብ በማወቁ ከሐሳይና ኲዓቲት ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ለዛሪስቶች የፈረንሣይ ሚስዮናውያን እየወረሱ ያባርሯቸው ስለነበረ በአንድ ኢጣሊያ ከፍተኛ የጦር መኰንን ግፍና አድራጎት ተናዶ (Ah! c'est la guerre que vous voulez? Eh bien vous l'aurez) ብሎ በመናገሩ[1] ወቀሳ ስለደረሰበት ይቅርታ ለመጠየቅ ተገዶ ነበር። ትርጉሙም እናንተ ጦርነት አይደለም የምትፈልጉት? ታገኙታላችሁ ማለት ነው። ሐቅ ነው የተናገረ ሐሰት አልተናገረም ጣሊያኖች ወደ አምባ አላጂ፤ መቀሌና አድዋ ጦርነቶች እያመሩ ነበሩ፤ ቄሱ የተናገረው እንደ ትንቢት ነበረ፤ ቄስ ስለሆነ ግን ይቅርታ እንዲጠይቅ አደረጉት። ፈረንሳዮች ሲባረሩ በአባ ሚኬኤሌ ዳ ካርቦናራ የሚመሩ ትምህርት አልባ የሆኑ የኢጣሊያ ተወላጅ የሆኑ ካፑቺኖች ለኢጣሊያ ታማኝ የሆኑ፤ ኢጣሊያ ድል ባገኘች ጊዜ የቤተክርስቲያኖች ደወል የሚደውሉ፤

1. Vico Mantegazza:ibd p.356





*Padre Michele da Carbonara,*

Controbattè l'azione dei Lazzaristi francesi che hanno sempre favorito gli Abissini

ዝነኛው አባ ሚከለ ዳ ካርቦናራ እና ረዳቶቻቸው ላዘሪስት የፈረንሣይ ሚሲዮናውያንን የተኩ፡፡



ከድል የሚመለሱ ወይም ወደ ጦርነት የሚሔዱ የኢጣሊያ ወታደሮች ቡራኬ የሚሰጡ ተተከሉ። ጣሊያኖች ምኒልክ ለጦርነት ተዘጋጅቶ እንደነበረና ብዛት ያለው ጦር በመምራት ወደ ትግራይ እየመራ መሆኑን ይወራ የነበረ ዜና የሚያስጋቸው እንደነበረ ሊገምቱ አልቻሉም። የአምባአላጂ ጦርነት አስፈላጊ አልነበረም። ጣሊያኖች በአብሪት ተወጥረው ስለነበረ ጣታደራዊ አትግቸውን ሊገምቱ አልቻሉም።

ኖቬምበር 30 አሪሞንዲ ለቶሴሊ ስለጠቅላይ አዛዡ ዓላማ ሊያስረዳው ለማጥቃት አስፈላጊ ባይሆንም ጠላት ወደፊት ከገፋ ግን መቋቋም እንደሚያስፈልግ ገልጾለታል።[1] ዲሴምበር 2 ሻለቃ ቶሴሊ ከራስ መኰንን የሰላም ንግግር እንዲያደረግ ቢጠይቅም፤ አክሉ ግን ለጦርነት የመጣ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሰዋል። ቶሴሊም ወዲያውኑ አንተ እያለ መልስ ሲሰጥ «ሰላም የምትፈልግ ከሆነ ወደፊት መግፋት የለብህም» የሚል መልስ ይልክለታል። ሻለቃ ቶሴሊ ከመቀሌ ወደ አምባአላጂ የተንቀሳቀሰው ኖቬምበር 25 ቀን ነበር የሔደበትም ዓላማ ጠላት ፍለጋ ወይም ደግሞ ከጠላት ጋር ጦርነት ለመግጠም ሳይሆን የእንዳመሆኒ እና አካባቢ ሕዝብ ለመረጋጋት እና ቀደም ብሎ አምባአላጂ ይገኝ ለነበረ ለሻምበል ፐርሲኮ ጦር እገዛ ለማድረግ ነበር። ኖቬምበር 26 አምባአላጂ ደረሰ። በ27 ወደ በላጉ ለምርቶ የኢትዮጵያ ጦር ወደፊት እየገፋ መሆኑን ማስረጃ አገኘ። በ28 ይኸንኑ የሚያረጋግጡ ሌሎች ማስረጃዎች አገኙ። በዚሁ ዕለት ጣሊያኖች ከበላጉ ወደ አምባአላጂ ተመለሱ። ከ29 እስከ ዲሴምበር 5 ለአንድ ሳምንት ምንም አዲስ ነገር አልተለፈጠረም። በዚሁ ጊዜ ሻለቃው ለመከላከያ ብቻ ያስብ ነበር። አምባአላጂም በጠላት እንደማትወረር እርግጠኛ በመሆን ግምት ነበረው። ተጨማሪ ጦርም አሪሞዲ እንደሚልክለት ተስፋ ነበረው። ዲሴምበር 5 ሻለቃ ቶሴሊ ድፍረት የተሞላበት ፍተሻ ለማድረግ በሉታና ተካ ማርያም የተባሉ ተራራዎች ጠላት ሰፍሮባቸው እንደሆነ ለማወቅ ሔዶ በጠላት ጦር እንዳልተያዙ አረጋግጦ ተመለሰ። በኢትዮጵያ በኩል የኃይል ሚዛን በሚገባ የሚያውቁ ከመሆኑም በላይ ኢጣሊያ በአምባአላጂ የነበራት ጦር ዝርዝር ማስረጃ ስለነበራቸው የሻለቃ ቶሴሊ ከባድ ድፍረት እያስገረማቸው ነበር ዲሴምበር 6 ቶሴሊ በጦርነቱ ዝግጅት በማድረግ ብቻ አሳለፈው። ዲሴምበር 7፤ 12 ሰዓት ተኩል ከኢትዮጵያ በኩል ተኩስ ተጀመረ። ብዙ ሳይቆዩ ጣሊያኖች አንድ መቶ አለቃ እግሩ ላይ ቆሰለባቸው፤ ወደ አቅራቢያ ቤተ ክርስቲያን ተወሰዶ በ3 ሰዓት የግራ ጦር ግንባራ ቸው ማፈግፈግ ግድ ሆነበት። በ4 ሰዓት የቀኝ ጦር ግንባራቸው በራስ መንገሻና በራስ አሉላ ጥቃት ደረሰበት፤ በ5 ሰዓት ገደማ አጠቃላይ መሸሽ ጀመሩ። የመሸሹ[2] ሁኔታ በአጣዳፊ፤ አሳፋሪ፤ አሰቃቂ ሁኔታ ነበር። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ዲሴምበር 3 ራስ መኰንን ስለ ሰላም ለመ ነጋገር በመጠየቅ ለጀኔራል ባራቲሪ ደብዳቤ ልኮ ነበር።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. 227

2 Vico Mantegazza:Ibd p.435-439



ጣሊያኖች ግን በግ ፌዝ በጣሊያንና ኢትዮጵያ በጦርነት ፍልሚያ ስለማይገኙ ስለሰላም ንግግር ማድረግ አጼ ምኒልክ ስለቶየ አስመጉባብት ለመነጋገር እሰፁ ካልሆነ በስተቀር ለመንገሻ[1] ብሉ ጦርነት አይገጥምም ብለው በመገመት ትኩረት ሳይሰጡት ቀሩ። ከሞት የተረፉት አንዱ የሆነው የመቶ አለቃ ፓጄላ (Pagella) ሲያወራ ከቶሴሊ ጋር ሆኖ በሚሸሹበት[2] ጊዜ በነበረው ትርምስ ሁለቱም ተጠፋፉ። በዚሁ ጊዜ በሚሸሹበት ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ከባድ እልቂት ደረሰበት። ሻለቃ ቶሴሊም ይከታተሉት በነበሩት ኢትዮጵያውያን ተገድለው ይሆናል ብሉ ገምቷል። አምባአላጂ ላይ ጣሊያኖች ጦርነት የገጠሙት ከ60,000 /ስልሳ ሺህ /የኢትዮጵያ ወታደሮች ጋራ ሲሆን እንደ ዶጋሊ (Dogali) ክብር አልተሰጠውም ካለ በኋላ የአምባአላጂ ተዋጊዎች ጥፋታቸውን በመስመር ሆነው ስላልሞቱ ነው ወይ? በማለት በግፌዝ ጽፈዋል።

ከኢትዮጵያ ወገን የተገኘው ሌላ ዜና የኢጣሊያኖቹ አስከሬኖች አንስተው ከቀበሩት አንድ ባለስልጣን እንዳረጋገጠው ጣሊያኖቹ በሙሉ ራቁታቸውን ነበሩ፤ ልብሶቻቸውን የተወሰዱባቸው ከራሳቸው ኢንዲጆኒ ወታደሮቻቸው ነበር ብሏል። ሻለቃ ቶሴሊ ራቁቱን ነበር፤ የእጅ ጓንት ግን ነበረው። ቶሴሊ የቆሰለው በአንድ ጥይት ደረቱን በስቶ የወጣ ነበር፤ በጎራዴም ቀኝ ጉንጩ ላይ ቆስሏል፤ ግራ እንገቱ ላይ እንደገና በጎራዴ ቆስሏል፤ በሌላ ክፍል ገላውም በሻንጃ ቆስሉ ነበር። ከሻለቃው አስከሬን ዙሪያ 13 የኢጣሊያ ወታደሮች አስከሬኖች ወድቀው ይገኙ ነበረ። 14 ጣሊያኖች ከውጊያ ቦታቸው ሸሽተው ወጥተው በአንድ ቦታ ተገኝተው ሲሞቱ የዶጋሊው የሻለቃ ታንቱሪ ዓይነት የጽሑፍ ገለጻ የሚመሳሰል ነው። ተዋጊዎቻቸውን አስጨርሰው ራሳቸው ብቻ አንድ ላይ ሆነው ከሞት ለማምለጥ ሲሞክሩ ሞተው መገኘታቸው ከዶጋሊ የባለ በመስመር ተሰልፈው እንደሞቱ ይቆጠራል። ከጦርነቱ በኋላ የሻምበል ታንቱሪ ዓይነት ወደ ሥፍራው ተልኩ ቢሆን ኖሮ በጦርነቱ ተካፋይ ከነበሩት ጣሊያኖቹ ግማሾቹ በአንድ ቦታ በውጊያ ቦታ ሳይሆን በመሸሽ ላይ እንዳሉ በደረሱበት ቦታ ሲያገኛቸው ከዶጋሊ ያላነሱ ታላቶች ጽፎ ለታሪክ ያስቀር ነበር። ስለዚህ በአምባአላጂም እንደ ዶጋሊ ከጣሊያኖች ግማሽ በመስመር ሆነው ሲሞቱ ሁለት የተማረኩ፤ ሶስት ሸሽተው ያመለጡ ናቸው። 13 የተባለም በስህተት ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ከሻለቃ ጋር የተቀበሩት ጣሊያኖች ከሻለቃው ጭምር 14 ሳይሆን 20 ነበሩ ፤ በጦርነቱ የተካፈሉ ጣሊያኖች 30 አማይደርሱ እንደነበረ ሲታወስ አንድ ላይ ያልተቀበሩ ቢኖሩ ከሶስት ወይም ሁለት አይበልጡም። የአምባአላጂ እልቂት እንደ'ት እንደ ዶጋሊ ክብር አልተሰጠውም የሚለው ጥያቄ ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ በአምባአላጂ የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች ከ30 አይበልጡም በዶጋሊ የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች 500 ነበሩ። በዶጋሊ ጣልያኖች በቀለም ወታደሮች ኢንዲጆኒ አልተጠቀሙም ጥቂት የነበሩ አልቆሰሉም አልሞቱም። በአምባአላጂ ግን ከተካፈሉት 2450 ወታደሮች 2420 «ኢንዲጆኒ» ነበሩ ከእነሱ ውስጥም 2000 የመቁሰልና የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል።

1. Vico Mantegazza:Ibd p.420

2. Vico Mantegazza:Ibd p.434

300 በደህና የተመለሱ ሊሆኑ የቀሩት 120 የት እንደደረሱ አይታወቅም። ጣሊያኖች ግን ያሳዘናቸውና የተጨነቁበት ስለራሳቸው ዜጋ የሆኑ የሞቱ ከ25 የማይበልጡ ብቻ ነበር። ስለኢንዲጀኒ የሞቱና የቆሰሉ ግን እንኳን ሊያዝኑላቸው ሰው እንደሞተ አልመሰላቸውም። ሻለቃ ቶሰሊ ጣሊያኖች ብሔራዊ ጀግና በኢጣሊያ ሕዝብ ከፍተኛ ዝና ያተረፈ በኢትዮጵያውያንም ከፍተኛ ክብር የተሰጠው እንጎሉ ከፍት የሆነው የማደራጀት ችሎታ ያለው፤ ብስለት ያለው ወዘተ ያልተባለለት ነገር የለም። ሐቁ ግን ተቃራኒ ነው ጨዋኝ ቅኝ ገዢዎች ከሚባሉ ጣሊያኖች አን ዱ ነው። 1ኛ. ከመቀሌ ወደ አምባአላጂ በተነሳበት ዕለት አንድ ከሐዲ የሚለው ኢትዮጵያዊ በሜዳው ፈጣን ፍ/ቤት ችሎት አደረኩ ብሎ ወዲያውኑ ተረሽኖ እንዲገደል ፈረደበት። 2ኛ. ራስ መኮንን በተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ ቢያደርጉለት እሩቁ ያለው ብዛት ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት በዕብሪት ተነሳስቶ ጦርነት መግጠም በመድፈሩ በሺህ የሚቆጠሩ የንፁህን ደም ማስጨረሱ ወንጀለኛ ነው። 3ኛ. ታማኝ የነበ፣ አስተርጓሚው የአዘጋ ተወላጅ የሰጠው አስተያየት ስለቶሰሊ ያለው አድናቆት ቢገልጽ ወደ ዋና ጉዳዩ ሲገባ «ትንሽ ተኩስ አንለዋወጥ ነበርን። ራስ መኮንንም የኢትዮጵያ ጦ ዋና አዛዥ እንደልማዱ ደብዳቤዎች ይጽፍ ነበር። ሻለቃም መልስ ይሰጥ ነበር። ራስ መኮን አምባአላጂ የንጉሡ መሬት ስለሆነ እንድትለቅ ብሎ ሲጽፍለት ሻለቃም እኔ ወታደር ነኝ ወደኋላ መመለስ አልችልም አንተ መጀመሪያ ተመለስ በኋላም እኔ ወደ ኋላ እመለሳለሁ»። በዚሁ ጊዜ ሁለቱ ንጉሦች ነገሩን በሰላም ይፈቱታል። የተያዙ ቦታዎች አይለቀቁም በጠላት ፊትም ወደ ኋላ መመለስ አያስፈልግም[1] ብሎ መልስ ሰጥቷል። ራስ መኮንን ብቻ ሳይሆን አጼ ምኒልክም ሰላም ፈላጊ እንደነበረ ጣሊያኖች ራሳቸው የመሰከሩት ነው።[2] 4ኛ. ቶሰሊ የጦር ስልት አዋቂ ቢሆን ኖሮ ለማሸነፍ ባይችልም በነበረው የጦር መሣሪያ የበላይነት እስከ ማታ ለመከላከል ቢችል ሌሊት በሽሽት ሳይሆን በስነ ስርዓት ወደ መቀሌ ስመመለስ ይችል ነበር። ሻለቃ ቶሰሊ ግን ጥቂት እንደተዋጋ ወደ ሽሽት ነው ያሰበው። አሸናፊ ጦርም በሁኔታው ተቀጥሞ እያሳደደ ሊጨርሳቸው ችሎዋል። ተጠባባቂ ሆኖ ተመድቦ የነበረ በመቶ አለቃ (Ricci) ሪቺ የሚመራው የአስከሮች ኢንዲጀኒ ጦር ወደ ፊት ወደ ውጊያ ገብቶ እንዲዋጋ ያደረገው በ3 ሰዓት ነበረ፤ 2 ሰዓት ጦርነቱ እንደተጀመረ። የመቶ አለቃውም በጦር ሜዳ ራሱ ሞተ፤ ከነበሩት መቶው /100/ ወታደሮቹም አምስት ብቻ በሕይወት ተረፉ[3] 5ኛ. በማታ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ቶሰሊ ባስተላለፈው ቴሌግራም ብዙ ብዙ ናቸው የሚያነዱት እንጨት እስከ እድማስ ይታየኛል። በሶስት አቅጣጫዎች የተሰለፉ ሌሎች የሚነዱ እንጨቶች የተየዘበራረቁ ሆኖ ይታያሉ የሚል ነ በረ። በዚሁ ጊዜ በኢጣሊያ ሀገር ግን የትኝ ግዛታቸው ኤርትራ ያንጃበባት የጦርነት አደጋ ዜና ሳይሰማ ሙሉ በሙሉ ሰላም የሰፈረነበት አድርገው ያሳ ዩ የነበረ ይህ ሁሉ እያወቀ ጦርነተ መግጠሙ የብዙ ሰው ሕይወት ለከንቱ ለሞት የዳረገ ወንጀለኛ ይባላል እንጂ ጀግና ሊባል አይችልም።

1 F.I.C.I : Ibd p.157

2 Vico Mantegazza: Ibd p.337

3 Vico Mantegazza: Ibd p.438



6ኛ. ጣሊያኖች ኢንዲጀኒ እንዲሞቱላቸው የሚፈልጓቸው ወታደሮች ነፍሳቸው እንጎ ላቸው የአንድ ሕፃን ነው እያሉ ሲያፌዙባቸው ይታዩ ነበር። 7ኛ. በአምባአላጂ የሞቱና የቆሰሱ የሰው ቁጥር የተሰያዩ ሰዎች የቀረቡ የተለያዩ ናቸው። ፍቺ እንዳቀረበው[1] እንደሚ ከተለው ነው። ከሞት የተረፉ ሰስት የኢጣሊያ መኮንኖች አንድ የተማረከ፤ ከኢንዲጀኒ ተዋጊዎች የሞቱና የቆሰሉ ሁለት ሺህ ነበሩ። በጦርነት ተካፋይ የነበረ የቶሰሊ ጦር በአጠቃላይ ሁለት ሺህ አራት መቶ አምሳ ነበረ።

## ቀ. የመቀሌ ከበባ

ጣሊያኖች የመቀሌ ምሽግ የሰሩሩት በታሪካዊ መቃብር ቦታ አራት ማዕዘናት የነበሩ ው ጥንታውያን ታሪካዊ መቃብሮችን እየቆፈሩ አጥንቶችን እያወጡ ነበር። የመቀሌ ምሽግ ዳይሰቀቅ የተደረገው የኢጣሊያ የባላይ መኮንኖች ከአምባአላጂ ሽንፈት በኋላ ስብሰባ ርገው ባሳለፉት ውሳኔ መሠ/ት

Giuseppe Galliano.



Maggiore Giuseppe Galliano.

ተምክህተኛው ሻለቃ ጋሊያኖ በአስተያየት ከመቀሌ ከበባ በኩብር እንዲወጣ ተደርጎ ዳግም በጦርነት እንዳይካፈል ቃል የገባበትን በማጠፍ በዓድዋ ጦርነት ተካፍሎ በጦር ሜዳ ታምር ይሰራል ተብሎ ሲጠበቅ በመሸሽ ላይ እንዳለ በኢትዮጵያ ወታደሮች ተገድሎ የዘዲኑኑን ዋጋ ያገኘ

ራስ መኮንን

ሻለቃ ጋሊያኖ የምሽጉ ኃላፊ ሆኖ የቀረው በፍላጎቱ ነበር። ጣሊያኖች በመቀሌ ተከበው ለመቅረት ተጨባጭ ዓላማ አልነበራቸውም የመቀሌ ምሽግ ቢለቀቅ ጀኔራል አሪሞንዲ ያቀረባቸው ምክንያቶች 1ኛ. በወታደሮችና በህገሪቷ የሞራል ውድቀት ያስከትላል። 2ኛ. እዚያው የተከማቹ ስንቅና ትጥቅ ለማውደም ጊዜ እናገኝም ነበር። ይዘነው ለመሔድም የመ ጓጓዣ ችግር ነበር።

1 F.I.C.I.

እነዚህ ምክንያቶች ግን ስንካላ ምክንያቶች ነበሩ። 3ኛ. በተለይ ሶስተኛ ምክንያት ምሽጉ በእጃችን መሆን ለወደፊቱ የሚሰነዘርባቸው የማጥቃት እርምጃ አገዛ ለማድረግ ታላቅ ሚና ሊጫወት ይችላል የሚለው ተጨባጭነት የሌለው ከንቱ ጉራ ነበረ። ምክንያቱም አለቃው ዋና አዛዡ እንኳን ለማጥቃት ዕርምጃ የመውሰድ የነበረው ሃሣብ ወደ ኋላ ወደ ዓዲቀይሀ ለማፈግፈግ ነበር። ዲሴምበር 22 በራስ መኮንን የተላከ አንድ መልዕክተኛ ከአንድ ደብዳቤ ጋር ወደ ቫለታ ጋሊያኖ ደላካል። ጥያቄውም እንደተለመደው «በንጉሥ ነገሥቱ ስም ይህን መሬት ለቀህ እንድትሔድ እጠይቅሃለሁ ይህን ካላደረክ ግን ጦርነት ለማድረግ ታስገድደኛለህ የክ ርስቲያን ደም በከንቱ ሊፈስ ያሳዝነኛል» የሚል ነበር። ቫለታ ጋሊያኖም አንተ እያለ የሰጠው መልስ «የእኔ ንጉሥ እዚሁ እንዲሆን አዞኛል እኔም ከዚህ አልንቀሳቀስም የፈለከውን አድርግ የማስጠነቅቅህ ግን እዚህ ከእኔ ጋር ምርጥ ጠብመንጃዎችና መድፎች እንዳሉኝ ነው። ሌሎች የተላኩ መልክተኞችም የዚሁ ተመሳሳይ መልስ ነበረ የተሰጣቸው። ጃንዋሪ 3 አንድ ኢጣሊያ አስከሪ በራስ መኮንን አሽከረኛ የሆነው የመቶ አለቃ ስካላ (Scala) ልዩ ሠራተኛ የነበረው የራስ መኮንን አዲስ ደብዳቤ ይዞ የመቶ አለቃ ቤርቲኒ ወይም ሌላ መኮንን ለመነጋገር እንዲላክለት የሚጠይቅ ተልኮ ነበር። ነገር ግን ቫለታ ጋሊያኖ ከሰው የማይቀጥረው የእሱ አስከሬ የነበረው መልዕክተኛ ሆኖ ሊመጣበት ተናዶ ሌላ ትልቅ ሰው አንተ ምን እንደምትፈልግ የሚነግረኝ ላክልኝ እኔም እልክልሃለሁ የሚል ነበር መልስ የሰጠው ራስ መኮንን እቶ ጊዮርጊስ የተባለው ከ8 የሸዋ ተወላጆች መልዕክተኞች ልኮ ጦርነት የምትፈልግ ከሆነ በአምባአላጂ ለአንተ ጓደኞች የደረሰባቸውን አስታውስ የአንተ ወገኖችን በመከተል ትልቅ እምናለሁ ብለህ የምትፈልግ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ አላይሃለሁ የሚል ነበር።

ለዚህም ጃንዋሪ 7 ቫለታ ጋሊያኖ የላከው መልስ በደብዳቤ እንደጠላት መስሎህ ነው የጻፍክልኝ እኔ ግን ወዳጅ ሰው ይመስለኝ ነበር አንተ በእኔ መንግሥት ላይ ጦርነት አደርጋለሁ ካልክ እግዚአብሔር የፈቀደው ይሆናል። እኔ ግን የወታደር ግዳጄን እፈጽማለሁ የሚል ነበር። ከጃንዋሪ 8 ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ጦር የማጥቃት እርምጃ ጀመረ፤ በተለይ ጃንዋሪ 10 እና 11 የራስ መኮንን ጦር ኃይለኛ ጥቃቶች ሰነዘረ፤ ከዚህ በኋላ ከበባውን ብቻ በማጠናከር ተወሰነ። የኢጣሊያ ጦር ውሃ በማጣት ለችግር ተጋለጠ። ጃንዋሪ 18 ለጥኛ አሽከርና ሀገሬ ገር የላከው ቴሌግራም ውሃ ስለሌለን ለመቋቋም አልቻልኩም። ምሽጉን ትተን እንወጣም ነገር ግን ትንሹ የመቀሌ ምሽግ ግዳጁን ይፈጽማል፤ ታላቅ ክብር ተጎናጽፎ ይዋታል። ጉረኛው ቫለታ ጋሊያኖ በአንድ በኩል ከምሽጉ ለቅቄ አልወጣም እያለ በሌላ በኩል ጃንዋሪ 9 ቀን የበታች ሹማምንቶችን ሰብስቦ እየተማጋ ከምሽጉ እንደሚወጣ የሚል ሃሣብ ሲያቀርብላቸው «ቪቫ ሊታሊያ» እያሉ ነበረ ሃሣቡን የተቀበሉት። በመሐሉ ግን ከባራቲዬሪ የተላከ መልዕክተኛ ከአጼ ምኒልክ በፊላተር አማካይነት የተደረደረው ስምምነት በመቀሌ ምሽግ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮች መሣሪያዎቻቸውን እንደያዙ እንዲወጡ ደህንነታቸውን እስከ ዓዲግራት ድረስ እንዲጠበቅ ለዚሁ ማካካሻ ግን የኢጣሊያ ጦር እንደ የሰላም ንግግር ለመጀመር መቀበል እንዳለበት የሚል ነበር። የኢጣሊያ ጦር ጃንዋሪ 22



ከምሽጉ ለቆ ወጣ፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተፈላጊ የነበረው የሰላም ንግግር መጀመር ግን ምናልባት የውጫሌውን ውል እንዲሰረዝ ለማድረግ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ በልዩ ልዩ ምክንያት በተለይ የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሰሜን በመገፋቱ ተረስቶ ቀረ።[1]

ጃንዋሪ 8 ነበረ የውሃ ምንጭ በሐበሾች እጅ የገባ ። ሐበሾች ከባድ ጥቃቶች ከሰነዘሩ በኋላ መሬት በመሬት እየተንፏቀቁ የውጭ መከላከያ ድረስ ዘልቀው ደርሰው ጉዳት ቢያደርሱም ራሳቸውም ጉዳት ስለደረሰባቸው አጼ ምኒልክ በምሽጉ ያሉ ኢጣሊያኖች በውሃ ጥም እጃቸው መስጠታቸው ስለ ማይቀር በኃይል መምከር ቀርቶ የከበባው ቁጥጥር ብቻ እንዲጠና ከር አዘዙ። በኢጣሊያ የወታደራዊ አታሼዎች ለኢጣሊያ አድናቆታቸቸውን ገልጸዋል። እንደ ተለመደው የጀርመኑ ትጉሠ ነገሥት ጉልየልሞ 2ኛ ታላቅ ኒሻን ለቫለታ ጋሊያኖ ሸልመውታል። የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ የማዕረግ እድገት በጦር ሜዳ ሙያ ፈቅዶለታል። አጼ ምኒልክ ይጠይቀው የነበረ 1ኛ. ወሰኑ ቀድሞ ወደነበረው መረብ፣ በለሳ፣ ሙና እንዲሆን 2ኛ. የውጫሌውን 17ኛው አንቀጽ እንዲሰረዝ 3ኛ የሰላም ንግግር እንዲጀመር ሲሆን የጣሊያን መንግሥት ግን ይህ የአጼ ምኒልክ ሃሣብ ሊቀበለው እንደማይችልና እንደማይፈልግ በመግለጽ ለጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ፌብሯሪ 8 በላከው ቴሌግራም 1ኛ. የዓዲግራትና ዓድዋ አካባቢ የኢጣሊያ እንዲሆን 2ኛ. የውጫሌውን ውል አጼ ምኒልክ እንዲቀበል 3ኛ. መቀሌና አምባአላጂ በጊ ዜያዊነት በኢጣሊያ አስተዳደር እንዲሆኑ በዚሁ መሠረት ንግግር ለማድረግ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተፈቀደለት መሆኑን የሚል ነበረ። ይህ የኢጣሊያ መንግሥት ሃሳብ ፌብሯሪ 11 ለአጼ ምኒልክ ሊገለጽለት ማንኛውም ንግግር ሊቋረጥ ችሏል። ጠቅላይ ምኒስትር ክሪስፒና የጦሩ አዛዥ ቴሌግራሞች ይለ ዋወጡ ነበር። ክሪስፒ ሀገሪቷ የምትጠብቀው ደንበኛ ድል የሐበሻ ጉዳይ ለአንዴም ለሁል ጊዜ እንደሚያልቅ እንዲደረግ ሲጠይቀው ባራቲሪም ከኢጣሊያ የሚላኩ ተጨማሪ ወታደሮች በዓዲግራት ከአሰባሰብኩ በኋላ የሸዋ ወታደሮችን ብቻቸው ወይንም ከሌሎች ጋራ ተሰብስበው እንደማወድማቸው ሙሉ እምነቴ ነው በማለት ነበረ ይመልስለት የነበረው።

ጣሊያኖች የውጫሌ ውል ከሚፈቅድላቸው በላይ ለመጠየቅ የሚያስችላቸው በቂ ወታደራዊ ኃይል አልነበራቸውም ራሱ ባራቴሪ ጃንዋሪ 7/ 1896 ዓ.ም. ለመንግሥቱ በላከው ሪፖርት ብዙ ችግሮች በተለይ ለነጭ ወታደሮች ቁጥር እንዳሉ እንዲሆኑ ከገለፀ በኋላ በራሴ ብዙ እምነት ስላለኝ አይደለም ተጨማሪ ወታደሮች የማልጠይቀው ለሀገሪቷ አዝኜ እይደለም። ነገር ግን ስንቃቸው ለማደራጀት ስለማልችል ነው ብሎ ነበር። በመንግሥት አባላት ማሕከል ከፍ ያለ ልዩነት ነበረ። ጠቅላይ ሚኒስትር ችግሮቹን ሁሉ መወጣት መቻል አለብን ብሎ ሲከራከር ሌላው ግን በድፍን ተጨማሪ ወታደ ሮች እንዲላኩ የሚቃወም ነበር። በዚሁ ጊዜ ከክሪስፒ መንግሥት አባል ሩዲኒ ሁኔታው በማክረር እንደሚከ ተለው ገልጧል።

1 F.I.C.L: Ibd p.164

በኢትዮጵያ ደጋዎች የነጭ ወታደር መጠቀም ቀላል ነገር አይደለም፤ ዝግጅት ያስፈልጋል፤ ይኼንን ለማድረግ ደግሞ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም የስንቅ ጉዳይ እንደ እንጊጀኛ ወታደር ነጭ ወታደር ቶሎ አሽከማችሁ ወደ ጦር ሜዳ መላክ አትችሉም። ስለዚህ ነው ጀነራል ባራቴሪ መንግሥት የሚልክለትን የነጭ ወታደር እንዲላክለት ያልፈለገው፤ ይህ ሁኔታ ለእኛ እንደማስጠንቀቂያ ነው። እኛ ልጆቻችን ለድል የሚያበቃቸው አስፈላጊውን ሁሉ ሳናሟላላቸው ብንልካቸው ለሚደርስባቸው ሁሉ በኃላፊነት እንጠይቃለን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለማሟላት ደግሞ ብዙ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው ብሎ ነበር።

## በ. የዓድዋ ጦርነት፤

የዓድዋ ጦርነት ሽንፈት ማስቀረት ይቻል ነበረ እየተባለ ብዙ ተተችቷል። ጀነራል ባራቴሪ ወደ ኋላ ወደ ዓዲ ቀይሕ ማፈግፈግ አስቦ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ፌብሯሪ








ግ፡ P. Antonelli.

አጼ ምኒልክ እና ጣሊያኖች አማካሪዎቻቸው የኢጣሊያ ክፋትለዘ ግዛ የሸዋ ፖለቲካ አራማጆች።







Menelic all'apogeo della sua potenza

በዓድዋ ጦርነት ተፋላሚዎች



Generale Oreste Baratieri



Regina Taitù.



Ras Maconnen.

25 ቴሌግራም ከላከለት በኋላ ግን ያላመነበት ጦርነት ከፍቶ ለሽንፈት ተዳርገዋል። ስለዚህ ለሽንፈቱ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት ባራቲሪ ሳይሆን ክሪስፒ ነው የሚሉ ወገኖች ብዙ ናቸው። ይኸንን ወቀሳ ያሰማ አብዛኛውን ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጀነራል ባራቲሪን ለመፍረድ በአስመራ ተሰይሞ የነበረው የጦር ፍ/ቤት ነው። ጀነራል ባራቲሪ ገና ከሚይና ጁን ወራት 1895 ዓ.ም ጀምሮ በመኸር ወራት ከምኒልክ ጋራ ጦርነት እንደሚኖር ለመንግሥቱ ያስጠነቅቅ ነበር። ዳሩ ግን በየጊዜው የሚልኩቸው ደብዳቤዎችና በሚልካቸው ቴሌግራሞች ወደ ሀገሩ እንዲመለስ እና በሌላ ሰው እንዲተካ ደጋግሞ ከመጠየቅ ሌላ ስለ ሀገሩ ችግር ወይንም በሰላማዊ መንገድ ወይም በጦር ሜዳ ለመፍታት የነገሩ ሁኔታ በተጨባጭ በማገናዘብ በደረሰው ወታደር ይጨመርልኝ ስንቅና ትጥቅ ይጨመርልኝ ከማለት በቀር በተግባር የመጨረሻ መፍትሔ የሚሆን ሐሳብ ለመንግሥት ሊያቀርብ አልቻለም። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ሌሎችም የበኒ አባሎች ኢጣሊያ የምትፈልገው የማያዳግም ታላቅ ድል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያ ችግር የሚፈታ መሆኑን በተደጋጋሚ ይገልጹለት ነበር። ለምሳሌ ጁን 7 ባራቲሪ በፃፈው ደብዳቤ «መንግሥታችን ከአጼ ምኒልክ ጋራ ሰላም ለማድረግ የሚቻል መሆኑን እምነት እንዳለው አላውቅም ወይንም ለምምከር አቅድ እንዳለው አላውቅም፤ አጼ ምኒልክ ሁኔታው እንደሚያመለክተው የእኛ የመስፋፋት ዓላማ ያሰፈራቸዋል፤ ምናልባትም የውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት ሰላም ቢደረግ ፈላጊው ይሆናል። እኛ በጦርነት አሸንፈን የያዝናቸውን መሬቶች ለመመለስ እንችላለንን? እኛ ብዙ ባሪያዎች ከወላዋይ ይዞ የተመለሰ ሽፍታ ጋራ የሰላም ንግግር ማድረግ እንችላለንን?» ብሎ ፅፎ ነበር። [1] ጁን 22 በላከው ሌላ ቴሌግራም የሥራ መልቀቂያ ለመጠየቅ የበታሁት የምጠይቀው ነገር ስለማይፈጸምልኝ ነው ካለ በኋላ አሁን የምጠይቀው ያሉኝ የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት እንዳለ እንዲሆን፤ የኢንዲጂኒ ወታደሮች ብዛት እንዲጨምር ነው ብሏል። [2] ባራቲሪ ለመመከበር ወደ ኢጣሊያ ተጠርቶ 1000 የኢንዲጂኒ ወታደሮች እንዲመለመሉ 700 የመጓጓዣ ከብቶች እንዲገዙ ተፈቀደለት [3] ባራቲሪ የጦርነት ደመና የሚያንዣብብ መሆኑን ስለተረዳ መንግሥት ባያስፈቅድ የሸዋ ጦርን ለማውደም 7ኛ እና 8ኛ ባታሊዮን እንዲጀኒ መልምሎ አደቀዋ ነበር። ምክንያቱም በአፋጣኝ አንድ እርምጃ ካልተወሰደ ኢጣሊያ በአንድ ትልቅ ጦርነት አዘት ልትወድቅ ትችላለች። በዚህ ጦርነት በአሸናፊነት እንደምንወጣ ባያጠራጥርም የሚጠይቀው ወጪ ለመገመት ግን አዳጋች ይሆናል። ሁለት መንገዶች ከፊታችን ተደቅኗል ሰላምና ጦርነት። እኔ በሰላማዊ መንገድ ችግሩ ለመፍታት እመርጥ ነበር።

ነገር ግን በቀጥታ ከንጉሡ ነገሥቱ ሆነ ወይንም አንድ ራስ ለምሳሌ ራስ መኮንን ሥልጣን እንዲይዝ አድርገን፤ ኢትዮጵያ የውጫሌ ውል እንድትቀበል የቅኝ ግዛታችን ወሰን ከመቀሌ በስተደቡብ እንዲሆን ለማድረግ መሞከር ያስፈልጋል።

1. E.Bellavita Ibd p. 193

2. E.Bellavita Ibd p. 194

3. E.Bellavita Ibd p. 197



በዓድዋ ጦርነት የተካፈሉ 4ቱ የኢጣሊያ ብሪጋዴር ጀነራሎች
ዳቦር ሚዳና አሪሞንዲ በጦር ሜዳ የተገደሉ
አልበርቶኔ በዓድዋ ተማርኮ አዲስ አበባ እስረኛ ሆኖ የቆየ ኤሌና ከዓድዋ ጦር ሜዳ
በሸሸበት ጊዜ የቆሰለ



I quattro generali brigadieri di Adua.
Gen. Vittorio Dabormida (medaglia d'oro).
2. Gen. Giuseppe Arimondi (medaglia d'oro).
Gen. Matteo Albertone
4. Gen. Giuseppe Ellena
(Civica Raccolta delle Stampe - Milano).

[1]ለዚሁ ፕላን የኢጣሊያ መንግሥት መልስ ባይሰጥም በተለይ በአሪሞንዲ የሚመራ የወታደሮች አስተሳሰብ ግን ከደብረ ዓይላ ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ችግር የራስ መንገሻ ጦር ተሸንፎ ተበታትኖ እንዲሰቀረን ሁሉ የሸዋ ጦርም በድፍረት ወደ ደቡብ ገስግሦን የምኒልክ ጦር ሳይደራጅ ደርሰን ድምጥማጡን ልናጠፋው እንችላለን የሚል እምነት ነበራቸው[2]። ይህ ግን ጣሊያኖች በሕልማቸው እንደታየያቸው የሚገመት እንጂ ወታደራዊ አቅማቸው የሚፈቅድላቸው አልነበረም።

ሻለቃ ቶሰሊ ወደ አንባአላጂ መሄድ የቻለው ለወታደራዊ ግደጅ ታዞ ሳይሆን ራሱ በተደጋጋሚ ለጀነራል አሪሞንዲ በጠየቀው መሠረት ነበር[3]።

የኢጣሊያ መንግሥት በወቅቱ የነበረው የኢኮኖሚ ችግር ለጦር ዝግጅት ገንዘብ መጨመር ስላልቻለ ከአጼ ምኒልክ ጋራ ለመስማማት ይዞታውን ማጥበብ ነበረበት። ይህ ባለመደረጉ ጣሊያኖች የስራቸውን ውጤት አገኙ። ጣሊያኖች በደረሰባቸው አሳፋሪ ሽንፈት የአንድ ሰው ወይንም የአንድ ቡድን ጉድለት አይደለም ኃላፊነቱን የምትወስደው መላው ሀገሪቱ ናት።

ራስ መኰንን ከአጼ ምኒልክ የሠላም ንግግር እንዲያደርግ ታዞ ወደ ትግራይ ሲሄድ ባራቴሪ በፌልተር አማካኝነት በቀጥታ የሰላም ንግግር እንዲደረግ ደብዳቤ ሲደርሰው ዲሴንበር 3 የራስ መኰንን ደብዳቤ እንደደረሰው በጀነራል አሪሞንዲ በኩል ባስተላለፈው ቴሌግራም ለንግግሩ ለሻለቃ ቶሰሌ ሙሉ ስልጣን የሰጠው መሆኑን ከገለፀ በኋላ ንግግሮች በጥንቃቄ መከናወን እንዳለባቸው አስጠንቅቆ ንግግር ይደረግ የሚለው ሐሳብ የማታለያ ዘዴ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩልም የሰላም ንግግር ውጤታማ የሚሆነው እኛ ኃይላችንን ስናሳይ ብቻ ነው ብሏል።[4]

ዲሴምበር 3 ባራቴሪ የሰላም ንግግር እንዲደረግ በቀጥታ ለራስ መኰንን በጀነራል አሪሞንድ አማካኝነት ደብዳቤ ፅፎ ነበር፤ ደብዳቤው ግን ጦርንቱ ስለተጀመረ ለራስ መኰንን አልደረሰውም። ችግሩ ባራቴሪ ስለ ንግግሩ ጥርጣሬ ሲኖረው አሪሞንዲ ግን አያምንበትም ነበር፤ ሻለቃ ቶሰሊም በባሰ ሁኔታ አያምንበትም ነበር።[5]

ዲሴምበር 3 ራስ መኰንን በቀና መንፈስ ከሻለቃ ቶሰሊ የፃፈለት ደብዳቤ የሰጠው መልስ የአብሪተኛ በባዶ ጉራ ምልክት ነበረ።[6]

1. E.Bellavita Ibd p. 206
2. E.Bellavita Ibd p. 206
3. E.Bellavita Ibd p. 206
4. E.Bellavita Ibd p. 212
5. E.Bellavita Ibd p. 214
6. E.Bellavita Ibd p. 214



ዲሴምበር 6 ከምሽቱ 12 ሰዓት ሻለቃ ቶሰሊ ለጀነራል አሪሞንዲ በፃፈው ደብዳቤ «ራስ መኰንን ትላንት በፃፈው ደብዳቤ እኛን ለማስፈራራት ሐሰት የተናገረ ይመስለኛል፤ ንጉሡ ዓዘቦ የደረሰ አይመስለኝም። ንጉሡ አሻንጌ ደርሷል ብሎ ራስ መኰንን ሐሰት የተናገረ ይመስለኛል። የራስ ሰብሐት ሁለት ሰላዮች ንጉሡ አሻንጌ እንደሚገኝ አረጋግጧል። ምናልባትም አልደረሰ ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በበኩሉ በኖቬንበር ወር «ትግራይ ከእንግዲህ ከኤርትራ ጋራ ተቀላቅሏል» እያለ ጉራውን ያሰማ ነበር።

ጀነራል አሪሞንዲ ባራቴሪ ባይከለክለው በኢትዮጵያ ተዋጊዎች ባለው ንቀት የተነሣ ወደ ደቡብ ገስግሶ ሳስታን በኢጣሊያ ቁጥጥር ለማድረግ አስቦ ነበር። የሚላኖ «ራዲካልስ» የሚባሉ ፀረ ቅኝ አገዛዝ አቋም የነበራቸው ወገኖች እንደ ሚርካቴሊ የተባለው ከዕንጣሉ በደብረ ዓይላ ጦርነት እስረኛ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አነጋግሮ ያገኘው መልስ «ይህ ጦርነት ቀላል ነው፤ ዋናው ጦርነት ከአንድ ወር ከ12 ቀን በኋላ ታገኙታላችሁ» ብለው እንደተናገሩ ዘግበዋል። በተለይ የዓይባ ቀኛአዝማች ኃይለማርያም የተናገረው ቃል ብሎ የወጣው «ሸዋ ለጦርነት ዝግጁ ነው። ጦርነቱም ኃይለኛ ነው የሚሆነው» የንጉሡ ወታደሮች ሁሉም ጠብመንጃ ታጥቀዋል ብዙ ጥይትም መድፎችም አሏቸው «ብዙ ጊዜ የጦር ልምምድ ያደርጋሉ» ብለዋል።[1]

የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብላንክ ኖቬንበር መጨረሻ «በኤርትራ ሁሉ ነገር ደህና ነው ሰላም ሰፍኗል» ብሎ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒም ኃላፊነት በጐደለው አነጋገር «በአፍሪካ ጦርነት እንደኛ ትልቅ ሀገር የሚያስጋው አይደለም» ብሏል።[2]

ሻለቃ ቶሰሊ ከአቅሙ በላይ የሆነ አደጋ አንዣብቦ እያየ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ሲገባው ጦርነት እንጥማለሁ ብሎ መሞከሩ ጀግንነት አይባልም በራሱና በሌላ ለው ሕይወት የተጫወተ ወንጀለኛ ነው። ወደ አምባአላጂ የሄደው በፍቃዱ ነው። አሁንም ከአንባላጂ ለቆ ለመውጣት የሚከለክለው ነገር አልነበረም። የኢትዮጵያ ሠራዊት ብዛት ከመቶ ሺህ በላይ ነው የሚለው አባባል የኢጣሊያ መንግሥት የተጋነነ ነው ብሎ አልተቀበለውም ነበር። እንደዚሁም ጀነራል ባልዲሴራ ባራቴሪን ለመተካት ወደ አፍሪካ ከመሄዱ በፊት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለማሸነፍ የሚያስፈልጋት የወታደር ብዛት ተጠይቆ 40.000 ያስፈልጋታል ብሎ የሰጠው አስተያየት የተጋነነ ነው ብሎ አልተቀበለውም ነበር።

ጣሊያኖች እኛን አንኳላችን የአንድ ሕፃን ልጅ ነው ብለው ሲገምቱን ራሳቸው በተለመደው የከሀደት ፀባያቸው ራስ መኰንን ግዛቱን ሐረር ትቶ ትግራይ በሚገኙበት ጊዜ ሐረር በወታደር አልተጠበቀችም ብለው በመገመት በዘይላ የእንግሊዝ ሶማሊያ በኩል ሐረርን ለመውረር አስበው ነበር። የእንግሊዝ መንግሥት ግን ከፈረንሳይ መንግሥት ጋራ መጣላት ስለማይፈልግ ጥያቄያቸውን ሳይቀበለው ይቀራል።

1. E.Bellavita Ibd p. 225
2. E.Bellavita Ibd p. 227

እንደገና ከመቀሌ ከበባ በኋላ[1] ጥያቄያቸውን አሻሽለው በሶማሌላንድ ሳይቆዩ ለማለፍ ብቻ ብለው ይጠይቃሉ። አሁንም የእንግሊዝ መንግሥት ሳይቀበላቸው ይቀራል። በእንግሊዝ ሳይሆንላቸው ሊቀር በፈረንሳይ ግዛት በጅቡቲ በኩል ለማለፍ እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃሉ። የፈረንሳይ መንግሥት ጣሊያኖች ከጀርመኖች ጋራ የሚያስተሳስራቸው ትሪፕል አሊያንስ። እንዲወጡ ቅድመ ሁኔታ ስለጠየቃቸው ሕልማቸው ሳይሳካላቸው ይቀራል።

በመጨረሻም በአሰብ በኩል ለመግባት እቅድ ያወጣሉ ይኸንን ዘመቻ የሚመራ በችሎታው በጣም የተመሰገነ ኩሎኔል ፒታሉጋ (Pittaluga) የተባለው ተመርጦ ከተጠና በኋላ ችግሩን ሊወጡ ባለመቻላቸው ውድቅ ሆኖ ቀርቷል። እነዚህ ሁሉ እቅዶች ሲሞከሩም ጥሩ ውጤት ሊያመጡ እንደማይችሉ የታወቀ ነው። ተሞክሮ ቢሆንም በራሳቸው ወታደሮች ሳይሆን እንደለማዳቸው በእንዲጂኔ ኤርትራውያን ተጠቅመው ኢትዮጵያን ፊት ለፊት ሲያቅታቸው በጀርባዋ ሊወጉት ነበር። ስለዚህ የዓድዋ ድል ድርብ ድል ነው። ይህ ሁሉ እቅድ የወጣው ደግሞ በትልቁ ጠቅላይ ሚኒስትራቸው በክሪስፒ ነው። ከመቀሌ ከበባ የተለቀቁ ወታደሮች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ እንጂ እንዳይዋጉ የሚል ቃል በውሉ ላይ ገብቶ ነበር፤ ነገር ግን ቃላቸውን አላከበሩም። ጣሊያኖች ከመቀሌ ሲለቀቁ ንግግር እንዲደረግ ቃል ገብተው ነበር። ነገር ግን ቃላቸውን አላከበሩም። አጼ ምኒልክ ከተለቀቁ ወታደሮች ዘጠኝ መኰንኖችና አንድ ባለሌላ ማዕረግ በመያዣ ይዞ አቆይቷቸው ነበር። ከትንሽ ቀን በኋላ ግን ከእቴጌ ጣይቱ የተላኩ መልእክተኞችና አንድ የአጼ ምኒልክ ደብዳቤ ይዘው ስለ ሰላም ንግግር እንዲደረግ የሚጠይቅ ወደ ጀኔራል ባራቴሪ ተልከው ነበረ። በዚሁ ጊዜ ጀኔራል ባራቴሪ ሻለቃ ሳልሳን ወደ አጼ ምኒልክ ስለንግግሩ ጉዳይ ለማወቅ ላከ። እሱም ሲመለስ አጼ ምኒልክ እርግጥ ሰላም ይፈልጋል ነገር ግን ጦርነት የሚፈልጉ ወገኖች ስላየሉ ምንም ማድረግ አልቻለም የሚል መልስ ይዞ ሲመጣ ባራቴሪ ፌብሯሪ 13 ለአጼ ምኒልክ የፃፈው ደብዳቤ «ስለ ሰላም ለመነጋገር የቀረቡት ቅድመ ሁኔታዎች የውጫሌ ውል እንዲሰረዝ የኢጣሊያ ባንዲራ ያውለበለበት ቦታዎች ለኢጣሊያ እንዳይሆኑ ለማድረግ ተቀባይነት የለውም። የሚሉ ስለሆነ እርሶን ለማስደሰት ስለ ሰላም ለመነጋገር ሻለቃ ሳልሳን ላኩሎት። ትክክለኛ ነገር ለእኛም ለእርሶም የሚሳካ መስሎኝ ነበር። አሁን ስለሰላም ንግግር ጉዳይ አብቅቷል። ሁላችን የመሰለንን ለማድረግ ነፃ ነን» የሚል ነበር። ጣሊያኖች የኢትዮጵያ ደጋግሞ ሰላም መፈለግ የደካማነት ምልክት ነበረ የተረጎሙት። በዚሁ መሠረት ኃላፊነት በጎደለባቸው ውሳኔዎች ብዙ ሕዝብ በከንቱ እንዲያልቅ አድርጓል።

ፌብሯሪ 28 የኢጣሊያ ጀኔራሎች ስብሰባ ተቀምጠው ዋና አዛዡ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ጠይቀዋቸዋል። ሀ/ ከመጣት ጀኔራሉ አልቤርቶኔ ተጀመረ። ወደ ኋላ ማፈግፈግ የማልቀበለው ነው ወደ ኋላ ማፈግፈግ እንደ ተሸነፍን ይቆጠራል ጠላት እንዲያጠቃን መጋበዝ ነው በማለት ንግግሩን ጨርሷል ለ/ ሁለተኛ ተናጋሪ ጀኔራል ዳቦርሚዳ ነበረ ወደ ኋላ ማፈግፈግ የወታደሮችና የሀገሪቷ ሞራል ይነካል፤ ካጋጠመ ማጥቃት ይመረጣል ብሏል።

1. E. Bellavita Ibd p. 257



ሐ/ ሶስተኛ ተናጋሪ ያቀርደቱ ጀግና ብለው የሚጠሩት ጀኔራል አሪሞንዲ ነበር፤ ለቅኝ ግዛታቸው ኢውሮጳውያን በቁጥር አነስተኛ ሆነው ነበር ሁል ጊዜ የተዋጉ የእኛም እንደዚሁ ነው። የተሻለ መሣሪያና መለዋወጫ ስላለን፤ የኢጣሊያ ወታደሮች ጀግንነትና ዲሲፒሊን፤ የመተኮስ ችሎታቸው የቁጥራቸው ማነስ ይተካል። ጊዜ ማባከን አያስፈልግም ጥሩ አጋጣሚ እያመለጠን ነው፤ ጠላት በአምባላጄና በመቀሌ ያገኛቸው ድሎች ተዝናንቶ ወደ ኋላ ለመሸሽ ነው የሚያስበው። በዚሁ ዓይነት ጦርነቱ በጠላት አሸናፊነት በእኛ ተሸናፊነት አለቀ ማለት ነው። የጠላት ወታደሮች ቁጥራቸው 80.000 እንኳን ቢሆን ስንት ናቸው በጠብመንጃ የታጠቁ? ከ50 ወይም 60 ሺህ አይበልጡም። ሰላዮች ማጋነን ይወዳሉ። እንደሚታወቀው ብዙ የሐበሻ ወታደሮች ምግብ እናመጣለን ብለው ወደ ተምቤን ሄደው ወደ ሀገራቸው ይሄዳሉ እንጂ ወደ ጦር ሜዳ አይመለሱም። ሁሉም እንደሚያውቀው የሸዋ ሰዎች ጥሩ ወታደሮች አይደሉም ፈሪዎች ናቸው፤ የሴት ፀባይ አላቸው። ቆርጠን እያጠቃን ወደ ዓድዋ ብንገሰግስ ፈጥነው ሸሽተው ይጠፉ ነበር። ወሳኝ ድል እንኳን ባናገኝ ጠላት እንዲሸሽ በማድረጋችን በከፊል እንዳሸነፍን እራሳችንን እንቆጥራለን። ስለዚህ ድል ለመቀዳጀት ወደ ዓድዋ ወደ ፊት መሄድ ይገባናል ብሏል። መ/ ጀኔራል ኤሊና ከኢጣሊያ በቅርብ ጊዜ የመጣ እንደመሆኑ መጠን እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ አጥቅተን ታላቅ ድል መቀዳጀት አለብን ባይ ነበር።

ስለዚህ የጀኔራል አሪሞንዲ ንግግር ሙሉ በሙሉ ደጋፊ ነበር። ጀኔራል ባራቴሪ ሰላዮች በአንድ ቃል እንደተናገሩት የኢትዮጵያ ጦር ወደ አክሱም ሄዷል፤ ራስ ወሌ ሞቷል፤ አጼ ምኒልክ ታሟል የሚሉ ስለሆነ ወደ ዓድዋ ለመንቀሳቀስ ወስኛለሁ ብሎ ነገራቸው። ፌብሯሪ 29 ማታ በ3:00 ሰዓት ከሳውራ ወደ ዓድዋ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ሲንቀሳቀሱ ጣሊያኖች 20.120 ወታደሮች ነበሯቸው የዓድዋ ጦርነት የተካሄደው በሶስት ጦር ግንባር ተከፋፍሎ ነበር።

ማርች አንድ ቀን 1896 ዓ.ም. በእኛ መጋቢት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. የአንደኛ ጦር ግንባር የግራ ጦር ግንባር በጀነራል አልበርቶኔ (Albertone) የሚመራ የኢንዲጂኒ ብርጌድ ነበር።

ሁለተኛ ጦር ግንባር የመሀል ጦር ግንባር በአቀርደቱ ጀግና የሚል ቅፅል የተሰጠው በጀኔራል አሪሞንዲ (Arimondi) የሚመራው የኢጣሊያኖች ብርጌድ ነበረ።

ሶስተኛ ጦር ግንባር የቀኝ ጦር ግንባር በጀኔራል ዳቦርሚዳ (Dabormida) የሚመራ ብርጌድ ነበር።

እራተኛ ብርጌድ የደጀን ጦር ከጀኔራል አሪሞንዲ በስተኋላ የተሰለፈ በጀኔራል ኤሊና (Elena) የሚመራ ብርጌድ ነበር።

የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀኔራል ባራቴሪ (Barattieri) ነበር የዓድዋ ጦርነት የተካሄደው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መሀከል ነው ለማለት አያስደፍርም። ጦርነቱ የተካሄደው በአንድ ወገን በኢትዮጵያ ወታደሮች በሌላ ወገን የኢጣሊያ ወታደሮችና ጭፍሮቻቸው

የኢንዲጂኒ ተዋጊዎች መካከል ነበር። የኢንዲጂኒ ተዋጊዎች በጣሊያኖች አስተዳደር ወታደሮች ሊባሉ አይችሉም፤ ትልቅ ክብር እንደተሰጣቸው ይቆጠራል። መደበኛ ከሆኑ አስከር ይባላሉ፤ መደበኛ ካልሆኑ ባንዳ ይባላሉ፤ ክተት የሚባሉም ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ጥምር ተዋጊዎች ነበረ ከኢትዮጵያ ጋራ ጦርነት የገጠሙት። ብዛታቸው በአማካኝ ግማሽ ጣሊያኖች ግማሽ እንዲጀኒ ነበሩ። ከዚህ በፊት የተደሩጉት ጦርነቶች ለምሳሌ በአምባአላጄ በኩዓቲ፤ በኢትዮጵያዊያንና በኢንዲጀኒ ኤርትራውያን መሐከል የተደረጉ ጦርነቶች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ጣሊያኖች በመሪነት አዋጊዎች ብቻ ነበሩ። በዓድዋ ጦርነቱ የተካፈሉ የኢጣሊያ ጀኔራሎች የደረሰባቸው ዕድል በጣም አሳፋሪ ነው። ጀኔራል አልበርቶኔ በኢትዮጵያ ሠራዊት ተማረከ፤ ጀኔራል አሪሞንዲና ጀኔራል ዳቦርሚዳ በጦር ሜዳ ተገደሉ፤ ጀነራል ኤሊና በሽሽት ጊዜ ስለቆሰለ ወዲያውኑ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ዋና አዛዦቸው ብቻ ነበረ ያልሞተና ያልቆሰለ።

ጦርነት በመጀመሪያ የገጠሙ የኢንዲጂን ብርጌድ ነበሩ። ሁለት ሰዓት ሳይሞሉ ብዙ ጉዳት ስለደረሰባቸው የኢትዮጵያ ሠራዊትም ለመቋቋም ስላልቻሉ በብዛት ወደ ኋላ ሲመለሱ ያገኛቸው አንድ በጀኔራል አሪሞንዲ ብርጌድ ውስጥ የአንድ ሬጂመንት አዛዥ የነበረው ኩሉኔል ብሩሳቲ የሚባለው የኢጣሊያ ወታደሮች ገና ተኩስ ሳይሰሙ ለሁለት ሰዓት በእሳት የተቃጠሉ እንዲጂኒ ተዋጊዎች በእብረተኛና የንቀት መንፈስ ተነሳስቶ ወደ ጦር ግንባር ሊመልሳቸው ሞክሮ አልተቻለውም። ጡሩምባ እያሰማ እንዲቆሙና እንዲሰበሰቡ ቢያዛቸው እንዲጂኒ ብቻ ሳይሆኑ ትጥቅ አልቆብናል የቆሰሉትን እናመላልሳለን እያሉ አለቆቻቸው መኰንኖች ጣልያኖችም ጭምር አልታዘዙትም። ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ ግን የራሱ የኢጣሊያ ወታደሮችና ራሱ ኮሎኔሉም በባሰ ሁኔታ ሲሸሹ ይታዩ ነበር። በመቀሌ ከበባ አዛዥ የነበረው ሻለቃ ጋሊያኖ ጀግና ተብሎ ታምር ይሰራል ተብሎ ሲጠበቅ ብዙ ሳይዋጋ ተገደለ በሶስቱ ጦር ግንባር የተደረጉ ትንቅንቅ ውጊያዎችና የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዴት አድርጎ በአስደናቂ ሁኔታ ሊያሸንፍ እንደተቻለ ሰፊ እርእስት እንደመሆኑ መጠን የዚሁ ጽሑፍ ዓላማ ስላልሆነ አልፈዋለሁ። ራሳቸው ጣሊያኖች እንደመሰከሩት አብዛኛው ሰው የሞተባቸው በጦር ሜዳ ሳይሆን በሚሸሹበት ጊዜ ነበር።

የጀኔራል አልቤርቶኔ የኢንዲጂኒ ብርጌድ የተዋጋው ከጠዋቱ 12 እስከ 4 ሰዓት ሲሆን ይኸን ያህል ጊዜ የመሰደቡትን ፊታውራሪ ገበየሁ በጦር ሜዳ ቆስሉ ስለ ሞተ በመሆኑ ጦርነቱ በኢትዮጵያ በኩል ጋብ ብሎ ስለነበረ ነው። የጀኔራል አሪሞንዲ ብርጌድ ጦርነት የጀመረው በ4 ሰዓት ተኩል ነበረ። በ6:30 ብርጌድ እንዳልነበረ ሆኗል።

ጀኔራል ኤሊና ወታደሮቹ ከጀኔራል አሪሞንዲ ጦር ጋር ተቀላቅለው እንዲዋጉ ቢደረጉም እሱ ግን እንደ ኢጋጣሚ ዋና አዛዥ ጀኔራል ባራቴሪ ፍተሻ በሚያደርግበት ጊዜ ሙሉ ቀን በአንድ ሾላ ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ስላገኘው ጦርነቱ ያለቀ መሆኑን እና የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ኋላ በመመለስ እየሸሸ መሆኑን ስለነገረው ከቀኑ 7 ሰዓት ከሌሎች ጦር መኰንኖች ጋር በመሆን ሸሽቶ ማምለጥ ችለዋል።



የጀኔራል ዳቦርሚዳ ብርጌድ ጦር እስከ ቀኑ 4:30 የሌሎች ብርጌዶች ዕድል ሳይየሰማ ከቆየ በኋላ በዚህ ሰዓት የተኩስ ድምጽ ተሰማ። በ5 ሰዓት ተኩሱ እየጨመረ መጣ ከቀኑ ከ9 ሰዓት ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ትእዛዝ ተሰጠ። የኢትዮጵያ ጦር ጣሊያኖች እንደሚሏቸው «ሸዋውያን» እያሳደዱ ይፈጁቸው ነበር። ደግነቱ ግን የኢትዮጵያ ጦር በመሸሽ የነበሩ ጣሊያኖችን ለመግደል አላተኮሩም፤ ከሞቱት ወታደሮች ንብረት መዝረፍ ብቻ ነበር የተያያዙት። በዚሁ ጊዜም ኃይለኛ ዝናብ መጣል ስለጀመረ ተኩሱ ሊቋረጥ ችሏል። ከዚያም መሽቶ ስለጨለመ ውጊያው ሊቋረጥ ችሏል። ማርች 4 ቀን በእኛ መጋቢት 26 ቀን ከቀኑ በ8 ሰዓት ከጦር ሜዳ የሸሹ የኢጣሊያ ተዋጊዎች 300 ሆነው ዓዲቀይህ ገቡ።

ባራቴሪ ማርች 3 ቀን ጠዋት ከዓዲቀይህ የጦር ሠራዊቱ ብዙ ቁጣና ተቃውሞ ያስከተለበት ታሪካዊው አወዛጋቢው የተባለው ረጅም ቴሌግራም ለኢጣሊያ መንግሥት ላከ። የቴሌግራሙ ሙሉ ቃል ትርጉም እንደሚከተለው ነው። «ቅዳሜ ወደ ዓድዋ የሸዋውያን የፊት ይዞታዎችን በነበሩት እርምጃ ወሰድኩ። ስለዚህ እርስ በእርሱ የሚገናኙ ብሬጌዶች በሶስት መሥመሮችና ሌላው ብርጌድ ደጀን በማድረግ ወደ ፊት ገሰገስኩ። የቀኝ ክንፍ ዳቦርሚዳ 6 ባታሉዮን ነጮች 4 መድፎች አንድ ባታሊዮን ሚሊሻ ነበረው። የመሀል ክንፉ አሪሞንዲ 5 ባታሊዮን ነጮች የኢንዲጂኒ ተዋጊዎች 2 መድፎች ነበሩት። የግራ ክንፍን አርቤርቶኔ 4 ባታሊዮን እንዲጂኒና አራት መድፎች ነበሩት። ደጀን ጦር ኤሌና 6 ባታሊዮን ነጮች አንድ እንዲጂኒ 2 መድፎች ባለ ፈጣን ተኩስ ነበሩት። ሁለቱ የግራና የቀኝ መሥመር ወታደሮች ከሳውሪያ ጦር ሰፈር እስከ ዓድዋ ሰላሽ ሜዳ ድረስ ያሉት መንገዶች ተከትለው መራመድ ነበረባቸው። የመሀል መስመር ጦር በመሀል መንገድ እየተጓዘ ግንኙነት መፍጠር ነበረበት። የደጀን ጦርም በዚሁ መሥመር ነበረ የሚጓዘው። መነሻ የጨረቃ ብርሀን በመጠቀም ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ነበር። የመጀመሪያ ግብ በቀኝ የረቢ አርአየኒ ኮረብታ ለመያዝ፤ በግራ የኪዳነምህረት ኮረብታ ለመቆጣጠር ነበረ። እነዚህ ፓራሌል መንገዶች የግራና የቀኝ የሚያርቁባቸው ለአንድ ልዩ ዓለት የተሰራ ወደ ላይ የሚወጣ ተራራ የራዮ ተራራ ለሁለት ተከፍሏል። ነገር ግን ከሱ ውጭ ወደ ምዕራብ መገናኛዎች ቀላል ናቸው እርስ በእርሱ ይታያሉ። አፕራሲዮኑ እንደታሰበው ተከናወነ። ጠዋት ኮረብታዎች ከጠላት ነፃ ስለነበሩ በአንድ ጊዜ ተያዙ። እኔም እስከ ረቢ አርእየኒ ኮረብታ ድረስ መጥቼ ስለነበረ ሁኔታው ተነገረኝ። ይህ በዚህ/ቅንዳለ በ1 ሰዓት በግራ በኩል ከኪዳነ ምህረት አልፎ ወደ ዓድዋ አቅጣጫ ከፍ ያለ ተኩስ እንደተመለከትኩ ለአልበርቶኔ ጦር የተሻለ እርዳታ እንዲያደርግና ከእሱ ጋራ በቅንጅት ለመሥራት እንዲችል የዳቦርሚዳ ጦር ወደፊት እንዲራመድና ወደ ማርያም ሸዊቶ ቦታ እንዲይዝ አደረኩ። የአሪሞንዲ ጦርን ወደ ረቢ አሪየኒ ኮረብታ ጠራኋቸው። በአንድ ሰዓት ተኩል ትንሽ ጊዜ በኋላ ምናልባት ከእኛ በአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ወደ አባገሪማ የሚተኮስ መድፍ ተሰማ። የግራ መሥመር ጦር ጦርነት ገጥሞ ነበረ፤ ነገር ግን ከተወሰነለት ቦታ በጣም አልፎ ነበር፤ ምክንያቱም አንድ ከአልበርቶኔ የተላከልኝ ማስታወሻ የቀረቶ ባታሊዮን ከኮረብታው ወደ ዓድዋ አቅጣጫ ተልኮ ነበር። ኃይለኛ ጦርነት ገጥሞት እንደነበረ እሱም ያለው ኃይል በሙሉ በስራ ላይ በመዋል ከጦርነቱ የቀረቶ ባታሊዮንን ለማላቀቅ

ሞክሮ እንደነበረ በማለት ሁኔታውን በመዘርዘር እንዲወቀው አድርጎ ነበር። በዚሁ ጊዜ በመጀመሪያ በበርሳሊየሪ ጦር በኋላም በቀረው ጦር አልበርቶኔን በመደገፍ ከኪዳነምህረት ኮረብታ ፊት ለፊት የሚገኘውን አንድ ከፍተኛ ቦታ እንዲይዝ ለአሪሞንዲ ብርጌድ ትእዛዝ ሰጠው። እንደዚሁም ሁለት ባለፈጣን ተኩስ መድፎች ወደዚሁ ሁለቱ ባለፈጣን ተኩስ መድ ፎች ወደዚሁ እንዲዛወሩ አደረገው። በዚሁ ወቅት ወደ ዓድዋ የሚወስዱ ከፍ ያሉ ቦታዎች ከፍተኛ ውጊያ ይካሄዱ ነበር።

ዳቦርሚዳ ወደ ግራ ድጋፍ እንዲሰጥና በቀጥታ አርቢርቶኔን እንዲረዳ ትዕዛዝ ሳኩሁ። ትዕዛዙ መድረሱን አላውቅም። ብዛት ያላቸው የጠላት ተዋጊዎች ከግራና ከቀኝ ወደ ከፍተኛ ቦታ ጫፎች ብቅ ማለት በመጀመራቸው የአልቤርቶኔ ጦር ቀስ በቀስ ማፈግፈግ ጀመረ። እንዲያውም ማፈግፈግ ቆሞ እንዲጂናች ወደ ፊት ገፍቶ ነበረ፣ /ፋታውራሪ ገበየሁ ሲሞት/ እኔም የዳቦርሚዳ ጦር ይሆናል ብዬ ግምት አደረብኝ ምክንያቱም እውነቱን ለማየት አንድ ተራራ ይከልለኝ ነበር። በዚሁ ወቅት ከከፍተኛ ቦታ ጫፎች ብዛት ያላቸው አንድ ላይ ተሰብስበው ይወርዱ በነበሩ ጠላቶች ባለፈጣን ተኩስ መትረየሶች ተኩስ ይከፈት ነበር። አርበርቶኔ አሪሞንዲ ከያዘው ቦታ በታች ጠንካራና ተስማሚ ወደ ኮረብታ የሚወርደው ቦታ አፈገፈገ። ይሄውን ቦታ ለማጠናከር በተጠባባቂ ተመድቦ የነበረው የሻለቃ ጋሊያኖ ባታሊዮን ቦታውን ያዘ። ነገር ግን የጠላት ተኩስ ብታት ያለው ባይሆንም የእኛ ይዞታዎች በጣም ምቹና ገዢ ቢሆኑም ወታደሮቹ በቡድን በሚመጡበት ጠላቶች ባዶ ቦታ አንግሉች በመጠቀም በተራራ ስር ቦታ ይዞ የነበረ ሁለት በርሳሌሪ ባታሊዮናች በፍጥነት ወደ ኋላ እንዲመለሱ አደረጋቸው። እንደዚሁም የቡፋሳቲ ሬጂመንት ባታሊዮናች ቦታውን ለቀቁ። የተጠባባቂ ደጀን የነበሩ የኤሊና ባታሊዮናችም ለመቋቋም አልቻሉም። ወደ ኋላ የሚሸሹ እያደና ገሩዋቸው ነበረ። በዚሁ ጊዜ ጠላቶች በታላቅ ድፍረት ወደ ያዝነው ቦታ እየመጡ በውስጣችን እየገቡ በቅርብ ሆነው በመኩንኖቹ ላይ እያተኮሩ ይተኩሱ ነበር።

ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው ማፈግፈግ ለማቆም ምክርም ትዕዛዝም ሊሰራ አልቻለም። በቀሩት ቦታዎችም ለማሰባሰብ መኩንኖች ያደረጉት መከራ ከንቱ ሆኖ ቀረ ምክንያቱም ወደ ፊት የሚገፉ ጠላቶች እና ጥቂት ከበታች ተኩራርተው የሚጋልቡ ሸዋውያን ፈረሰኞች ሁሉም ነገር እንዲበታተን ለማድረግ በቂ ሆነው ነበረ። ከዚህ በኋላ እውነተኛ እልቂት ይደ ርስብን ጀመር። ወታደሮች ያስ መሣሪያ ከተገኘን እንሰለብም የሚል እምነት ስለነበራቸው እንደ እብዶች መሣሪያቸውን ትጥቃቸውን ይወረውሩ ነበር። ሁሉም ምግባቸውና ለብርድ የሙቀ ልብሳቸውን ይወረውሩ ነበር። እኔ ከጀኔራል ኤሊና ከኮሎኔል ቡቴሻኒና ከቡፋሳቲ ጋራ ሆነን ወደ ኖና ስፈራቸው ወደ ሳውሪ እንዲያመሩ ያደረግነው መከራ ከንቱ ሆኖ ቀረ። ሁሉም ወደ ሰሜን ወደ ሰሬ መንገድ ፊታቸውን ያዞሩ ነበር። ሌሊት ቆመን የማፈግፈጉ ስርዓት እንዲኖረው ሞክረን ነበረ። ነገር ግን በእንደዚህ ያለ ግዜ በሚፈጠረው በሌሊቱ ለለመግባባት የተነሳ ለሁለት ተከፈልን ግማሾቹ ከኮ/ሉ ቡቴሻኒ ቡፋሳቲ ጋራ ወደ ማይግዳይ ሲያመሩ ሌሎች ከእኔ፣ ጀኔራል ኤሊና ሻለንዛና ጋራ ሆነን ወደ ዓዲቀይህ መጣን። ስለ ጀኔራል ዳቦርሚዳ ብርጌድ ምንም ወሬ የለኝም እንደዚሁም ስለ ጀኔራል አርቢርቶኔ።



ጀኔራል አሪሞንዲ ተቃራኒ ወሬዎች ይሰማሉ። የቆሰሉትን መጠን በትክክል ለማወቅ አልቻልኩም። በጦርነት የተካፈሉ የነጭ ባታሊዮን ወታደሮች እንደገና ለማደርጀት ያስቻል መስሉ ነው የሚታየኝ። የእንዳጂኒ ተዋጊዎች ብዙ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ተስፋቆ ነዋል፤ በነጮች ወታደሮች አዳም ምክንያት ሞራላቸው የተነካ መሆን አለበት። ሁሉም ሽፍቶችና የመስኖ ጠላቶች ነፍስ ዘርቷል። የማይበገር የመከላከያ ሠራዊት የተያዘው በሽፍቶች የተከበበ የኃዲግራት ምሽግ ለቆ እንዲወጣ ማዘዝ አደገኛ ይመስለኛል። ባሬ ሌሎች ወደ ሰገነይቲና አስመራ ለመሄድ ፍላጎት አለኝ። ለጊዜው ሳምቤቲ ነገ ጠዋት አስመራ ስለሚመጣ የቅኝ ግዛት መንግሥት ይረከባል እና ከሚኒስትሩ ይቀበላል [1]

ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች እስከ ምፅዋ እንዲመለሱ ለምን አልተደረገም ወይንም ለውጫሌ ውል መሠረት ወደ ተፈቱደላቸው አጼ ምኒልክ ለሁ ውርዲ መንግሥታት የሆኑ ዳን ድንበር ብሎ ወደ እስታወቀው ወሰን ለምን እንዲመለሱ አልተደረገም ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚችል ማስረጃ የለም። ጣሊያኖች እንደገኑ በሚሉት ማስረጃዎች [2] የኢትዮጵያ ሠራዊት እስከ ትራፊዕ ዘልቆ መሀል በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ለመግባት እቅድ ነበረ ው። በዓድዋ በተደረደገው ስብሰባ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ሠራዬና ወደ አክለጉዛይ እንዲገባ ተወስኖ ነበር። ማርች 3 ደጃዝማች ስንጋል የባሕታ ሐጎስ ወንድም ከዓድዋ ተነስቶ ወደ በለሳ እንዲሄድ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። ማርች 6 የሸዋ ጦር ወደ እንጢጮ ተንቀሳቅሶ ነበር። በዚሁ ቀን ባልዲሴራ ወደ ሮማ የላከው ቴሌግራም ሁኔታው ከባድ ነው፤ ያለው ሠራዊት 15.000 የኢጣሊያ ወታደሮች እና 5000 እንዳጂኒ በጦርነቱ የተደናገጡ ናቸው። የሸዋ ጦር ምናልባት ከጉራዕ እና አስመራ መሀል ለመከፈር እየመጣ ነው። ማርች 6 ደጃዝማች አርአያ ዳዕሮ ተክሌ ይዞ ነበር፤ የበለሳ መምህር አዝማች አበራ ሐጎስ ተፈልግና በአንድ የንጉሡ ፊታውራሪ ተይዞ ነበረ። ራስ ስብሐትም ማይመረት በመያዝ እስከ ዶጎዓሊ ድረስ ዘልቆ ከዓዲግራት የነበረው ግንኙነት እንዲቋረጥ አድርጎ ነበር። በአክለጉዛይ መሉ የንጉሡ ጦር ወደ ፊት መግፋት ለማመቻቸት ዓመጾኞች ተንቀሳቅሰው ነበር።

ጣሊያኖች ሲያሸንፉ እንበሶች ሲሆኑ ሲሸነፉም ግልፀቶች ነው የሚሆኑት። ከዓድዋ ጦርነት በፊት ከአጼ ምኒልክ፣ ከራስ መኩንን፣ ከእቴጌ ጣይቱ፣ በተደጋጋሚ ይቀርብላቸው ለነበረ ስለ ሰላም ጥያቄ በእብሪት ውድቅ ሲያደርጉ ቆይተው አሁን ግን የሰላም ንግግር ፈላጊዎች እነሱ ሆኑ። ለዚሁም ሻለቃ ሳልሳ ሶስት ጊዜ ወደ አጼ ምኒልክ ተላከ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሠራዊት ፈረስ ማይ ከተሰበሰበ በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ሳይንቀሳቀስ ተቀምጦ ማርች 20 ቀን ቀስ በቀስ ወደ ሀገሩ መመለስ ጀመረ። አጼ ምኒልክ ወደ ጉራዕ ሳይዘልቅ ወደ ሸዋ የተመለሰበት በቂ ምክንያት ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል አጼ ምኒልክ ልክ 7 ዓመት ከዓድዋ ጦርነት በፊት አጼ ዮሐንስ በመተማ በሞተ ጊዜ ማለት ማርች 10 ቀን 1889 ዓ.ም. በእኛ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. አጼ ምኒልክ ማርች 26 ቀን 1889 በእኛ

---

1. E. Bellavita ibd p. 392-393

2.E. Bellavita ibd p. 418

መጋቢት 18 ቀን 1881 ዓ.ም. ለኢጣሊያ ንጉሥ ደብዳቤ ፅፈዋል የጻፈውም ደብዳቤ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው። ከዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ፣ የሐረር፣ የከፋና የጋላ ሀገሮች ንጉሥ ለኢጣሊያ ኃይለኛ እና ወዳጅ ንጉሥ ኡምቤርቶ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. በመተማ አንድ ልዩ አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጥሯል። ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስ ከመሪዎቻቸው በሙሉ ጋራ ሆነው ወደዚያው ሄደው ስለነበረ ከደርቡሾች ጋራ ተዋግተው ተሸንፈው ቆስለው ሞተዋል። ስለዚህው የእኔ መልእክተኞች ወደ ግርማዊነትዎ እስኪመጡ ድረስ እኔም ከአንቶኔሊ ጋራ ስለምልካቸው እና ለግርማዊነትዎ በሆዱ ያለው ሁሉ እስኪምገልፅልዎት ድረስ ግርማዊነትዎ በምፅዋ ለሚገኙ ጀኔራሎች በትግራይ በኩል የሚገኙት ሹፍቶች የሚና ገሩትን እንዳይሰሟቸው እና የጦር መሣሪያ እንዳይገባ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉላቸው እለምንታለሁ። ከዚሁ ዜና በኋላ ሁሉም ለኢትዮጵያ ዘውድ መብት እንዳላቸው ለማስማት ይፈልጋሉ። የግርማዊነቶ ወታደሮች አስመራ ገብተው አጠንክረው እንዲይዙ። በዚሁ በኩል መንገዶቹ እንደተያዙና በመካከሉ ጦር እንዲጠናከሩ እንዲያደርጉ እለምናዎታለሁ። ይህ ሁሉ ነገር ለግራማዊነቶ ለመናገር የሚያስደፍረኝ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከብዙ ዓመት ጀምሬ እመኘው የነበረ ዘውድ መብትም ያለኝ ስለሆነ ሊሰጠኝ ነው የኢትዮጵያም ሰላምና ዕረፍት ሊሰጣት ስለሆነ ነው[1] አጼ ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ ወደ ሸዋ ሊመለስ ለትግራይ ሹሞች ከጣሊያኖች ጋራ ያላቸው ችግር ራሳችሁ በራሳችሁ ተወጡ እንደማለት ይቆጠራል እነሱም ደካማ ነበሩ ሁሉም በራስ መንገሻ የሚታዘዙ አልነበሩም።

አጼ ዮሐንስ ከሞቱ ከአራት ቀን በፊት ቀንደኛ የትግራይ ጠላት የሸዋ ፖለቲካ አራማጅ አንቶኔሊ ከአዲስ አበባ ለኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር የጻፈው ደብዳቤ እንዲህ ብሎ ነበር ንጉሥ ምኒልክ አብዛኛው የትግራይ ሹማምንቶች በአጼ ዮሐንስ መጥፎ አስተዳደር የደከመ ሀገራቸው በኢጣሊያ ቢያዝ ደስታቸው መሆኑን ያረጋግጣል። ይህ አጋጣሚ ሁኔታ በዝምታ ማለፍ አያስፈልግም። ምክንያቱም ትግራይ እንደገና ነፍስ እንዲዘራና እንዲጠናከር ጊዜ በመሥጠት በስህተት መውደቅ እንችላለን። ይሄም ቀን ከመጣ ለጨካኝ እና አዲስ የትግራይ ገዢ ልንጋለጥ እንችላለን በሸዋ በኩል አንድ ወዳጅ የሆነ ንጉሥ አለን[2] ጣሊያኖች የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሀገሩ ሲመለስላቸው አፎይታ አግኝተው እስረኞቻቸውን ለማስለቀቅ ነበረ ሐሳባቸው። በኢትዮጵያ የተማረኩ የኢጣሊያ እስረኞች 1700 ነበሩ። በመንገድ በድካም፣ በበሽታ ስለሞቱባቸው ተለቀው ወደ ሀገራቸው በሚሄዱበት ጊዜ የተቆጠሩ 1300 ብቻ ነበሩ።

ስለ ሐስረኞችም ስለ ሰላም ንግግርም ወደ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ መልዕክተኛ ሆኖ የተላከው ሻለቃ ነራሲኒ የሚባለው ነበር። ሴፕቴንበር 10/1886 ዓ.ም. በዘይላ በኩል ሐረር ገብቶ ራስ መኮንን የደመቀ አቀባበል አድርገውለታል። በኦክቶበር ሻለቃ ነራሲኒ ከኢትዮጵያ ጋራ ስምምነት የተደረሰ መሆኑን ለመንግሥቱ ሲገልፅ ስለ አጠቃላይ ሰላም በሚመለከት።

1. Carlo Rossetti Ibd. p. 59

2. Carlo Rossetti Ibd. p. 57



1ኛ. ኢጣሊያና ኢትዮጵያ በጦርነት እንዳልሆኑ፣

2ኛ. የውጫሌ ውል ውድቅ እንደሆነ፣

3ኛ. የኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነትና ሉዐላዊነት ኢጣሊያ ትቀበላለች፣

4ኛ. የወሰኑ ጉዳይ አሁን እንዳለ መረብ፣ በለሳ፣ሙና ሆኖ ከዚሁ የሰላም ውል ከአንድ አመት በኋላ በወዳጅነት እንዲወሰን፣

5ኛ. የመጨረሻው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት ለሌላ መንግሥት አሳልፎ እንዳይሰጥ በራሱ ፍቃድ መልቀቅ ከፈለገም ለኢትዮጵያ ብቻ እንዲመልስ የሚሉ ነበሩ፣

### ምርኮኞችን በሚመለከት

1ኛ. ምርኮኞች ነፃ እንደሆኑ በዘይላ በኩል ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ወደ ሐረር እንዲሰበሰቡ፣

2ኛ. የኢጣሊያ ቀይ መስቀል በጂልዴላ እንዲረከባቸው፣

3ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት ምርኮኞችን ለመቀለብ ያወጣው ውጪ የኢጣሊያ መንግሥት እንዲከፍል ማርች 26 ቀን 1898 ዓ.ም. በፊርማቸው አፅድቀዋል። በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ ፓርላማ ኖቬንበር 30 ቀን 1896 ባደረገው ስብሰባ ሙሉን አፅድቋል። በኢጣሊያ ፓርላማ አባል በሆነው ኢምብሪያኒ የሚመሩ ከኤርትራ ለቀን እንውጣ የሚሉ ወገኖች ነበሩ። ሐሳባቸው ግን 26 ደጋፊ ሲያገኙ 53 ታአቅቦ ድምፅ በ184 ተቃውሞ ውድቅ ሆኖባቸዋል። በዚሁ ተስፋ ሳይቆርጡ የቅኝ ግዛት ተቃዋሚዎች የሶሻሊስቶች መሪ ኢምብሪያኒ አማካኝነት አለከራኖች ከፍተኛ ወጪና ውርደት ብቻ ነው ኢጣሊያ የምታተርፈው በማለት ከኤርትራ ለቃ እንድትወጣ ለማድረግ ሞክሮ ነበር።

2 .ሁለተኛ ወገን ከመንግሥት በኩል ከበሳ ደጋ በሙሉ ብቻ ለቆ በምፅዋና አርቂቆ ብቻ እንዲወሰን ሐሳብ ቀርቦ ነበር።

3. ሌላ ወገን በጎ እስተሳሰብ አለን የሚሉ አሁን ያለው ወሰን እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ኢጣሊያ ከማንኛውም መስፋፋት ተቆጥባ ለደረሰባት ሽንፈት እበቀላለሁ ብላ ሳታስብ ከአቢሲኒያ ጋራ በሰላም እንድትኖር

4. አነለተኛ ወገን በወታደር ክፍል የሚደገፍ ለጊዜው ብቻ ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ ተቀብላ ከአቢሲኒያ ጋራ ሰላም እንድትመሠርት ቀስ በቀስ በኤርትራ እየተጠናከረች ሐዳ በሚሰጢር ለዘመቻ ተዘጋጅታ ከፍተኛ ጦርነት እካሂዳ የደረሰባትን ሽንፈት እንድትበቀል የሚሉ ነበር። ማርች 5 ቀን 1897 ዓ.ም. የኢጣሊያ መንግሥት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሩዲኒ አማካኝነት ስለ አፍሪካ ልዩ ልዩ ሀሳቦችና ዕቅዶች ያሰራጫል። አፕሪል 14 1897 ከፓርላማ አቦሎቸ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ይቀርባሉ ከመንግሥትም ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ አፕሪል 22 ወደ ድምፅ መስጠት ይተላለፋል።

1ኛ. ኢጣሊያ ኤርትራን ለቃ እንድትወጣ የሚጠይቅ በከፍተኛ ተቃውሞ ውድቅ ይሆናል፤

2ኛ. የኦክቶበር 26 የሰላም ውል ቁርጡ እስኪታወቅ ድረስ ፖርላማ ስለ አፍሪካ ጉዳይ ክርክሩ እንዲያዘገይ የሚለውን በድምፅ ብልጫ ውድቅ ይሆናል።

3ኛ. መንግሥት ስለ አፍሪካ ባወጣው ፕላን ፖርላማው ይስማማል የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት ያገኛል። እንደገና ስለ አፍሪካ ጉዳይ ዲሴንበር 16/1897 ኢጣሊያ ከአፍሪካ ለቃ መውጣት አለባት ከሚሉ ወገኖች በፖርላማ ጥያቄ ቀርቦ 81 ድምፅ ደጋፊ ሲያገኝ 172 ተቃውሞ ስለገጠመው ውድቅ ይሆናል። ይህውም ስለ አፍሪካ የመጨረሻ ክርክር ይሆናል። ስለ ከሠላ ጉዳይ ግን የኢጣሊያ መንግሥት ደርቡሾችን በመፍራት እንዲሁም የመንግሥት ወጪውን ለመቀነስ የእንግሊዝ መንግሥት እንዲረከበው በመለመን ለእንግሊዝ አስረከባት። በእንግሩ ግን የእንግሊዝ መንግሥት ከዚህ ቀደም በደርቡሾች የደረሰበት ሽንፈት ከምንም ሳይቆጥር ምንም እንኳን ያልተዘጋጀ ቢሆንም ዲሴንበር ወር 1897 ከኢጣሊያኖች ሊረከብ ችሏል። አንዳንድ ጣሊያኖች ከከሰላ ለቆ መውጣት ለሀገራቸው ከዓድዋ ሽንፈት የበለጠ ውርደት ነው ብለውታል።



La liberazione di Adigrat: arrivo del ten. Bodrero sotto le mura del forte (disegno di Ximenes)

ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች ዓዲግራት ውስጥ የተከበቡ ወታደሮቻቸውን ባሻጥር ያስለቀቁ መሆናቸውን የታወቀ ሊሆን በጀል አድራጊነት የገቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ይህ ስእል አመላቷል፡፡



# የዓድዋ ጦርነት የሞቱና የቆሰሉ በሁለቱ ወገኖች

1. ከሁሉ አከራካሪ የሆነው በዓድዋ ጦርነት የሞቱ የኢጣሊያ ወታደሮችት ነው።[1] በ1938 በኢጣሊያ መንግሥት የታተመው መጽሐፍ ኢጣሊያኖች ብቻ በሚመለከት በጦርነቱ እየተካፈሉ ወታደሮች 11.430፤ 553 የጦር መኰንኖች 10.877 ተራ ወታደሮች፤ ያልሞቱና ያልተማረኩ 4555፤ ከእነሱ ውስጥም 265 የጦር መኰንኖች፤ 4290 ተራ ወታደሮች ነበሩ። የሞቱና የተማረኩ ኢንዲጀኒ ሳይጨምር 7043 ሲሆኑ ከእነሱም 288 የጦር መኰንኖች፤ 6755 ተራ ወታደሮች።

በመጨረሻ የተደረጉ ጥናቶች ግን የሞቱና የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች 262 (46 ከመቶ)፤ 3772 ተራ ወታደሮች (38 ከመቶ) እንደበሩ ተረጋግጧል ካለ በኋላ ስለ ኢንዲጀኒ ወታደሮች የሞቱና የቆሰሉ ለማወቅ እንዳልተቻለ ገልጦ ሆኖም የደረሰባቸው ጉዳት ከባድ ስለነበረ በአማካኝ በጦርነቱ ከተካፈለው የደረሰው ጉዳት 50 ከመቶ ሊሆን እንደሚችል ገልጧል።

1406 አስካሪ ምርኮኞች የቀኝ እጃቸውና የግራ እግራቸው ተቆርጧል 6 አስካሪና 30 የኢጣሊያ አስር አለቆችና ተራ ወታደሮች ተሰልፏል። በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው ጉዳት የሞቱ 8000፤ የቆሰሉ 10.000 ተገምቷል ብሎ ገልጿል።

2ኛ. አልቤርቶ ፖሌራ[2] በደረሰው መጽሐፍ በመግቢያ ላይ እንደተገለጸው የኢጣሊያ ሠራዊት 286 የጦር መኰንኖች 6.800 ተራ ወታደሮች በጦር ሜዳ ተገድሉበታል 1700 አብዛኛው የቆሰሉ ተማርኳል። በኢትዮጵያ የደረሰው ጉዳት 17.000 ነው ብሏል።

3ኛ. አ ብሮንዙዎሊ በደረሰው መጽሐፍ[3] የኢጣሊያ ሠራዊት በጦርነቱ ከተካፈሉ 9.837 ተራ ወታደሮች 3.772 በጦር ሜዳ ሞቷል (38 ከመቶ) በላይ እንዲሁም በጦርነቱ ከተካፈለ 571 የጦር መኰንኖች 262 (46 ከመቶ) በጦር ሜዳ ሞቷል። የኢንዲጀኒ ወታደሮች የሞቱና የቆሰሉ አይታወቅም ሆኖም የደረሰባቸው ጉዳት ከባድ ስለነበረ በአጠቃላይ ኢጣሊያ ካሰለፈቻቸው ወታደሮች በአማካኝ (50 ከመቶ) የሞቱና የቆሰሉ ናቸው ተብሎ ተገምቷል። በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ጉዳት በትክክል ባይታወቅም የሞቱ 6.000 የቆሰሉ 10.000 መሆናቸውን ተገምቷል ብሏል።

4ኛ. ሉካ ዴይ ሳቤሊ[4] በደረሰው መጽሐፉ የኢጣሊያ ሠራዊት ከሞቱበት 6.000 ወታደሮች 4.600 ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች ሲሆኑ 268 የጦር መኰንኖች ነበሩ የቆሰሉ ከ500 በላይ የበሩ የተማረኩ 1.700 ነበሩ።

1.Fici p. 206

2. Alberto Pollera La guerra di Adua XII

3. A Bronzuoli Adua p. 67

4. Luca Del Sabelli La Storia Di Abissinia Vol.3 p.422

በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው ጉዳት የሞቱት 7.000 ነበሩ የቆሰሉት 10.000፣ 2.000 ቆይተው ሞቷል ብሏል። አጼ ምኒልክ በኤርትራውያን ኢንዲጆች ላይ የሚሰጠውቅጣት ራሱ ጣሊያ መግባት አልፈለገም አቡነ ማቴዎስ ፍርድ እንዲሰጡ መብት ሰጧቸው በዚሁ መሠረት በአቡኑ ትዕዛዝ ወዲያውኑ የቀኝ እጃቸውና የግራ እግራቸው እንዲቆረጡ ተደረገ።

በዚሁ ዘገባ የሚታየው አዲስ ነገር በሌሎች ታሪክ ፀሐፊዎች ያልተገለጠ የቁስለኞች ቁጥር ነው። በማንኛውም ጦርነት የቆሰለኞች ቁጥር ከሚሞቱ ከፍ ብሎ እንደሚገኝ የታወቀ ነው በዓድዋ ጦርነት ግን ባልተለመደ ሁኔታ ቁጥራቸው ከሞቱት በጣም ዝቅ ብሎ መገኘቱ ጣሊያኖች የሞቱት በሽሽት ላይ እንዳሉ መሆኑን ያሳያል።

5ኛ. ታዋቂው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ኮንቲ– ሮሲኒ[1] በጻፈው የኢጣሊያ ጦር ቁጥሩ ከ17.000 ትንሽ ያነሰ ነበረ ከእነሱ ውስጥም 6.400 ኢንዲጆች ነበሩ ብሏል። 4.900 ነጮች ወደ አንድ ሺህ የሚጠጉ ኢንዲጆች ተገድለዋል ብሏል። ሌላ አንድ ሺህ የሚጠጉ ኢንዲጆች ተማርከው አንድ እግራቸውና አንድ እጃቸው ተቆርጧል ብሏል። ኢጣሊያና ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ የሰላም ውል ሲፈራረሙ ኦክቶበር 1896 ኢጣሊያ 1580 ምርኮኞች ተመልሰውላታል፣ ከኢትዮጵያ ስለቀለባቸው የተደረገላቸው ወጪ መካካሻ ኢጣሊያ 10 ሚሊዮን ሊሬ ከፍላለች።

6ኛ. ኮራዶ ዞሊ[2] በደረሰው መጽሐፍ በዓድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያ በኩል የሞቱና የቆሰሉ 16.000 ነበሩ። ከኢጣሊያ የሞቱና የቆሰሉ 8.000 ነበሩ ምርኮኞች 1.800 ሲሆኑ ግን ደርሶባቸው ከነበረ ቆሰልና በሽታ ስለሞቱባቸው ከእሥር ተለቀው የተመለሱ ትንሽ ከ1.800 የሚበልጡ ነበሩ።

7ኛ. ካርሎ አናራቶኔ[3] በዓድዋ ጦርነት የተካፈሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች 80.000 ብቻ ነበሩ። በኢጣሊያ በኩል በጦርነቱ የተካፈሉ የጦር መኰንኖች 551 ተራ ወታደሮች 10.550፣ ኢንዲጆች፣6.790 ነበሩ። የሞቱ 4.600 ጣሊያኖች ከእነሱ ውስጥም 2ጀነራሎች፣ 2 ኰለኔሎች፣ 267 የጦር መኰንኖች፣ 2000 ኢንዲጆች። የቆሰሉ ተማርከው እጃቸውና እግራቸው የተቆረጡ ኢንዲጆች ጥምር 2000 ነበሩ። የኢጣሊያ ምርኮኞች 1.752 ነበሩ ከእነሱ ውስጥም 150 የጦር መኰንኖች ነበሩ፣ ነገር ግን ከጦርነቱ አንድ ወር በኋላ አፕሪል 7 አጼ ምኒልክ ምርኮኞቹ 2400 እንደነበሩ ለሻለቃ ሳልሳ አስታውቀው ነበረ። በኢትዮጵያ በኩል በጦርነት፣ በረሃብና በበሽታ የሞቱ የቆሰሉ በአጼ ምኒልክ 20.000 ወታደር እንደሚገመት ዘግቧል።

---

1. Conti- Rossini Etiopia e genti d'Etiopia
2. Corrado Zoli CronacheEtiopichep. 187
3. Carlo Annaratone In Abissinia p.346



# የዛሬ ዘመን የሸዋ ፖለቲካ አራማጆች

ጣሊያኖች እና አጼ ምኒልክ ሊያስማማቸው የቻለ ነገር ሁለቱም በአንድ የጋራ ጠላት በአጼ ዮሐንስ ላይ የጠብመንጃቸው አፈሙዝ ያነጣጥሩ ስለነበረ፣ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል ጽንሰ ሀሳብ በመመራት ነበረ።

አጼ ዮሐንስ እንደ አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ አንድነት ለድርድር የማያቀርብ ስለነበረ፣ የጣሊያኖች ፍላጐት የማያሟላ ቀንደኛ የኢጣሊያ ጠላት ነበረ። ቃሉም አንድ ቀን ሳያጥፍ ነበረ በጦር ሜዳ በጀግንነት የሞተው።

አጼ ዮሐንስ ለአጼ ምኒልክም የሥልጣን ተቀናቃኝ በመሆኑ ብቸኛ ባለጋራ ነበረ።

ከዚህ በላይ አንቲኖሪ በጻፈው ደብዳቤ እንደተገለጸው በፀረ አጼ ዮሐንስ የቅኝ ገዥነት ዓላማቸው፣ ኢትዮጵያን በቁጥጥራቸው ለማዋል የነበራቸው ፍላጐት እውን ለማድረግ፣ እንደ ፖለቲካ መሣሪያ ሊጠቀሙበት ቢመክሩም፣ ጣሊያኖች አጼ ምኒልክን በእኩል ደረጃ አያዩት አልነበረም። የሚደራደሩት «ምንም ቢሆን ጥቁር ንጉሥ መሆኑን መዘንጋት የለብንም» እያሉ ዝቅ አድርገው ይመለከቱት ነበር። እምዬ ምኒልክ ግን በየዋህነቱ ለኢጣሊያ ንጉሥ በላከው ደብዳቤ የመንግሥቴ ጠባቂ (የሸዋ መንግሥት) እያለ ይጽፍለት ነበር፣ ካርዲናል ማሳያንም አባቴ እያለ ይጠራው ነበር።

በዘመናችን፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ 100ኛ ዓመት በሚከበርበት ወቅት፣ ከጥንት ከእነ አንቲኖሪ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሸዋ ፖለቲካ አራማጆች በአዲስ አበባ አቆጥቁጠው ይታያሉ። የዓድዋ ድል መታሰቢያ 100ኛ አመት በሚመለከት መአሕድ የበዓሉ አከባበር፣ ጦርነቱ በተካሄደበት በዓድዋ ሳይሆን በአዲስ አበባ መከበር አለበት ብሎ በመጠየቅ የካቲት 10 ቀን 1988 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ለሕዝብ ጥሪ ሲያስተላልፍ በአዲስ አበባ በየመንገዱ ከተሰጡ ጹሑፎች ውስጥ የሚከተሉት ቃላቶች ይገኙበታል።

«የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀጥቅጠው ሰመግዛት የዘመቱ ቅኝ ገዥዎችና ለዚያ ለረከሰ እምነታቸው እውነት ያሰለፉቸው ጥቁር ባንዳዎች ከነጭ ሰው በፊት እኛ እንሙት ብለው ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱ ሁሉ የሀፍረት ማቅ ከንብንባቸውን ለምንግዜም ከራሳቸው ሊያወርዱት በማይችሉበት ሁኔታ ዓድዋ ላይ ታሪክ ተሰርቷል። ይህ ታሪክ ወሬ ያኢትዮጵያ ሕዝብ እና እምዬ ምኒልክ የማይነጣጠሉ ናቸው።

የዘመናችን የታሪክ ክህደት ምንጩም በዓድዋ ጦርነት ወቅትና ከዚያም በፊት ሆነ በኋላ በኢትዮጵያ ጠላትነት የምናውቃቸው ባንዶቹ እንቅስቃሴ ውጤት ነው።

ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የእድገት ጐዳና የመሩንን፣ ባቡር፣ ስልክ፣ ፖስታ፣ የውሃ ቧንቧ፣ መኪና የመሳሰሉትን ስናወሳ እምዬ ምኒልክን ማስታወሳችን አይቀሬ ነው።

ከቅኝ ገዢዎች ጋር የተደረገው ጦርነት በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጮች በጥቁር መንግሥት ጦር ድባቅ ተመተው የተሸነፉበት የዓድዋ ጦርነት ሲነሳ ኢትዮጵያና እምዬ ምኒልክ የጦርነቱ ውሎ ሲነሳ ደግሞ የኢጣሊያን መሪዎችና ሽንፈታቸው ከእነርሱም ጋር

ተሰለፈው የታሪክ ሞት የሞቱ ከሳባት ሺህ በላይ የሆኑ ባንዶች ከቶውኑ የማይነሣጠሉና የማይዘከሩ ናቸው።»

ይህን መግለጫ ያቀረበው መላው አማራ ሕዝብን እንወክላለን የእጼ ምኒልክ ደጋፊዎች ነን ከሚሉ ወገኖች ነው። ነገር ግን ይህ ስሜት የመላው አማራ ሕዝብ ስሜት አይደለም፤ መላው የአማራ ሕዝብን ከማይወክሉ ከጥቂት ግለሰቦች የመነጨ ስሜት ነው። ለአንድ መቶ ዓመት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሲከበር የኖረው፤ በተለይ በአፍሪካ ደረጃ ወንድር የ100ኛ ዓመት ለማክበር በምንዘጋጅበት ዋዜማ እጼ ምኒልክ በአድዋ ጦር ሜዳ ኃያል አውሮፓዊት መንግሥት ነኝ የምትለው ኢጣሊያን በማሸነፍ ነው እንጂ ሰባት ሺህ ባለቀለም ከጣሊያኖች ጎን የተሰለፉ ኢትዮጵያውያን ባንዳዎችን በመግደሉ ያገኘው ጀግንነት በሚል መፈክር እውለብልበን አይደለም። ኢትዮጵያውያን ሁላችን በተለይ የዓድዋ ድልን በምናከብርበት ጊዜ እርስ በእርሳችን መወቃቀስ ባልተገባ ነበር። ይህ በመእህድ የወጣ መግለጫ ከአንድ ታላቅ የፖለቲካ ቡድን የማይጠበቅ ርካሽ ጥራዝ ነጠቅ ወቀሳና ተራ ስድብ ግን መልስ ሊሰጠው ይገባል። ስለባንዳዎች ወይንም ከኢጣሊያ ጎን ተሰልፎ የገዛ ሀገሩን የመውጋት ጉዳይ ከተነሣ የመጀመሪያ ባንዳ፤ የባንዳዎች ቁንጮ ራሱ ምኒልክ መሆኑን የማይካድ ሀቅ በመሆኑ ጥቂት ታሪካዊ ክንውኖች መጥቀስ ይቻላል።

1ኛ. በሰሜን ኢትዮጵያ የጣሊያኖች ግንኙነት በማይታወቅበት ጊዜ በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት አጼ ምኒልክ በሸዋ የኢጣሊያኖች ወዳጅነት መሰርቶ ነበረ። ስለዚህ ምኒልክ የመጀመሪያ ባንዳ ነው።

2ኛ. በዶጋሊ የሞቱ የኢጣሊያ ወታደሮችን በእፋር በርሀ የሞቱ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎችን እኔ እበቀላችኋለሁ። ከእናንተ በፊት እኔ ልሙትላችሁ ብሎ በተደጋጋሚ ለጣሊያኖች የገለጸላቸው ወዳጃቸው የነበረ ምኒልክ ነው።

3ኛ. ምኒልክ የሀገሩ ዳር ድንበር ጉዳይ ለአውሮጳ መንግሥታት ለማስታወቅ በጻፈው ደብዳቤ አሥመራን እና ምጽዋን ለጣሊያኖች በመሸጥ የጣሊያኖች መሬት መሆናቸውን በማመን በሰሜን የኢትዮጵያ ወሰን ከቺከቲ (20 ኪሎ ሜትር ከአስመራ) በስተደቡብ መሆኑን ገልጾዋል።[1]

4ኛ. እጼ ምኒልክ የሀገሬ ወሰን ነው ብሎ ያመነበትን በማጠፍ ጣሊያኖች ከጉናቸው የሚያሰልፏቸው ባለቀለም ወታደሮች ለመመልመል ያስፈልገናል ብለው በጠየቁት መሠረት አይበቃችሁም ብሎ እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ያለውን መሬት ጨምሮ ሰጣቸው። ተገሎም በውሜሌ ውል የሌለ የኩናማ መሬትም ሰጣቸው።

5ኛ. ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ ጣሊያኖችን አሳዶ መሬቱን ለመመለስ መብትና ኅይታ ሊኖረው ይቼንን ማድረግ አልፈለገም። ይኸውም ሌላ የምኒልክ ክህደት ነው።

6ኛ. በጉዳ ጉዲ (ጉንደት) ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ትጥናለህ የሚል ሀሰት ተስፋ ከግብጻውያን ሲሰጠው ምኒልክ የሸምበር 1876 ዓ.ም. ከግብጾች

1. Traversi : Let Marefia p. 379



እስላሞችጋራ ተስማምቶ እጼ ዮሐንስን ለመውጋት ተዘጋጅቶ ነበረ። ግብጾች በሰሜን ኖበምሥራቅ ጦር ግምባሮች ስለተሸነፉ ግን እትዱ ላይላካ ቀረ

በታሪክ የሀፍረት ማቅ የተከናነበ በክሀዲነት ከታሪክ የማይፋቅ እላፋሪ ተግባር በመስራት ያለፈ የሀገሩን ሕዝብና መሬት የሸጠ እምዩ ምኒልክ ነው እንጂ እንደ እቃ የተሸጡ ጭቁን ሕዝቦች አይደሉም። ባንዳም ተብሎ መጠራት የሚገባው ሚኒልክ ብቻ ነው። ባንዳ ሆኖ በጣሊያኖች ያልተቀጠረ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም አይገኝም። የንቃት ሕሊና ማነስ ስለሆነ ለጣሊያኖች የሚቀጠሩት ሰዎች ሥራና ደመወዝ ከማግኘታቸው በቀር አርቀው ማየት የማይችሉበት ጸመን ይኖሩ የነበሩ ናቸው።

በዘመናችን የታሪክ ክህደት ምንጩም፤ ዋና ባንዳ አድርገን የምናውቀው ምኒልክ ብቻ ነው። ይኸም ሆኖ ስህተት በመስራቱ ከመውቀስ እልፈን የነበረበት ዘመን ስንመልከት በጠላትነት እንመለከተውም። የኤርትራ ነፃ ሀገር መፈጠርም የምኒልክ ክህደት ያመጣው ውጤት ነው። ለዚህም ሌላ ማንም ሰው በኃላፊነት አይጠየቅበትም። ምኒልክም የክህደት ተግባር የፈጸመበት ምክንያት ከሀገሩ ከኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት ዘውድን ለመጫን ፍላጎቱን ስለሚያስቀድም ነበር። የሸዋ መኳንንት፤ እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ መኳንንት የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ሲሸጥ ከመቃወም አላቋረጡም ነበረ። ምኒልክ ግን በሥልጣኑ እፍና ዝም አሰኛቸው።

የምኒልክ ደካማ ጎን ስዩስታውስ ጠንካራ ጎንንም ማስታወስ ያስፈልገናል። በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ምኒልክ መላው ኢትዮጵያን ለአንድ አላማ፤ በአንድነት ማሰለፍ መቻሉ፤ ለድል መብቃቱ፤ ለኢትዮጵያ አስደናቂ የጀግንነት ክብርና ዝና ማትረፉ ከጠንካራ ጎኑ አንዱና ዋነኛው ነው። ምኒልክ በለዘብተኝነት ሀገርን የማስተዳደር ችሎታም ነበረው። ምኒልክ በዘመናችን የእሱ ደጋፊዎች ነን የሚሉ እንደሚያስቡት የጎላ ጥላቻ አልነበረውም። ሁለቱ የአጼ ምኒልክ ታማኝ ሚስቶች ጣይቱና ባፋና የሰሜን ኢትዮጵያ ተወላጆች ነበሩ። ጣሊያኖች በየጊዜው በዘመኑ ያቀርቧቸው የነበሩ ሪፖርቶች ችግር እንደፈጠረባቸው ብለው በተደጋጋሚ ከመግለጽ ያላቋረጡት ጉዳይ ምኒልክ ከሾማቸው መኳንንቶች ብዙዎቹ የሰሜን ኢትዮጵያ ተወላጆች እንደነበሩ ነው የሚያስገነዝበን። በዚሁ ምክንያት ጣሊያኖች እንደሚሉት የሸዋ ፖለቲካቸው ለማራመድ ምኒልክን ሃሳብ በማስቀየር፤ በየጊዜው እንቅፋት ያጋጥማቸው እንደ ነበረ ነው የምንረዳው።

በመእህድ መግለጫ መሠረት በዓድዋ ጦርነት የተሸነፉና የሞቱ ከጣሊያኖች ወገን የእምዩ ምኒልክ ወዳጆች ስለሆኑ ቁጥራቸው ስንት እንደነበሩ ሳይጠቀስ ከባንዶዎች ወገን የታሪክ ሞት የሞቱ ከሰባት ሺ በላይ የሆኑ ባንዳዎች ናቸው ይላል። አባባሉ ግን ፈጽሞ ከእውነተኛ ታሪክ የራቀ፤ ልብ ወለድ ነው። በዓድዋ ጦርነት የሞቱና የቆሰሉ በኢጣሊያ ወገን ራሳቸው ጣሊያኖች ቁጥራቸው እንዳወጡት፤ የሞቱ ጣሊያኖች ሰባት ሺ ሲሆን ከአንዲጃኒ (ባንዳዎች) ስንት እንደሞቱ ራሳቸው ጣሊያኖች በትክክል ሊያውቁት አልቻሉም። የዚህ ዝርዝር ከዚህ በላይ ተገልጿል።

የመጽሐፉ መግለጫ እውነት ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በዓድዋ ጦር ሜዳ ጦርነት የገጠሙትው ከኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ጋራ መሆኑ ቀርቶ የኢጣሊያ ተዋጊ ወታደር ያልተሳተፈበት ከኢጣሊያ መሪዎች እና ከኤርትራውያን ጋራ ብቻ መሆኑ ነው።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፣ እንዲሁም የአውሮጳ ታሪክ ፀሀፊዎች፣ በመጽሐፉ ውስጥ ከተሰገሰጉ ጥቂት ግለሰቦች በስተቀር ኢትዮጵያ በአጼ ምኒልክ መሪነት በዓድዋ ጦር ሜዳ ድል የተቀዳጀችው በአምስት ጀኔራሎች የሚመራ በኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ላይ መሆኑን በሚገባ ያውቃል። ከጣሊያኖች ጉን ተሰልፈው ስለሞቱ ባንዳዎች ከዳተኛው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢጣሊያኖች ወዳጅ አጼ ምኒልክ የሀገሬ ሰዎች አይደሉም ብሎ ለጣሊያኖች እንደ እቃ የሸጣቸው አሳዛኝ ሞት ሞቱ ተብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀዘኑን ሊገልጽላቸው የሚገባ ናቸው እንጂ ከጣሊያኖች አብልጦ በጠላትነት የሚያያቸው አይደሉም። የመጽሐፉ መግለጫ የሚያስገነዝበን አሁንም ጣሊያኖች የእጅ አዙር ቅኝ ገዢነታቸውን እያራመዱብን የሚገኙ መሆናቸውን ነው። ድሮ ኢትዮጵያውያንን እርስ በርሳቸው ለማፋጀት በይፋ የሸዋ ፖለቲካ፣ የትግራይ ፖለቲካ ብለው ይጠሩት ነበረ። ዛሬ ዓላማው ሳይቀየር ስም ብቻ በመቀየር የኢትዮጵያን ሕዝብ በማይወክሉ በጥቂት ግለሰቦች አማካይነት ጣሊያኖች ቀድሞ የሰመዱት የጠላትነት ሥራቸውን እያራመዱብን ይገኛሉ። ከእነ አንቶኔሊ ጀምሮ በሸዋ ፖለቲካ ተኮትኩተው ያደጉ የልጅ ልጆች በሸዋ እንዳሉ ሁሉ በሰሜን ኢትዮጵያም በትግራይ ፖለቲካ ተኮትኩተው ያደጉ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም ግን አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉሳ አያምንም።

ፖስታ፣ ባቡር፣ መኪና፣ ወዘተ...ወቅቱ ስለፈቀደ በዳግማዊ ምንሊክ መጀመራቸው ለምኒልክ ልዩ ውለታ የሚያሰጠው አይደለም። ይልቁንስ በስልክ ስም ምኒልክን የሚያስወቅሱ ሁኔታዎች በወቅቱ ተፈጥረው ነበረ። ከአሥመራ ወደ አ/አ የተዘረጋው የስልክና የቴሌግራም መስመር ስለላ ለማድረግ ስለሚመቻቸው ከምኒልክ የበለጠ ጣሊያኖች ነበረ እንዲዘረጋ የፈለጉት። በየጣቢያው በኢትዮጵያ መሬት በስልክና ቴሌግራም ሥራ የኢጣሊያ መንግሥት በጣሊያኖች ሠራተኞች ብቻ እንዲካሄድ አጥብቆ ይፈልግ ነበረ። የዋሁ ምኒሊክ ግን ጣሊያኖች ወዳጆቼ እንደመሆናቸው መጠን እንደበጉ አድራጊዎችና አሰልጣኞች በመቁጠር፣ ከጣሊያኖች ጉን ኢትዮጵያውያን ረዳት አፕሬተሮች (ሰልጣኞች) በየጣቢያው እንዲመደቡ አድርጉ ነበረ። እነዚህ ኢትዮጵያውያን በጣሊያኖች የማይፈለጉዋቸው ስለነበረ ብዙ ጊዜ በመሐከላቸው ጭቅጭቅ ይነሳ ነበረ። አንዳንዶቹ በጣሊያኖች ተከሰው ወደ ምኒልክ ለፍርድ ቀርበው ከባድ ቅጣትና ጥቃት ይደርስባቸው ነበር። ጣሊያኖችም ማስቀጣት በመቻላቸው ይደሰቱበት ነበር።



# ስለ ዓድዋ ጦርነት ከኮንቲ–ሮሲኒ የቀረበ

ስለ ዓድዋ ጦርነት ኮንቲ–ሮሲኒ ሰፋ ያለ ካቀረባቸው ዘገባዎች ወደ ኤርትራ ቅኝ ግዛታቸው በተናጠል ሸሽተው በደህና የገቡ 258 የጦር መኰንኖች፣ 4.666 ነጭ ወታደሮችና ወደ 4000 የሚጠጉ ኢንዲጀኒ ነበሩ። የቆሰሉ 461 ጣሊያኖች ከእነሱ ውስጥም 30 የተሰለቡ፣ 552 ኢንዲጀኒ ከእነሱ ውስጥም 6 የተሰለቡ፣ እግራቸውና እጃቸው ከተቆረጡ ሌላ።

የተገደሉ 289 መኰንኖች 4600 የኢጣሊያ ወታደሮች፣ ከአንድ ሺ ብዙ የማይበልጡ ኢንዲጀኒ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነው በመሸሽ ፍጥነት ስላላቸው ነው። ከዓድዋ ወደ አዲስ አበባ የእግር ከባድ ጉዞ 7 የጦር መኰንኖች፣ 70 ተራ ወታደሮች ሞተዋል።ምርኮኖች 1900 ወደ ሸዋ (አዲስ አበባ) ያመሩ፣ 170 በትግራይ የቀሩ ከእነሱ ውስጥም በአዲስ አበባ 54 መኰንኖች፣ በትግራይ 6 የጦር መኮንኖች ነበሩ። ከእስር በመንገድ ያመለጡ 235።

ምርኮኖች ከአዲስ አበባ ወደ ሀገሩቸው የተመለሱ 1580።

በፊታውራሪ ለማ የሚታዘዙ ወታደሮች በደጀዝማች በሻህ ሞት የተናደደ ተማርከው በእጃቸው ከገቡ ወታደሮች 70 ነጮችና 230 ኢንዲጀኒ ጨፍጭፈው በመግደል ግፍ በመፈጸማቸው ፊታውራሪ ለማ በአጼ ምኒልክ ትእዛዝ ታስሮ ወደ እንድ አምባ ተልኳል።

አስካሪ የተማረኩ 800 የሚጠጉ ነበሩ። ከእነሱም ብዙዎቹ ሊማረኩ የቻሉት የቆሰሉ ወይንም በሽሽት ጊዜ የዘገየ ኢጣሊያዊ አለቃቸው ትተን እንሄድም በማለታቸው ነው። ከእነሱ ውስጥ በአቡነ ማቴዎስ ትእዛዝ የግራ እግራቸውና የቀኝ እጃቸው የተቆረጡ በትክክል ስንት እንደ ሆኑ ባይታወቅም በእግር ጉዞ እድርገው በየመንገዱ በበሽታ፣ በድካም፣ በረሃብ ከሞቱት ሌላ ትንሽ ከ400 የሚበልጡ አሥመራ ገብተው የሕክምና እርዳታ አግኝተዋል።

ስለ ኢትዮጵያ ጦር የሞቱና የቆሰሉ ለማወቅ አስቸጋሪ ስለሆነ ኮንቲ ሮሲኒ ከተለያዩ ሰዎችን የተለያዩ አስተያየቶች አውጥቷል።

1. ኮንቲ ሮሲኒ በግሉ ካገኛቸው መረጃዎች የሞቱ 7000 የቆሰሉ 10.000 ነበሩ። ተመሳሳይ ቁጥር (Berkeley) እና (Keller) የተባሉ ዘግበዋል።
2. በአዲስ አበባ የፈረንሣይ ወኪል ከጻፈው ደብዳቤ የሞቱ የኢትዮጵያ ወታደሮች 3867 እንደነበሩ ገልጧል።
8. ሌሎች ምንጮች የሞቱ ከ4000 እስከ 5000 እንደሚደርሱ አውጥቷል።
4. ከሩሲያ በኩል የተገኙ ዘገባዎች የሞቱ 4000 የቆሰሉ 6000 ነበሩ።
5. አቡነ ማቴዎስ የሞቱ 4500 እንደነበሩ ገምቷል።
6. አጼ ምኒልክ ለፈረንሣይ ሪፑብሊክ ፕሬዝዳንት በላኩት ደብዳቤ የተገደሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች 5000 እንደነበሩ ገልጧል።

7. (Augusto Wylde) የሞቱ ከ5000 እስከ 6000 ፣ በከባድ የቆሰሉ 8000 እንደሚደርሱ ገምቷል።

8. ገራዝማች የሴፍ እስረኛው ሆኖ ለነበረው ለጀነራል አልበርቲኒ እንደነገረው የሞቱ 8000 ከእነሱ ውስጥም 2000 ከጦርነቱ በኋላ ባሉት ቀናት፣ የቆሰሉ 10.000 እንደነበሩ ገምቷል።

9. ለንጉሡ ነጋሪት ቅርብ የሆነ ሌላ ሰው የሞቱ 12.000 የቆሰሉም 12.000 መሆናቸውን ለጀነራል አልቤርቲኒ ገልጾለታል።

ኮንቲ ሮሲኒ በድሉ ኢትዮጵያ ያልተጠቀመችበት መኖሩን ዘግቧል። በዓድዋ ጦርነት ማግሥት 15 ወይንም 20.000 የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ኤርትራ ቢገቡ ተበታትነው ይገኙ ከነበሩ ኢጣሊያ ወታደሮች ተቃውሞ ሳይገጥማቸው ምፅዋ እርቀቱ ለመድረስ ባይችሉም ሳብርጉማ ዲግዲግታ ተራራዎች ለመድረስ ይችሉ ነበረ፤ ለጀነራል ባልዲሴራ ችግር መፍጠር ብቻ ሳይሆን ለለዘለቄታው ኢጣሊያ ከኤርትራ እንድትወጣ የምትገደድበት ሁኔታ ይፈጠር ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት ጉዳት ቢደርስበትም ጦርነቱን ለመቀጠል ከፍተኛ ስሜት ነበረው፤ ለመዝረፍ ካልሆነ ተዋጊ ኃይል እራቱ እንደማያጋጥመው ይተማመን ነበር። በአዲስ አበባ የሰላም ውል በሚደረግበት ጊዜ አጼ ምኒልክ ለኢጣሊያ መልእክተኛ ነራዚኒ እንደነገረው የትግራይ መኳንንቶች የኤርትራ ወኪሎች እስከ ሰሐቲ ድረስ ጦርነቱ እንዲቀጥል ይገፋፉኝ ነበር ብሉ ገልጾለታል።

ይኸን ቢደረግም በቂ ተቃዋሚ ኃይል ሲያጋጥም በድል አድራጊነት ይከናወን እንደነበረ ገልጾስት ነበር። ዕቅዱ በተግባር ማዋልም ተሞክሮ ነበር። መረጃ ሰብሳቢዎች ወደ ሰሜን ተልከው ምቹ መንገዶችና ውሃ የሚገኙባቸው ቦታዎችን እንዲጠቁሙ ተልከው ነበረ። አዝማች ሰንጋል በጽሑፍ እንዲያቀርብ ታዞ ነበር። ዓድዋ ላይ የሰራዊቱና የአከለጉዛይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋራ ካልተባበሩ ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ማስጠንቀቂያ አዋጅ ሲለግ ለኢጣሊያ ታማኝ የሆነው የሰራዬ ሕዝብ በብዛት ወደ ጣሊያኖች በመሰደዱ በሐልሐል መጠለያ ተዘጋጅቶለት ነበር። ደጀዝማች ሐጎስ ተፈሪ አዝማች አበራ፣ ከንጉሡ ጦርም አንድ ክፍል ወደ ጉራዕ በሚወስደው መንገድ በበለሳ ወንዝ ሰፍረው ነበረ። በጀርባቸው ራስ ስብሐት ማይ መረት እስከ ዶንጎሎና ገለባ ሰፍሮ ነበረ። ደጃዝማች እርአያ ሌላው የወራረው መስመር ከዓዕሮ ተከለ እስከ መረብ ይቆጣጠር ነበር። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ከእንጢጮ ወደ ሐማሴን መንቃት ጀምሮ እንደነበር የኢትዮጵያ መንግሥት የሰጠው መግለጫ አረጋግጧል። ትክክለኛ ወሬዎች ለጣሊያኖች ሊደርሱ የቻሉት በኢትዮጵያውያን ታስሮ የነበረ ማርች 3 የተለቀቀ የደምበላሱ ከንቲባ ማና ነበረ። ከንቲባው በተናገረው መሠረት የኢትዮጵያ ሠራዊት ጦርነቱን ለመቀጠል ወስኖ ነበር የተመረጠው የወረራ መስመርም በለሳ ማይ ለራው ጉራዕ ሲሆን ስለዚህ መስመር አዝማች ሰንጋል ትክክለኛውን መረጃ እንዲያቀርብ ታዞ ነበር። ከዓድዋ መነሻ ቀን ማርች 4 ወይንም 5 እንዲሆን ተወስኖ ነበር። ጣሊያኖች ከጦር ሰፈራቸው እንደማይወጡ የሚል እምነት ነበረ የኢትዮጵያ ጦርም



ጥቃት እንደማይፈጽምባቸው ሆኑ በወረራ እንደተያዘ ይቆጠር ነበር፤ ጣሊያኖች ድንገት ከጦር ምሽጋቸው ከወጡ ግን ውጊያ እንደሚከፈትባቸው ተወስኖ ነበር። ነገር ይህ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ደቡብ የመልስ ጉዞ ጀመረ። አጼ ምኒልክ ለነራዚኒ እንደገለጸለት ለዚሁ ውሳኔ የደረሰ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ በማሰብ ነው ብሏል። የመንገድ ችግርና የውሃ እጥረት እንዳለ ተወርቶ ነበር፤ ይህ ሁሉ ግን ሐሰት ነው። የውሃ እጥረት ሊያጋጥም የሚችለው የምኒልክ ጦር በሙሉ ሴቶች የቤት ሠራተኞች የጋማ ከብቶች ጭምር ቢንቀሳቀስ ብቻ ነው። አንድ ጠንካራ ጦር ብቻ ቢንቀሳቀስ ግን ችግር ሊፈጠር አይችልም ነበር፤ ምክንያቱም ከአንድ ወር በኋላ 42.000 የነበረው የባልዲሴራ ጦር ምንም ችግር ሳያጋጥመው ነበረ የሰፈረበት።

**Nel 1890 nasce la Colonia Eritrea, mentre Menelich fa il doppio gioco.**

## Menelich invoca Baldissera

Già comandante di una brigata nella spedizione del gen. San Marzano, Antonio Baldissera, un bravissimo ufficiale padovano di origine austriaca che aveva combattuto contro i piemontesi nel '59, aveva assunto nel 1888 il comando delle truppe e poi il Governo della Colonia.

Toccò dunque a Baldissera raccogliere l'appello di Menelich ad estendere l'occupazione militare verso il Tigrè. Il primo passo fu Cheren, in Eritrea, trampolino verso l'Asmara.

Per occupare l'Asmara, Baldissera aveva chiesto a Roma altri quattro Battaglioni Indigeni, 1700 nazionali, una batteria, e almeno 500 muli. Ma i piani di Crispi erano diversi, fondati sulla politica del *divide et impera*, cioè sullo sfruttamento delle rivalità tra i ras abissini dello Scioa e del Tigré.

Gli ultimi giorni di maggio del 1889, due colonne italiane muovono su Cheren, dove la banda del *barambaras* Kafèl presidia il fortino. La banda viene disarmata e, lasciata a Cheren una piccola guarnigione, i nostri rientrano a Massaua.

In giugno vengono occupate Sabarguma e Ghinda. Il 2 agosto tre colonne si arrampicano verso i prati dell'Asmara, a 2350 metri d'altezza, trascinando i cannoni sull'orlo dei burroni; il giorno dopo Baldissera si installa all'Asmara nel palazzo di ras Alula. Da qui, il governatore militare lancia il suo proclama: « Coltiva, o coltivatore, Commercia, o commerciante. Non temere. Chi governerà è il Governo d'Italia... Io sono venuto per arricchire e per proteggere il paese, non per distruggere... ».

Sembra l'inizio di un'era di pa-



**Il Negus Menelich**

*Divenuto Negus d'Abissinia nell'89, Menelich (nella foto) incoraggiò Baldissera a occupare tutto il Tigrè.*